






የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION


# በኢትዮጵያ የአፋር እና የአማራ ክልሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ የተደረገ ምርመራ ሪፖርት

*መጋቢት 2 ቀን 2014 ዓ.ም.*



# በኢትዮጵያ የአፋር እና የአማራ ክልሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ የተደረገ

# ምርመራ ሪፖርት

## ማውጫ

አንኳር ጉዳዮች ..... 3
መግቢያ ..... 19
የምርመራው ሥነ-ዘዴ ..... 21
የሕግ ማዕቀፎች ..... 25
ሀገራዊ እና ክልላዊ አውድ ..... 32
በምርመራው የተለዩ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ..... 35
1. በሲቪል ሰዎች፣ ሲቪል ተቋማት እና ሌሎች ጥበቃ በሚደረግላቸው ሰዎች ላይ ጥቃት ማድረስ ..... 35
2. ከሕግ አግባብ እና ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ የሲቪል ሰዎች ግድያዎች እና የአካል ጉዳቶች ..... 45
3. የጭካኔ፤ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት ..... 54
4. የዘፈቀደ እስር፣ ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወር ..... 57
5. ወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃቶች ..... 61
6. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ..... 71
7. በንብረት ላይ የተፈጸመ ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ውድመት ..... 76
8. የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ክልከላ ..... 83
9. ኢኮኖሚያዊ፡ ማኅበራዊና የባሕል መብቶች ..... 86
10. በሕፃናት ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶች ..... 90
11. አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ..... 94
ተጠያቂነት ..... 103
ምክረ ሃሳብ ..... 109
አባሪዎች ..... 111
አባሪ 1 ..... 111
ኢሰመኮ ምርመራ ያደረገባቸው እና የትግራይ ኃይሎች በአፋር እና በአማራ ክልል ..... 111
..... 114
አባሪ 2 ..... 115
የግጭት ተሳታፊዎች ዝርዝር ..... 115
አባሪ 3 ..... 117
ከኢሰመኮ ለትግራይ ክልል እንዲላክ የተዘጋጀ ደብዳቤ ..... 117
አባሪ 4 ..... 123
ከኢሰመኮ ለኢ.ፌ.ድ.ሪ. መከላከያ ሚኒስቴር የተላከ ደብዳቤ ..... 123
አባሪ 5 ..... 126
ከኢሰመኮ ለትምህርት ሚኒስቴር የተላከ ደብዳቤ ..... 126
አባሪ 6 ..... 128
ከኢሰመኮ ለፌዴራል አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የተላከ ደብዳቤ ..... 128
አባሪ 7 ..... 130
ከኢሰመኮ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተላከ ደብዳቤ ..... 130
አባሪ 8 ..... 132
ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መከላከያ ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ ..... 132
አባሪ 9 ..... 134
ከጤና ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ ..... 134
አባሪ 10 ..... 138
ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ ..... 138

አባሪ 11 .......... 152
ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ መልስ .......... 152
አባሪ 12 .......... 153
ከፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የተሰጠ መልስ .......... 153

# አንኳር ጉዳዮች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) ከተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን በትግራይ ክልል ከተከሰተው ጦርነት ጋር በተያያዘ በተለይ በትግራይ ክልል እና በተወሰነ መጠን በሌሎች አካባቢዎችም ስለነበረው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ያወጡት የጣምራ ምርመራ ሪፖርት ይታወሳል፡፡ የጣምራ ምርመራ ሪፖርቱ በጊዜ ረገድ በወቅቱ ለመሸፈን የቻለው ጦርነቱ ከተነሳበት ከጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. እስከ የፌዴራሉ መንግሥት የተናጠል ተኩስ ማቆም አድርጎ ከትግራይ ክልል መውጣቱን እስካስታወቀበት ሰኔ ወር 2013 ዓ.ም. ድረስ ብቻ ነበር፡፡

በሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎች በአፋርና አማራ ክልሎች በከፈቱት ወታደራዊ ጥቃት በርካታ ቦታዎችን መቆጣጠራቸውን ተከትሎም ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተከስተዋል፡፡

ኢሰመኮ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ ወር 2014 ዓ.ም. ድረስ ባሰማራው የሰብአዊ መብቶች ምርመራ ቡድንና ተከታታይ የምርመራ ስልቶች በአፋርና አማራ ክልሎች ተስፋፍቶ በቆየው ጦርነት የተከሰቱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሯል፡፡ በጦርነቱ ተሳታፊ የነበሩት ወገኖች በአንድ በኩል የትግራይ ኃይሎችና ተባባሪ ሚሊሺያዎች (በአንዳንድ አካባቢዎች የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ወይም በተለምዶ ኦነግ ሸኔ በመባል የሚጠሩትን ታጣቂ ኃይሎችን ጨምሮ) እና በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግሥት የፀጥታ ኃይሎች (የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊትና ሌሎች የፀጥታ አካሎች፣ የአማራ እና የአፋር ክልል የፀጥታ ኃይሎችንና ተባባሪ ሚሊሺያሚሊሺያን ጨምሮ) ሲሆኑ፤ ምርመራው በጦርነቱ ተሳታፊ ወገኖችና ተባባሪ ተዋጊዎች ተፈጸሙ የተባሉ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን ይመለከታል፡፡


በተጨማሪም የዚህ ምርመራ ዋነኛ ትኩረት በአፋርና አማራ ክልሎች ላይ ቢሆንም፤ በተወሰነ መጠን በትግራይ ክልል የተፈጸሙ የአየር ጥቃቶችን በሚመለከትም ኢሰመኮ ክትትል እና ምርመራ አድርጓል፡፡

የምርመራው ዋና ዓላማ በጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች በሲቪል ሰዎች ላይ የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን ከነፃታዊ እንድምታው መለየት ነው፡፡ የምርመራውን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ኮሚሽኑ የሚሰጣቸው ምክረ ሃሳቦች የመብት ጥሰቶችን የፈጸሙ ሰዎችና ቡድኖችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶችን ማገዝ፤ ተጎጂዎች ፍትሕ እና ተገቢውን የካሳ እና መልሶ መቋቋም ድጋፍ እንዲያገኙ ማስቻል እና ወደፊት ተመሳሳይ ጥሰቶች ዳግም እንዳይፈጸሙ ማስቻል ነው፡፡

በአጠቃላይ 29 አባሎች የነበሩት የኢሰመኮ የምርመራ ቡድን በአፋርና በአማራ ክልሎች በጦርነቱ በተጎዱ በርካታ ቦታዎች በአካል በመገኘት ምርመራ አድርጓል፡፡

| በአፋር ክልል | |
|---|---|
| ፈንቲ ረሱ ዞን | የያሎና እዋ ወረዳዎችን፣ በአውራ ወረዳ ደራይቱ ከተማን፣ በጉሊና ወረዳ ጋሊኮማ ቀበሌ፤ |
| በኪልበቲ ረሱ ዞን | አባኣላ ወረዳን፣ በበርሃሌ ወረዳ ኩሱርቱ፣ አሰዳ እና አደአርዋ፣ |
| በአውሲ ረሱ ዞን | በአዳአር ወረዳ ቡርቃ፣ ዋአንቱ እና ፉርሳ ቀበሌዎች እና የጭፍራ ከተማ፣ |
| በአማራ ክልል | |
| ሰሜን ጎንደር ዞን | ደባርቅ ወረዳ፣ ድብ ባሕር ንዑስ ወረዳን፣ ቦዛ ቀጠና (አዲ‚ጋግራ፣ አብርሃም እና አዳጋር ቀበሌዎችን)፣ ዳባት ወረዳ ጭና ቀበሌ፣ በአዲ አርቃይ ወረዳ የዛሬማ ንዑስ ወረዳ፣ |
| በሰሜን ወሎ ዞን | የጋሸና እና አርቢት ከተሞች፣ በዋድላ ወረዳ የሐሙሲት ከተማ፤ በላስታ ወረዳ የዳቦ፣ ድብኮ እና ሹምሽሃን፤ ላሊበላ ከተሞችን እንዲሁም በመቄት ወረዳ የደብረዘቢጥ ቀበሌን፣ ጣጃ እና ፍላቂትና ገረገራ ከተሞችን፤ መርሳ፣ ወልዲያ፣ |
| በደቡብ ወሎ ዞን | አምባሰል ወረዳ የወረባቡ እና ተሁለደሬ ወረዳዎችን፣ በአምባሰል ወረዳ የውጫሌ ከተማን፤ ሃይቅ፣ ደሴ እና ኮምቦልቻ ከተሞች፤ |
| በሰሜን ሸዋ ዞን | የአጣዬ ከተማን ካራቆሬ ቀበሌን በመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ የመሃል ሜዳ ከተማን፣ መዘዞ ንዑስ ወረዳን፣ የቀወት ወረዳ የለን ቀበሌ እና ሸዋ ሮቢት ከተማን፣ አንጻኪያ ገምዛ ወረዳ፣ |
| በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን | የደዋ ጨፋ ወረዳ፣ ከሚሴ እና ሰንበቴ ከተሞች |

እንዲሁም በትግራይ ክልል ደቡብ ምሥራቅ ዞን እንደርታ ወረዳ ደብረናዝሬት ጣብያ ቶጎጓ ጎጥ እና መቀሌ አካባቢዎች የተፈጸሙ የአየር ጥቃቶችን በሚመለከት እና የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦትን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ከተጎጂዎች፣ ከምስክሮች እና ከሚመለከታቸው ምንጮች መረጃዎችና ማስረጃዎችን ሰብስቧል፡፡




1 በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎች

ኮሚሽኑ በዚህ የምርመራ ሂደት በአጠቃላይ 427 ሚስጥራዊ ቃለ መጠይቆችን፣ ከልዩ ልዩ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችና ኃላፊዎች ጋር 136 ስብሰባዎችን እና ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ከሃይማኖት መሪዎች እና ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር 12 የቡድን ውይይቶችን ያደረገ ሲሆን፤ ይህም ተጎጂዎችን፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ የየአካባቢው ነዋሪዎችና የዓይን ምስክሮችን፣ የሆስፒታልና ጤና ተቋም ባለሙያዎች፣ የእርዳታ ድርጅቶችና፣ ሲቪል ማኅበራትን ይጨምራል። ከዚህ በተጨማሪም ኮሚሽኑ ለምርመራው ስራ የሚያስፈልጉትን መረጃዎችና የሰነድ ማስረጃዎች ጭምር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ልዩ ልዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ምንጮች ሰብስቧል።

ኮሚሽኑ ምርመራውን ያካሄደው አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎችን በተለይም በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች፣ በሰብአዊነት ሕጎች ወይም ዓለም አቀፍ የጦርነት ሕጎች፣ በዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ፣ በሌሎችም ዓለም አቀፍ መርሆዎች እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሕግጋት መሰረት ነው። ኢሰመኮ በሰበሰባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች መነሻነት ግኝቶች ወይም ድምዳሜዎች ላይ ለመድረስ የተጠቀመው የማስረጃ ምዘና ስልት፤ በተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ምርመራዎች

ጥቅም ላይ የሚለውን “ምክንያታዊ አሳማኝነት” (reasonable grounds to believe) የተሰኘውን የማስረጃ ምዘና ስልት ነው፡፡

ይህ ሪፖርት ጦርነት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የተፈጸሙ ሁሉንም ጥሰቶችን የሚሸፍን አይደለም፡፡ ሆኖም ምርመራው በተከናወነባቸው ስፍራዎች የተፈጸሙ ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ዋነኛ ጠባዮችና ሁኔታዎችን እና አጠቃላይ የጥሰት ዓይነቶችን ወካይ በሆነ መልኩ አካትቷል፡፡

## የምርመራው ግኝቶች

ከጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በትግራይ ኃይሎችና በመከላከያ ሠራዊት መካከል የተጀመረው የትጥቅ ግጭት ለወራት ከቀጠለ በኋላ፤ ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. የፌዴራሉ መንግሥት የተናጠል ተኩስ ማቆም ማድረጉን አሳውቆ ከትግራይ ክልል ዋና ከተማ መቀሌና አብዛኛው የትግራይ አካባቢዎች ለቅቆ ወጣ፡፡ የትግራይ ኃይሎችም በተከታይ ቀኖች የመቀሌን ከተማና ሌሎችም የተለቀቁ የትግራይ ክልል ቦታዎችን መቆጣጠራቸውን አሳወቁ፡፡

ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የትግራይ ኃይሎች በአጎራባች የአፋርና አማራ ክልል አካባቢዎች ላይ በከፈቱት ወታደራዊ ጥቃት በርካታ ቦታዎችን መቆጣጠር ጀመሩ፡፡ እስከ ጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የትግራይ ኃይሎች ከኦነግ ሸኔ ጋር ትብብር የፈጠሩ መሆኑንም በማሳወቅ ጭምር በአፋርና አማራ ክልሎች በርካታ ቦታዎችን ተቆጣጥረው ቆይተው ነበር፡፡ ከኅዳር ወር 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የፌደራሉ መንግሥት ከክልሎቹ መስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት በከፈቱት መጠነ ሰፊ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ፤ የትግራይ ኃይሎችና ኦነግ ሸኔ በአፋርና አማራ ክልል ተቆጣጥረዋቸው ከነበሩ ቦታዎች ወጥተው በፌዴራሉ መንግሥትና የክልሉ መስተዳድሮች ቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የትግራይ ኃይሎች በጥር ወር 2014 ዓ.ም. ጀምሮ በአፋር ክልል ዳግም በከፈቱት ወታደራዊ ጥቃት 5 ወረዳዎችንና የአብአላ ከተማን ተቆጣጥረው ይገኛሉ፡፡

ጦርነቱ በአብዛኛው ሲቪል ሰዎች በሚኖሩባቸው የከተማ እና ገጠራማ አካባቢዎች በመካሄዱ በጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች በተወሰዱ የኃይል እርምጃዎች ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሲቪል ሰዎች ሞተዋል፤ ለአካል እና ለሥነልቦና ጉዳት ተዳርገዋል፤ ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶችም ተፈጽመውባቸዋል፡፡ እንዲሁም በንብረት ላይ በተለይም በትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፣ የመንግሥት አስተዳደር ተቋማት እና በመሰረተ ልማቶች ላይ ሰፊ ዘረፋ እና ውድመት ተከስቷል፡፡ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችም ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው ለዘርፈ ብዙ ችግር ተጋልጠዋል፡፡ የኮሚሽኑ ምርመራ ግኝቶች በጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች በተለያየ ደረጃ የተፈጸሙ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን ያሳያሉ፡፡

## በሲቪል ሰዎች፣ ሲቪል ተቋማት እና ሌሎች ጥበቃ በሚደረግላቸው ሰዎች ላይ የደረሱ ጥቃቶች[1]

በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው በሲቪል ሰዎች ላይ በተለይም በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ጭምር እንዲሁም በሲቪል ሰዎች ቁሶች ላይ ተገቢው ጥንቃቄ ያልተደረገበት፣ የመለየት መርህን ያልተከተለና ያልተመጣጠነ ጥቃት ፈጽመዋል። ሲቪል ሰዎችን እንደከለላ በመጠቀም በመኖሪያ ቤቶች እና በከተሞች ውስጥ ጦርነት በማካሄድ በሲቪል ሰዎች ላይ ሞት፣ አካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት እንዲከሰት አድርገዋል። በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግን በሚጥስ መልኩ ከባድ መሳሪያዎችን ተኩሰዋል፤ የአየር እና የድሮን ድብደባዎችን ፈጽመዋል። ኮሚሽኑ በአፋር እና በአማራ ክልሎች ምርመራ ባደረገባቸው ሥፍራዎች ሆነ ተብለው የተፈጸሙ ሕገወጥ ግድያዎችን ሳይጨምር፤ በጦርነት ውስጥ በሲቪል ሰዎች ላይ በደረሰ የሕይወትና የአካል ጉዳት ብቻ ቢያንስ 403 ሲቪል ሰዎች ለሞት እንዲሁም 309 ሲቪል ሰዎች ለቀላል እና ከባድ የአካል ጉዳት ተዳርገዋል።

ለምሳሌ የትግራይ ኃይሎች ሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ከሌሊቱ 9:00 ሰዓት አካባቢ በአፋር ክልል ጋሊኮማ ቀበሌ የጋሊኮማ ተራራ ላይ ሰፍረው የነበሩ የአፋር ልዩ ኃይሎችን በሚያጠቁበት ወቅት ሲቪል ሰዎችን ሳይለዩ በፈጸሙት ጥቃት 27 ሕፃናትን ጨምሮ 107 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል፤ 35 ሰዎች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት አድርሰዋል። ከዚህ በተጨማሪም የትግራይ ኃይሎች በአማራ ክልል እና በአፋር ክልል የሚገኙ በርካታ ከተሞችን ከመቆጣጠራቸው አስቀድሞ ከተሞች ላይ በተኮሷቸው ከባድ መሳሪያዎች ሲቪል ሰዎች እንዲሞቱ እና እንዲቆስሉ አድርገዋል፤ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገባ የሲቪል ሰዎችን መኖሪያ ቤቶችን፣ የትምህርት፣ ጤና እና የሕዝብ አስተዳደር ተቋማትን እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማትን አውድመዋል። የትግራይ ኃይሎች ከነሃሴ 12 እስከ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. በደባርቅ ወረዳ የአዲጋግራ፣ የአብርሃም እና የአዳጋት ቀበሌዎችን በመያዝ፤ የአርሶ አደሮችን ቤት እንደ ምሽግ አድርገው በመዋጋታቸው በመከላከያ ሠራዊት በተተኮሱ ከባድ መሳሪያዎች 6 ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል። የትግራይ ኃይሎች በአማራ ክልል በወረባቡ ወረዳ በቆዩባቸው ቀናት የተለያዩ ፈንጂዎችን ቀብረው እና በሜዳ ጥለው በመሄዳቸው 5 ሕፃናት ሲሞቱ፣ 1 ሕፃን አካል ጉዳት ደርሶባታል።

በሌላ በኩል የመከላከያ ሠራዊት በአማራ ክልል ወልዲያ ከተማ ታኅሣሥ 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 9:00 ሰዓት ከሕዝብ ጋር ተቀላቅለው የነበሩ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ላይ በፈጸመው የድሮን ጥቃት በአንድ ሕንፃ በረንዳ ላይ ሻይ ቡና፣ ምግብ፣ ውሃ የሚሸጡ በተለምዶ 'ሱቅ በደረቴ' በመባል የሚጠሩ የጎዳና ላይ ነጋዴዎች እና አገልግሎት በመጠቀም ላይ የነበሩ 6 ሲቪል ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 4 ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል።

በሪፖርቱ ላይ በዝርዝር እንደተመለከተው የትግራይ ኃይሎች ሲቪል ሰዎችንና አካባቢዎችን እንደከለላ በመጠቀም፣ ፈንጂዎችን ያለልዩነትና ጉዳት በሚያደርስ መልክ በመጠቀም እንዲሁም ሁለቱም

[1] Attacks on civilians and civilian objects which enjoy special protection under international humanitarian law

ተፋላሚ ወገኖች ሲቪል ሰዎችንና ተቋሞችን ከጉዳት ለመከላከል ተገቢውንና የተሟላ ጥንቃቄ ባለማድረግ ባካሄዱት ጦርነት ለብዙ ሲቪል ሰዎች ሕይወት መጥፋት፣ የአካል ጉዳት፣ ንብረት እና መሰረተ ልማት ውድመት እና መፈናቀል ምክንያት ሆነዋል፡፡

## ሕገወጥና ከዳኝነት ውጪ የተፈጸመ ግድያ[2]

ኢሰመኮ ምርመራ ባደረገባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች በጦርነቱ ተሳታፊ በሆኑ ኃይሎች በተለይም እና በዋነኝነት በትግራይ ኃይሎች ቢያንስ 346 ሲቪል ሰዎች በሕገወጥ መንገድ ተገድለዋል፡፡ የትግራይ ኃይሎች ይህን መሰሉን ሕገወጥ ግድያ ሲፈጽሙ ምክንያት ሲያደርጉ የነበረው ተጠቂዎቹን "ለመንግሥት ኃይሎች ሰላይ ናችሁ፤ የግላችሁን የጦር መሳሪያ አምጡ፤ ንብረት እንዳይወሰድ ተከላክላችኋል፤ የመከላከያ፣ የልዩ ኃይል ወይም የፋኖ ታጣቂዎችን አግዛችኋል" ወይም "የት እንዳሉ ታውቃላችሁ" ወይም "የነዚሁ አባላት የሆኑ ሰዎች ቤተሰብ ናችሁ" በሚል ምክንያትና፣ እንዲሁም አካባቢዎቹን በሚቆጣጣሩበት ወቅት በትግራይ ኃይሎች ላይ ለደረሰባቸው ጥቃት ወይም የትግራይ ታጣቂዎች እና ትግራይ ላይ ለደረሰ ሞት እና ጉዳት የበቀል/አጸፋ እርምጃ መሆኑን ጭምር በግልጽ እየተናገሩ ብዙ ሲቪል ሰዎችን በጅምላ እና በነጠላ ገድለዋል፡፡ በተመሳሳይ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች በተቆጣጠሯቸው ስፍራዎች በነበሩ የመንግሥት አስተዳደር ኃላፊዎች እና ቤተሰቦቻቸው ላይ እንዲሁም መንግሥትን ይደግፋሉ ያሏቸው ሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ግድያን ፈጽመዋል፡፡ በሌላ በኩል የመከላከያ ሠራዊት፣ የአማራ ልዩ ኃይል፣ ፋኖ እና ሚሊሺያዎችም የትግራይ ኃይሎች እና ኦነግ ሸኔ አባላት ወይም ደጋፊ ናቸው በሚል የጠረጠሯቸው ሰዎች ላይ ሕገወጥና ከዳኝነት ውጪ የሆኑ ግድያዎችን ፈጽመዋል፤ የአካል ጉዳትም አድርሰዋል፡፡

ከሕገወጥ ግድያዎች ውስጥ ለምሳሌ፤ የትግራይ ኃይሎች በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ዳባት ወረዳ ጭና ቀበሌ ከነሃሴ 24 እስከ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. በቀበሌው በቆዩበት ወቅት ቢያንስ 47 ሲቪል ሰዎችን (41 ወንዶች እና 6 ሴቶች) ገድለዋል፡፡ ሟቾች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የተረሸኑ፣ እንዲሁም ተይዘው እጆቻቸውን ወደኋላ ታስረው የተገደሉ ሲሆን በተለይም የመንግሥት ኃይሎች ወደ ቀበሌው እየተቃረቡ በመምጣታቸው የትግራይ ኃይሎች ከአካባቢው ሲያፈገፍጉ በየቤቱ እና በየሰፈሩ ያገኟቸውን ነዋሪዎች እየገደሉ ሄደዋል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ሸዋ ዞን በአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ አሰለሴ ቀለበት ወንበር ቀበሌ አምቦውሃ ጎጥ ኅዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ለቀብር የተሰበሰቡ ሲቪል ሰዎች ላይ በመተኮስ እና ቤት ለቤት በመግባት 40 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል፡፡ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት በአፋር ክልል ካሳጊታ ከተማ አትኮማ አካባቢ የ9 ዓመት ሕፃን እና የ18 ዓመት ወጣት ሴት በትግራይ ኃይሎች ደረት እና ጭንቅላታቸው ላይ በጥይት ተመትተው ተገድለዋል፡፡ በአጣዬ ከተማ የ01 ቀበሌ ኅዳር 14 ቀን 2014 ዓ.ም. የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች የቀበሌው አመራር የነበሩ ግለሰብን አባት እና ወንድም ልጃችሁን አምጡ በሚል ከያዟቸው በኃላ ልዩ ስሙ ቆሮ ከሚባል ቦታ ላይ ገድለዋቸዋል፡፡

[2] Unlawful or extra-judicial killings

በሌላ በኩል በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ደዋ ጨፋ ወረዳ ልዩ ቦታው እንቶሊ አካባቢ በታኅሣሥ ወር 2014 ዓ.ም. የመከላከያ ሠራዊት ወታደሮች ቁጥራቸው ወደ 30 የሚጠጉ ሰዎችን በጅምላ በጥይት ደብድበው ገድለዋል፡፡ ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን በላስታ ወረዳ 024 ቀበሌ ዳቦ ከተማ የአማራ ልዩ ኃይል አባላት የትግራይ ኃይሎችን ቀልባችኋል በሚል የተዘጋ መኖሪያ ቤት ላይ ተኩሰው አንድ እናትን ግራ እግሯ ላይ፤ ሕጻን ልጇን ደግሞ ግራ እጇ ላይ በጥይት የመቷት ሲሆን፤ ሕጻኗ ሕክምና በማጣቷ ደም ፈሷት ሞታለች፡፡ በሸዋ ሮቢት ከተማ ኅዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎችን ደግፋችኋል በሚል አራት ወንድ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ሲቪል ሰዎች በፋኖና በአርሶ አደር ታጣቂዎች ተገድለዋል፡፡

## የጭካኔ፣ ኢሰብአዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት[3]

የትግራይ ኃይሎች በቁጥጥራቸው ስር በገቡ የአፋር እና አማራ ክልል አካባቢዎች ነዋሪዎችን ገንዘብ አምጡ፣ መረጃ አምጡ፣ የደበቃችሁትን መሳሪያ አውጡ፣ በሚሉና የመሳሰሉ ምክንያቶች በሲቪል ሰዎች ላይ በጭካኔ የመደብደብ፣ የማዋረድ እና የማሰቃየት ተግባር ፈጽመዋል፡፡ ለምሳሌ በጋሸና ከተማ ኅዳር 3 ቀን 2014 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አንድ ግለሰብን ገንዘብ እንዲሰጣቸው ለማስገደድ ከደበደቡት በኋላ በወንዝ ውሃ ውስጥ በመድፈቅ አሰቃይተዋል፤ እግሩ ላይ ሚስማር መትተው አሰቃይተዋል እንዲሁም ብልቱን በካራ ተልትለዋል፡፡ ወደ ተጎጂው ቤት በመሄድ ገንዘቡን ከወሰዱ በኋላም ሚስቱን በመደብደብ አሰቃይተዋል፡፡ ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. በአማራ ክልል ወረባቡ ወረዳ ቀበሌ 020 የትግራይ ኃይሎች የ20 ዓመት ወጣት እንስሳትን በመጠበቅ ላይ እያለ “የሶዶማ አካባቢ ተዋጊዎችን ትመስላለህ” በሚል ድብደባ እና ማሰቃየት ካደረሱበት በኋላ በጥይት ተኩሰው ገድለውታል፡፡ የትግራይ ኃይሎች በወረዳው 6 ቀበሌዎች ውስጥ በ10 ሰዎች (8 ወንዶች እና 2 ሴቶች) ላይ ድብደባ እና የአካል ጉዳት አድርሰዋል፡፡ የአካል ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል በቀበሌ 018 ነዋሪ የሆነ የ30 ዓመት ወጣት ሐምሌ 25 ቀን 2013 ዓ.ም የትግራይ ኃይሎች ከቤቱ በመውሰድ እግሩን እና እጁን ገልብጠው በማሰር እስከ ነሃሴ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ታስሮ በቆየበት ወቅት በተለያየ ጊዜ ድብደባ የፈጸሙበት ሲሆን በድብደባውም ጉዳት እንደደረሰበት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## የዘፈቀደ እስር፣ ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወር[4]

የጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች ዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶችን እና የሰብአዊነት ሕጎችን ድንጋጌ በሚጥስ መልኩ የዘፈቀደ እስር፣ ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወር ፈጽመዋል፡፡ የትግራይ ኃይሎች ዓለም አቀፍ የጦር ወንጀልን እና በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ሊያቋቁም በሚችል መልኩ የእገታ እና አስገድዶ መሰወር ተግባራትን የፈጸሙ ሲሆን፣ የፌዴራል፣ አማራ እና የአፋር ክልል የፀጥታ

[3] Torture and other cruel, inhuman, and degrading treatment or punishment

[4] Arbitrary detentions, abduction, and enforced disappearances

ኃይሎች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ዐውድ ውስጥም ቢሆን የጥብቅ አስፈላጊነት፣ ተመጣጣኝነት እና ከመድልዎ ነፃ መሆን መርሆዎች ከሚፈቅዱት ውጪ መጠነ ሰፊ የዘፈቀደ እስር ፈጽመዋል፡፡

በአማራ ክልል ዳባ ከተማ ኅዳር 4 ቀን 2014 ዓ.ም. "የአመራርና የሚሊሺያ ስምና ቤት ጠቁም" በማለት በትግራይ ኃይሎች የተያዘ አንድ ሰው ቀኑን ሙሉ በገመድ ከዛፍ ጋር እንደታሰረ፣ ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ተፈቶ ባዶ ቤት ያለምግብ አሳድረውት፤ በነጋታው ከሌላ ታሳሪ ጋር በግዳጅ ተወስደው ታጣቂዎቹ በሚሄዱበት ሁሉ የጦር መሳሪያና ጥይት ሲያሸክሟቸው እና ውሃ ሲያስቀዷቸው ቆይተው ከሦስት ሳምንት በኋላ እንደተለቀቁ ለኮሚሽኑ አስረድቷል፡፡ በአፋር ክልል ቡርቃ ቀበሌ ሙዴና አካባቢ ለገበያ የመጡ 8 ሰዎች በትግራይ ኃይሎች በግዳጅ የተወሰዱ ሲሆን ኮሚሽኑ ምርመራውን እስካከናወነበት ጊዜ ድረስ ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን አያውቁም፡፡

ከታገቱ በኋላ ኢሰብአዊ ድርጊት የተፈጸመባቸው እና የተገደሉም ይገኙበታል፡፡ ለምሳሌ የትግራይ ኃይሎች አጣዬ ከተማን ኅዳር 6 ቀን 2014 ዓ.ም ሲቆጣጠሩ 01 ቀበሌ ነዋሪ የነበሩ አንድ ነጋዴ ቤት በመግባት እና ግለሰቡን በማገት ለ5 ቀናት ከቆዩ በኋላ አጣዬ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ስሙ ኤፌሶን ቁጥር 2 ትምህርት ቤት ውስጥ ‹‹ፋኖ ትቀልባለህ፣ ወታደር ታበላለህ፣ ቤትህ የወታደር ካምፕ ነው›› በሚል ምክንያት ኅዳር 10 ቀን 2014 ዓ.ም. ለኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች አሳልፈው ሰጥተዋቸው ኅዳር 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ጃራ ዎታ በሚባል ቦታ ላይ ተገድለዋል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ከትግራይ ኃይሎች ጋር ሊተባበሩ ይችላሉ፤ የፀጥታ ስጋት ናቸው በሚል በሺዎች የሚቆጠሩ በተለይ የትግራይ ተወላጆችን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ተፈጻሚነት ካላቸው የሰብአዊ መብቶች መርሆዎች ውጪ አስረው አቆይተዋል፤ በርካቶችም ያሉበት ሳይታወቅ፤ የቤተሰብ እና የሕግ ባለሙያ ጉብኝት ተነፍገው ለወራት ቆይተው ነበር፡፡

**ወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃቶች[5]**

የትግራይ ኃይሎች በአፋርና አማራ ክልሎች የሚገኙ ቦታዎችን ተቆጣጥረው በቆዩበት ጊዜ መጠነ ሰፊ፣ ጭካኔ የተሞላበትና እና ስልታዊ የሆነ በተናጠል እና በቡድን የተፈጸመ የአስገድዶ መድፈር ጥቃት በሴቶች፣ በሕፃናት ሴቶችና አረጋዊያን ሴቶች ላይ አድርሰዋል፡፡

ለምሳሌ በደቡብ ጎንደር ዞን ጋይንት ወረዳ ንፋስ መውጫ ከተማ ሁለት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አስገድደው ደፍረዋት ብዙ ደም የፈሰሳት ሴት በጓደኛዋ ቤት ስታገግም ቆይታ ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ አክስቷ ቤት ስትሄድ በመንገድ ያገኟት ሌሎች የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በድጋሚ አስገድደው ሊደፍሯት ሲወስዷት ስለነበረው ሁኔታ ስታስረዳ፡

[5] Sexual and gender-based violence (SGBV)

*“አንደኛው ታጣቂ ሊደፍረኝ ሱሪዬን ሲያወልቅ ደም ሲመለከት አስጠላሁት እና ተፋብኝ፤ ሰደበኝ እኔም ተስፋ ቆርጬ ራሴን ላጠፋ እያሰብኩ ስለነበር አልፈራሁትም፤ መልሼ ስሰድበው ተናዶ የጠመንጃውን አፈ ሙዝ በማህፀኔ ውስጥ ከተተው:: ሕመሙ ከአቅም በላይ ስለነበር ራሴን ሳትኩ:: አሁን ለፊስቱላ በሽታ ሕክምና እየተከታተልኩ ነው::” ብላለች::*

በሸዋ ሮቢት ከተማ በትግራይ ኃይሎች የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ከደረሰባቸው ተጎጂዎች መካከል የ34 ዓመት ሴት ጥቃቱ በተፈጸመባት ማግስት በገመድ ታንቃ ሞታ የተገኘች ሲሆን፤ በደረሰባት ጥቃት የተነሳ ሕይወቷን አጥፍታ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል::

በአማራ ክልል ሀይቅ ከተማ ነዋሪ የሆነች ተጎጂ አራት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች እየተፈራረቁ የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ፈጽመውባት መንግሥት ቦታውን ከተቆጣጠረ በኋላ ሕክምና ስታደርግ በተላላፊ በሽታ መያዟ የተነገራት መሆኑን አስረድታለች::

በመሀል ሜዳ መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ቀበሌ 03 የቡድን አስገድዶ መድፈር ጥቃት የደረሰባት የ20 ዓመት ተጎጂ ቀኑን በማታስታውሰው ዕለት ሻይና ቡና ንግድ በምትሰራበትና በምትኖርበት የኮንቴይነር ቤት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በመምጣት አብረዋት የነበሩትን የ80 ዓመት አባቷን አውጥተው ውጪ ግንድ ላይ አስረው የ2 ዓመት ሕፃን ልጇ ባለበት ለ3 እንደደፈሯት አስረድታለች::
በደባርቅ ወረዳ ድብባህር በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በተደጋጋሚ አስገድዶ መድፈር ተጎጂ የሆነች ሴት ስታስረዳ

*“በየተራ እየመጡ ይደፍሩኝ ነበር:: ሲደፍሩኝ፣ የእናንተ ሰዎች የእኛን ሴቶች ለ10 ሆነው ነበር የሚደፍሩት ይሉኝ ነበር:: እኛ እነሱን ለመበቀል ነው የመጣነው እንጂ በአክሲል ነበር የምንዳረው ይላሉ:: እየተመላለሱ 15 ታጣቂዎች ደፍረውኛል” በማለት አስረድታለች::*

በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን ያሎ ወረዳ ነዋሪ የሆነች ተጎጂ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂ ቤቷ መጥቶ የባሏን መሳሪያ እንድትሰጠው ሲጠይቃት ባለቤቷ ምንም አይነት መሳሪያ እንደሌለው በመግለጿ ካራ አውጥቶ ሊወጋት ሲል ይተወኛል በሚል ብር እንደሰጠችውና ብሩን ከወሰደ በኋላ ግን በልጆቿ ፊት አስገድዶ እንደደፈራት አስረድታለች::

በአማራ ክልል ከሚሴ ከተማ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ፈጽመዋል:: ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ለፍተሻ በገቡበት መኖሪያ ቤት የነበረችን ሴት ብሔሯ አማራ መሆኑን ጠይቀው ከተረዱ በኋላ ደብድበው በቡድን በመሆን አስገድደው ደፍረዋታል፤ ቤቷ ውስጥ የነበረ ገንዘብም ወስደውባታል::

የትግራይ ኃይሎች በሁለቱም ክልሎች ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ስፍራዎች የቤት ለቤት ብርበራ ሲፈጽሙ እንደነበር እና ሴቶችን የመከላከያ፣ የአማራ ልዩ ኃይል እና የፋኖ ሚስት ናችሁ በማለት

የማንገላታት፣ ምግብ እንዲያበስሉ የማስገደድ እና በተናጠልና በቡድን የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ይፈጽሙባቸው እንደነበር ኮሚሽኑ በርካታ ማስረጃዎች የሰበሰበ ሲሆን ቢያንስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶች የጥቃቱ ሰለባ እንደሆኑ ይገመታል፡፡

ሆኖም ተጎጂዎች የደረሰባቸው ወሲባዊ ጥቃት በማኅበረሰቡ ከታወቀ ሊደርስባቸው የሚችለውን መድሎ እና መገለል በመፍራት ብዙውን ጊዜ ጉዳታቸውን ለመናገር የማይፈልጉ በመሆኑ ኮሚሽኑ ብዙ ተጎጂዎችን ለማነጋገር ባለመቻሉ የጥቃቱ ስፋት በዚህ ሪፖርት ከተመለከተው በእጅጉ ከፍ ያለ እንደሚሆን ኮሚሽኑ ያምናል፡፡

በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በአፋርና አማራ ክልሎች ተስፋፍተው የተፈጸሙ ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃቶች የተጎጂዎችን እና የጥቃቱ ዒላማ የተደረጉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ሰብአዊ ክብር ለመጉዳት እና ለማዋረድ፣ በአብዛኛው በሴቶች ላይ በሙሉ ያለልዩነት፣ አልፎ አልፎም አጥቂዎቹ ሆነ ብለው ለጥቃቱ ዒላማነት በመረጧቸው ሴቶች ላይ ሆነ ተብሎ ታቅዶ በግፍና በጭካኔ፣ በግልጽ የበቀል ስሜት፣ በቡድን አስገድዶ በመድፈር፣ ድርጊቱን ሆነ ተብሎ በቤተሰብ ፊት በመፈጸምና፣ ባዕድ ነገር (የጠብ መንጃ አፈ ሙዝ) በማህፀን በመክተት ጭምር፣ በታጣቂዎቹ ኃላፊዎች ይሁንታ እና ዝምታ የተፈጸመ በመሆኑ፤ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በሴቶች ላይ የፈጸሙት ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃትን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለጦርነት አላማ እንዳዋሉት የሚያስረዳ ነው፡፡ እነዚህ የመብት ጥሰቶችም በጦርነት ዐውድ ውስጥ የተፈጸሙ በመሆናቸው የጦር ወንጀልም ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

### የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች[6]

በትግራይ ክልል የነበረው ጦርነት ወደ አጎራባች ክልሎች መስፋፋቱን ተከትሎ በተለይም የትግራይ ኃይሎች በአማራ እና አፋር ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ወራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች ከቤታቸውና መኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለው ለከፍተኛ አካላዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሌሎች ጉዳቶች ተዳርገዋል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት በተፈጠረው የፀጥታ ስጋት እና በትግራይ ኃይሎች በተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እና የንብረት ዝርፊያዎች ነዋሪዎች ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆነዋል፡፡

ተፈናቃዮች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከመለያየት በተጨማሪ፤ የምግብ፣ የአልባሳት፣ የመኝታ፣ የጤና አገልግሎቶች የመሳሰሉ የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦቶች የተሟሉላቸው ባለመሆኑ፤ በተለይም የሴቶች ንጽሕና መጠበቂያ፣ ለሕፃናት፣ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ እና የተሟላ አቅርቦት ባለመኖሩ ልዩ ድጋፍ የሚሹትን የሕብረተሰብ ክፍሎች ችግር ይበልጥ አባብሶታል፡፡

በርካታ ተፈናቃዮች ወደመኖሪያ አካባቢያቸው በተመለሱበት ወቅትም፤ የመኖሪያ ቤቶቻቸው እና ልዩ ልዩ ንብረታቸው፣ የእርሻ ማሳዎች እንዲሁም የአካባቢያቸው መሰረታዊ አገልግሎት ተቋማት

[6] Internally Displaced Persons (IDPs)

በመዘረፋቸው እና በመውደማቸው ምክንያት ተመላሽ ተፈናቃዮች የምግብ እጥረት፣ የሕክምና አገልግሎት ማጣትን ጨምሮ ለተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋልጠዋል፡፡

**በንብረት ላይ የተፈጸመ ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ውድመት**[7]

በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ እና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በተደራጀ መልኩ የትግራይ ኃይሎች በመንግሥት አስተዳደር ተቋማት፣ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (በተለይ የጤና ተቋማት እና የትምህርት ተቋማት) ፣ በግል ንብረቶች እና በንግድ ተቋማት ላይ መጠነ ሰፊ ዘረፋ፣ ገፈፋ እና የንብረት ውድመት ፈጽመዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ሕግና ሥርአት መፍረሱን ተከትሎ የተወሰኑ የየአካባቢዎቹ ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎችም በዝርፊያው ተግባር ተሳትፈዋል፡፡

በአብዛኛዎቹ ምርመራ በተደረገባቸው አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች ሆነ ተብሎ በታቀደ፣ በተጠና፣ በተደራጀ መንገድ ስልታዊ የዘረፋና ገፈፋ ተግባር በተለይ የሕክምና መሳሪያ ቁሳቁስ፣ ማሽኖችን እና የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመዝረፍና በመግፈፍ፣ በመኪና በመጫን ወስደዋል፡፡

በተለይም ከሆስፒታሎች እና የሕክምና መስጫ ተቋማት መድኃኒቶችን፣ እንደ ኤክስ ሬይ፤ አልትራ ሳውንድ፤ የደም መመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ ማሽነሪዎች፣ አምቡላንሶች እና ሌሎችም የሕክምና መሳሪያዎች ተዘርፈው ተወስደዋል፡፡ በተለይ በሕክምና መሳሪያዎች እና ማሽኖች ላይ የተፈጸመው ዝርፊያ በባለሙያ እየታገዘና ማሽኖቹ በጥንቃቄ እየተፈቱና እየተነቀሉ ተወስደዋል፡፡
በአማራ ክልል 40 ሆስፒታሎች፣ 453 ጤና ጣቢያዎች፣ እና 1850 የጤና ኬላዎች (በድምሩ በአማራ ክልል ብቻ 2343 የጤና ተቋማት) ፤ እንዲሁም በአፋር ክልል 2 ሆስፒታሎች፣ 19 ጤና ጣቢያዎች እና 45 የጤና ኬላዎች (በድምሩ በአፋር ክልል 66 የጤና ተቋማት) ፤ በአጠቃላይ በሁለቱ ክልሎች በ 2409 የጤና ተቋማት ላይ ጥቃት፣ ጉዳትና ዝርፊያ በመድረሱ አገልግሎታቸው ተቋርጧል፡፡ (ከጤና ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ)[8]

በአማራ ክልል 1025 ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ፤ 3082 ደግሞ በከፊል ወድመዋል፡፡ በአፋር ክልል 65 ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ሲወድሙ 138 ደግሞ በከፊል ወድመዋል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱ ክልሎች 1090 ት/ቤቶች ሙሉ በሙሉ 3,220 ደግሞ በከፊል ወድመዋል፡፡ (ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ)[9]

[7] Pillage, looting, and destruction of property
[8] ከጤና ሚኒስቴር በቀን 10/06/2014 በተላከ ደብዳቤ
[9] ከትምህርት ሚኒስቴር በቀን 24/06/2014 በተላከ ደብዳቤ

በፋይናንስ ተቋማት በተለይም በ18 የንግድ ባንኮች 346 ቅርንጫፎች ላይ በቢሊዮን ብሮች የሚቆጠር ዘረፋ እና ውድመት ደርሷል። (ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገኘ መረጃ)[10]

የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸው አንዳንድ አካባቢዎች የዘረፋ እና የንብረት ውድመት በፈጸሙባቸው የሕዝብ አስተዳደር ተቋማትና የግለሰብ ንብረቶች እንዲሁም ለወታደራዊ ካምፕ እና ሌሎች አገልግሎቶች የተጠቀሟቸው ትምህርት ቤቶች፣ ታሪካዊ ስፍራዎች እና ጤና ተቋማት ግድግዳዎች ላይ የስድብ መልዕክቶችን በመፃፍ እና በሕንጻዎች ወለል ላይ፣ ጠረጴዛና መሳቢያዎች እንዲሁም ወንበሮች ላይ ሆነ ተብሎ በመጸዳዳት ጭምር አበላሽተዋል። በዚህ ረገድ ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል የደሴ ንጉስ ሚካኤል ቤተመንግሥት (አይጠየፍ አዳራሽ) የንጉስ ኢያሱ እልፍኝ አዳራሽ በሚል በሚጠራው ቤት ላይ እና በአጣዬ ከተማ ጤና ጣቢያ ላይ የደረሱት ብልሽቶች የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህ ምርመራ በተመለከታቸው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የበርካታ ሰዎች የንግድ መደብሮች እና የመኖሪያ ቤቶች የሚገኙ ከዕለት የምግብ ፍጆታና አልባሳት ጀምሮ እስከ ንግድ እቃዎች እና ሸቀጦች፤ አላቂ የምግብ ፍጆታዎች፣ እህሎች፣ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ የቤት እንስሳትና ሰብሎች እንዲሁም ገንዘብ በትግራይ ኃይሎች ተዘርፈው ተወስደዋል፣ የቀንድ እና የጋማ ከብቶችን በጥይት መትተው ገድለዋል።

በሌላ በኩል በተለይም በአማራ ክልል የትግራይ ኃይሎች ተቆጣጥረዋቸው ከነበሩ ስፍራዎች ከለቀቁ በኋላ በአንዳንድ አካባቢዎች ከትግራይ ኃይሎች ጋር ተባብረዋል የተባሉ ሰዎች እና ለደኅነታቸው በመስጋት ከተሞቹን ጥለው በሸሹ የትግራይ ተወላጆች ንብረቶች በልዩ ልዩ የመንግሥት ታጣቂዎችና በተወሰኑ የየአካባቢው ነዋሪ ሰዎች ተዘርፈዋል። በወቅቱ በስፍራው የነበሩ የፌደራል መንግሥት እና የአማራ ክልል የፀጥታ ኃይሎች በቂ ጥበቃና የመከላከል እርምጃ አልወሰዱም። ለምሳሌ በሸዋ ሮቢት ከተማ ውስጥ የትግራይ ተወላጆች መኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ድርጅቶች በተወሰኑ የአካባቢው ነዋሪ ሰዎች ተዘርፈዋል። እንዲሁም በሰንበቴ ከተማ ጃሪ ዋታ የገጠር ቀበሌ የፋኖ አባላት የሆኑ ሰዎች አንዳንድ መኖሪያ ቤቶችን እየሰበሩ መዝረፋቸውን፤ በአጣዬ ከተማም የግለሰቦች ቤቶች ተሰብረው ዘረፋ መፈጸሙን ነዋሪዎች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

## የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ክልከላ[11]

በትግራይ፣ በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ በጦርነቱ ምክንያት ከፍተኛ ሰብአዊ ቀውስ የተከሰተ ሲሆን፣ የሰብአዊ እርዳታ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በተለይ በአፋር ክልል ጦርነቱ አሁንም በመቀጠሉ ምክንያት በአፋር እና ትግራይ ክልሎች ሰብአዊ እርዳታን ለማድረስ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል። የጦርነቱ እና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታ ለሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት የፈጠረው እንቅፋት የሚታወቅ ቢሆንም፤ በተለይ ወደ ትግራይ ክልል የሚደርሰው ሰብአዊ እርዳታ ላይ በፌደራል

[10] ከኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ በቀን 24/06/2014 በተላከ ደብዳቤ
[11] Denial of access to humanitarian assistance

መንግሥት እና በክልል መንግሥታት የሚደረጉ አስተዳደራዊና ቢሮክራሲያዊ መስፈርቶችና የስራ ሂደቶች አስፈላጊው እርዳታ በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት እንዳይደርስ እንቅፋት ሆኗል።

የፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ለኢሰመኮ በሰጠው መረጃ እስከ ጥር 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ የመንግሥትና የአጋር ድርጅቶችን የእርዳታ ስራ በማስተባበር ከ 8 ሚሊዮን በላይ ለሆኑ በጦርነቱ ምክንያት እርዳታ ላስፈለጋቸው ሰዎች የምግብና ሌሎች አይነት አስፈላጊ እርዳታዎች መቅረቡን፤ በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግሥት እርዳታ እንዳይደርስ የተደረገ ክልከላ አለመኖሩንና ሆኖም በጸጥታ መደፍረስና በጦርነቱ ምክንያት የእርዳታ አቅርቦት መስተጓጎል እንደሚያጋጥም ገልጿል[12]።

የአፋርና አማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩበት ወቅት ወደ ስፍራዎቹ መድረስ አስቸጋሪ የነበረ እና በተወሰነ መጠን ሲደርስ የነበረው ሰብአዊ እርዳታ በጣም ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን፤ ለዚህም ዋነኛው ምክንያቶች የጦርነት ሁኔታው፣ የግጭቱ ተሳታፊ ኃይሎች ያስቀመጧቸው ኬላዎች እና በእርዳታ አቅርቦቱ እና ሰራተኞች ደኅንነት ላይ የነበረው ስጋት መሆኑ ይገለጻል። የአፋርና አማራ ክልል አብዛኛዎቹ ስፍራዎች በፌደራል እና በክልሎቹ መንግሥታት ቁጥጥር ስር ከገቡ በኋላ የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት የተሻሻለ ቢሆንም ካለው ፍላጎት አንፃር በቂ እንዳልሆነ ኮሚሽኑ ተገንዝቧል።

### ኢኮኖሚያዊ፡ ማኅበራዊና የባሕል መብቶች[13]

ለዓመታት የተገነቡ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመት በመድረሱ ምክንያት የሰዎች የጤና መብት፣ በቂ ምግብ፣ ውሃ እና የንጽሕና ሁኔታ የማግኘት እና የትምህርት መብቶች ላይ እንዲሁም እንደ የኤሌትሪክ ኃይል፣ ባንክ እና ስልክ የመሳሰሉ መሰረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ ጉዳት ደርሷል። የትግራይ ኃይሎች ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የአማራ እና አፋር ክልሎችን የተለያዩ አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ጊዜያት በመንግሥት ተቋማት እና በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል።

በነዋሪዎች የመኖርያ ቤቶች፤ እርሻዎች እና የቤት እንስሳት ላይ ባደረሱት ዝርፊያና ውድመት ነዋሪዎቹን ለመጠለያና ለምግብ ችግር አጋልጠዋል። በተለይም በጤና እና ትምህርት ተቋማት ላይ በደረሰው ዝርፊያ፤ ውድመት እና ቃጠሎ የየአካባቢው ነዋሪዎች የጤና እና ትምህርት አገልግሎት ማግኘት እንዳይችሉ ያደረገ ሲሆን፣ በርካታ ነፍሰጡር እናቶች በሕክምና እጦት ሕይወታቸው አልፏል። ለአብነትም በአማራ ክልል መቄት ወረዳ ሸሆድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በወረዳው የሚገኝ ብቸኛ ሆስፒታል ሲሆን በደረሰበት ሰፊ ዘረፋ እና ውድመት ምክንያት አገልግሎት መስጠት በማቆሙ በወረዳው 8 ነፍሰጡር እናቶች በሕክምና ማጣት ሕይወታቸው አልፏል።

[12] የፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በቀን 16/06/2014 ቁጥር-H2-መመ-35/2 በተላከ ደብዳቤ
[13] Economic, social, and cultural rights

## በሕፃናት ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶች[14]

በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች በጦርነቱ ተሳታፊ አካላት በተወሰዱ የኃይል እርምጃዎች ሕፃናት ለሞት፣ ለአካል እና ለሥነ ልቦና ጉዳት እንዲሁም ለወሲባዊ ጥቃት ተጋልጠዋል፤ የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች በመውደማቸው የጤና፣ የትምህርት እና በቂ የኑሮ ሁኔታ የማግኘት መብቶቻቸው ተጥሰዋል። ወላጆቻቸው እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት ላይ የተፈጸሙ ግድያዎች፣ ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃቶች፣ የአካል ጉዳቶች፣ እንዲሁም በርካታ ሲቪል ሰዎች በጦርነቱን ምክንያት የተፈናቀሉ በመሆኑ ካስከተለው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነልቦና ጉዳት በተጨማሪ፤ ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸው ሊያገኙት ይገባ የነበረውን ጥበቃ እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል። የሕክምና ተቋማት በመውደማቸው እና በመዘረፋቸው በቂ ሕክምና ለማግኘት ሳይችሉ ሕይወታቸው ያለፈ ሕፃናትም አሉ።

በጦርነቱ ተሳታፊ አካላት በተወሰዱ የኃይል እርምጃዎች በርካታ ሕፃናት ተገድለዋል፤ በአቅራቢያቸው ያሉ ሕክምና ተቋማት በመውደማቸው እና በመዘረፋቸው በቂ ሕክምና ለማግኘት ሳይችሉ ሕይወታቸው ያለፈ ሕፃናትም ነበሩ።

የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በአማራ ክልል ጭና ቀበሌ አንድን አባት ከገደሉ በኋላ የ7 ዓመት ሕፃን ልጃቸውንም “ይህ አድጎ ነው የሚወጋን” ብለው በእናቱ ፊት በጥይት ተኩሰው ገድለዋል። በተዋጊ ኃይሎች በተፈጸሙ ሲቪል ሰዎችን ባልለዩ፣ ጥንቃቄ ባልታከለባቸው እና ተመጣጣኝ ባልሆኑ የከባድ መሳሪያ ጥቃቶች በርካታ ሕፃናት ተገድለዋል፤ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ሐሙሲት ከተማ በመከላከያ ሠራዊት የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ አንድ የ2ሁለት ዓመት ሕፃን እና አባት ሲገደሉ ሌሎች ሁለት የቤተሰቡ አባላት ደግሞ ቆስለዋል። በዚሁ ከተማ አካባቢ በመኖሪያ ቤት ላይ ያረፈ ሌላ ከባድ መሳሪያ የ5 እና የ16 ዓመት እህትማማቾችን ገድሏል። በአማራ ክልል ዳባት ወረዳ በድብ ባሕር ንዑስ ወረዳ እንጨት ለመልቀም የወጣችን የ14 ዓመት ታዳጊ ሕፃን ሁለት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች “የእናንተ ወታደሮች የእኛን እናቶች አእና እህቶች ደፍረዋል፤ ስለዚህ እናንተም መደፈር አለባችሁ” ብለው በጥፊ ከመቷት በኋላ አንደኛው ታጣቂ አስገድዶ እንደደፈራት ተጎጂዋ አስረድታለች።

## የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን[15]

በጦርነቱ ተፋላሚ ኃይሎች በተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ምክንያት በርካታ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ተገድለዋል፤ የአካል እና የሥነ ልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ እንዲሁም አረጋዊያን ሴቶች በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ወሲባዊ ጥቃቶች ተፈጽሞባቸዋል። በተጨማሪም ቤት ንብረታቸው ወድሟል እንዲሁም በሚጦሯቸው እና በሚደግፏቸው ቤተሰቦቻቸው

[14] Violations against children
[15] Persons with disabilities and older persons

ላይ በተፈጸሙ ግድያዎች፣ የአካል ጉዳቶች እና የንብረት ዘረፋ እና ውድመቶች ምክንያትም ያለጧሪ እና ደጋፊ ቀርተዋል፤ ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነልቦናዊ ቀውስ ተዳርገዋል።

በአማራ ክልል ሸዋ ሮቢት ከተማ ኅዳር 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ጠዋት 3፡00 ሰዓት አካባቢ አንድ የ70 ዓመት አረጋዊ፤ ቀበሌ 05 ከሚገኘው ሱቃቸው በተቀመጡበት የትግራይ ታጣቂዎች ሲጋራ እንዲሰጧቸው ሲጠይቋቸው “ደሀ ዘርፈህ ብላ የሚል መንግሥት የለም” ብለው በመመለሳቸው ብቻ በሱቃቸው ውስጥ እንዳሉ በጥይት ደረታቸውን መትተው ገድለዋቸዋል።

የወልዲያ ከተማ ቀበሌ 04 ነዋሪና የሆኑ የ60 ዓመት አረጋዊት ነሃሴ 5 ቀን 2013 ዓ.ም. በትግራይ ኃይሎች ታጣቂ አስገድዶ መድፈር ተፈጽሞባቸዋል።

የአዕምሮ ሕሙማን በተለይ በትግራይ ኃይሎች ከሌሎች ሲቪል ሰዎች በበለጠ የጥቃት ዒላማ ተደርገዋል። ሕሙማኑ የትግራይ ኃይሎች ወደ ተቆጣጠሯቸው ከተሞች ሲገቡ በመንገድ ላይ በመገኘታቸው፣ ወይም መንቀሳቀስ በተከለከለባቸው ሰዓታት ሲንቀሳቀሱ በመገኘታቸው፣ ወይም የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ባለመቻላቸው፣ ወይም ለሚጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ባለመቻላቸው፣ ወይም የመንግሥት ሰላዮች ናቸው በሚል ጥርጣሬ መገደላቸውን ኮሚሽኑ ያሰባሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ። በርካታዎቹ የአዕምሮ ሕሙማን ለመገደላቸው ዋነኛው ምክንያት ለመንግሥት ኃይሎች መረጃ የሚያቀብሉ ሰዎች እንደ አዕምሮ ሕሙማን መስለው በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በሚገኙ ቦታዎች ውስጥ ይሰልላሉ የሚል ጥርጣሬ ነው። የአዕምሮ ሕሙማንን በሰላይነት የመጠርጠር አመለካከት በመንግሥት ኃይሎች ዘንድም እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ። በሰንበቴ ከተማ ይኖር የነበረ አንድ የአዕምሮ ሕመምተኛን የመከላከያ ሠራዊት አባላት “የትግራይ ኃይሎች ተላላኪ ነው” በማለት ሁለት ጊዜ ወስደውት የአካባቢው ሰው ሕመምተኛ መሆኑን አስረድቶ ያስጣሉት ቢሆንም በመጨረሻ የመከላከያ ሠራዊት ምሽግ ሰርቶ የነበረበት ቦታ ተገሎ ተገኝቷል።

**ምክረ ሃሳብ**

ሪፖርቱ ለሁሉም የጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ዝርዝር ምክረ ሃሳቦችን አካቷል። ከነዚህም ምክረ-ሃሳቦች መካከል፣

1. የጦርነቱ ተሳታፊዎች በአባሎቻቸው ለተፈጸሙ ጥሰቶች ኃላፊነት በመውሰድና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተኩስ አቁም በማድረግ ለጦርነቱ ሰላማዊ መፍትሔ ለማፈላለግ በቁርጠኝነት እንዲሰሩ፤

2. ያታዊ ጥቃት የፈጸሙትን ጨምሮ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊነት ሕጎች ጥሰት የፈጸሙ እና ያስፈጸሙ ሰዎችና ቡድኖች ሁሉ ተጠያቂ ለማድረግ ገለልተኛ፣ ተአማኒ እና የሰብአዊ መብቶች ደረጃውን የሚያሟላ የወንጀል ምርመራ እና የክስ ሂደት በአስቸኳይ እንዲጀመር፣

3. ተጎጂዎችን፣ የተጎዱ አካባቢና ተቋሞችን መልሶ የማቋቋም ስራ በልዩ ትኩረት እንዲከናወን፤

4. ሀገራዊ፣ አሁጉራዊና ዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡ ለሰላማዊ መፍትሔ፣ ለፍትሕ እና ለመልሶ ማቋቋም ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርግ የሚጠይቁት ይገኙበታል።

# መግቢያ

1. በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ኃይሎች እና በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መካከል ከተደረገው ጦርነት ጋር ተያይዞ መፈጸማቸው የተዘገበ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) ከተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ጋር በጋራ ያካሄደውን የምርመራ ሪፖርት ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ የጋራ ሪፖርቱ ከጦርነቱ መነሻ ጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፌዴራሉ መንግሥት የተናጠል የተኩስ አቁም አውጆ አብዛኞቹን የትግራይ ክልል አካባቢዎች ለቅቆ እስከወጣበት እስከ ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ በነበረው ወቅት የተፈጸሙ ጥሰቶችን የሚመለከት ነበር፡፡ ከጋራ ሪፖርቱ በተጨማሪ በተለይም ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. በኋላ ጦርነቱ ወደ አፋር እና አማራ ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች መስፋፋቱን ተከትሎ ኮሚሽኑ በወቅቱ ምርመራ ለማካሄድ በቻለባቸው በአማራ ክልል ከፊል የሰሜን ወሎ ዞን እና ከፊል ደቡብ ጎንደር ዞን አካባቢዎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶችና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን የተመለከተ የምርመራ ሪፖርት በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም. ማውጣቱም ይታወሳል፡፡

2. በትግራይ ኃይሎች ወታደራዊ እንቅስቃሴ ጦርነቱ ወደ የአፋርና አማራ ክልሎች ተስፋፍቶና በርካታ አካባቢዎች በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በተወሰደው ወታደራዊ እርምጃ የትግራይና የኦነግ ሸኔ ኃይሎች ከአብዛኛዎቹ ቦታዎች ለቀው እስከወጡበት ጊዜ ድረስ የነበረው የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ዋነኛ ጠባዮችና ሁኔታዎችን የተመለከቱ መረጃዎች በዚህ ሪፖርት በዝርዝር የተዘገቡ ቢሆንም፤ ይህ ሪፖርት ሁሉንም ጥሰቶች የሚሸፍን አይደለም፡፡ ኮሚሽኑ ከመስከረም 18 እስከ ጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ.ም. እንዲሁም ከታኅሣሥ 14 እስከ 26 ቀን 2014 ዓ.ም. በአፋርና በአማራ ክልሎች የምርመራ ቡድኖችን በማሰማራት እንዲሁም በተከታታይ የምርመራ ስልቶች ለአራት ወራት ጥልቅና ሰፊ የምርመራ ስራ አካሂዷል፡፡ ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም ከተባበሩት መንግስታት ጋር ያደረገው የጣምራ ምርመራ ሪፖርት በአብዛኛው በትግራይ ክልል ላይ ያተኮረ የነበረ ሲሆን፤ በአንጻሩ ይህ ሪፖርት በአብዛኛው በአፋርና በአማራ ክልሎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ በተወሰነ መጠን በትግራይ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች የተፈጸሙ ጥሰቶችን ያካትታል፡፡

3. የዚህ ምርመራ ዋነኛ ዓላማዎች፡-

   - በጦርነቱ ሂደት በተፋላሚ ኃይሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን ከነፃታዊ እንድምታቸው መለየት እና ጥሰቶቹን የሚያሳዩ ትክክለኛ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ማሰባሰብ እና መሰነድ፤
   - ለተፈጸሙ ጥሰቶች ተጠያቂነት እንዲኖር የሚደረጉ ጥረቶችን ማገዝ፤ ለተጎጂዎች የተሟላ የካሳ፣ መልሶ ማቋቋም እና ድጋፍ እንዲደረግ ግፊት እና ውትወታ ማድረግ፤

- በምርምራው ግኝቶች መሰረት ግልጽ እና ሊፈጸሙ የሚችሉ ምክረ ሃሳቦችን ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ እርምጃዎች እንዲወሰዱና የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል ማስቻል፤ ወደፊትም ተመሳሳይ ጥሰቶች እንዳይከሰቱ መከላከልን ማስቻል ናቸው፡፡

# የምርመራው ሥነ-ዘዴ

**አጠቃላይ**

4. ምርመራ የተካሄደባቸው ቦታዎች የተመረጡት ኮሚሽኑ አስቀድሞ ባከናወነው የቅድመ ምርመራ ክትትል መሰረት ሲሆን፣ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተፈጽሞባቸዋል ተብለው የተለዩ እና ምርመራው በሚከናወንበት ወቅት ከፍ ያለ የደኅንነት ስጋት ያልነበረባቸው ቦታዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ምርመራ የተመለከታቸው ቦታዎች፤ በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን የያሎና እዋ ወረዳዎችን፣ በአውራ ወረዳ ደራይቱ ከተማን፣ በጉሊና ወረዳ ጋሊኮማ ቀበሌን፤ በኪልበቲ ረሱ ዞን አባኣላ ወረዳን፣ በበርሃሌ ወረዳ ኩሱርቱ፣ አሰዳ እና አደአርዋን፣ በአውሲ ረሱ ዞን በአዳአር ወረዳ ቡርቃ፣ ዋአንቱ እና ፉርሳ ቀበሌዎች እና የጭፍራ ከተማን ሲሆኑ፤ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ዞን ደባርቅ ወረዳ፣ ድብ ባህር ንዑስ ወረዳን፣ ቦዛ ቀጠና (አዲጋግራ፣ አብርሃም እና አዳጋር ቀበሌዎችን)፣ ዳባት ወረዳ ጭና ቀበሌ፣ በአዲ አርቃይ ወረዳ የዛሬማ ንዑስ ወረዳን፣ በሰሜን ወሎ ዞን የጋሸና እና አርቢት ከተሞች፣ በዋድላ ወረዳ የሐሙሲት ከተማ፤ በላስታ ወረዳ የዳቦ፣ ድብኮ እና ሹምሽሃን፤ ላሊበላ ከተሞችን እንዲሁም በመቄት ወረዳ የደብረዘቢጥ ቀበሌን፣ ጣጃ እና ፍላቂትና ገረገራ ከተሞችን፤ መርሳ፣ ወልዲያ፣ ፤በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ የወረባቡ እና ተሁለደሬ ወረዳዎችን፣ በአምባሰል ወረዳ የውጫሌ ከተማን፤ ሃይቅ፣ ደሴ እና ኮምቦልቻ ከተሞችን፤ በሰሜን ሸዋ ዞን የአጣዬ ከተማን ካራቆሬ ቀበሌን በመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ የመሃል ሜዳ ከተማን፣ መዘዞ ንዑስ ወረዳን፣ የቀወት ወረዳ የለን ቀበሌ እና ሸዋ ሮቢት ከተማን፣ አንጻኪያ ገምዛ ወረዳን እንዲሁም በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን የደዋ ጨፋ ወረዳ፣ ከሚሴ እና ሰንበቴ ከተሞች ናቸው፡፡ እንዲሁም በትግራይ ክልል ደቡብ ምስራቅ ዞን እንደርታ ወረዳ ደብረናዝሬት ጣብያ ቶጎጓ ጎጥ እንዲሁም በመቀሌ ከተማ እና አካባቢው የተፈጸሙ የአየር ጥቃቶች እና የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦትን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ከተጎጂዎች፣ ከምስክሮች እና ከሚመለከታቸው ምንጮች መረጃዎችና ማስረጃዎችን ሰብስቧል፡፡

5. ኮሚሽኑ ምርመራውን ባካሄደበት እንዲሁም መረጃ እና ማስረጃዎችን በሰበሰበበት እና በመዘነበት ወቅት የገለልተኝነት፣ ግልጽነት፣ ታማኝነት መርሆች በመመራት ሲሆን፣ ለኮሚሽኑ የመረጃ ምንጭ የነበሩትን ምስክሮች እና ተጎጂዎች በመለየት እና መረጃ በመሰብሰብ ሂደት ሚስጥራዊነትን፣ የምስክሮች ደህንነት ጥበቃን እና ለተጨማሪ ጉዳት አለማጋለጥ መርህን ተከትሏል፡፡ በመሆኑም ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የመረጃ ምንጮች ለደህንነታቸው ሲባል በዚህ ሪፖርት ስማቸው አይጠቀስም፡፡

## የማስረጃ ምዘና ደረጃ

6. ኢሰመኮ ይህንን ምርመራ ሲያከናውን የተጠቀመው የማስረጃ ምዘና ደረጃ በተመሳሳይ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራዎች እንዲሁም በዓለም አቀፍ አጣሪ ኮሚሽኖች ወይም የእውነት አፈላላጊ አካላት ጥቅም ላይ የሚውለውን "የምክንያታዊ አሳማኝነት" (reasonable grounds to believe) ተብሎ የሚታወቀውን የማስረጃ ምዘና መስፈርትን ነው፡፡ በዚህም መሰረት ኮሚሽኑ የአንድ ጥሰት መፈጸም ወይም አለመፈጸምን አስመልክቶ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ጉዳዩን አስመልክቶ ከተለያዩ ተዓማኒነት ካላቸው ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች እርስ በእርስ ተመሳሳይነት ያለው ወይም የማይጣረስ መረጃ መስጠታቸውን እና አንድ ምክንያታዊ እና ጥንቁቅ የሆነን ሰው ሊያሳምን በሚችል አግባብ ስለ አንድ ነጠላ ክስተት ወይም ስልት እና አሰራርን የሚያሳይ ተደጋጋሚ ጥሰትን (አዝማምያ/pattern) የሚያስረዳ ሲሆን ነው፡፡

7. "የምክንያታዊ አሳማኝነት" የማስረጃ ምዘና ደረጃ የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ከሚያስፈልገው "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" መስፈርት ዝቅ ያለ በመሆኑ፤ የኮሚሽኑ ግኝቶች በግለሰቦች ደረጃ የዓለም አቀፍ ሕግ ጥሰቶች መፈጸማቸውን በማረጋገጥ የወንጀል ቅጣትን ለመጣል የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ ሆኖም ግን ኮሚሽኑ የተጠቀመው የማስረጃ ምዘና ደረጃ በግኝቶቹ ላይ ተጨማሪ የወንጀል ምርመራዎች እንዲደረጉ የሚያስገድድ እና የወንጀል ጥፋተኛነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ሲሟሉ፤ አጥፊዎች በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማስገደድ የሚያስችል ነው፡፡

8. ኮሚሽኑ ለምርመራ የለያቸው ጉዳዮች የተመረጡት የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም ሲሆን፣ ከእነዚህም መስፈርቶች መካከል ተፈጸመ የተባለው ጥሰት ክብደት መጠን፣ ተፈጸሙ የተባሉ ጥሰቶች ተደጋጋሚነትን አዝማምያ ለማሳየት ካላቸው አስረጂነት፣ ከተጎጂዎች ቁጥር፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ምስክሮች እና ደጋፊ የሆኑ ማስረጃዎችን ከማግኘት እና የተለያዩ ስፍራዎችን ከመወከል አንጻር ተገምግመው የተመረጡ ናቸው፡፡ የኮሚሽኑ የሰው ኃይል አቅም እና ምርምራውን ለማከናወን የሚፈጀው ጊዜም ከግምት ውስጥ ገብቷል፡፡

9. በዚህ የምርመራ ሪፖርት ላይ የተጠቀሱት ግኝቶች ቢያንስ አንድ ተዓማኒነት ካለው የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ምንጭ እና ቢያንስ ሁለት ከሚሆኑ ተጨማሪ ገለልተኛ እና ተዓማኒነት ካላቸው ምንጮች የተረጋገጡ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በተለይ ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃትን በተመለከተ ኮሚሽኑ በሌሎች ቦታዎች ካገኛቸው መረጃዎች ጋር የሚመሳሰሉ እንዲሁም ተለይተው ከታወቁ ተደጋጋሚ የጥፋት አሰራር ስልቶች (Patterns of violations) ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ምስክርነቶችን ከአንድ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ምንጭ (ተጎጂዎች) ተቀብሏል፡፡

## የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

10. ኮሚሽኑ ከተጎጂዎች እና ምስክሮች ጋር ቃለ-መጠይቆችንና የቡድን ውይይቶችን በማድረግና የመስክ ምልከታዎችን በማድረግ እንዲሁም አግባብነት ካላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና አስረጂ የሰነድ ማስረጃዎችን በመመልከት መረጃዎች እና ማስረጃዎችን አሰበስቧል፡፡ በዚህ መሰረት ከተጎጂዎች እና ምስክሮች ጋር 427 ቃለ-መጠይቆች ተደርገዋል፤ ምርምራ በተደረገባቸው አካባቢዎች በዞን፣ ወረዳ እና ቀበሌ ደረጃ ከሚገኙ የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር 136 ስብሰባዎች እና ቃለመጠይቆች እንዲሁም ከሰብዓዊ እርዳታ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ቃለ-መጠይቆች ተደርገዋል፡፡ አጠቃላይ ሁኔታን የሚያሳዩ መረጃዎችን በተመለከተ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ከሃይማኖት መሪዎች እና ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር 12 የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎች ተሰባስበዋል፡፡ ኮሚሽኑ የመቃብር ቦታዎችን፣ በጦርነቱ የተዘረፉ እና የወደሙ ሆስፒታሎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ጣቢያዎችን፣ የእምነት ተቋማትን፣ የግል እና መንግሥት ተቋማትን፣ የፖሊስ እና የሚሊሺያ ጽ/ቤቶችን እና ተፈናቃዮች የሚገኙባቸውን መጠለያዎች በመመልከት ተጨማሪ መረጃ አሰባስቧል፡፡

11. በኮሚሽኑ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተተነተኑ በኋላ የተደረሰባቸውን ግኝቶችን መሰረት በማድረግ በተለዩ ጉዳዮች ላይ የጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች እና የሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት ምላሽ እና አስፈላጊ መረጃዎች እንዲሰጡ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሠራዊት፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና እና የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን መልስ እና መረጃዎች የሰጡ በመሆኑ በዚህ ሪፖርት ተካትቷል፡፡ በምርመራው የተለዩትን ጉዳዮች ለትግራይ ክልል ለመላክ የተደረገው ጥረት ባለው የግንኙነት ችግር ምክንያት አልተሳካም፡፡

## የምርመራው ውስንነቶች እና የገጠሙ ተግዳሮቶች

12. በዚህ የምርመራ ሪፖርት ከተሸፈኑት ስፍራዎች በተጨማሪ በሌሎች ጦርነት በተካሄደባቸው ቦታዎች ተገኝቶ ምርመራ ለማካሄድ እቅድ የነበረ ቢሆንም፣ በነበረው የጦርነት እንቅስቃሴና የደኅንነት ስጋት አንፃር በታቀደው ስፋት የምርመራ ሥራውን ለማከናወን አልተቻለም፡፡

13. ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ድርጊቱ እንደተፈጸመባቸው በማህበረሰቡም ሆነ በቤተሰቦቻቸው ከታወቀ ሊደርስባቸው የሚችለውን መድሎ እና መገለል በመፍራት በርካታ ተጎጂዎች ለኮሚሽኑ መረጃ ለመስጠት ሳይፈቅዱ ቀርተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ጦርነቱ በተካሄደባቸው ስፍራዎች በተለይ የአስገድዶ መድፈር ድርጊት የተፈጸመባቸው በርካታ ተጎጂዎችን ለማነጋገር ባለመቻሉ የጥቃቱ ስፋት በዚህ ሪፖርት ከተመለከተው በእጅጉ ከፍ ያለ እንደሚሆን ኮሚሽኑ ያምናል፡፡

14. በተጨማሪም የሰሜን ጎንደር ዞን ፖሊስ መምሪያ ኃላፊዎች እና በድብባሕር ንዑስ ወረዳ ጤና ጣቢያ እና ድብባህር ልደታ ቤተክርስቲያን ግቢዎች ውስጥ ሰፍረው የነበሩ የመከላከያ ሠራዊት አባላት

የምርመራውን ዓላማ በአግባቡ ባለመረዳት፣ ኮሚሽኑ ከበላይ ፀጥታ አካል ልዩ የጽሑፍ ፍቃድ ካላመጣ በማለትና፣ የኮሚሽኑ ባለሞያዎች በአካባቢው በነበሩበት ወቅት መረጃ ባለመስጠት፣ ምልከታ በመከልከል እና ለማነጋገር ፈቃደኛ ባለመሆን፤ ለምርመራ ስራው ትብብር የማድረግ የሕግ ግዴታቸውን ሳይወጡ ቀርተዋል።

15. ኮሚሽኑ ይህን የምርመራ ስራ የሚያካሂደው እጅግ ውስን በሆነ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስና ሎጂስቲክ ተቋማዊ አቅም እንዲሁም በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ከሚገኙ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ችግሮች ዙሪያ ከሚሰራቸው ሥራዎች ጎን ለጎን በመሆኑ፤ ሁሉንም የሰብአዊ መብቶች ችግሮች በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ምላሽ ለመስጠት አልተቻለም።

## ምስጋና

16. ኢሰመኮ በምርመራ ወቅት ትብብር ላደረጉለት አካላት ሁሉ ምስጋና ያቀርባል። በተለይ ተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ ምስክሮች እና ሌሎች የመረጃ ምንጮች ጥሰቶችን የተመለከቱ እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን በማካፈላቸው፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት መረጃዎችን ለኮሚሽኑ በመስጠታቸው ይህ ምርምራ በተሳካ ሁኔታ ሊከናወን ችሏል።

# የሕግ ማዕቀፎች

## የምርመራው አጠቃላይ የሕግ ማዕቀፍ

17. ይህ ምርመራ የተከናወነው አግባብነት ያላቸውን የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች፣ ሰብአዊነትና ወንጀል ሕግጋት እና መርሆዎችን እንዲሁም ብሔራዊ/ሀገራዊ ሕግጋትን መሰረት በማድረግ ነው። የተለዩ ጥሰቶችን የሚመለከቱ ዝርዝር የሕግ ትንታኔዎች በሚመለከተው ክፍል ስር ቀርበዋል።

### ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት

18. ኢትዮጵያ ዋና ዋና ከሚባሉት ዘጠኝ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ ሰባቱን አጽድቃለች። እነዚህም፦

ሀ.ማሰቃየትን እና ሌሎች ዓይነት ኢሰብአዊ ወይም አዋራጅ አያያዝን እና ቅጣትን ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት፤
ለ.ዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት፣
ሐ.በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ማንኛውንም ዓይነት መድሎዎች ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት፤
መ.ማንኛውንም ዓይነት ዘርን መሰረት ያደረገ መድሎ ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት፤
ሠ.ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና የባሕል መብቶች ስምምነት፤
ረ.የሕፃናት መብቶች ቃልኪዳን፣ ሕፃናትን በጦርነት ስለማሳተፍ የተደረገ ተጨማሪ ፕሮቶኮል፣ ሕፃናትን መሸጥን፣ ለሴተኛአዳሪነት እና ወሲብ ቀስቃሽ ለሆኑ ተግባራት መጠቀምን ለማስወገድ የተደረገ ተጨማሪ ፕሮቶኮል፤
ሠ.የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ናቸው።

19. ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ የሚከተሉት አህጉራዊ ስምምነቶች ፈራሚ አገር ነች።

ሀ. የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች መብቶች ቻርተር፤
ለ.የአፍሪካ ሴቶች መብቶች የሚመለከት የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች መብቶች ቻርተር ተጨማሪ ስምምነት /ማፑቶ ፕሮቶኮል/፤
ሐ.የአፍሪካ ሕፃናት መብቶች እና ደኅንነት ቻርተር፤
መ.የአፍሪካ አረጋውያን መብቶች የሚመለከት የአፍሪካ የሰዎች እና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር ተጨማሪ ስምምነት፤
ሰ. የአፍሪካ ሕብረት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍ ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) ናቸው።

ከእነዚህ ስምምነቶች በተጨማሪም ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ልማዳዊ ሕጎች በኢትዮጵያ ተፈጻሚነት አላቸው።

20. ኢትዮጵያ ከላይ በተመለከቱት ስምምነቶች እና በልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕጎች እውቅና ያገኙ መብቶችን በአገሪቱ ድንበር ወሰን ወይንም ስልጣን ስር ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ ያለ አድልኦ የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል። ይህ ግዴታ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ፈጻሚዎችን ለፍርድ ማቅረብን እንዲሁም መብታቸው የተጣሰባቸው ሰዎች ፍትሕና ካሳ ማስገኘትን እና ወደፊት የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ማስቆምን ጨምሮ ፈጣን፣ በቂ እና ውጤታማ የሆነ መፍትሔ የማስገኘትን ግዴታ ይጨምራል። የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ እና ዓለም ዓቀፍ የሰብአዊነት ስምምነቶች በጦርነት ወቅት የጣምራ ተፈጻሚነት ያላቸው በመሆኑ በጋራ እና በተጣጣመ መልኩ ሊተረጎሙ ይገባል።

## ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ

21. የሰብአዊነት ሕግ በጦርነት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎችን ባሕሪያት እና ተግባራት የሚመለከት ሕግ ነው። ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ስምምነቶች በጦርነቱ ተሳታፊ ያልሆኑ፣ ተሳታፊ መሆን ያቆሙ ወይም በግጭቱ/ጦርነቱ ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ ያልሆኑ ሰዎችን ማጥቃትን ይከለክላሉ፤ ሰብአዊነት ያለው አያያዝ /እንክብካቤ የማግኘት መብታቸውን ያረጋግጣሉ እንዲሁም በጦርነቱ የሚሳተፉ አካላት የጦር ኃይልን/መሳርያን የግጭቱን ዓላማ ለማሳካት በሚያስችል መጠን ብቻ ማለትም፤ የግጭቱ የመጨረሻ ዓላማ ምንም ይሁን ምን የጦር ኃይል አጠቃቀሙ የጠላትን ወታደራዊ አቅም ለማዳከም በሚያስችል መጠን ብቻ እንዲሆን ያስገድዳሉ[16]።በጦርነቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሀይሎች ሁሉ ተፈጻሚነት ላላቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ስምምነት ድንጋጌዎች ተገዢ የመሆን ግዴታ አለባቸው።

22. ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እና የሌላቸው ጦርነቶች መካከል ልዩነት ያደርጋል። ዓለም አቀፍ ግጭቶች ሁለት ወይም ከዛ በላይ ቁጥር ያላቸው አገራት የጦር ኃይላቸውን ወይም እነርሱን በሚወክል ሌላ አካል አማካኝነት የሚያደርጉት ጦርነትን የሚመለከት ነው።[17]ዓለም አቀፋዊ ያልሆኑ ግጭቶች ደግሞ በአንድ አገር ድንበር ውስጥ በሀገሪቱ መንግሥት እና አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ኃይሎች መካከል ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ኃይሎች እርስ በእርስ የሚያደርጉትን ጦርነት/ግጭት ያመለክታል።[18]

23. ዓለም አቀፋዊ ያልሆኑ ግጭቶችን የሚመለከቱት ሕግጋት በዋነኛነት የጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀጽ 3 እና የጄኔቫ ስምምነቶች ተጨማሪ ፕሮቶኮል ሁለት ናቸው። ዓለም አቀፋዊ ያልሆኑ

[16] M Sassoli, AA Bouvier AA and A Quintin(eds), How Does Law Protect in War? (3rd edn, Geneva: ICRC, 2011), Vol I, Pt1, at 1.

[17] Prosecutor v Bemba, Decision Pursuant to Article 61(7)(a) and (b) of the Rome Statute on the Charges of the Prosecutor Against Jean-Pierre Bemba Gombo, ICC-01/05-01/08-424, Trial Chamber II, 15 June 2009, paragraph 223. See also Geneva Conventions, common Article

[18] Protocol Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949, and relating to the Protection of Victims of Non-International Armed Conflicts (Protocol II), 8 June 1977, Article 1

ግጭቶችን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያላቸው ተጨማሪ ድንጋጌዎች የተወሰኑ ዓይነት የጦር መሳርያዎችን አጠቃቀም ለመከላከል፣ ለመወሰን ወይንም ለመቆጣጠር የተደረገ ስምምነት (Convention on Certain Conventional Weapons) እና በልማዳዊ የሰብአዊነት ድንጋጌዎች ውስጥ ይገኛሉ፡፡

24. በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መሰረት አንድ ግጭት ወይም ጦርነት ዓለም አቀፋዊ ያልሆነ ጦርነት ነው ተብሎ እንዲመደብ ሦስት መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው፡፡ የመጀመሪያው በመደበኛ የሕግ ማስከበር እርምጃዎች ምላሽ ሊያገኝ ያልቻለ እና ከፍ ያለ መጠን ያለው ጦርነት/ግጭት መኖር ሲሆን፣ ይህም በግጭቱ የቆየበትን ጊዜ፣ በጥቅም ላይ የዋሉ የጦር መሳሪያዎችን እና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚወሰን ነው፡፡ ሁለተኛው ግጭቱ በአንድ ሀገር ግዛት ወስጥ በአንድ በኩል በመንግሥት እና በሌላ በኩል አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች መካከል ወይም ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የታጠቁ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት መካከል መከናወኑ ነው፡፡ ሦስተኛው ታጣቂ ቡድኖቹ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግጋት መሰረት እንደ አንድ ተካፋይ ወገን ለመቆጠር ወታደራዊ ዘመቻዎችን ለማከናወን እንዲሁም ዓለምአቀፍ ሰብአዊነት ሕግጋትን ለማክበር በሚያስችል መልኩ በቂ አደረጃጀት እና ቁጥጥር ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

25. የዚህ ምርምራ ትኩረት የሆነው ጦርነት በመንግሥት ኃይሎች በአንድ ወገን እንዲሁም የትግራይ ኃይሎችና የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች በሌላ ወገን በመሆን በሀገሪቱ ወሰን ክልል ውስጥ የሚያከናውኑትን በጦር መሳርያ የታገዘ ግጭት በመሆኑ እንደ ዓለም አቀፋዊ ያልሆነ ጦርነት የሚመደብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ግጭት ተካፋይ የሆኑት ኃይሎች ላይ፣ እንዲሁም በእነዚህ ኃይሎች ትዕዛዝ፣ አመራር እና ቁጥጥር ስር ያሉ ታጣቂዎች እና አጋዥ ኃይሎች ላይ በሙሉ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ እና አግባብነት ያላቸው ልማዳዊ ሕግጋት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

26. ኢትዮጵያ የሚከተሉትን አጠቃላይ እና ልዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ስምምነቶች ፈራሚ ሀገር ናት፦

ሀ. የጄኔቫ ስምምነቶች (1949) እና ተጨማሪ ስምምነት 1፣2 እና 3
ለ. አፋኝ እና መርዛማ ጋዞች እንዲሁም ባክቴሮሎጂካል ዘዴዎችን ለመከልከል የተደረገ የጄኔቫ ስምምነት /1925/
ሐ. ባዮሎጂካል ጦር መሳርያዎችን ለመከልከል የተደረገ ስምምነት /1972/
መ. የኬሚካል ጦር መሳርያዎችን ለመከልከል የተደረገ ስምምነት /1993/
ሠ. ፀረ ሰው ፈንጂን ለማገድ የተደረገ ስምምት /1997/
ረ. ባህላዊ ንብረቶችን /ቁሶችን ለመጠበቅ የተደረገው የሄግ ስምምነት እና የ1945 ተጨማሪ ስምምነት

27.የሁሉም ጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀጽ 3 እና ተጨማሪ ፕሮቶኮል 2 በዚህ ጦርነት ላይ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡ እነዚህ ስምምነቶች ሲቪል ሰዎች፣ በግጭቱ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸው

ሌሎች ሰዎችን የሚመለከቱ ጥበቃዎችን የያዙ ናቸው፡፡ የጋራ አንቀጽ ሶስት የጦርነቱ ተካፋይ ኃይሎች ሁሉ በጦርነቱ ተካፋይነት የሌላቸው ወይም ተካፋይ መሆን ያቆሙ ሰዎች ጎጂ/አሉታዊ/ የሆነ ልዩነት ሳይደረግባቸው ሰብአዊነት በተሞላበት ሁኔታ እንዲያዙ ያስገድዳሉ፡፡ ጦርነትን በማካሄድ ወቅት ተዋጊ ኃይሎችን ከሲቪል ሰዎች መለየት፤ ተመጣጣኝነት እና ጥንቃቄ ለሚሉት መርሆዎች ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡

28. መንግሥታት ሴቶች እና ሕፃናትን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው የሰብአዊነት እና የሰብአዊ መብቶች ሕግጋትን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ሴቶችና እና ሕፃናት ሴቶችን ጨምሮ በጦርነት ሂደት ውስጥ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እንዳይፈጸምባቸው የሚከላከሉ ልዩ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡

### ዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ

29. ዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ በዓለም አቀፍ ወንጀልነት የተፈረጁ ከፍ ያሉ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግጋት ጥሰቶች ፈጻሚዎች በግለሰብ ደረጃ ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ነው[19]፡፡ መንግሥታት ይህን መሰል ወንጀሎችን በተመለከተ ተጠያቂነት እንዲኖር የማድረግ ተቀዳሚ ግዴታ አለባቸው፡፡ ለዚህም የወንጀል ድርጊቶቹ እና መርሆዎቹ በአገራዊ ሕጎች ውስጥ በበቂ ጥልቀት እንዲካተቱ በማድረግ የሀገር ውስጥ ፍርድ ቤቶች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በተከተለ መልኩ ውሳኔ ለመስጠት በቂ ስልጣን እንዲኖራቸው የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

30. ዓለም አቀፍ ወንጀሎች የጦር ወንጀል፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል እና የዘር ማጥፋትን ወንጀልን ያካትታሉ፡፡ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (crimes against humanity) በሰላማዊ ወቅትም ሆነ በጦርነት ወቅት በሲቪል ሰዎች ላይ የሚፈጸም መጠነ ሰፊ እና ከፍ ያለ የመብት ጥሰት ሲሆን እንደ ግድያ፣ ባርነት እና ሌሎች ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን የሚያካትት እና ፖለቲካዊ አቋምን፣ ዘርን፣ ሃይማኖትን ወይም መሰል ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ሊፈጸም የሚችል ነው፡፡[20]

31. የዘር ማጥፋት ወንጀል አንድን ማኅበረሰብ፣ ብሔር፣ ዘር እና የሃይማኖት ቡድን በሙሉ ወይንም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የሚተገበሩ የተከለከሉ ተግባራትን ያመለክታል፡፡ በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን የቡድኑን አባላት አካላዊ እና ሥነልቦናዊ ደኅንነት ወይንም የቡድኑን ህልውና እና ሥነ-ህይወታዊ ቀጣይነት ላይ ያነጣጠሩ ተግባራትን ያካትታል፡፡[21]

32. የጦር ወንጀል ማለት በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት/የጦርነት ሕግ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እና ልማዳዊ ሕጎች ከባድ ጥሰት ሲሆን፣ በዓለም አቀፋዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ባልሆኑ ጦርነቶች ውስጥ ሊፈጸም

[19] ICRC, General Principles of International Criminal Law.
[20] Rome Statute of the International Criminal Court, Article 7
[21] Convention on the Prevention and Punishment of the Crime of Genocide, 9 December, 1948, Article 2

የሚችል ነው::[22] የሕግ ጥሰቱ ከባድ ነው ተብሎ የሚወሰደው በሕግ ማዕቀፉ ጥበቃ የተደረገላቸውን ሰዎች ወይም ንብረቶች አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ እና የሕጉን መሰረታዊ መርሆዎች የሚጥስ ከሆነ ነው::

33. ግለሰቦች ዓለም አቀፋዊ ወንጀሎችን ፈጽመው፣ ለመፈጸም ተዘጋጅተው፣ አቅደው፣ እንዲፈጸም ትዕዛዝ ሰጥተው ወይንም እንዲፈጸሙ አነሳስተው የተገኙ እንደሆነ ለዚሁ ተግባራቸው ተጠያቂ ይሆናሉ:: ከዚህም በተጨማሪ የጦር ወንጀለኞችን መርዳት እና ማበረታታት እንዲሁም እነዚህን መሰል ወንጀሎች እንዲፈጸሙ ድጋፍ መስጠት እና ማመቻቸትም ተጠያቂነትን ያስከትላል::

34. የጦር አዛዦች እና ሌሎች ባለሥልጣኖች እንደየሁኔታው ራሳቸው በግል ለፈጸሙዋቸው፣ እንዲፈጸሙ ትእዛዝ ለሰጡባቸው ወይንም ላነሳሷቸው ወንጀሎች እንዲሁም በእነርሱ ሙሉ ሥልጣን ወይም ዕዝ ወይም ቁጥጥር ስር ባሉ አካላት አማካኝነት ይህን መሰል ወንጀሎች እየተፈጸሙ መሆኑን ወይንም ሊፈጸሙ መሆኑን እያወቁ ድርጊቱ እንዳይፈጸም ለማድረግ የሚያስችል አስፈላጊ እና ምክንያታዊ እርምጃዎችን ሁሉ ያልወሰዱ እንደሆነ ተጠያቂነት አለባቸው::

35. ኢትዮጵያ የሮሙ የዓለም አቀፍ ወንጀል ፍርድ ቤት ስምምነት አባል ባትሆንም አብዛኞቹ የስምምነቱ ድንጋጌዎች የዓለምአቀፍ ልማዳዊ ሕግ ደረጃ ያላቸው በመሆኑ እነዚህ ድንጋጌዎች በሀገሪቱም ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

36. ኢሰመኮ በዚህ የሰብአዊ መብቶች ምርመራው በጦርነቱ ተፋላሚ ኃይሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን የለየ ቢሆንም፣ የምርመራው ግኝቶች በራሳቸው ግለሰባዊ የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በቂ ባለመሆናቸው፤ ይህን ምርመራ መሰረት አድርጎ የተሟላ የወንጀል ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል::

## ብሔራዊ ሕግጋት

37. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ) ሕገ-መንግሥት በምዕራፍ 3 ከዘረዘራቸው የሰብአዊ መብቶች በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሀገሪቱ የሕግ አካል እንደሆኑና[23] በሕገ-መንግስቱ ውስጥ የተካተቱ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ከሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ መርሆዎች እንዲሁም አገሪቱ ከተቀበለቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተርጎም እንዳለባቸውም ይደነግጋል::[24]

---

[22] Rome Statute of the International Criminal Court, Article 8

[23] የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9/4/

[24] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 13/2/

38. ሕገ-መንግስቱ የተወሰኑ ሰብአዊ መብቶች በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት እገዳ የሚደረግባቸው መሆኑን ገልጾ፣ ሆኖም ከኢ-ሰብአዊ አያያዝ የመጠበቅ፣ የእኩልነት እና ከአድልኦ የመጠበቅ መብቶችን እና ሌሎች የተወሰኑ ሰብአዊ መብቶች በአስቸኳይ ጊዜ ወቅትም እገዳ የማይጣልባቸው እንደሆኑ ይደነግጋል። እንዲሁም በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (ዘር ማጥፋትን፣ ያለፍርድ የሚደረጉ ግድያዎችን እና በግዳጅ መሰወርንና ማሰቃየትን በሚያካትት መልኩ አስቀምጦታል) በይርጋ እንደማይታገዱ፤ ይቅርታ እና ምህረትም ተፈጻሚ እንደማይሆንባቸው ይደነግጋል።

39. በ1996 ዓ.ም. የወጣው የወንጀል ሕግ እንደየደረጃው ሰው መግደል፣ አካል ጉዳት ማድረስ፣ በሕገወጥ መንገድ ነጻነትን ማሳጣት፣ ጠለፋ፣ ፖለቲካዊ ጠለፋ፣ ሰውን በባርነት መያዝ፣ አስገድዶ መድፈር እና ሌሎች ወሲባዊ ጥቃቶች፣ውንብድና፣ ዘረፋ እና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስን ክልከላ የሚያደርጉ እና ቅጣቶችን የሚያስቀምጡ ድንጋጌዎችን ይዟል። የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 269 የዘር ማጥፋት ወንጀልን የሚከለክል እና ቅጣት የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ የወንጀል ድርጊቱን የትርጓሜ መሰረት ከዓለም አቀፍ ስምምነቶችም በላይ በማስፋት የፖለቲካ ቡድኖች ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን እንዲጨምር ያደርጋል። ሕጉ በአንቀጽ 270 ስር ግድያ፣ ማሰቃየት እና ኢሰብአዊ አያያዝ፣ አስቦ ሕዝብን ለረሃብ መዳረግ፣ ማደህየት ወይም ኑሮውን ማናጋት፤ በኃይል ማፈናቀል፣ መበተን፣ ማጋዝ፣ አስገድዶ ስራ ማሰራት፤ ለስለላ ማስገደድ፤ ዜግነት ማሳጣት ሃይማኖት ማስለወጥ፤ በግዳጅ የወሲብ ንግድ ስራ ማሰማራት፤ አስገድዶ መድፈር፣ በወጆ /በመያዣነት/ መያዝ፣ ማስፈራራት፣ ማሸበር፣ የጅምላ ቅጣት፣ የበቀል ድርጊት፣ ንብረት መውረስ፣ ማውደምና ለራስ ማድረግ፣ የቤት እንስሳት መውረስ፣ የታሪካዊ እና ሥነጥበባዊ ቁሶችን ማጥፋት ማፍረስ ከጥቅም ውጭ ማድረግ፣ ታሪካዊ እና የሥነ ጥበብ ቦታዎችን፣ ቤተእምነቶችን ለወታደራዊ ዓላማ ማዋል፣ በተቆጣጠረው ስፍራ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ግልጋሎቶችን አለማቅረብ/እንዳይቀርቡ ማድረግ፣ ስደተኞችን ማጥቃት፣ ከ18 ኣመት በታች የሆኑ ልጆችን በጦርነት ማሳተፍ ለወታደርነት መመልመል፣ ዘላቂ ወይንም መጠነ ሰፊ ጉዳትን የሚያደርስ መሳርያ እና የውግያ ዘዴ መጠቀም፣ ኃይል ማመንጫዎች እና ግድቦችን መምታት እና ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጪ ቅጣት መወሰን እና ማስፈጸም የመሳሰሉ ወንጀሎችን ይዟል።

ከአንቀጽ 273 - 274 በጦርነት ወቅት የሚከናወን ዝርፊያ፣ ገፈፋ እና የባህር ውንብድና የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን እንዲሁም ከአንቀጽ 281 - 283 የሰብአዊ ድርጅቶች ሰራተኞች፣ ንብረት እና ምልክቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የወንጀል ድርጊት ያደርጋል፤ ቅጣትም ያስቀምጣል።

## የሰብአዊ መብቶችን ጥሰት የመመርመር ፣ ክስ የማቅረብ እና ተገቢውን መፍትሔ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ

40. ከዚህ በላይ እንደተገለጸው መንግሥት በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና ሰብአዊነት ሕግጋት ላይ የሚፈጸሙ ከፍ ያሉ ጥሰቶችን የመመርመር እና አጥፊዎችን ለፍርድ የማቅረብ ግዴታ አለበት። ይህን በመሰሉ ጥሰቶች ላይ የሚደረግ ምርመራ ገለልተኛ በሆነ አካል መደረግ እንዲሁም ፈጣን፣ ጥልቅ፣ ግልጽ እና ውጤታማ መሆን አለበት።በተጨማሪም ለተጎጂዎች መፍትሔ ለማስገኘት ጥረት የማድረግና ለደረሱ ጉዳቶች ካሳ መገኘቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ጥሰቶቹ ዳግም እንዳይከሰቱ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታም አለበት።

***መንግሥታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ኃይሎች***

41. መንግስታዊ ያልሆኑ ያሉ የታጠቁ ኃይሎች ማለት በአንድ ግዛት/አካባቢ ላይ ቁጥጥር ያላቸው እና መንግሥት መሰል ተግባራትን የሚከውኑ አካላት ናቸው። እነዚህ ኃይሎች በስራቸው ያሉ ሰዎችን ሰብአዊ መብቶች የማክበር ግዴታ አለባቸው። በውግያ ተሳትፎ የሚያደርጉ የታጠቁ መንግስታዊ ያልሆኑ ኃይሎች በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ለተቀመጡ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች ተገዢ መሆን እና ማክበር አለባቸው። በተጨማሪም ተዛማጅነት ያላቸው ልማዳዊ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት በሁሉም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

# ሀገራዊ እና ክልላዊ አውድ

42. ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. በፌዴራል መንግሥት እና በትግራይ ኃይሎች መካከል የተጀመረው ጦርነት ለስምንት ወራት ያህል በዋናነት በትግራይ ክልል ውስጥ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት የተናጠል ተኩስ አቁም ውሳኔ ማስተላለፉን አስታውቋል። ውሳኔውን ተከትሎም የመንግሥት ኃይሎች የምዕራብ ትግራይ አካባቢዎችን ሳይጨምር በትግራይ ክልል ተቆጣጥረዋቸው ከነበሩ አካባቢዎች ለቅቀው ወጥተዋል።

43. የትግራይ ኃይሎች ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም. መቀሌ ከተማን መቆጣጠራቸውን በማሳወቅ፣ በሕወሃት የሚመራው የክልሉ መንግሥት ወደ ስልጣኑ ተመልሶ ክልሉን የማስተዳደር ተግባር መጀመሩን ገልጸዋል። የተናጠል ተኩስ አቁሙን ለመቀበልም ቅድመ-ሁኔታዎችን ያስቀመጡ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል የኤርትራ ሠራዊት እና የአማራ ክልል ኃይሎች ከትግራይ ክልል ሁሉም አካባቢዎች እንዲወጡ እና ያልተገደበ ሰብአዊ እርዳታ ወደ ትግራይ መግባት እንዲፈቀድ የሚሉት ይገኙበታል።

44. የትግራይ ኃይሎች ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በወሰዱት ወታደራዊ እርምጃ አጎራባች ወደሆኑት የአፋር እና የአማራ ክልሎች በመግባት የተለያዩ አካባቢዎችን መቆጣጠር ጀመሩ። በቀጣይ ወራትም የትግራይ ኃይሎች በሁለቱ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ በርካታ ቦታዎችን በመቆጣጠርና ወደ አዲስ አበባ ከተማ በመገስገስ በታኅሣሥ ወር 2014 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ከአዲስ አበባ 150 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኙ የሰሜን ሸዋ አካባቢዎች ደርሰው ነበር።

45. በጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም. መጨረሻ የትግራይ ኃይሎች በአማራ ክልል የኦሮሚያ ልዩ ዞን አካባቢዎች መድረሳቸውን ተከትሎ ከኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት (በተለምዶ ኦነግ ሸኔ በመባል የሚጠራው ታጣቂ ቡድን) ጋር ጥምረት ፈጥረው መዋጋት እንደጀመሩና አዲስ አበባን ለመቆጣጠር የመጨረሻ ግፊት እንደሚያደርጉ ገለጹ። ሁለቱ ኃይሎች በነሃሴ ወር 2013 ዓ.ም. ወታደራዊ ትብብር ለማድረግ ከስምምነት ላይ መድረሳቸውን አሳውቀው የነበረ ሲሆን፣ የውጊያ መረጃዎችን እንደሚለዋወጡ እና ሁኔታዎች ሲፈቅዱ ደግሞ በጋራ የሚዋጉ መሆኑን ገልጸው ነበር። በወቅቱ የኦነግ ሸኔ ኃይል መሪዎች በምዕራብ፣ በማዕከላዊ እና በደቡብ ኦሮሚያ የሚገኙ በርካታ ከተሞችን መቆጣጠራቸውን እና ወደ ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ እየተቃረቡ እንደሆነም ይገልጹ ነበር።

46. የትግራይ ኃይሎች ወደ አማራ እና አፋር ክልሎች መግባታቸውን ተከትሎ የክልሎቹ እና የፌዴራል መንግሥታት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል። የአማራ ክልል መንግሥት ሃምሌ 18 ቀን 2013 ዓ.ም የክተት አዋጅ በማወጅ በክልሉ በመንግሥትም ሆነ በግላቸው መሳሪያ የታጠቁ ነዋሪዎች ሁሉ *"የትግራይ ኃይሎችን ለመመከት የታወጀውን የሕልውና ዘመቻ እንዲቀላቀሉ"* ጥሪ አስተላልፈዋል። በቀጣይ ወራትም የትግራይ ኃይሎች ደሴ እና ኮምቦልቻ ከተሞችን ጨምሮ አብዛኛውን ደቡብ ወሎ አካባቢዎች መቆጣጠራቸውን ተከትሎ ጥቅምት 21 ቀን 2014 ዓ.ም. የአማራ ክልል ምክር ቤት

ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ የትግራይ ኃይሎችን በመደበኛ የሕግ ማስከበር ሥርዓት ብቻ ማሸነፍ ስለማይቻል መላው የክልሉ ሕዝብ ዘመቻውን እንዲቀላቀል አስቸኳይ ጥሪ አቅርቧል።

47. በተመሳሳይ ጊዜም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ሕዝቡ “የክት” ጉዳዩን አቆይቶ “ህወሓትን ለመመከት፣ ለመቀልበስና ለመቅበር ማናቸውንም መሳሪያ እና አቅም ይዞ በሕጋዊ አደረጃጀት እንዲዘምት” ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። ይህንን ተከትሎም የአፋር፣ አማራ፣ የሲዳማ፣ ኦሮሚያ እና የሶማሌ ክልል ልዩ ኃይሎች፣ ፖሊሶች፣ ሚሊሺያዎች እና ሌሎች የወጣቶች አደረጃጀቶችን ጨምሮ የመንግሥት የጦር ኃይል አካል በመሆን የትግራይ ኃይሎች ወደ አዲስ አበባ የሚያደርጉትን ግስጋሴ ለማስቆም ከመከላከያ ሠራዊት ጎን በጦርነቱ ተሳትፈዋል። በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድ ወደ ጦር ግንባር በመሄድ መከላከያ ሠራዊቱ የሚያደርገውን ጦርነት ለመምራት መወሰናቸውን በመግለጽ ወደ ግንባር መዝመታቸውን አሳውቀዋል።

48. ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. የፌዴራሉ መንግሥት በመላው ሀገሪቱ ተግባራዊ የሚደረግና ለስድስት ወር የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል። በአዋጁ ለፀጥታ አካላት ከተሰጡት ስልጣኖች መካከል በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል መከላከያ ኃይልን ወይም የትኛውንም ሌላ የፀጥታ አካል በማሰማራት ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ ትዕዛዝ የመስጠት፣ የሰዓት ዕላፊ ገደብ የመወሰን እና ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራል ተብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሥር ማዋል የሚሉት ይገኙበታል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በግንቦት ወር 2013 ዓ.ም ህወሓት እና ኦነግ ሸኔን በሽብርተኝነት መፈረጁ ይታወሳል።

49. ከኅዳር ወር 2014 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ መንግሥት በጦርነቱ የተወሰኑ ስትራቴጂካዊ ግንባሮች ከፍተኛ የመልሶ ማጥቃት መጀመሩን ካስታወቀ በኋላ የትግራይ እና ኦነግ ሸኔ ኃይሎች ግስጋሴ እየተገታ፤ ተቆጣጥረዋቸው ከነበሩት ቦታዎች መልቀቅ መጀመራቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች መውጣት ጀመሩ። ታኅሣሥ 10 ቀን 2014 ዓ. ም. የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት ደብረጽዮን ገብረሚካኤል (ዶ/ር) ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) በላኩት ደብዳቤ ኃይሎቻቸው ከነበሩባቸው የአማራ እና አፋር ክልል አካባቢዎች "ለሰላም ዕድል ለመስጠት" ለቀው እንዲወጡ ማዘዛቸውን ገልጸዋል። ይህም ውሳኔ ወዲያው ተግባራዊ እንደሚሆንና ፤ ግጭቶች በአፋጣኝ ቆመው ድርድር እንዲጀመር ጠይቀዋል። አክለውም የትግራይ ኃይሎች "ከነሙሉ አቅማቸው" መሆናቸውንና ሽንፈትም እንዳልገጠማቸው ጠቅሰዋል። በአንጻሩ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የትግራይ ኃይሎች ከአማራ እና አፋር አካባቢዎች በጦርነት ተሸንፈው እንደለቀቁ ገልጿል።

50. ታኅሣሥ 14 ቀን 2014 ዓ.ም. የፌዴራሉ መንግሥት ከትግራይ ኃይሎች ነጻ በማውጣት በቁጥጥሩ ስር ባስገባቸው የአፋርና የአማራ ክልል ቦታዎች ላይ እንዲቆይ እና ወደ ትግራይ ክልል እንዳይገባ ትዕዛዝ መተላለፉን አሳውቋል። ጥር 18 ቀን 2014 ዓ.ም. የፌደራል መንግሥት ለሀገሪቱ ስጋት የነበረው “የሀገር ህልውና እና ሉዓላዊነት አደጋ” መቆጣጠር የሚቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱን በማሳወቅ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመላ ሀገሪቱ ለስድስት ወራት ተጥሎ የነበረውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳ ውሳኔ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ የተወካዮች ምክር ቤት ይህንኑ ውሳኔ በመቀበል የካቲት 8 ቀን 2014 ዓ.ም. አዋጁን አንስቶታል።

51. ይህ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅት በአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን እና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሰላማዊ የፖለቲካ መፍትሄ ጥረቶች የተጀመሩና የጦርነት ሁኔታው በተወሰነ መጠን የቀነሰ ቢሆንም፤ በመንግሥት እና በትግራይ ኃይሎች መካከል የተኩስ አቁም ስምምነት ባለመኖሩ፤ ግጭቱ እንደቀጠለ ይገኛል። የፌደራል መንግሥት በትግራይ ክልል የአየር እና የድሮን ጥቃቶች ያካሄደ ሲሆን፣ የትግራይ ኃይሎች ደግሞ በተወሰኑ የአማራ ክልል ድንበር አካባቢዎች ከአደረጉት ጥቃት በተጨማሪ በተለይ ከጥር ወር 2014 ዓ.ም. መጀመሪያ ጀምሮ በአፋር ክልል ድንበር በኩል በከፈቱት ወታደራዊ ጥቃት ተመልሰው ወደ አፋር ክልል አካባቢዎች በመግባት ይህ ሪፖርት ይፋ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ በአፋር ክልል የኪልበቲ ረሱ ዞን ውስጥ ያሉ የተለያዩ አምስት ወረዳዎችና የአብአላ ከተማን ተቆጣጥረዋል።

# በምርመራው የተለዩ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች

## 1. በሲቪል ሰዎች፣ ሲቪል ተቋማት እና ሌሎች ጥበቃ በሚደረግላቸው ሰዎች ላይ ጥቃት ማድረስ

### መግቢያ

52. በመንግሥት ኃይሎች እና በትግራይ ኃይሎች መካከል የሚደረገው ጦርነት ወደ አፋርና አማራ ክልሎች መስፋፋቱን ተከትሎ በተፋላሚ ኃይሎች መፈጸማቸው የተዘገቡት ጥሰቶች ሆን ብሎ በሲቪል ሰዎች ላይ የሚደረጉ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ግድያ እና የአካል ጉዳት ማድረስን፤ በሲቪል ሰዎች እና ጥበቃ በተደረገላቸው ተቋማት ላይ ጥቃት ማድረስን እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የሲቪል ሰዎች ንብረቶች ውድመትን ያካትታሉ። ኢሰመኮ ምርመራውን ባካሄደባቸው የአፋር እና አማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ብቻ በጦርነቱ ተፋላሚ ኃይሎች ከመለየት፣ ጥንቃቄ እና ተመጣጣኝነት መርሆዎች ውጪ በሲቪል ሰዎች መኖሪያ አካባቢዎች ላይ በተፈጸሙ የከባድ መሳሪያ ጥቃቶች ቢያንስ 403 ሰዎች መገደላቸውን፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለቀላል እና ከባድ የአካል ጉዳት መዳረጋቸውን እንዲሁም በሲቪል ሰዎች ንብረቶች እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥበቃ በተደረገላቸው በጤና ተቋማት፤ በትምህርት ቤቶች፤ በሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ወታደራዊ ጠቀሜታ በሌላቸው የግልና የመንግሥት ተቋማት ንብረቶች ላይ ያለልዩነት የተፈጸሙ ጥቃቶችንና የደረሱ ውድመቶችን ሰንዷል።

### የሕግ ማዕቀፍ

53. ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ በጦርነት ወቅት ጦርነቱ ሊካሄድ የሚችልባቸው መሳሪያዎች እና ዘዴዎች ላይ ወሰን በማድረግ ሲቪል ሰዎችን እና የሲቪል ተቋማትን ከጥቃት ይከላከላል፤ ጥበቃ ያደርጋል።[25] ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕጋት በሲቪል ሰዎችና ሲቪል ግዑዞች (civilian objects) ላይ በማጥቃትም ሆነ በመከላከል ወቅት ጉዳት ማድረስን ይከለክላሉ።[26]

54. "መለየት" መሠረታዊ የሰብአዊነት ሕግ መርህ ሲሆን በጦርነቱ የሚካፈሉ አካላት ያለባቸውን ሲቪል ሰዎችን እና የሲቪል ግዑዞችን/ዕቃዎች ወይም ቁሳቁሶችን ከወታደራዊ ዒላማዎች የመለየት ኃላፊነትን ይመለከታል።[27] አንድ ነገር ወታደራዊ ዒላማ ነው ተብሎ ለመወሰድ በተፈጥሮው፣ በሚገኝበት ቦታ፣

[25] ICRC; What is international Humanirtarian Law?

[26] Protocol Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949, and Relating to the Protection of Victims of Non-International Armed Conflicts (Protocol II). Articles 13 et seq.

[27] ICRC, Customary IHL Database, Rule 1. Principle of Distinction Between Civlians and Combatants. https://ihl-databases.icrc.org/customary-ihl/eng/docindex/v1_rul_rule1

በተግባሩ እና ጥቅሙ የተነሳ ውጤታማ ወታደራዊ እርምጃ ለመፈጸም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው መሆን እና ይህ ነገር ሙሉ ለሙሉ መውደሙ፣ መደምሰሱ፣ መያዙ ወይም ጥቅም እንዳይሰጥ መደረጉ በወቅቱ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ግልጽ/የማያጠራጥር ወታደራዊ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ መገኘት አለበት::[28]

55. ሲቪል ሰዎች በውጊያ በቀጥታ እስካልተሳተፉ ድረስ እንዲሁም በውጊያ ሲሳተፉ የነበሩ ማናቸውም ሰዎች ቢሆኑ፣ በውጊያው መሳተፍ ካቆሙበት ወቅት ጀምሮ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ስር ጥበቃ ይደረግላቸዋል::[29] በውጊያ በቀጥታ ያልተሳተፉ ወይም መሳተፍ ያቆሙ ሰዎች ላይ ሆነ ብሎ ጥቃት መሰንዘር የጦር ወንጀል ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል::[30] በተጨማሪም የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ወታደራዊ እና ወታደራዊ ያልሆኑ ዒላማዎችን ላይ ልዩነት ሳያደርጉ ጉዳት ማድረስን ይከለክላል::[31]

56. ጥንቃቄ የማድረግ መርህ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መሰረት በጦርነት ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች ሁሉ በሚወስዷቸው ወታደራዊ እርምጃዎች የሲቪል ሰዎች ሕይወት እና የሲቪል ግዐዞች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ወይም ጉዳቱ እጅግ እንዲቀንስ የሚቻለውን ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልፃል::[32]

57. በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ሌላው መሰረታዊ መርህ ተመጣጣኝነት ነው:: የተመጣጣኝነት መርህ በተዋጊ ኃይሎች በወታደራዊ ዒላማዎች ላይ የሚፈጽሙት ማንኛውም ጥቃት በሲቪል ሰዎች ሕይወት፣ አካል እንዲሁም ሲቪል ዕቃዎች ወይም ንብረቶች ላይ ከፍተኛ እና ሊገኝ ከሚችለው ወታደራዊ ጠቀሜታ አንጻር ተመጣጣኝ ያልሆነ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ጥቃቱ መፈጸም እንደሌለበት ይደነግጋል::[33]

[28] ICRC, Customary IHL Database, Practice Relating to Rule 8. Definition of Military Objectives. https://ihl-databases.icrc.org/customary-ihl/eng/docindex/v2_rul_rule8
[29] Article 3 common to the four Geneva Conventions.
[30] Rome Stature of the International Criminal Court, 17 July 1998, Article 8.
[31] Supra note 12
[32] ICRC, Customary IHL Database, Rules 15 and 22.
[33] ICRC, Customary IHL Database, Rule 14.

**ከመለየት፣ ጥንቃቄ እና ተመጣጣኝነት መርህ ውጪ የተፈጸሙ ጥቃቶች[34]**

58.የትግራይ ኃይሎች በአፋር ክልል በጋሊኮማ ቀበሌ ሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ከሌሊቱ 9:00 ሰዓት አካባቢ ባደረሱት ጥቃት 27 ሕፃናትን ጨምሮ 107 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል፡፡ በዚሁ ጥቃት 35 ሰዎች ከቀላል እስከ ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 5 ሕፃናት ይገኙበታል፡፡ የትግራይ ኃይሎች የያሎ፣ አውራ እና ጉሊና ወረዳዎችን ከተቆጣጠሩ በኋላ በእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ ስምንት ቀበሌዎች በጦርነቱ ምክንያት ለደህንነታቸው በመስጋት ተፈናቅለው የመጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሲቪል ሰዎች በጋሊኮማ ቀበሌ በሚገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጤና ጣቢያ ውስጥ እንዲሁም በአካባቢው በሚገኝ ሜዳማ ስፍራ ላይ በጊዜያዊነት ተጠልለው ይገኙ ነበር፡፡ ከጋሊኮማ ትምህርት ቤት እና ጤና ጣቢያ በቅርብ ርቀት (በግምት 3 ኪ.ሜ) ላይ በሚገኘው የኡፋ ተራራ ላይ የአፋር ክልል ልዩ ኃይል እና ሚሊሺያ ይገኙ ነበር፡፡

59.የትግራይ ኃይሎች የኡፋ ተራራ ላይ ከባድ መሳሪያ መተኮሳቸውን ተከትሎ የአፋር ክልል ልዩ ኃይል እና ሚሊሺያዎች ተራራውን በመልቀቅ በስተምስራቅ በኩል ወደሚገኘው የጋሊኮማ ተራራ አፈገፈጉ፡፡ የትግራይ ኃይሎች የጋሊኮማ ተራራን ማጥቃት ሲጀምሩ በከባድ መሳሪያ እና በተኩስ ድምጽ ተደናግጠው በአቅራቢያቸው ወደሚገኙት ወናሳ ሜዳ እና ጉሊና ወንዝ በመሸሽ ላይ በነበሩ እንዲሁም በጋሊኮማ ቀበሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጤና ጣቢያ ውስጥ ተጠልለው በነበሩት ተፈናቃዮች እና ነዋሪዎች ላይ የትግራይ ኃይሎች በቀላል እና ከባድ መሳሪያዎች የታገዘ ጥቃት ከፍተዋል፡፡ በዚህም ወደ ወናሳ ሜዳ ሲሮጡ የነበሩ ሲቪል ሰዎች ላይ በደረሰ ጥቃት ብቻ 23 ሲቪል ሰዎች ወዲያውኑ እንደሞቱ የተጎጂ ቤተሰቦች እና ነዋሪዎች ያስረዳሉ፡፡ አንድ ተጎጂ ስለ ሁኔታው ለኮሚሽኑ ሲገልጹ፦

> *“የከባድ መሳሪያው ድምጽ ልክ እንደ መብረቅ ነጎድጓድ ነበር ሲተኮስም አካባቢው ላይ ብርሀን ይታይ ነበር፡፡ በከባድ መሳሪያው ድምፅ ደንግጠን ወደ ሜዳው ስንሸሽ ጥይት እንደዝናብ እላያችን ላይ ወረደብን” ብለዋል፡፡*

60.በትግራይ ኃይሎች በጋሊኮማ ትምህርት ቤት ላይ የተተኮሰው ከባድ መሳሪያ ባስነሳው እሳት ምክንያት ለተፈናቃዮች በእርዳታ የመጣ ምግብ የተከማቸበት የትምህርት ቤቱ መጋዘን ውስጥ የነበሩ 8 ሲቪል ሰዎች ተቃጥለው መሞታቸውን፣ እንዲሁም በመጋዘኑ ውስጥ የነበረው የእርዳታ ምግብ ሙሉ በሙሉ መቃጠሉን የዓይን እማኞች አስረድተዋል፡፡ በጥቃቱ ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ዲግዲጋ ጤና ጣቢያ ከሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. ከጠዋቱ 1:00 ሰዓት ጀምሮ ከመጡ ሲቪል ሰዎች መካከል 68 ሰዎች (39 ወንዶች እና 29 ሴቶች) ሲሞቱ፣ ከነዚህ ውስጥ 27 ሚኞች ዕድሜያቸው ከ2-15 ዓመት የሆኑ ሕፃናት ናቸው፡፡ በተመሳሳይ 43 ሲቪል ሰዎች በጥቃቱ ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ዱብቲ አጠቃላይ ሆስፒታል ከሐምሌ 29 እስከ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ለሕክምና እርዳታ የመጡ ሲሆን ከነዚህ መካከል 8 ሰዎች (6 ሴቶች እና አንድ የ9 ዓመት ሕፃንን ጨምሮ 2 ወንዶች) ሞተዋል፡፡

[34] Attacks in violation of the principles of distinction, precaution and proportionality

ከዚህም በተጨማሪ 35 ሰዎች (አምስት ሕፃናትን ጨምሮ 30 ሴቶች እና 5 ወንዶች) ከቀላል እስከ ከባድ የሆነ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

61. ሐምሌ 9 ቀን 2013 ዓ.ም. በአፋር ክልል በያሎ ወረዳ በትግራይ ኃይሎች ወደ ጎቢ-ዱራ ከተማ በተተኮሰው ከባድ መሳሪያ በመኖሪያ ቤታቸው የነበሩ 3 ሲቪል ሰዎች (አንድ የ85 ዓመት አዛውንት እና አንድ አራስ እናት ከነልጇ) መገደላቸውን የዓይን እማኞች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

62. ሐምሌ 16 ቀን 2013 ዓ.ም. በአማራ ክልል በሚገኘው አዲ አርቃይ ከተማ ላይ የትግራይ ኃይሎች ከባድ መሳሪያ በመተኮሳቸው የ6 ወር እና የ5 ዓመት ሕፃናትን እንዲሁም የ60 ዓመት አረጋዊን ጨምሮ 6 ሰዎች (3 ወንዶች እና 3 ሴቶች) የገደሉ መሆኑን ኮሚሽኑ ከተጎጂ ቤተሰብ እና ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል።

63. ትግራይ ኃይሎች ከነሃሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በአፋር ክልል በርሀሌ ወረዳ፣ አላ ቀበሌ በሚገኙ ሶስት መንደሮች (ኩሱርቱ፣ አሰዳ እና አድአርዋ) ባደረሱት በከባድ መሳሪያ የታገዘ ጥቃት 13 ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል። ከነዚህም ውስጥ 12 ወንዶች እና 1 ሴት ሲሆኑ ስድስቱ ዕድሜያቸው ከ3 ወር እስከ 15 ዓመት የሆኑ ሕፃናት መሆናቸውን የተጎጂ ቤተሰቦች እና የዓይን እማኞች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። በእነዚህ ሶስት መንደሮች በትግራይ ኃይሎች በተከፈተው ጥቃት ዕድሜያቸው ከ 10 እስከ 16 ዓመት የሆኑ 3 ሕፃናትን ጨምሮ በ6 ሲቪል ሰዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለው የአካል ጉዳት ደርሷል።

64. ጥቅምት 6 ቀን 2014 ዓ.ም. በትግራይ ኃይሎች የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ አፋር ክልል በጭፍራ ወረዳ አስኮማ ቀበሌ ቡልቡላ ጃራ (አንዳ ጃራ) መንደር ወድቆ በፍንጣሪው አንዲት የ 10 ዓመት ሕፃን ስትሞት በአንድ የ30 ዓመት ሴት ደግሞ እግሯ ላይ የአካል ጉዳት ማድረሱን ተጎጂዎች እና ምስክሮች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። ኢሰመኮ ተጎጂዋን ባነጋገረበት ወቅት ይህንኑ ጉዳት የተመለከተ ሲሆን ከባድ መሳሪያው በወደቀበት ወቅት በአካባቢው ምንም አይነት የታጠቀ ኃይል ያልነበረ መሆኑን ገልጻለች።

65. በአማራ ክልል አጣዬ ከተማ ኅዳር 5 ቀን 2014 ዓ.ም. በትግራይ ኃይሎች በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ በከተማዋ ቀበሌ 03 ልዩ ስሙ አጣዬ አደባባይ ተብሎ በሚጠራ ሥፍራ 6 ሲቪል ሰዎች መገደላቸውን እንዲሁም በዚሁ እለት በከተማው ልዩ ስሙ ድሬ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ላይ የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑ 2 ሰዎችን ጨምሮ 3 ሲቪል ሰዎች በቤታቸው እያሉ በተተኮሰው ከባድ መሳሪያ መገደላቸውንና ሌሎች 2 ሲቪል ሰዎች መቁሰላቸውን፤ ከባድ መሳርያው የወደቀባቸው የሲቪል ሰዎች መኖሪያ ቤቶች ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ መሆናቸውንና አንድ ሕንጻ ደግሞ ጉዳት እንደደረሰበት ኮሚሽኑ ከተጎጂዎች፣ ከምስክሮች፣ ከከተማው አስተዳደር፣ የሰነድ ማስረጃዎችና በመስክ ምልከታ በሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ችሏል። የትግራይ ኃይሎች ወደ አጣዬ ከተማ ከመግባታቸው በፊት ከከተማው በስተሰሜን አቅጣጫ የሚገኘውን ተራራ በመቆጣጠር በመንግሥት መከላከያ ሠራዊት ቁጥጥር ስር ወደነበረችው አጣዬ ከተማ የከባድ መሳሪያ በተደጋጋሚ መተኮሳቸውን እና ከኅዳር 5

ቀን ጀምሮ እስከ ኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ የትግራይ ኃይሎች ከተማውን ተቆጣጥረው መቆየታቸውን ምስክሮች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

66. በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን መሀል ሜዳ ከተማ ኅዳር 9 ቀን ማታ 12 ሰዓት አካባቢ በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ፍንጣሪ የቆሰለን አንድ ሲቪል ሰው ለማንሳት የሄዱ 4 የአንድ ቤተሰብ አባላትና 1 ጎረቤት (3 ወንዶችና 1 ሴት) በድጋሚ በተተኮሰ ሌላ የከባድ መሳሪያ ፍንጣሪ ሲገደሉ 6 ሲቪል ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል። ምስክሮች በወቅቱ የትግራይ ኃይሎች በአካባቢው እንዳልገቡና አካባቢውን የተቆጣጠሩት በማግስቱ ኅዳር 10 እንደሆነ ገልጸዋል። ኮሚሽኑ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ከባድ መሳሪያዎቹ በመከላከያ ሠራዊት እንደተተኮሱ ተገንዝቧል።[35]

67. ኅዳር 12 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 1:30 ሰዓት አካባቢ በወቅቱ በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበረው በአማራ ክልል ላስታ ወረዳ ድብኮ ከተማ በተደረገ የድሮን ድብደባ፣ እንዲሁም ጥቅምት 2 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 6:00 ሰዓት አካባቢ የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ለገበያ በወጡ ሲቪል ሰዎች ላይ በማረፉ በድምሩ 5 ሲቪል ሰዎች ሲገደሉ 19 ሰዎች ደግሞ የተለያየ መጠንና ዓይነት ያለው የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በጥቃቶቹ ከተገደሉት ሲቪል ሰዎች መካከል አንድ የ 2 ዓመት ሴት ሕፃን፣ የ80 ዓመት አረጋዊ እንዲሁም ከቆሰሉት መካከል ሁለት ሕፃናት እና የ 70 ዓመት አረጋዊ ይገኙበታል፤ ሁለት መኖሪያ ቤቶችም ወድመዋል። ኅዳር 12 ቀን 2014 ዓ.ም. የደረሰው የድሮን ድብደባ የሁለት ግለሰቦች ቤት ላይ ያነጣጠረ ሲሆን ጥቃቱ ከመድረሱ በፊት ባሉት ቀናቶች የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በተደጋጋሚ ጥቃቱ በደረሰበት ቤት እና በአካባቢው ከበሉና ከጠጡ በኋላ በአቅራቢያ ወደሚገኘው ተራራ ይሄዱ እንደነበር ሆኖም ጥቃቱ በደረሰበት ዕለት በስፍራው እንዳልነበሩ ከምስክሮች ለመረዳት ተችሏል።

68. በተመሳሳይ ሁኔታ በመርሳ ከተማ ታኅሣሥ 6 ቀን 2014 ዓ.ም. በተሳቢ መኪና ተሳፍረው ወደ ደሴ አቅጣጫ ለመሄድ በሚል ለጊዜው በመንገድ ላይ ቆመው በነበሩ የትግራይ ኃይሎች ላይ በመከላከያ ሠራዊት በተፈጸመ የድሮን ጥቃት በአካባቢው በግብይት ላይ የነበሩ 9 ሲቪል ሰዎች ሲገደሉ ሌሎች 9 ሲቪል ሰዎች ላይ ቀላል እና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል።

69. ታኅሣሥ 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ወልዲያ ከተማ ቀበሌ 02 በተለምዶ ፒያሳ በተባለው አካባቢ በመከላከያ ሠራዊት በተፈጸመ የድሮን ጥቃት በአንድ ሕንፃ በረንዳ ላይ ሻይ ቡና፣ ምግብ፣ ውሃ የሚሸጡ በተለምዶ 'ሱቅ በደረቴ' በመባል የሚጠሩ የጎዳና ላይ ነጋዴዎች እና አገልግሎት በመጠቀም ላይ

---

[35] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒቴር ለኮሚሽኑ በሰጠው መልስ "በየትኛውም ጦርነት ተጓዳኝ ጉዳቶች ሊኖሩ የሚችሉ ቢሆንም በተለይ ደግሞ የአሸባሪው ቡድን ከሚከተለው የማጭበርበር የጦርነት ስልት አኳያ ተጓዳኝ ጉዳቶች ከፍ ማለታቸው የማይቀር ነው። ጠላት የሲቪል መገልገልያ ተቋማትን ለወታደራዊ ዓላማ ይጠቀም የነበረ ሲሆን የግለሰብ መኖሪያ ቤቶችንም ሳይቀር ለጦርነት ጥቅም አውሏል። በመሆኑም ከባድ መሳሪያ ተኩስ ወቅት ጠላትን ኢላማ ያደረጉ ተኩሶች በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት የማስከተላቸው እድል ሰፊ በመሆኑ ኮሚሽኑ ያቀረበውን ምርመራ መነሻ በማድረግ መከላከያም የደረሱ ተጓዳኝ ጉዳቶችን በማጥናት በቀጣይ አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ ይሆናል።" ብሏል። (አባሪ ቁጥር 8)

የነበሩ 6 ሲቪል ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 4 ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል፡፡[36] ከሟቾች መካከል አንድ አካል ጉዳተኛ ይገኝበታል፡፡ ጥቃቱ በተፈጸመበት አካባቢ ብዛት ያላቸው የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ምግብ እና ሻይ ቡና እየተጠቀሙ የነበረ መሆኑን በጥቃቱ ክንዳቸውና ዓይናቸው ላይ የመቁሰል ጉዳት የደረሰባቸው ተጐጂ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል፡፡

70.በትግራይ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች በመከላከያ ሠራዊት በተፈጸሙ የአየር እና ድሮን ጥቃቶች በሲቪል ሰዎች እና ተቋማት ላይ ጉዳቶች መድረሳቸውን ለኢሰመኮ መረጃዎች ደርሰውታል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የጣምራ ምርመራው ሪፖርት በሸፈነው ጊዜ ውስጥ ተከስቶ የነበረው የሰኔ 15 ቀን 2013 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 7፡00 ሰዓት በትግራይ ክልል ደቡብ ምስራቅ ዞን እንደርታ ወረዳ ደብረናዝሬት ጣብያ ቶጎጓ ጎጥ በሚገኘው የመገበያያ ቦታ የአየር ድብደባ የተከናወነ ሲሆን በጥቃቱ ቢያንስ 40 ሰዎች ሲሞቱ ከ 200 በላይ ሰዎች ደግሞ ቀላል እና ከባድ ጉዳት እንደደረሰባቸው ኮሚሽኑ ከተጎጂዎች እና ከሕክምና ባለሙያዎች ያገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡ በአየር ጥቃቱ ሕፃናትን ጨምሮ በስፍራው የነበሩ ሲቪል ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በአየር ድብደባው ምክንያት የኤሌክትሪክ ገመዶች፣ የመኖርያ ቤቶች እና የንግድ ቤቶች (በስፍራው የሚገኘው ብቸኛ የእህል ወፍጮ ቤትን ጨምሮ) ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፡፡

71.ጉዳቱ በደረሰበት እለት አምቡላንሶች ከመቀሌ ከተማ ወደስፍራው እንዳይጓዙ በመከላከያ ሠራዊት በመከልከላቸው ምክንያት በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የሕክምና እርዳታ ለማግኘት ወደ ሆስፒታሎች መውሰድ የተቻለው በቀጣይ ቀናት ነበር፡፡ በወቅቱ የመከላከያ ሠራዊት አመራሮች እንደገለጹት፣ በነበረው የፀጥታ ስጋት ምክንያት ወደ ቦታው መንቀሳቀስ አስቸጋሪ ስለነበር ለተወሰነ ሰዓታት ክልከላ እንደነበር፤ ሆኖም ከረፋዱ 11፡00 ሰዓት ጀምሮ ግን የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ አንቡላንሶች ወደ ስፍራው መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ቢነገራቸውም "በተባበሩት መንግሥታት አሰራር መሰረት ከረፋዱ 11፡00 ሰዓት በኋላ መንቀሳቀስ እንችልም" የሚል መልስ በመስጠታቸው አምቡላንሶቹ በዕለቱ አለመድረሳቸውን አስረድተዋል፡፡

72.በስፍራው የነበረውን ወታደራዊ ዒላማ በሚመለከት ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ምስክሮች እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች እንደሚሉት በቦታው ታጣቂዎች እንዳልነበሩ እና ስፍራው የገበያ ቦታ መሆኑን ሲገልጹ፤ በአንጻሩ በወቅቱ በስፍራው የነበሩት የመከላከያ ሠራዊት ኃላፊዎች ግን ጥቃቱ በተፈጸመበት ቦታ የሰኔ 15 የሰማዕታት በዓልን ለማክበር በሚል የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ተሰብስበው እንደነበር፤ አካባቢውን የትግራይ ኃይሎች ለወታደራዊ ዓላማ ይጠቀሙበት እንደነበረና በጥቃቱ ሰዓት 200 የሚሆኑ ትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ተሰባስበው እንደነበር በተገኘ መረጃ መሰረት የተወሰደ እርምጃ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

---

[36] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመከላከያ ሠራዊት ይህንን እና ሌሎች በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት ያደረሱ የድሮን ጥቃቶችን አስመልክቶ በሰጠው ምላሽ "ከድሮን ጥቃት ጋር በተያያዘ ኢላማን ለይቶ በመምታት ረገድ የጎላ ስህተት የማይፈጠር ቢሆንም ከወታደራዊ ጠቀሜታቸው አኳያ ኢላማ በተደረጉ ቦታዎች (ተቋማት ላይ) የደረሰ ተጓዳኝ ጉዳት ካለ በተቋሙ የሚረጋገጥ እና አስፈላጊው እርምት የሚወሰድበት ይሆናል ብሏል። (አባሪ ቁጥር 8)

73.ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ቀናት በመቀሌ ከተማ እና አካባቢው በደረሱ የአየር እና የድሮን ጥቃቶች በሲቪል ሰዎች እና ሲቪል ተቋማት ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ኮሚሽኑ በልዩ ልዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች አጣርቷል። ከነዚህም ውስጥ ጥቅምት 8 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በመቀሌ ከተማ መሶቦ አካባቢ በደረሰ አየር ጥቃት የ9፣ የ12 እና የ14 ዓመት ሕፃናት እረኞች ከነ ከብቶቻቸው የሞቱ ሲሆን በአንድ ሰው ላይም አካል ጉዳት ደርሷል። በተመሳሳይ ዕለት ከምሽቱ 12፡30 ሰዓት ላይ መቀሌ ከተማ በሚገኘው ፕላኔት ሆቴል ላይ በደረሰ አየር ጥቃት በንብረት ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን በ 6 ሰዎች ላይ አካል ጉዳት ደርሷል። ጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. በመስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪንግ የጎማ መጋዘን ላይ በደረሰ የአየር ድብደባ ምክንያት 2 ሰራተኞች ሲሞቱ በ7 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል። ጥቅምት 12 ቀን 2014 ዓ.ም. በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ አሪድ ግቢ አካባቢ ከቀኑ 5፡40 ሰዓት በተደረገው የአየር ድብደባ በ11 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል። ጥቅምት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 10፡00 አከባቢ በመቀሌ ከተማ ላጪ በሚባል አከባቢ ባለው የከተማው መብራት ኃይል ንዑስ ማከፋፈያ ጣቢያ (sub station) ላይ የድሮን ድብደባ የተፈጸመበት ሲሆን በድጋሚ በተፈጸመ የድሮን ድብደባ በመጀመሪያው ጥቃት የተቀሰቀሰውን እሳት በማጥፋት ላይ የነበረ የእሳት አደጋ ሰራተኛ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

74.በመቀሌ ከተማ በተለያዩ ቀናት በግለሰቦች ቤቶች ላይ የድሮን ጥቃቶች የተፈጸሙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ጥቅምት 18 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት በመቀሌ ከተማ ሰሜን ክፍለ ከተማ 06 ቀበሌ ደረቅ ወደብ በሚባል አከባቢ በሚገኙት የግል መኖርያ ቤቶች ላይ በተፈጸመ የአየር ድብደባ 2 የ10 ዓመት ሕፃናትን ጨምሮ 6 ሰዎች ሲሞቱ በ24 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።

75.ኮሚሽኑ ከላይ ከተዘረዘሩት ጥቃቶች ጋር በተያያዘ በሰበሰበው መረጃ ከጥቃቶቹ በፊት ሲቪል ሰዎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚያሳስቡ ምንም አይነት የቅድመ ማስጠንቀቂያ እርምጃዎች እንዳልነበሩ ለማወቅ ተችሏል።

**ሲቪል ሰዎችን እንደ ከለላ መጠቀም**

76.የትግራይ ኃይሎች በአማራ ክልል የመቄት ወረዳን ከሐምሌ 24 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ መስከረም 1 ቀን 2014 ዓ.ም. ተቆጣጥረው በነበሩበት ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እና የአማራ ልዩ ኃይል የመቄት ወረዳ አካባቢዎችን ለማስለቀቅ ባደረጉት ጦርነት በርካታ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል። በመቄት ወረዳ ደብረዘቢጥ ቀበሌ፣ የትግራይ ኃይሎች የሲቪል ሰዎች መኖሪያ ቤቶችን ምሽግ አድርገው ሲዋጉ ከመከላከያ ሠራዊት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ የሁለት ሲቪል ሰዎች ሕይወት አልፏል። የትግራይ ኃይሎች ከነሃሴ 12 እስከ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. በደባርቅ ወረዳ፣ ቦዛ ቀጠና በሚባሉ የአዲ ጋግራ፣ የአብርሃም እና የአዳጋት ቀበሌዎችን ይዘው በነበረበት ወቅት፤ የአካባቢው ቀበሌዎችን የውጊያ ሜዳ፤ የአርሶ አደሮችን ቤት እንደ ምሽግ አድርገው ይጠቀሙ ነበር። በዚህ ምክንያት በ መከላከያ ሠራዊት ወደ አርሶ አደሮች ቤቶች በተተኮሱ ከባድ መሳሪያዎች 6 ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል።

77. በነሐሴ 25 ቀን 2013 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎች በአማራ ክልል ደብረዘቢጥ ቀበሌ ውስጥ በነበረ ውጊያ የነዋሪዎችን ቤት እንደምሽግ በመጠቀም ከባድ መሳሪያዎችን አጥምደው ተታኩሰዋል:: በዚህ ምክንያት ከመከላከያ ሠራዊት የተተኮሱ ከባድ መሳሪያዎች አርሶ አደሮች ግቢዎች ላይ በመውደቃቸው የሁለት ሲቪል ሰዎች ሕይወት አልፏል:: ኮሚሽኑም ከባድ መሳሪያ ያረፈባቸው ቦታዎችን ተመልክቷል:: በዚሁ ቀበሌ በነሃሴ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. የግለሰብ መኖሪያን በምሽግነት በመጠቀም ሲዋጉ የነበሩ የትግራይ ኃይሎች ላይ በመከላከያ ሠራዊት የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ የ13 ዓመት ታዳጊ ልጅ ሕይወቱ ማለፉን እና ሌሎች 3 ሰዎች ላይ አካላዊ ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚች ቤተሰቦች እና ተጎጂዎች ለኢሰመኮ አስረድተዋል::

78.በአርቢት ከተማ አጤ ውኃ ሜዳ እና በከተማዋ ዙሪያ ወደ 7 ኪ.ሜ የሚረዝም የጋሸና ግንባር ተብሎ ይጠራ የነበረ ምሽግ የትግራይ ኃይሎች ሰርተው የነበረ በመሆኑ፤ የመከላከያ ሠራዊት በከተማው ላይ ተደጋጋሚ የከባድ መሳሪያ ድብደባ ማድረሱን ነዋሪዎች ገልጸዋል:: በአርቢት ከተማ 017 ቀበሌ ጥቅምት 3 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 10:00 ሰዓት ገደማ አንድ የግለሰብ መኖሪያ በከባድ መሳሪያ በመመታቱ 3 ሕፃናትን ጨምሮ 7 ሲቪል ሰዎች ሲገደሉ ሶስት ሰዎች ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል:: ከባድ መሳሪያው በወደቀበት አካባቢ የትግራይ ኃይሎች ምሽጎች እንደነበሩና ከባድ መሳሪያው የተተኮሰውም በወቅቱ በመንግሥት መከላከያ ሠራዊት ቁጥጥር ሥር ከነበረው ከገረገራ አቅጣጫ እንደነበር ከምስክሮች ለመረዳት ተችሏል:: የአካባቢው አስተዳደር ለኮሚሽኑ በሰጠው መረጃ መሰረት ከሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. እስከ ታኅሣሥ 8 ቀን 2014 ዓ.ም. ቀበሌ 032 ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተደረጉ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ልውውጦች እና የድሮን ድብደባ ምክንያት 45 ሲቪል ሰዎች ሞተዋል፤ 25 ሲቪል ሰዎች ቆስለዋል፤ 460 መኖሪያ ቤቶችም በከባድ መሳሪያ ወድመዋል:: በዚሁ ከተማ ቀበሌ 017 በተመሳሳይ ጥቃቶች 42 ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል፤ 59 ሰዎች ቆስለዋል፤ 678 መኖሪያ ቤቶች ደግሞ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን የእርሻ ሰብልና መኖም ተቃጥሏል::

79.በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን በምትገኘው የሃይቅ ከተማ ቀበሌ 01፣ 02 እና 05 ከጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ኅዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም. በከተማዋ ውስጥ በነበሩት የትግራይ ኃይሎች እና በ መከላከያ ሠራዊት መካከል በተካሄደ ከፍተኛ የከተማ ውስጥ ውጊያ በሁለቱም ኃይሎች በተተኮሱ ከባድ መሳርያዎች እና በተኩስ ልውውጥ 7 ወንድ፣ 2 ሴት እና 1 ሕፃን፣ በድምሩ 10 ሲቪል ሰዎች መገደላቸውንና 5 ወንድ እና 3 ሴት፣ በድምሩ 8 ሲቪል ሰዎች መቁሰላቸውን እንዲሁም በከተማው በርካታ የመኖሪያ ቤቶች ላይ በተደጋጋሚ በመተኮሱ ጉዳት መድረሱን ኮሚሽኑ ከተጎጂዎች፣ የከተማው አስተዳደር እንዲሁም በምልከታ ለመረዳት ችሏል::

80.በዚሁ ከተማ ቀበሌ 05 አንድ ወጣት ልጃቸው በከባድ መሳሪያ ፍንጣሪ ከሞተባቸው ቤተሰቦች እንዲሁም ከጎረቤቶቻቸው ለመረዳት እንደተቻለው በአካባቢው ከባድ መሳሪያ ከሁለቱም ወገን ይተኮስ ነበር፣ እንዲሁም ሁለቱም ተዋጊ ኃይሎች የሲቪል ሰዎች ቤቶችን እንደምሽግ በመጠቀም በከተማው ላይ ከባድ ውጊያ ተካሂዷል:: ወጣቱ በከባድ መሳሪያ ፍንጣሪ በሞተበት ጊዜ ከአባቱ ጋር በመኖሪያ ግቢያቸው ውስጥ ተቀምጦ የነበረ ሲሆን በወቅቱ የጸጥታ ሁኔታ በአግባቡ መቅበር እንኳን ስላልተቻለ

ቤተሰቦቹ በመኖሪያ ቤታቸው ሳሎን ውስጥ ለመቅበር ተገደው እንደነበር እና ከአንድ ሳምንት በኋላ አስክሬኑን አውጥተው በሙስሊም መካነመቃብር እንደቀበሩት ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

81. በተመሳሳይ ሁኔታ በአማራ ክልል መርሳ ከተማ ነሃሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የመከላከያ ሠራዊት ወደ ከተማው በመግባት በከተማው ቀበሌ 04 መኖሪያ ሰፈሮች ውስጥ ከነበሩ የትግራይ ኃይሎች ጋር ባደረጉት ውጊያ ከ30 በላይ ሲቪል ሰዎች በተባራሪ ጥይት ከመኖሪያ ቤታቸው እና መንገድ ላይ በመሸሽ ላይ ሳሉ መገደላቸውን እንዲሁም ሁለቱም ኃይሎች ከግለሰቦች መኖሪያ ግቢዎች በመግባት ቤቶችን እደከለላ ይጠቀሙ የነበረ መሆኑን ኮሚሽኑ ከምስክሮች ያገኘው መረጃ ያስረዳል። በዚሁ ዕለት በከተማው ቀበሌ 01 እና 03 ውስጥ የሚገኙ ሁለት የግለሰቦች መኖሪያ ቤቶች በመመታታቸው 3 ሲቪል ሰዎች መገደላቸውንና 3 መቁሰላቸውን ኮሚሽኑ ከምስክሮች ያገኘው ማስረጃ ያሳያል።

82. ታኅሣሥ 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አካባቢ በወልዲያ ከተማ መቻሬ በተባለው አካባቢ በመኖሪያ ቤት በራፍ ላይ ከባድ መሳርያ ወድቆ አንድ የ16 ዓመት ልጅ ተገድሏል። ጥቃቱ የተፈጸመበት መኖሪያ ቤት አካባቢ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ከባድ መሳርያዎችን አስቀምጠው ወደ መንግሥት ጦር በደቡብ አቅጣጫ ሲተኩሱ የነበረ መሆኑን እና ልጃቸው የተገደለው የመንግሥት ኃይሎች ለተኩሱ በሰጡት ምላሽ መሆኑን የሟች ቤተሰቦች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። የሟች አባት የአደጋውን አሰቃቂነት ሲገልጹ፦

*"ልጄ መሞቱ ብቻ ሳይሆን አሟሟቱ እንደወጉ አለመሆኑ እጅግ ያሳዝነኛል ምክንያቱም አስከሬኑን ከባድ መሳርያው ወደመሬት ውስጥ ሰርስሮ አስገብቶትና አካሉ ተበጣጥሶ ተቆፍሮ ወጥቶ የተቀበረ በመሆኑ ልረሳው የማያስችለኝና እጅግ ዘግናኝም በመሆኑ ነው" ብለዋል።*

## በሰብአዊነት ሕግ ጥበቃ የተደረገላቸው ንብረቶች ላይ የደረሰ ውድመት

83. በአፋር ክልል ካሳጊታ ከተማ ከጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ በከተማው የሚገኙ የተለያዩ በሰብአዊነት ሕግ ጥበቃ የተደረገላቸው ንብረቶች እና ቦታዎች ላይ ጥቃት ደርሷል። የካሳጊታ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያ እና አባስ መስጂድ ላይ በተለያየ ጊዜያት በመከላከያ ሠራዊት እና በትግራይ ኃይሎች መካከል በነበረው የተኩስ ልውውጥ እንዲሁም በከባድ መሳርያ ጉዳት እንደደረሰባቸው ከዓይን እማኞችና ከመስክ ምልከታ በተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል። የትግራይ ኃይሎች ካሳጊታ ከተማ በቆዩበት ጊዜ የመስጂዱ ቅጥር ግቢ እና የካሳጊታ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን እንደ ወታደር ካምፕ መጠቀማቸውን እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ጀርባ ታንክ አስቀምጠው እየተኮሱ እንደነበረና የመከላከያ ሠራዊት በወሰደው የአፀፋ ጥቃት ትምህርት ቤቱ እና መስጂዱ እንደተጎዱ ለመረዳት ተችሏል።

### ፈንጂዎችን ያለልዩነት ጉዳት በሚያደርሱ መልኩ መጠቀም

84. የትግራይ ኃይሎች በአማራ ክልል በወረባቡ ወረዳ ከነሃሴ 24-29 ቀን 2013 ዓ.ም በቆዩባቸው ቀናት ውስጥ በየአከባቢው የተለያዩ ዓይነት ፈንጂዎችን ቀብረው እንደሄዱ እና ይህ ምርመራ እስከተካሄደበት ጊዜ ድረስ ተቀብረው ያሉ እና ያልወጡ ፈንጂዎች መኖራቸውን ከምስክሮች እና ከአገር ሽማግሌዎች ለመረዳት ተችሏል። በወረዳው ቀበሌ 018 ውስጥ ነዋሪ የሆኑ እና በእርሻ ስራ ላይ የነበሩ ሕፃናት በመስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎች ተቀብሮ እና ተጥሎ ያገኙትን ፈንጂ በመነካካት ላይ እያሉ በመፈንዳቱ 5 ሕፃናት (3 ሴቶች እና 2 ወንዶች) ሕይወት ወዲያውኑ ሲያልፍ 1 ሕፃን ጉዳት ደርሶባት በደሴ ሆስፒታል የሕክምና ክትትል እየተደረገላት እንደነበር ተገልጿል። ኮሚሽኑም በአከባቢው የተቀበሩ ፈንጂዎች መኖራቸውን ተመልክቷል።

### ተፅዕኖ

85. ከዚህ በላይ የተገለጹት በተለያዩ መንገዶች የተፈጸሙ ጥቃቶች ለበርካታ ሲቪል ሰዎች ሞትና የአካል ጉዳት ምክንያት በመሆናቸው የሰዎችን በሕይወት የመኖር መብት ጥሰዋል። በተጨማሪም በርካታ የሕዝብ መገልገያ ተቋማት (በተለይም የጤና እና የትምህርት ተቋማት) ፣ የኃይማኖት ተቋማት እና የግል ንብረቶችም ለወታደራዊ ዓላማ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በተጨማሪ በተለያዩ ጥቃቶች ለጉዳትና ለውድመት ተዳርገዋል። ከነበረው ጦርነት እና ጥቃት ሕይወትን ለማትረፍ እንዲሁም በተፈጠረው የሕዝብና የመንግሥት መሠረተ-ልማቶች አገልግሎት መቋረጥ ምክንያት በርካታ ሲቪል ሰዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለዋል።

### ማጠቃለያ

86. ኢሰመኮ በሰበሰበው መረጃ መሠረት በጦርነቱ ተሳታፊ በሆኑ ኃይሎች በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሲቪል ሰዎች (በወንዶች፣ በሴቶች፣ በወጣቶች፣ በሕፃናትና ታዳጊዎች፣ በአካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ጨምሮ) እንዲሁም በሲቪል ሰዎች ቁሶች ላይ ጥቃት ተፈጽሟል። ጥቃቶቹ በዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ሕግ መሠረት የተቀመጡትን የመለየት፣ ተገቢ ጥንቃቄ የማድረግ፣ የተመጣጣኝነት፣ ሲቪል ሰዎችን እንደ ከለላ ያለመጠቀም እንዲሁም ያለልዩነት ጉዳት የሚያደርሱ ፈንጂዎች አጠቃቀም ላይ የተቀመጡ ክልከላዎችን እና መርሆዎችን በመተላለፍ የተፈጸሙ ናቸው።

87. በጦርነት ምንም ዓይነት ተሳትፎ የሌላቸው ሲቪል ሰዎች እና/ወይም የሲቪል ሰዎች ቁሶች ላይ ቀጥተኛ የሆነ ወታደራዊ ጥቃት ማድረስ ከባድ የሆነ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰት ነው፤ የጦር ወንጀልንም ሊያቋቁም ይችላል። በተጨማሪም ሲቪል ሰዎችንና ቁሶችን እንደከለላ በመጠቀም ለተዘዋዋሪ ጥቃት ተጋላጭ ማድረግ እንዲሁም ይህንን ያደረገን ተፋላሚ ለማጥቃት ሲባል የሚደረግ ልየታ፣ ጥንቃቄ እና ተመጣጣኝነት መርሆዎችን ያልተከተለ ወታደራዊ እርምጃ ተመሳሳይ የተጠያቂነት እና የኃላፊነት ውጤት አለው። በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መሠረት ፈንጅዎችን ያለልዩነት ጉዳት በሚያደርስ መልክ መጠቀምም ተመሳሳይ ተጠያቂነት እና ኃላፊነትን ያመጣል።

## 2. ከሕግ አግባብ እና ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ የሲቪል ሰዎች ግድያዎች እና የአካል ጉዳቶች

### መግቢያ

88.ጦርነቱ በተካሄደባቸውና ኢሰመኮ በዚህ ምርመራ በሸፈናቸው አካባቢዎች ብቻ ቢያንስ 346 ሲቪል ሰዎች ከሕግ አግባብና ከፍርድ ሂደት ውጪ በጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች ተገድለዋል፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም ቀላል እና ከባድ የአካል እንዲሁም የሥነ ልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ በተለይ የትግራይ ኃይሎች እና የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት (በተለምዶ ኦነግ ሸኔ በማለት የሚጠራው ታጣቂ ቡድን) በጦርነት ውስጥ ተሳትፎ ያልነበራቸውን በርካታ ሲቪል ሰዎች ላይ ሕገወጥ እና የፍርድ ሂደትን ያልተከተለ ግድያ ፈጽመዋል፤ የአካል እና የሥነልቦና ጉዳት አድርሰዋል፡፡ የመከላከያ ሠራዊት፣ የአማራ ልዩ ኃይል እና የፋኖ ታጣቂዎችም የትግራይ ኃይሎች እና ኦነግ ሸኔ በአማራ እና አፋር ክልሎች የሚገኙ ስፍራዎችን ተቆጣጥረው በነበረበት ወቅት ከታጣቂ ኃይሎቹ ጋር ተባብረዋል ወይም ደጋፊ ናቸው ያሏቸው ሲቪል ሰዎች ላይ ግድያዎችን መፈጸማቸውን ኮሚሽኑ ያሰባሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

### የሕግ ማዕቀፍ

89.ከፍርድ ውጪ የሚፈጸሙ ግድያዎች ቃሉ እንደሚያመለክተው ሆን ተብሎ ከፍርድ ቤት ሂደት እና ውሳኔ ውጪ በሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ግድያዎች ሲሆኑ ከመብቶች ሁሉ መሰረታዊ ተደርጎ የሚወሰደውን በሕይወት የመኖር መብት የሚጥሱ ናቸው፡፡[37] በሕይወት የመኖር መብት ኢትዮጵያ ፈርማ ባጸደቀቻቸው እንደ ዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳንና የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር ያሉ በርካታ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እንዲሁም እንደ ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ያሉ ልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግ (International Customary Law/Jus Cogens) ደረጃን የያዙና ሁሉንም ሀገራት የሚገዙ የሕግ ማዕቀፎች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥበቃ የተደረገለት መብት ነው፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃም በሕገመንግስቱ አንቀጽ 15 ጥበቃ የተደረገለት ሲሆን፣ መብቱን በመጣስ የሚፈጸም ከፍርድ ውጪ ሰዎችን የመግደል ድርጊት የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል ተደንግጓል፡፡[38]

90.ይህ ምርመራ በለያቸው ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎች በጦርነት አውድ ውስጥ የተፈጸሙ እንደመሆናቸው ከመደበኛው የሰብአዊ መብቶች ሕግ እና የወንጀል ሕግ በተጨማሪ የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት/የጦርነት ሕግም ከሌሎቹ የሕግ ማዕቀፎች ጋር ተመጋጋቢ የሆነ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በመንግሥት፣ በትግራይ ኃይሎች እና በኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች መካከል የተካሄደው ጦርነት በዓለም ዓቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መሰረት ዓለም አቀፋዊ ያልሆነ ጦርነት ተብሎ የሚመደብ እንደመሆኑ፣ በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉም ኃይሎች ሲቪል ሰዎችን ጨምሮ በሕጉ ልዩ ጥበቃ የተደረገላቸውን

[37] International Covenant on Civil and Political Rights, Article 6.
[38] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 538 እና ተከታዮቹ፣ አንቀጽ 270/ሀ

ሰዎች ከሞት እና ከአካል ጉዳት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው::[39] ጦርነትን በሚያካሂዱበት ወቅትም እነዚህኑ ዒላማ ከማድረግ መቆጠብ፣ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ጥበቃ የተደረገላቸውን ሰዎች ከተዋጊ ኃይሎች መለየትን እና ኃይል ለመጠቀም አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜም ቢሆን ተመጣጣኝነትን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል::[40] እነዚህን መስፈርቶች ባልተከተለ መልኩ በሚወሰድ እርምጃ የሚከሰት የሲቪል ሰዎች እና ሌሎች ጥበቃ የተደረገላቸው ሰዎች ሞት በሕይወት የመኖር መብትን የሚጥስ ሲሆን በሰብአዊነት ሕግ መሰረት የጦር ወንጀል (war crime) ሊሆንም ይችላል::[41]

**የምርመራው ግኝቶች**

91.የትግራይ ኃይሎች ወደ አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ዳባት ወረዳ ጭና ቀበሌ ነሃሴ 24 ዕለት ሌሊቱን በመግባት እስከ ነሃሴ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. ቀበሌውን ተቆጣጥረው በቆዩበት ወቅት ቢያንስ 47 ሲቪል ሰዎችን (ወንድ 41 ሴት 6) ገድለዋል:: ሟቾች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዲሁም ከተያዙ በኋላ እጆቻቸው ወደኃላ ታስረው የተገደሉ ሲሆን፣ በተለይም የመንግሥት ኃይሎች ወደ ቀበሌው እየተቃረቡ በመምጣታቸው የትግራይ ኃይሎች ሲያፈገፍጉ በየቤቱ እና በየሰፈሩ ያገኟውን ነዋሪዎች እየገደሉ መሄዳቸውን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ነዋሪዎች ገልጸዋል:: የተጎጂዎች ቤተሰብ የሆኑ የሃይማኖት አባት ስለሁኔታው ሲያስረዱ፦

> *"ነሃሴ 24 ሌሊት (2013 ዓ.ም) ቤት ለቤት እየዞሩ፣ የት ትወጣላችሁ?፣ የት ትሄዳላችሁ? እያሉ እንዳንወጣ ከለከሉን:: ነሃሴ 25ቀን (2013 ዓ.ም.) ጠዋት ሸሽተው የቆዩ አንድ ልጄ እና የወንድሜ ልጅ እኔን ለመጠየቅ ወደ ቤት ተመለሱ:: ይህንን ያዩ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች የቤቱን በር እንድከፍት አዘዙኝ:: በር ከፍቼ፣ 2 ወጣት ልጆች ቤት ውስጥ አሉኝ ብዬ አስረዳሁ:: እነሱም ልጆቹ ምንም ትጥቅ እንደ ሌላቸው አጣርተው ከቤት እንዲቀመጡ አስጠንቅቀውን ወጡ:: በዚሁ መሰረት እስከ ነሃሴ 27 ቀን (2013 ዓ.ም.) ቤት ውስጥ ያለ ምግብ ቆየን:: ነሃሴ 27 ቀን (2013 ዓ.ም.) 6:00 ሰዓት ሲሆን ልጆቹ እርቧቸው ከቤት ወጥተው ከጎረቤት ምግብ ወስደው ሲመለሱ ምግቡን ተቀብለዋቸው በጥይት መትተው ገደሏቸው:: በእለቱ ቀብር ስለተከለከልን በማግስቱ ሌሊት 8:00 ሰዓት በጭና ተክለኃይማኖት ቤተክርስቲያን ቀብራቸው ተፈጸመ::" ብለዋል::*

[39] Supra note 11.
[40] *ibid*
[41] Supra note 15, Article 8/2/a

92. ልጃቸው እና ጨቅላ ሕፃን የልጅ ልጃቸው በትግራይ ኃይሎች የተገደሉባቸው አንድ ነዋሪ ሁኔታውን ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ፦

*“በግጭቱ ጊዜ የአዕምሮ ጭንቀት የጤና ችግር ያለባት እና ሕፃን ልጅ ያላት ልጄ ከኔ ጋር ነበረች። በጦርነቱ ምክንያት ተረብሻ ወጥታ ነበር። ነገር ግን ልጄ ከእነ 11 ወር ሕፃን ልጇ በጥይት ተገድላ በሜዳ ወድቃ ተገኘች። ባለቤቴ ደግሞ መጀመሪያ እንደወጣ አልተመለሰም። የት እንደተወሰደ አላውቅም።” ብለዋል።*

93. ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው አንዲት የቀበሌው ነዋሪ እንዳስረዱት የትግራይ ኃይሎች የቤታቸውን በር እንዲከፍቱ ሲያዟቸው እምቢተኛ በመሆናቸው በበር ቀዳዳ ተኩሰው እግራቸውን በጥይት ያቆሰሏቸው ሲሆን ከሁለት ቀናት በኃላ ደግሞ የሃይማኖት አባት የሆኑ ባለቤታቸውን ቤታቸው በር ላይ በጥይት መተው ከገደሉ በኋላ አስከሬናቸው ለሦስት ቀናት ቆይቶ ተቀብሯል። ይህ ከሆነ በኋላም የ7 ዓመት ሕፃን ልጃቸውን “ይህ አድጎ ነው የሚወጋን” በማለት ገድለውት እንደሄዱ ገልጸዋል። በጭና ቀበሌ በትግራይ ኃይሎች በተፈጸመው ጥቃት የሞቱ ነዋሪዎች በጭና ተክለኃይማኖት እና ዲና ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያናት ቀብራቸው ተፈጽሟል። ኮሚሽኑ በጭና ተክለኃይማኖት ቤተክርስቲያን የጅምላ መቃብሮችን የተመለከተ ሲሆን፣ በሃይማኖት አባቶች እና በተጎጂዎች ቤተሰቦች በአንድ መቃብር እስከ 12 ሰዎች የተቀበሩ መሆኑን ገልጸዋል።

94. የትግራይ ኃይሎች ከሸዋ ሮቢት ከተማ አቅራቢያ በምትገኘው በቀወት ወረዳ የለን ቀበሌ ሲደርሱ የአካባቢው የሚሊሺያ ኃይል ውጊያ ገጥሞ አንድ የትግራይ ኃይሎች አመራር፣ አንድ ታጣቂ፣ እና ከእነርሱ ጋር የመጡ የጤና ባለሙያዎች መገደላቸውን ተከትሎ፤ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ኅዳር 10 ቀን 2014 ዓ.ም. ዕድሜያቸው ከ12 እስከ 55 ዓመት የሚሆናቸው 19 ወንዶችና 1 ሴት አጠቃላይ 20 ሲቪል ሰዎችን በመንገድ ላይ፣ በቤታቸው አካባቢና በቤታቸው ውስጥ እንዳሉ በመያዝ እና አንዳዶችን እጃቸውን ወደኃላ በማሰር በጥይት መትተው ገድለዋል። አንድ የዓይን ምስክር በሚከተለው መልኩ ያየችውን አስረድታለች፦

*“ኅዳር 10 ቀን (2014 ዓ.ም.) ከሸሸሁበት ተመልሼ ነበር። ተኩስ ሲጀመር ከአንድ ሰው ጋር ማሽላ ውስጥ ተደብቀን ቆይተን ወደሌላ ቦታ ለመሸሽ ስንወጣ [የትግራይ] ታጣቂዎች እኛን እና ሌሎች ሁለት ሰዎችን ያዙን። ከኔ ጋር የነበሩትን ሦስቱን ሰዎችን ጫማ አስወልቀው ከደበደቧቸው በኋላ ዓይኔ እያየ ሦስቱንም ሰዎች በጥይት ደረታቸውን መትተው ገደሏቸው። እነርሱ ከተገደሉበት ቦታ ሌሎች ሦስት ሰዎች ተገድለው አስከሬናቸውን ወድቆ አይቻለሁ። እኔን መረጃ ስጪን ብሎ አንዱ ከመታኝ በኋላ ተነጋግረው ለቀቁኝ።” ብላለች።*

ሌላ የአንድ ሟች ቤተሰብ እና ምስክር ስለድርጊቱ ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ፡-

*“ኅዳር 10 ቀን (2014 ዓ.ም.) እኔ ከሸሸሁበት ቦታ 11፡00 ሰዓት ላይ ተመልሼ ስመጣ አንድ ወንድሜን እና አንድ የአጎቴን ልጅ ጨምሮ 8 ሰዎች አባዙር የውሀ መተላለፊያ ቦይ አካባቢ በሸርጣቸው እጃቸውን ወደ ኃላ ታስረው የተለያየ አካላቸው በጥይት ተመትተው ተገድለው አገኘኋቸው። የሁሉንም አስከሬን ከአንድ ሰው ቤት አሳድሬ በማግስቱ ስድስቱን ማሪያም ቤተ ክርስቲያን እና ሁለቱን ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቀበርናቸው።” ብሏል።*

95.በሰሜን ሸዋ ዞን በአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ አሰለሌ ቀለበት ወንበር ቀበሌ ወደሚገኘው አምቦውሃ ኀጥ ኅዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በ3 አቅጣጫ ሲገቡ፣ የአካባቢው አርሶ አደሮች እና የሚሊሺያ ውጊያ ገጥመዋል። የትግራይ ኃይሎች ከተማውን እንደተቆጣጠሩ በሼህ አብደላ መካነ መቃብር ቦታ በዕለቱ በሕመም ምክንያት የሞቱ አንዲት የመንደሩን ነዋሪ ለመቅበር የተሰበሰቡ ሲቪል ሰዎች ላይ በከፈቱት ተኩስ 13 ለቀብር የወጡ ሲቪል ሰዎችን (ሁሉም ወንዶች ናቸው) ገድለዋል። ከዚህ ቀጥሎም የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ቤት ለቤት በመግባት 27 ሲቪል ሰዎችን በጥይት ገድለዋል። በዚህም በአሰለሌ ቀለበት ወንበር ቀበሌ ብቻ በኅዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም. በጠቅላላው 40 ሲቪል ሰዎችን የትግራይ ኃይሎች መግደላቸውን ኮሚሽኑ ከተጎጂዎች፣ ከቤተሰቦቻቸው እና ከምስክሮች ተረድቷል። ከተገደሉት ሲቪል ሰዎች በተጨማሪ የትግራይ ኃይሎች በ85 ሲቪል ሰዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለው የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን ከወረዳው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

96.ነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. በአፋር ክልል በበርሀሌ ወረዳ አላ ቀበሌ የትግራይ ኃይሎች ባደረሱት ጥቃት ዕድሜያቸው ከ3 ወር እስከ 15 ዓመት የሆኑ 6 ሕፃናትን ጨምሮ 13 ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል። አንዲት 6 የቤተሰብ አባሎቿ በጥቃቱ የተገደሉባት ነዋሪ ስለሁኔታው እንደሚከተለው አስረድታለች፡-

*“ የመንደሩ ብዙ ሰዎች ከገበያ ውለን ስንመለስ የወታደር ልብስ የለበሱ የትግራይ ታጣቂዎች ቤታችን አካባቢ ተሰብስበው አየናቸው። ወዲያው ወደ እኛ ጥይት መተኮስ ጀመሩ። ቦምብ ወረወሩብን። እኛም መሸሽ ጀመርን። ከእኔ ጋር ሲሸሹ የነበሩ ቤተሰቦቼ በቦምብ እና ጥይት እየተመቱ ወደቁ። በእህቴ ጀርባ ላይ ታዝሎ የነበረ የ3 ወር ሕፃን ልጅም በጥይት ተመቶ ተገደለ። ኃዘኔን በጣም ያከፋውና ያመመኝ ሳይቀበሩ መቅረታቸው ነው።” ብላለች።*

97.የትግራይ ኃይሎች አፋር ክልል ደራይቱ ከተማ መግባታቸውን ተከትሎ የከተማው ነዋሪ ወደ ተለያየ ቦታ ሲሸሽ በወቅቱ በነበረባት ህመም መሸሽ ያልቻለች አንዲት እናት ተገድላ የተገኘችበትን ሁኔታ የሟች ቤተሰብ ለኮሚሽኑ እንደሚከተለው አስረድቷል፡-

*"ሚች የእናቴ ዘመድ ናት። ጎረቤት ነበርን። 5 ልጆች ነበሯት። አንደኛው ልጅ የሚጠባ ሕፃን ነው። ጦርነቱ ተጀምሮ ማታ ሁሉም ሰው ሲሸሽ እኛም አሴላ ወደሚባል ቦታ ሸሸን። እሷ ግን ሰውነቷ መንቀሳቀስ ስላልቻለ እርሷን፣ የሚጠባው ልጇን እና ከሱ ከፍ የሚለውን ልጅ እዛው ትተን መሄድ የሚችሉትን ልጆቿን ብቻ ይዘን ወደ ገጠር ሸሸን። አካባቢው ተረጋግቷል ተብሎ ስንመለስ እሷ ሞታ ሕፃኑ ልጇ ጡቷን እየጠባ አገኘነው። እኔ ከሷ ልጆች ሁለቱን እያሳደግሁ ነው።"*

98. ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ሲሆን በአፋር ክልል ካሳጊታ ከተማ አትኮማ አካባቢ የዘጠኝ ዓመት ሕፃን እና የ18 ዓመት ሴት ታዳጊ ውሃ ለመቅዳት ወደ አስኤላ ወንዝ በሄዱበት በትግራይ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት እንደተገደሉ ምስክሮች እና የተጎጂ ቤተሰቦች ገልጸዋል። ኮሚሽኑ ያነጋገረው የዓይን እማኝ እንደገለጸው ልጆቹ ውሃ እየቀዱ እያሉ ሦስት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አንደኛዋን አንገቷ ላይ ሁለተኛዋን ደግሞ በግንባሯ ላይ በጥይት በመምታት ገድለዋቸዋል። በወቅቱ ድርጊቱን የተመለከቱ ግለሰብ ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ፦

*"የዘጠኝ ዓመት ሕፃኗን አስከሬን ተሸክሜ ወደ ቤት ስወስድ የትግራይ ታጣቂዎች መንገድ ላይ አግኝተውን "ወደ የት ነው የምትወስዳት? አፋሮች ሁሉ አንድ ናቸው" በማለት በእኔም ላይ ተኩሰውብኝ እጄ ቆስሏል።" በማለት አስረድተዋል።*

99. በሰሜን ወሎ ዞን የሚገኘው የጋሸና ከተማ በመንግሥት እና በትግራይ ኃይሎች መካከል በተለያየ ወቅት ከፍተኛ ውጊያ ተካሂዶበታል። ከሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የትግራይ ኃይሎች ከተማዋን ለአራት የተለያዩ ጊዜያት ተቆጣጥረው ቆይተዋል። በነዚህ ጊዜያት "መከላከያ ሠራዊትን አግዛችኋል፣ ምግብ ውሃ ሰጥታችኋል፣ አስጠልላችኋል፣ የፋኖ፣ የልዩ ኃይል ወይም የሚሊሺያ አባል ናችሁ፣ መሳሪያ ስጡን" በሚሉ እና ሌሎች ምክንያቶች ቢያንስ 57 ሲቪል ሰዎችን ገድለዋል። ነሐሴ 16 ቀን 2014 ሌሊት በጋሸና ከተማ ቀበሌ 13 ልዩ ቦታው ዳና ጊዮርጊስ አካባቢ በመንግሥት ወታደሮችና በትግራይ ኃይሎች መካከል ውጊያ ሲካሄድ ቆይቶ በአካባቢው የነበሩ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ወደ አንድ ቤተሰብ ቤት በመምጣት ምግብ እንዲሰጧቸው ጠይቀው ከተመገቡ በኋላ አስቀድመው ማርከው ይዘዋት የነበረች አንድ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂን ሌሊቱን ከቤታቸው በር ላይ ገድለዋት ሄዱ። በነጋታው ነሐሴ 17 ቀን ጠዋት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ወደ አካባቢው ሲደርሱ የሚቿን አስክሬን በራቸው ላይ በማየታቸው መኖሪያ ቤታቸውን አስከፍተው የቤቱን አባወራ ከደበደቡ እና ካሰቃዩ በኋላ ወደ ጓሮ በመውሰድ በሚስትና በልጆቻቸው ፊት ገድለዋቸዋል። የ21 እና የ25 ዓመት ወጣት የሆኑ ሁለት የሟች ወንድ ልጆችን ደግሞ አስረው ወደ ኮን (የዋድላ ወረዳ ዋና ከተማ) ከወሰዷቸው በኋላ በዚያው ገድለዋቸው፣ አስክሬናቸው ተመልሶ ዳና ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን መቀበሩን የሟቾች ቤተሰቦች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

100. በአማራ ክልል ደባርቅ ወረዳ ቦዛ ቀጠና በሚባሉ የአዲጋግራ፣ የአብርሃም እና የአዳጋት ቀበሌዎችን ከነሐሴ 12 እስከ ነሐሴ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎች ተቆጣጥረው ቆይተዋል። በቀበሌዎቹ በቆዩባቸው ቀናት የትግራይ ኃይሎች 20 ሲቪል ሰዎችን (17 ወንድ 3 ሴት) ተኩሰው ገድለዋል። ኢሰመኮ ያነጋራቸው ምስክሮች ሟቾች በቤታቸው እያሉ፣ በመንገድ ላይ ሲንቀሳቀሱ እና ከብት

በመጠበቅ ላይ እንዳሉ በጥይት ተመትተው የተገደሉ መሆኑን አስረድተዋል። በተጨማሪም የትግራይ ኃይሎች የመቄት ወረዳን ተቆጣጥረው በነበሩበት ወቅት 74 ሲቪል ሰዎችን መግደላቸውን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ይገልጻሉ። ኮሚሽኑ በምርመራው በመቄት ወረዳ በደብረዘቢጥ ቀበሌ ብቻ የ7 ዓመት ሕፃንን ጨምሮ 5 ሰዎች በትግራይ ኃይሎች መገደላቸውን አረጋግጧል።

101. በሰሜን ወሎ ዞን በዋድላ ወረዳ ሐሙሲት ከተማ ጥቅምት 6 ቀን 2014 ዓ.ም. ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ገደማ ለሌሊት የቤተክርሲቲያን አገልግሎት ቤተ-ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ የተቀመጡ 12 አገልጋዮችን የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች “የቆሰሉ የአብይ ወታደሮችን ደብቃችኋል፣ አሳዩን” በሚል ከቤተ-ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ካስወጡ በኋላ በደረታችው እንዲተኙ አደርገው ደብድበዋል። ሰዎቹም ወደ ቤተ-ክርስቲያን የመጡት ለአገልግሎት ብቻ እንደሆነና የመንግሥት ወታደር እንዳልደበቁ ቢገልጹም የቤተ-ክርስቲያኑን ቄስ-ገበዝ እና የዕቃ ቤት ኃላፊ ተኩሰው ገድለዋቸዋል። በስፍራው የነበሩ አንድ ካህን ሁኔታውን ሲያስረዱ፦

> *“ቄስ [ስም]ን ከገደሉት በኋላ እኔን ከአስከሬኑ ጎን አስተኙተው እንደዚህ ቄስ ከምናደርግህ እውነቱን ተናገር አሉኝ። እኔም ለአገልግሎት ነው የመጣሁት የማውቀው ነገር የለም አልኳቸው። ሌሎችንም እንደዛ አደረጓቸው ግን የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ነገሯቸው። ከዚያም የቀረነውን አገልጋዮች እዚያው ሐሙሲት ከተማ ከቅዳሜ ምሽት 5፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ እሁድ ከሌሊቱ 5፡00 ሰዓት ድረስ ባዶ ቤት ውስጥ ያለ ምግብና ውሃ አስረው አቆይተውን ለቀቁን” ብለዋል።*

102. ኮሚሽኑ በደሴ ከተማ ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ምስክሮች እና ከመንግሥት አካላት ባገኘው መረጃ መሰረት የትግራይ ኃይሎች በከተማው ከጥቅምት 20 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ኅዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ በቆዩበት አንድ ወር ከስምንት ቀን ጊዜ በርካታ ሲቪል ዜጎች መግደላቸውን አረጋግጧል። ደሴ ከተማ በገቡባቸው የመጀመሪያ ሁለት ቀናት ማለትም ጥቅምት 20 እና 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በከተማው ልዩ ስሙ ጢጣ በሚባለው አካባቢ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ወደ ደሴ ከተማ ሲገቡ መንገድ ላይ በመገኘታቸው ብቻ እድሜያቸው ከ20-50 ዓመት የሆኑ ስድስት ሰዎችን (5 ወንድ ፣ 1 ሴት) በጥይት ተኩሰው ገድለዋል። ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ምስክሮች ትክክለኛ ቀኑን በማያስታውሱት ዕለት በከተማው ሀገር ግዛት ቀበሌ ልዩ ቦታው ወ/ሮ ስህን ኮሌጅ አካባቢ አንድ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂ በአካባቢው ተቀምጦ የሕዝቡን እንቅስቃሴ ሲያይ ቆይቶ ድንገት መተኮስ በመጀመሩ ውሃ በመቅዳት ላይ የነበረ አንድ የ14 ዓመት ወንድ ሕፃን ሕይወቱ ያለፈ ሲሆን በተገደለው ልጅ ሰውነት አልፎ የወጣው ጥይት የ9 ዓመት ሴት ሕፃን ቁርጭምጭሚት ላይ በማረፍ የአካል ጉዳት አድርሷል። በደሴ ከተማ የምርመራ ስራ እያከናወኑ የሚገኙ የፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ የትግራይ ኃይሎች ደሴ ከተማን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ጊዜያት 40 ሰዎችን መግደላቸውን እንዲሁም በ85 ሰዎች ላይ ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

103. የትግራይ ኃይሎች ከጥቅምት 21 እስከ ኅዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ የኮምቦልቻ ከተማን ተቆጣጥረው ቆይተዋል። ኮሚሽኑ ባደረገው ምርመራ የትግራይ ኃይሎች በከተማው በርካታ ሲቪል

ሰዎችን መግደላቸውን እና ማቁሰላቸውን ከዓይን እማኞች፣ ከሟቾች እና ተጎጂዎች ቤተሰቦች፣ ከሕክምና ተቋማት እንዲሁም ከመንግሥት አካላት አረጋግጧል። ጥቅምት 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በግምት ከቀኑ 8 ሰዓት ዲዳ በሚባል አካባቢ በመንገድ ላይ ሲሄድ የነበረ የ26 ዓመት ወጣት ቁም ሲሉት ሮጦ ሌላ ሰው ቤት በመግባቱ ወጣቱ የገባበት ቤት ተከትለው በመግባት ወጣቱን እና ቤት ውስጥ የነበረች አንዲት ሴትን ተኩሰው የገደሉ ሲሆን፣ ሌላ የ6 ዓመት ሕፃን ታፋዋ ላይ በጥይት ተመትታ የአካል ጉዳት ደርሶባታል። ጥቅምት 21 ቀን 2014 ዓ.ም. ቀበሌ 03 ልዩ ቦታው በርቸሌ በሚባል ቦታ ከሌሊቱ 7፡00 ሰዓት አካባቢ "የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች የተደበቀ ስንቅ እና መሳሪያ አለ አምጪ በተጨማሪም በሆቴል ቤትሽ ውስጥ የሚሰሩ ሴት ሰራተኞችን አቅርቢልን" በማለት እድሜዋ 35 ዓመት የሚሆናትን የቤቱን ባለቤት ሦስት ቦታ ላይ በጥይት በመምታት ከባድ የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን እንዲሁም በ12 ዓመት ሴት ልጃቸው (ግራ እግር ባት) ላይ በጥይት በመምታት ቀላል የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን፤ በተጨማሪም ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 9፡00 ሰዓት አካባቢ ተመልሰው ወደ ቤቱ በመምጣት 55 ዓመት የሆናቸውን አባት "መሳሪያ ደብቀሀል አምጣ" በሚል ጭንቅላታቸውን በመደብደብ ጉዳት አድርሰውባቸዋል።

104. የትግራይ ኃይሎች አጣዬ ከተማን ኅዳር 6 ቀን 2014 ዓ.ም. እንደተቆጣጠሩ በከተማው 01 ቀበሌ ነዋሪ የነበሩ አንድ ነጋዴ ቤት ውስጥ ከገቡ በኋላ የግለሰቡን እንቅስቃሴ በማገት ቤት ውስጥ አብረው ለ5 ቀናት ከቆዩ በኋላ ኅዳር 10 ቀን 2014 ዓ.ም. አጣዬ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ስሙ ኤፌሶን ቁጥር 2 ትምህርት ቤት ውስጥ "ፋኖ ትቀልባለህ፣ ወታደር ታበላለህ፣ ቤትህ ካምፕ ነው" በሚል አስረው በማቆየት ለኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች አሳልፈው ሰጥተዋቸዋል። የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች "ሁለተኛውን አብይ አግኝተናል" እያሉ በከተማ ውስጥ የመከላከያ ሠራዊትን ዩኒፎርም አስይዘው ካስዞሯቸው በኋላ ኅዳር 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ልዩ ስሙ ጃራ ምታ ከሚባል ቦታ ላይ ገድለዋቸዋል። አስከሬናቸው ከ16 ቀናት በኋላ ተነስቶ ኅዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም. አጣዬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን የተቀበረ መሆኑን የሟች ቤተሰቦች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

105. በአጣዬ ከተማ የ01 ቀበሌ ኅዳር 14 ቀን 2014 ዓ.ም. የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች የቀበሌው አመራር የነበሩ ግለሰብን አባት እና ወንድም ከቤታቸው በመያዝ "ልጃችሁን አምጡ" ካሏቸው በኋላ በባጃጅ በማሳፈር ልዩ ስሙ ቆሮ ከሚባል ቦታ ላይ በመውሰድ ገድለዋቸዋል። ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የቀበሌው አመራር እንደገለጹት በኅዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም. የሟች ወንድማቸውን አስከሬን በተገደለበት ቦታ ላይ ማግኘት ቢችሉም የአባታቸው አስክሬን ግን በጅብ የተበላ በመሆኑ ሳያገኙት መቅረታቸውን ገልጸዋል።

106. በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ደዋ ጨፋ ወረዳ ልዩ ቦታው እንቶሊ አካባቢ በታኅሣሥ ወር 2014 ዓ.ም የመጀመሪያ ሳምንት (ቀኑ በትክክል ያልታወቀ) የመከላከያ ሠራዊት አባላት ወታደሮች በሁለት አይሱዙ መኪኖች ተጭነው የመጡ ቁጥራቸው ወደ 30 የሚጠጉ የኦነግ ሸኔ አባሎች ናቸው ያሏቸውን ሰዎች በጅምላ በጥይት ደብድበው ገድለዋል። ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ምስክሮች ስለተገደሉት ሰዎች ሲያስረዱ "ወጣቶች እና ረጃጅም ጺም የነበራቸው ትላልቅ ሰዎች" በማለት የገለጿቸውን ሰዎች የመከላከያ ሠራዊት አባላቱ በተሽከርካሪ ጭነው ወደስፍራው ካመጧቸው

በኋላ ግድያ በተፈጸመበት ቦታ ለ 3 ቀናት ያክል ድብደባ እየፈጸሙባቸው ቆይተው በጥይት ደብድበው ገድለዋቸዋል፤ ግድያውን ከፈጸሙ በኋላ ወታደሮቹ በቦታው የሚኞች አስከሬን እንዳይነሳ ክልከላ ሲያደርጉ ቆይተው የሔዱ በመሆኑ አስክሬኖቹ እየሸተቱ ከ10 ቀናት በላይ ሳይቀበሩ እንደቆዩ ተናግረዋል፡፡

107. ታኅሣሥ 14 ቀን ኢሰመኮ በስፍራው ከመድረሱ ሶስት ቀናት አስቀድሞ የአካባቢው ነዋሪዎች ሚኞችን አፈር አልብሰዋቸዋል፡፡ አስከሬኖቹ አፈር ከመልበሳቸው በፊት የተመለከቱ ግለሰብ ለኮሚሽኑ እንዳስረዱት የተገደሉት ሰዎች ከደዋጨፋ ወደ ካራቆሬ ከተማ በሚወስደው የአስፋልት መስመር ዳር ላይ ሳይቀበሩ ለረጅም ቀናት የቆዩ በመሆኑ ለንግድ ስራ በመንገዱ በሚመላለሱበት ወቅት የተገደሉት ሰዎችን ማንነት ለማጣራት ሲሞክሩ የኦነግ ሸኔ አባላት እንደሆኑና ባቲ ከተማ አካባቢ ተይዘው መጥተው የተገደሉ መሆኑን ከአካባቢው ሰዎች መስማታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ የደዋጫፋ ከተማ ነዋሪ የሆነ ወጣት ለንግድ ስራ ከደዋ ጨፋ ወደ ሰንበቴ ከተማ በመሄድ ላይ እያለን ከዚህ አካባቢ የተረሸኑ የአነግ ሸኔ አባላት ሳይቀበሩ አሉ እንያቸው ተብሎ ተሳፋሪው ከመኪና በመውረድ ሲመለከት አብሮ የነበረ መሆኑን በመግለጽ መቼ እና በማን እንደተገደሉ እንዳላየ ይሁን እንጅ በመከላከያ ሠራዊት እርምጃ የተወሰደባቸው ሰዎች ናቸው ሲባል እንደሰማ እና አስከሬናቸው ወድቆ መመልከቱን ገልጿል፡፡ ኮሚሽኑ ግድያው የተፈጸመበት ስፍራ በተገኘበት ወቅት አፈር ያልለበሰ የአንድ ሰው አስከሬን፣ የሌላ ሚች የተቆረጠ ጭንቅላትን ጨምሮ የተቆራረጠ የሰውነት ክፍል እና የተለያዩ የሲቪል ሰዎች ልብሶችን በስፍራው ተመልክቷል፡፡

108. በሰንበቴ ከተማ ቆደማ የገጠር ቀበሌ ኅዳር ወር 2014 ዓ.ም ረቡዕ ዕለት ከምሽቱ 1፡00 ሠዓት ሲሆን 5 ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው የሸኔ አባል ናችሁ ተብለው ተጠርጥረው በመከላከያ ከተያዙ በኋላ አንዱ ሮጦ ማሽላ ማሳ ውስጥ በመግባት ሲያመልጥ የቀሩት 4 ሰዎች (ሦስት ወንድማማቾች እና አንድ የአጎታቸው ልጅ) ከመኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ በጥይት ተገድለው ተገኝተዋል፡፡ የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች እነዚህን ልጆች የት እንዳደረሷቸው የመከላከያ ሰራዊቱን ጠይቀው የነበረ ቢሆንም "ወደ ሸዋሮቢት ልከናቸዋል" የሚል መልስ ማግኘታቸውን፤ ነገር ግን ሚኞቹ መኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ ተገድለውና ተቀብረው እንደተገኙና አስከሬናቸው በቤተሰብ ወጥቶ በመቃብር ስፍራ የተቀበሩ መሆኑን ምስክሮች አስረድተዋል፡፡

109. ኅዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም. በአማራ ክልል አርቢት ከተማ አካባቢ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ጤፍ ሲያጭዱ የነበሩ ሰዎችን አስቁመው እንዴት "በዛሬው ቀን ጤፍ ታጭዳላችሁ የጁንታ ተባባሪ ናችሁ" በማለት ከደበደቧቸው በኋላ ከመካከላቸው አንድ ሰውን ገድለው ሌሎች ሦስት ሰዎችን እንዳቆሰሉ በወቅቱ ቦታው ላይ ነበሩ እማኞች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

110. ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን በላስታ ወረዳ 024 ቀበሌ ዳቦ ከተማ ውስጥ ከቀኑ 8፡00 አካባቢ የአማራ ልዩ ኃይል አባላት በቤት ለቤት ፍተሻ ላይ በነበሩበት ወቅት ጦርነቱን በመፍራት በሯን ዘግታ በቤት ውስጥ ሕፃን ቃቅፋ የተቀመጠች አንዲት ሴት ላይ "የትግራይ ኃይሎችን ቀልባችኋል" በሚል በሩ እንደተዘጋ ተኩሰው እናትየውን ግራ እግሯ ላይ፤ ህጻኗን ደግሞ

ግራ እጇ ላይ በጥይት የመቷት ሲሆን ህጻኗ ሕክምና በማጣቷ ደም ፈሷት መሞቷን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው እማኞች አስረድተዋል።

111. ሰንበቴ ከተማ በመንግሥት ኃይሎች ቁጥጥር ስር ከገባች በኋላ ቢያንስ አራት ሲቪል ሰዎች በተለያየ ቀን በፋኖ ታጣቂዎች ተገድለዋል። አንድ ግለሰብ በአጣዬ ከተማ የመከላከያ ሠራዊትን የሚጫን እቃ አግዞ ሲመለስ እንደተገደለ ከዚያም የእርሱ የቀብር ስነስርአት ላይ ለመቃብር ጭቃ መመረጊያ ውሃ ሊያመጣ የሔደ አንድ ሰው በሄደበት በፋኖ ታጣቂዎች እንደተገደለ በዚህም ምክንያት የቀብር ስርአቱ ከተቋረጠ በኋላ በነጋታው በመከላከያ ሠራዊት አጋዥነት ቀብሩ መፈጸሙን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ነዋሪዎች ገልጸዋል። ሌሎች ሁለት የከተማው ነዋሪዎችን ደግሞ የፋኖ ታጣቂዎች ከሰንበቴ ከተማ ወደ አጣዬ ወስደው እንደገደሏቸውና አስክሬናቸው እንዳይነሳ ተከልክሎ በጅብ ከተበላ በኋላ የሟች ቤተሰቦችን በሚያውቁ ሰዎች አማካይነት ተነግሯቸው አስክሬኖችን አንስተው መቅበራቸውን የሟች ቤተሰቦች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

112. በሌላ በኩል መንግሥት የሸዋ ሮቢት ከተማን ከተቆጣጠረ በኋላ ኅዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም. የትግራይ ተወላጆች የሆኑ እና የትግራይ ኃይሎችን ደግፋችኋል በሚል አራት ወንድ ሲቪል ሰዎች በፋኖና የአርሶ አደር ታጣቂዎች ተገድለው አስክሬናቸው መንገድ ላይ ለሦስት ቀን ያህል ከቆየ በኋላ ኅዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም. ተነስቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ የተገደሉ ተጨማሪ ሲቪል ሰዎች ስለመኖራቸው ለኮሚሽኑ መረጃዎች የደረሱት ቢሆንም ለማረጋገጥ አልተቻለም።

113. በጦርነቱ ተሳታፊ ወገኖች በተለይ ከፍርድ ውጪ ግድያ ከተፈጸመባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የአዕምሮ ሕሙማን ይጠቀሳሉ። በዚህ ላይ የኮሚሽኑ የምርመራ ግኝቶች በአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች በሚለው የዚህ ሪፖርት ክፍል ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል።

**ተፅዕኖ**

114. በጦርነቱ ተሳታፊ የነበሩ ተዋጊ ኃይሎች በቁጥጥራቸው ስር በነበሩ አካባቢዎች በሲቪል ሰዎች ላይ በተለያዩ ምክንያቶች በፈጸሟቸው ግድያዎች ሳቢያ ከደረሰው የሕይወት መጥፋት በተጨማሪም በርካታ ቤተሰቦች ያለ አስተዳዳሪ፣ ጧሪ እና ደጋፊ እንዲቀሩ፤ ለከፍተኛ የሥነልቦና ጉዳትም እንዲዳረጉ ምክንያት ሆኗል።

**መደምደሚያ**

115. ጦርነቱ በተካሄደባቸው የአማራ እና አፋር ክልል አካባቢዎች በጦርነቱ ተሳታፊ በሆኑ ታጣቂ ኃይሎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል፤ የአካል እና የሥነ ልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል። የትግራይ ኃይሎች በዋናነት ለግድያዎቹ ምክንያት ሲያደርጉ የነበረው "ለመንግሥት ኃይሎች ሰላይ ናችሁ፤ መሳሪያ አምጡ፣ ንብረት እንዳይወሰድ ተከላከላችኋል፤ በአካባቢያችሁ የመከላከያን፣ ልዩ ኃይልን ወይም ፋኖ ታጣቂዎችን አግዛችኋል ወይም የት እንዳሉ ታውቃላችሁ

ወይም የነዚሁ አባላት ሆኑ ሰዎች ቤተሰብ ናችሁ" በሚል እንዲሁም አካባቢዎቹን በሚቆጣጣሩበት ወቅት በትግራይ ኃይሎች ላይ ለደረሰባቸው ጥቃት ወይም የትግራይ ታጣቂዎች እና ትግራይ ላይ ለደረሰ ሞት እና ጉዳት የበቀል/አጸፋ እርምጃ መሆኑን ጭምር በግልጽ እየተናገሩ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ሲቪል ሰዎችን በጅምላ እና በነጠላ ገድለዋል:: የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች በዋናነት በተቆጣጠሯቸው ስፍራዎች በነበሩ የመንግሥት አስተዳደር ኃላፊዎች እና ቤተሰቦቻቸው ላይ እንዲሁም መንግሥትን ይደግፋሉ ያሏቸው ሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ግድያን ፈጽመዋል:: የመከላከያ ሠራዊት፣ የአማራ ልዩ ኃይል፣ ፋኖ እና ሚሊሺያዎችም የትግራይ ኃይሎች እና ኦነግ ሸኔ አባላት ናቸው ያሏቸው ወይም ድጋፍ አድርገዋል በሚል የጠረጠሯቸው ሰዎች ላይ ከፍርድ ውጪ ግድያዎችን ፈጽመዋል፤ የአካል ጉዳትም አድርሰዋል:: በጦርነቱ ተሳታፊ በሆኑ ኃይሎች የተፈጸሙ ድርጊቶች በጦርነት ወቅት ሲቪል ሰዎችን ተጠቂ ወይም ዒላማ እንዳይሆኑ የመጠበቅ ግዴታን አስመልክቶ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግም ሆነ በሰብአዊ መብቶች ሕግ እንዲሁም በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ የተቀመጡ ክልከላዎችን በግልጽ የሚጥስ እና የጦር ወንጀል እንዲሁም በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል ሊሆን የሚችል ነው::

## 3. የጭካኔ፤ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት

**መግቢያ**

116. ጦርነቱ በተካሄደባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በተለይ የትግራይ ኃይሎች የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ሲቪል ሰዎችን ኢ-ሰብአዊ በሆነ እና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ማሰቃየታቸውን፤ መደብደባቸውን እና ማንገላታታቸውን የኮሚሽኑ ምርመራ ያሳያል:: የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ሲቪል ሰዎችን መረጃ፣ ገንዘብ እና የደበቃችሁትን የግል የጦር መሳሪያ ስጡን በሚሉ እና ሌሎች ምክንያቶች ደብድበዋል፤ አሰቃይተዋል፤ በተወሰኑ አጋጣሚዎችም ከደበደቡ እና ካሰቃዩ በኃላ ተጎጂዎቹ ላይ ግድያን ፈጽመዋል::

**የሕግ ማዕቀፍ**

117. ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊነት/ጦርነት ሕጎች የጭካኔ እና ማሰቃየት ተግባራትን በየትኛውም ሁኔታ በጥብቅ ይከለክላሉ::[42] በመሆኑም በሰላም ጊዜም ሆነ በጦርነት ወቅት ተዋጊ ኃይሎች ጥበቃ በተደረገላቸው ሲቪል ሰዎች ላይም ሆነ በሌሎች በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ የተያዙ ወይም በሌላ ሁኔታ በቁጥጥራቸው ስር የገቡ ተዋጊዎችም ላይ ምንም ዓይነት የጭካኔ ተግባር መፈጸም አይችሉም:: በተ.መ.ድ የጭካኔ፣ ኢሰብአዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት ክልከላ ስምምነት

[42] See IHL; the four Geneva Conventions of 1949 (GC I, Article 12; GC II, Article 12; GC III, Articles 13, 17 and 87; GC IV, Articles 27 and 32; GC I-IV common article 3 and arts 50, 51, 130 and 147 respectively; Additional Protocol I of 1977 (Article 75(2)(a)(ii)); and Additional Protocol II of 1977 (Article 4(2)(a)). Rome Statute of the International Criminal Court (ICC) Article 8(2)(a)(ii) and 8(2)(c)(i) and (ii)) and (Article 7(1)(f) and (k)). IHRL; UDHR Article 5, ICCPR Article 7, CAT Article 2(2), and CRC Article 37(a), ACHPR Article 5.

በተመለከተው ትርጓሜ መሰረት የጭካኔ እና የማሰቃየት ተግባር (torture) በሰዎች ላይ ሆን ተብሎ መረጃን ወይም የእምነት ቃልን ለማግኘት፣ በቅጣት መልክ፣ ለማስፈራራት ወይም ለማስገደድ ወይም በሌላ መድሎ ላይ በተመሰረተ ማንኛውም ምክንያት የሚፈጸም በአካል ወይም በሥነ ልቦና ላይ ከፍ ያለ የስቃይ ስሜትን የሚያደርስ ድርጊት እንደሆነ ይገልጻል::[43]

118. በትግራይ ኃይሎች እና በመንግሥት መካከል በተካሄደው ዓለም አቀፋዊ ያልሆነ ጦርነትን በሚመለከቱት የሕግ ማዕቀፎችም የትኛውም ታጣቂ ኃይሎች ሰፊ እና ስልታዊ በሆነ መልኩ ድርጊቱን የፈጸሙ እንደሆነ ድርጊቱ የጦር ወንጀል (War Crimes) እና/ወይም በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (Crimes against Humanity) ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል::

## የምርመራው ግኝቶች

119. ሐምሌ 3 ቀን 2013 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎች በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን የከለዋን ከተማ ነዋሪ የሆነችን የ30 ዓመት ሴት "የመንግሥት ሰላይ ነሽ" በሚል ምክንያት በመንገድ ስትጓዝ ከያዟት በኃላ ለሁለት ተከታታይ ቀናት ከባድ ድብደባ ፈጽመዋባታል:: ተጎጂዋ የደረሰባትን ለኮሚሽኑ በሚከተለው መንገድ አስረድታለች፡-

> *"ከፊተሹኝ በኋላ አሳድረውኝ በጠዋት እንደሚለቁኝ ነግረውኝ ተራራው ላይ ወሰዱኝ:: ሲነጋ እንዲለቁኝ ስጠይቃቸው አንደኛው በደረቅ እንጨት ዱላው ተሰባብሮ እስኪያልቅ ድረስ ደጋግሞ በላዬ ላይ አወረደብኝ:: የአብይ መረጃ ነሽ፣ እያሉ እየተቀባበሉ በመሳሪያ ሰደፍ፣ በእርግጫ፣ በጥፊ እና በእንጨት እየደበደቡ እና እንደሚገሉኝ እየዛቱ ሁለት ቀን አቆዩኝ:: ከዛም በመኪና ጭነው ወደ ከለዋን መልሰውኝ ለ5 ቀናት በቆርቆሮ ቤት ውስጥ አስረው አቆዩኝ" ብላለች::*

በተጎጂዋ ትከሻ ላይ የድብደባ ጠባሳዎችን ኮሚሽኑ ተመልክቷል::

120. በደቡብ ወሎ ዞን የተሁለደሬ ወረዳ በቀበሌ 017፣ 14 ነዋሪዎች ከነሐሴ 27 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. በትግራይ ኃይሎች በደረሰባቸው ድብደባ እና ማሰቃየት ለጉዳት እንደተዳረጉ ተጎጂዎች፣ የቀበሌው አስተዳዳሪዎች እንዲሁም በአካባቢው የነበሩ ምስክሮች ለኢሰመኮ አስረድተዋል:: ድብደባው እና ማሰቃየቱ ሲፈጸም የነበረው በዋነኝነት በክላሽ መሳሪያ ሰደፍ፣ በብረት እና ከብረት በተሰሩ መግረፊያዎችና በእንጨት ዱላዎች ሲሆን ድብደባው በአብዛኛው የሚደረገው ሰዎቹን በማሰር ነው:: በተጨማሪም በዚሁ ቀበሌ በነሐሴ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. የአካባቢው ነዋሪዎችን ሚሊሺያ ወይም ፖሊስ ናችሁ በማለት የትግራይ ኃይሎች በቁጥጥር ስር እንዳዋሏቸው እና ድብደባ ካደረሱባቸው በኋላ ከመካከላቸው 1 ነዋሪን በጥይት ተኩሰው እንደገደሉ የዓይን እማኞች እና ከሟች ጋር በቁጥጥር ስር ውሎ የነበሩና ከጥቃቱ ያመለጡ ነዋሪዎች አስረድተዋል::

[43] CAT Article 1.

121. ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. በአማራ ክልል ወረባቡ ወረዳ ቀበሌ 020 የትግራይ ኃይሎች የ20 ዓመት ወጣት እንስሳትን በመጠበቅ ላይ እያለ “የሶዶማ አካባቢ ተዋጊዎችን ትመስላለህ” በሚል ድብደባ እና ማሰቃየት ካደረሱበት በኂላ በጥይት ተኩሰው ገድለውታል። የትግራይ ኃይሎች በወረዳው 6 ቀበሌዎች ውስጥ በ10 ሰዎች (8 ወንድ እና 2 ሴቶች) ላይ ድብደባ እና የአካል ጉዳት አድርሰዋል። የአካል ጉዳት ከደረሰባቸው መሀከል በቀበሌ 018 ነዋሪ የሆነ የ30 ዓመት ወጣት ሐምሌ 25 ቀን 2013 ዓ.ም የትግራይ ኃይሎች ከቤቱ በመውሰድ እግሩን እና እጁን ገልብጠው በማሰር እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ድብደባ የፈጸሙበት ሲሆን በድብደባውም ጉዳት እንደደረሰበት ለማረጋገጥ ተችሏል። በተመሳሳይ ቀበሌ ነዋሪ የሆነ የ40 ዓመት ጎልማሳ በትግራይ ኃይሎች በሰደፍ እና በዱላ ድብደባ እደተፈጸመበት እንዲሁም ሊገሉት በጥይት ተኩሰው እንደሳቱት አስረድቷል።

122. የትግራይ ኃይሎች በጋሸና ከተማ በቆዩበት ወቅት የአማራ ልዩ ኃይልና መከላከያን አብልታችኂል፣ አጠጥታችኂል፣ መሳሪያ አላችሁ አስረክቡ፣ ብር አላችሁ አምጡ፣ የሚሊሺያ ቤት አሳዩን በሚል ምክንያት ሲቪል ሰዎችን አሰቃይተዋል። ለአብነት በከተማው ቀበሌ 013 ነዋሪ ከሆኑት አንድ ግለሰብ ቤት ኅዳር 3 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 4:00 ሰዓት “ብር እንዳላችሁ ሰምተናል ስጡን” ሲሉ ነዋሪዎቹ ብር እንደሌላቸውና መስጠት እንደማይችሉ በመመለሳቸው ከባድ ድብደባ ከፈጸሙባቸው በኂላ የቤቱን አባወራ ለብቻ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ወንዝ በመውሰድ ልብሱን አስወልቀው በውኃ እየደፈቁ ከደበደቡት እና በሚስማር እግሩን ሁለት ቦታ ከወጉት በኂላ ብልቱን በካራ ተልትለውታል። ተጎጂው በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ለኮሚሽኑ ሲገልጽ፦

> *“ልብሴን አስወልቀው ዘቅዝቀው በውሃ ሲደፍቁኝ ራሴን ሳትሁ፤ ሲደበድቡኝ ህመሙ አይሰማኝም ነበር። በሚስማር ሁለቱን እግሬን ሲበሱኝም ምንም አልመለስሁላቸውም። በኂላ ግን ብልቴን በካራ ሲተለትሉኝ ህመሙ አቃተኝና ብሩ አለ፤ ውሰዱት ብዬ ከቤት ያስቀመጥኩትን 20,000 ብር ሰጠኂቸው” ብለዋል።*

ታጣቂዎቹ ገንዘቡን ከወሰዱ በኂላ ባለቤታቸውን ቤት ውስጥ ብር እንደነበረ ባልሽ ሲያምን አንቺ ግን የለም ብለሽ ዋሸሽን በማለት ከፍተኛ ድብደባ ፈጽመውባቸዋል።

123. በተመሳሳይ በጋሸና ከተማ 02 ቀበሌ አንድ የ65 ዓመት አረጋዊን የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ከፍተኛ ድብደባ፣ ማሰቃየትና እንግልት አድርሰውባቸዋል። ተበዳዩ የሚኖሩበት ቤት እና ለአልጋ ኪራይ በሚል በግቢያቸው ውስጥ በሰሯቸው ክፍሎች ውስጥ የትግራይ ኃይሎች ከተማዋን በተቆጣጠሩ ቁጥር እርሳቸውን ወደ አንድ ትንሽ ክፍል እንዲገቡ በማድረግ የቀረውን ቤት ሁሉ ይጠቀሙበት እንደነበር፤ በመጀመሪያ ቤታቸውን የቁስለኛ ማከሚያ ቤት እንዳደረጉት ይገልጻሉ። ሆኖም ታኅሣሥ 3 ቀን 2014 ዓ.ም. የመጡት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ለዝርፊያ የመጡ መሆኑን እና ገንዘብ አምጣ በሚል የደረሰባቸውን እንደሚከተለው ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፦

> *“ቤት መጡና ብር አምጣ አሉኝ። የለኝም ስላቸው ደበደቡኝ በሽተኛዋን ባለቤቴን ሳይቀር ክፉኛ ደበደቧት። ከዚያ ቤት ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ መፈተሽ ጀመሩና በሙዳይ የቆጠብነው 8500 ብር ነበር እሱን ሲያገኙት ወሰዱት። በኂላ ለኃላፊዎቻቸው ሂጄ*

*እንዴት እንደዚህ ይደረጋል ብዬ ሳመለክት እናንተማ ከዚህ በላይም ይገባችኋል፤ ጋሸና ላይ 80 ሰው ተደፈረ 400 ሰው ተገደለ ብላችሁ ለሚዲያ ቃል ሰጥታችኋል ብሎ አስፈራራኝ" ብለዋል።*

**ተፅዕኖ**

124. የትግራይ ኃይሎች በቁጥጥራቸው ስር በነበሩ አካባቢዎች በነዋሪዎች ላይ በተለያዩ ምክንያቶች የፈጸሟቸው የጭካኔ እና የማሰቃየት ተግባራት በተጎጂዎች ላይ ከፍ ያለ የአካል እና የሥነ ልቦና ጉዳት ያደረሱ ሲሆን ይህ በተለይ ተጎጂዎች በሕክምና እንዲረዱ የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ ያልነበረ ከመሆኑ አንጻር የተጎጂዎችን ስቃይ እንዲበረታ ያደረገ ነው።

***መደምደሚያ***

125. የትግራይ ኃይሎች በቁጥጥራቸው ስር በገቡ የአፋር እና አማራ ክልል አካባቢዎች ሲቪል ሰዎችን ላይ የጭካኔ እና የማሰቃየት ተግባር ፈጽመዋል። ለመንግሥት ኃይሎች መረጃ ታቀብላላችሁ፤ መሳሪያ አምጡ፣ ንብረት እንዳይወሰድ ተከላክላችኋል፤ በአካባቢያችሁ የመከላከያ፣ ልዩ ኃይል ወይም ፋኖ ታጣቂዎች የት እንዳሉ ታውቃላችሁ ወይም የነዚሁ አባላት የሆኑ ሰዎች ቤተሰብ ናችሁ በሚል እንዲሁም አካባቢዎቹን በሚቆጣጠሩበት ወቅት በትግራይ ኃይሎች ላይ ለደረሰባቸው ጥቃት ወይም የትግራይ ታጣቂዎች እና ትግራይ ላይ ለደረሰ ሞት እና ጉዳት የበቀል/አጸፋ እርምጃ መሆኑን ጭምር በግልጽ እየተናገሩ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ሲቪል ሰዎችን ደብድበዋል፤ አሰቃይተዋል፤ ለአካል እና የሥነ ልቦና ጉዳትም ዳርገዋል።

126. ይህ በጦርነት ወቅት ሲቪል ሰዎችን ተጠቂ ወይም ዒላማ እንዳይሆኑ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግም ሆነ በሰብአዊ መብቶች ሕግ እንዲሁም በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ የተቀመጡ ክልከላዎችን በግልጽ የሚጥስ እና የጦር ወንጀል እንዲሁም በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል ሊሆን የሚችል ነው።

## 4. የዘፈቀደ እስር፣ ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወር

***መግቢያ***

127. በዚህ ክፍል ኢሰመኮ ምርመራ ባደረገባቸው በአማራ እና አፋር ክልሎች አካባቢዎች የተፈጸሙ የዘፈቀደ እስር፣ ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወር ክስተቶችን ይዳሰሳል። ኮሚሽኑ በተለያዩ አካባቢዎች ሲቪል ሰዎች ከጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች ጋር ባላቸው ወይም አላቸው ተብሎ በተገመተ ግንኙነት ምክንያት መያዛቸውን፣ መታገታቸውን እና አንዳንዶቹ እስካሁንም ድረስ አለመገኘታቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች ደርሰውታል። አንዳንዶቹ የታገቱ ሰዎች በያዛቸው ወይም ባገታቸው ኃይል ተገድለዋል፤

አካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ስለሆነም ይህ ክፍል በዚህ ሪፖርት ውስጥ በጦርነቱ ሂደት በሲቪል ሰዎች ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ከሚዳስሰው ክፍል ጋር አብሮ የሚታይ ነው።

**የሕግ ማዕቀፍ**

128. የዘፈቀደ እስር በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ድንጋጌዎች የተከለከለ ተግባር ነው። ሰዎች ነፃነታቸውን የሚገፈፉበት ሂደት የሕግ የበላይነትን ባከበረ መልኩ መከናወን አለበት። የዘፈቀደ እስር የሕግ መሰረት የሌለው እስር ሲሆን ተገቢነት የሌለው፣ ፍትሀዊ ያልሆነ እና ሕጋዊ ሥነ ሥርአቶችን ያልተከተለ እስርን ይጨምራል።[44] ብሔርን፣ ፆታን፣ ዕድሜን እና ሌሎች መድሏዊ ምክንያቶችን መሰረት ያደረገ እስር ደግሞ በመሰረታዊነት የዘፈቀደ እስር እንደሆነ ይቆጠራል።

129. በጦርነት ወቅት ከሰላም ጊዜ በተለየ ሁኔታ በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች ሊያዙ እንደሚችሉ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ድንጋጌዎች ቢያስቀምጡም፣ በዚህ ወቅትም ቢሆን የሕጋዊነት፣ የጥብቅ አስፈላጊነትና ተመጣጣኝነት እና ከመድልዎ ነፃ መሆን የሚሉትን የሰብአዊ መብት መርሆዎችን ባከበረ መልኩ መሆን ይኖርበታል።[45]

130. ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወር በሕይወት ከመኖር፣ ከጭካኔ እና ኢሰብአዊ አያያዝ የመጠበቅ፣ ፍትሕ የማግኘት እና ሌሎች መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥበቃዎችን የሚጥሱ ተግባራት ናቸው። ዓለም አቀፋዊ ባልሆነ ጦርነት ጊዜ የጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወርን ለመከላከል የተያዙ ሰዎችን የመመዝገብ እና ደኅንነታቸውን የማስጠበቅ ግዴታ አለባቸው።መንግሥታት በማንኛውም ጊዜ ሰዎችን በታጠቁ ኃይሎች እና ቡድኖች ከአስገድዶ መሰወር እና ከመታገት የመጠበቅ ኃላፊነትም አለባቸው።[46]

**የምርመራ ግኝቶች**

131. የትግራይ ኃይሎች ቁጥጥራቸው ስር በነበሩ እና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው አካባቢዎች እገታ እና አስገድዶ መሰወር ፈጽመዋል። በተለይም የመንግሥት አመራር፣ ሚሊሺያ ወይም ፋኖ አባል ነበራችሁ፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትንና የአማራ ልዩ ኃይልን አግዛችኋል ምግብና ውሃ ሰጥታችኋል፤ እንዲሁም የአካባቢውን አመራርና ታጣቂ ስምና ቤት አሳዩን በሚል ምክንያቶች፤ ግለሰቦችን የማገት እና የአስገድዶ መሰወር ተግባራት ተፈጽመዋል። በአማራ ክልል ወልድያ ከተማ 04 ቀበሌ የትግራይ ኃይሎች ነሐሴ 24 ቀን 2013 ዓ.ም. አንድ የ25 ዓመት ወጣትን የፋኖ ደጋፊነህ በሚል በሚኒባስ መኪና ከለቅሶ ቤት የተወሰደ ሲሆን ምርመራው እስከሚከናወንበት ቀን ድረስ ያለበት አልታወቀም።

---

[44] Human Rights Committee, General Comment No. 35, (article 9, ICCPR)

[45] Human Rights Committee, General Comment No. 29, (Article4, ICCPR).

[46] 24th International Conference of the Red Cross, Res. II,

132. በአንዳንድ አካባቢዎች መረጃ እንዲሰጡ በሚል በትግራይ ኃይሎች የተያዙ ሰዎች በግዳጅ ጦር መሳሪያና ጥይት እንዲሸከሙ እና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲሰጡ ተደርገዋል። በአማራ ክልል ዳቦ ከተማ ኅዳር 4 ቀን 2013 ዓ.ም. የአካባቢውን አመራርና የሚሊሺያ ስምና ቤት ጠቁም በማለት የተያዘ አንድ ሰው ቀኑን ሙሉ በገመድ ከዛፍ ጋር እንደታሰረ፣ ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ተፈቶ ባዶ ቤት ያለምግብ ማደሩን እና በነጋታው ሌላ ከተያዘ የከተማው ነዋሪ ጋር ተወስደው ወታደሮቹ በሚሄዱበት ሁሉ የጦር መሳሪያና ጥይት እንዳሸከሟቸው እና ለብዙ ቀናት ውሃ ካስቀዷቸው በኋላ በተያዙ በሶስተኛ ሳምንታቸው እንደተለቀቁ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

133. በኃይል ታግተው ከተወሰዱ በኋላ የተለቀቁ የተወሰኑ ሲቪል ሰዎች ሲኖሩ በሌላ በኩል ከታገቱ በኋላ ኢሰብአዊ ድርጊት የተፈጸመባቸው እና የተገደሉም ይገኙበታል። ለአብነትም የትግራይ ኃይሎች አጣዬ ከተማን ኅዳር 6 ቀን 2014 ዓ.ም ሲቆጣጠሩ 01 ቀበሌ ነዋሪ የነበሩ አንድ ነጋዴ ቤት በመግባት እና ግለሰቡን በማገት ለ5 ቀናት ከቆዩ በኋላ ኅዳር 10 ቀን 2014 ዓ.ም. አጣዬ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ስሙ ኤፌሶን ቁጥር 2 ትምህርት ቤት ውስጥ ‹‹ፋኖ ትቀልባለህ፣ ወታደር ታበላለህ፣ ቤትህ የወታደር ካምፕ ነው›› በሚል ምክንያት አስረው ካቆዩአቸው በኋላ ለኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች አሳልፈው ሰጥተዋቸው ኅዳር 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ጃራ ዎታ በሚባል ቦታ ላይ ተገድለዋል።

134. በሌላ በኩል ነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. በአፋር ክልል በርሀሌ ወረዳ አላ እና አስጉቢ ቀበሌዎች ከሚገኙት ሦስት መንደሮች (ኩሱርቱ፣ አሰዳ እና አድአርዋ) አካባቢ ከትግራይ ክልል ጋር አዋሳኝ በሆነ ቦታ በሚገኝ ኩሬ ውሃ ለመቅዳት 27 አህያ ጭነው የሄዱ 10 ልጃገረዶች በድንበሩ አቅራቢያ የነበሩ የትግራይ ታጣቂዎች ታግተው ከሰዓታት ቆይታ በኋላ ተለቀዋል።

135. የትግራይ ኃይሎች ተቆጣጥረዋቸው በነበሩ አካባቢዎች የተያዙበት ምክንያት እና አሁን የሚገኙበት ሁኔታ የማይታወቅ ሲቪል ሰዎችም ይገኛሉ። ለምሳሌ ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. በአፋር ክልል ቡርቃ ቀበሌ ሙዴና የተባለ ቦታ ለገበያ የመጡ 6 ግለሰቦች እና ሌላ 2 የቡርቃ ቀበሌ ነዋሪ ነጋዴዎች ከነፍየሎቻቸው መኪና ላይ ተጭነው የተወሰዱ ሲሆን ይህ ምርመራ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን እንደማያውቁ ገልጸዋል። ከአፋር ክልል ካሳጊታ ከተማ በትግራይ ኃይሎች ተይዘው ከተወሰዱ ሰዎች ውስጥ የአንዱ እህት የሆነች ሴት እንደገለጸችው፦

> *“ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ካሳጊታ ከተማ ላይ በነበረው ጦርነት ምክንያት ሸሽተን አራ ቀበሌ ከገባን በኋላ ወንድሜ ሲፊ ከሚባል ቦታ አፋሮች ወደ ካሳጊታ ከተማ ገብተዋል የሚል ወሬ ሰምቶ ሄዶ በመጥፋቱ እሱን ፍለጋ ወጣን። የትግራይ ኃይሎች በሰፈሩበት ወራኢሉ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠገብ የወንድሜን ጫማ አግኝቼ ወንድሜ የት አለ? ብዬ ስጠይቃቸው የምናቀው ነገር የለም፣ ወንድምሽን እኛ አልገደልንም፣ ከዚህ ሂዱ ካልሆነ እንገድላችኋለን ብለው ሲያስፈራሩኝ የወንድሜን ጫማ ይዤ ተመለስኩ ። አሁን ወንድሜ እንደሞተ ነው የሚሰማኝ” በማለት አስረድታለች።*

136. በሌላ በኩል ከትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ነፃ በወጡ አካባቢዎች ‹‹የፀጥታ ስጋት ናቸው፣ ከትግራይ ኃይሎች ወይም ከኦነግ ሸኔ ጋር ተባብረዋል፣ ወይም መረጃ አቀብለዋል›› በሚል ምክንያት በፌደራል የፀጥታ አካላትና በአማራ እና አፋር የፀጥታ ኃይሎች ቁጥራቸው የበዛ ሰዎች ታስረዋል፡፡ በተለይም የኢፌዴሪ መንግሥት ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ በመላው አገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ማወጁን ተከትሎ ለፀጥታ አካላት ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራሉ ተብለው ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠሩ ሰዎችን ይዞ የማቆየት ስልጣን በመሰጠቱ ጦርነቱ ከነበረባቸው ስፍራዎች ውጪ በሚገኙ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በተለይ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ሲቪል ሰዎች ከምክንያታዊነት በራቀ እና በመድሎ ላይ በተመረኮዘ መልኩ ተይዘው ታስረዋል፡፡

137. ከእነዚህ እስሮች ውስጥ ጥቂቶቹ በሚመለከታቸው የፀጥታ አካላት መረጃ መሰረት የተፈጸሙ ሲሆን አብዛኛዎቹ ግን ከህብረተሰቡ ተገኘ በተባለ ጥቆማ መሰረት በአብዛኛው የትግራይ ብሔር ተወላጅ የሆኑ ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ እድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ ወንዶች እና ሴቶች አረጋውያን፣ ሕጻናት ልጆች በማጥባት ላይ የነበሩ ሴቶች፣ የአዕምሮ ህመም ያለባቸው እና ተከታታይ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ሰዎችም ጭምር ተይዘው ታስረዋል፡፡ ፖሊስ ጣቢያዎች እና የተያዙ ሰዎችን የማቆያ ስፍራዎች የተጣበቡ፣ በቂ መጸዳጃ፣ አየር እና ብርሃን በማያገኙ የነበሩ ሲሆን በቂ የምግብ እና የጤና አገልግሎት አልነበራቸውም፡፡ በአብዛኛው አካባቢዎች የታሰሩ ሰዎችን ጉዳይ የማጣራት ሂደት እጅግ የዘገየ ወይም ያልተጀመረ ነበር፡፡

138. ከታሰሩት ሰዎች ውስጥ ጋዜጠኞች የሚገኙበት ሲሆን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከመታወጁ ጥቂት ቀናት በፊት ጀምሮ ቢያንስ 16 ጋዜጠኞች በኦሮሚያ፣ በፌደራል እና በአዲስ አበባ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የታሰሩበት ስፍራ ለቀናት ያልታወቀ፣ ለረጅም ጊዜ በቤተሰብ መጎብኘት ያልቻሉ ሰዎች ይገኙበታል፡፡ ይህ ሪፖርት በሚፃፍበት ወቅት ታስረው የነበሩት አብዛኛዎቹ ጋዜጠኞች የተለቀቁ ቢሆንም የተወሰኑት በእስር ላይ ነበሩ፡፡

139. በአጠቃላይ ከአስቸኳይ ጊዜ ከአዋጁ ጋር በተያያዘ ሰዎችን የመያዝ ሁኔታ በተወሰነ መጠን በሂደት እየተሻሻለ መጥቶ የነበረ ቢሆንም፤ ጦርነቱ በነበረባቸው አካባቢዎችም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች በፌደራል እና በክልል መንግሥታት ሰዎችን በቁጥጥር ስር በማዋል ረገድ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መተግበር ባለበት መንገድ በተለይም "የጥብቅ አስፈላጊነት፣ ተመጣጣኝነት እና ከመድልዎ ነፃ መሆን" የሚሉትን የሰብአዊ መብት መርሆዎችን ባከበረ መልኩ አልተተገበረም፡፡

**ተፅዕኖ**

140. ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የዘፈቀደ እስር፣ ጠለፋ እና አስገድዶ መሰወር የደረሰባቸው ተጎጂዎች እና የተጎጂ ቤተሰቦች ለከፍተኛ አካላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ቀውስ ተዳርገዋል፤ እንዲሁም በህብረተሰቡ መካከል ያለውን ማኅበራዊ መስተጋብር ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች በጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች አሁንም የተያዙ ሰዎች የሚገኙ ሲሆን፣ የተሰወሩ ሰዎች ቤተሰቦቻቸው የደረሱበትን አሁንም ድረስ ማወቅ ባለመቻላቸው በጭንቀት ውስጥ ይገኛሉ፡፡

**ማጠቃለያ**

141. ጦርነቱ በተካሔደባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች ዓለም አቀፍ የጦር ወንጀልን እና በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ሊያቋቁም በሚችል መልኩ የእገታ እና አስገድዶ መሰወር ተግባራትን ፈጽመዋል። በሌላ በኩል የፌዴራል፣ የአማራ እና የአፋር ክልል የፀጥታ ኃይሎች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውድ ውስጥም ቢሆን መጠነ ሰፊ የዘፈቀደ እስር ፈፅመዋል።

## 5. ወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃቶች

**መግቢያ**

142. ኮሚሽኑ በአፋር እና አማራ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ በተለያዩ አካባቢዎች በሴቶች ላይ ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች የተፈጸመባቸውን ሴቶች፣ የዓይን እማኞች የቤተሰብ አባላት፣ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች እና አገልግሎት ሰጪ የሆኑ መንግስታዊ ተቋማትን ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን አሰባስቧል። ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች በተለያዩ እድሜ ክልል የሚገኙ በመሆናቸው የተሟላ ምስል ለማግኘት ይህንን ክፍል በዚህ ሪፖርት ሕፃናትን እንዲሁም አረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞችን ከሚመለከቱት ክፍሎች ጋር በጋራ መመልከት ያስፈልጋል።

143. የትግራይ ኃይሎች በሴቶች ላይ በተናጠል እና በቡድን የአስገድዶ መድፈር ጥቃት፣ የአስገድዶ መድፈር ሙከራዎች እና አካላዊ ጥቃቶች አድርሰዋል። ኮሚሽኑ ምርምራ ባደረገባቸው አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በሴቶች ላይ ጥቃት የተፈጸመው በትግራይ ኃይሎች ሲሆን ከአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ተሁለደሬ ወረዳ አንዲት ተጎጂ ላይ በመከላከያ ሠራዊት አባል ወሲባዊ ጥቃት መፈጸሙን ነዋሪዎች እና የአካባቢው አስተዳደር ለኮሚሽኑ የገለጹ ቢሆንም ተጎጂዋ ለደህንነቷ በመስጋት መረጃ ለመስጠት አልፈቀደችም።

144. በዚህ ሪፖርት ላይ የተጠቀሰው የተጎጂዎች ቁጥር፣ የተገለጹት የጥቃት አይነቶች እንዲሁም ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች የሚገኙባቸውን አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ የሚያንጸባርቅ ሳይሆን የፆታዊ ጥቃቱን ጠባይ እና ሁኔታ በተወሰነ መጠን ብቻ የሚያሳይ ነው ።

**የሕግ ማዕቀፍ**

145. ኢትዮጵያ መሰረታዊ የእኩልነት እና የመድሎ ክልከላ መርህን የሚደነግጉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ያጸደቀች ሲሆን ከእነዚህ መካከልም የሴቶችን የእኩልነት መብቶች ለማስከበር

የወጡ የቃል ኪዳን ሰነዶችን በማፅደቅ የሀገሪቱ የሕግ አካል አድርጋለች[47]:: ከእነዚህም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የወጣውን ስምምነት እና የአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል /ማፑቶ ፕሮቶኮል/ በዋቢነት ይጠቀሳሉ:: በተጨማሪም የፆታ እኩልነት በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ተረጋግጧል::

146. በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የወጣው ስምምነት መሰረት የተቋቋመው ኮሚቴ ፆታዊ ጥቃቶችን በተመለከተ ባወጣው የተጠቃለሉ ምክረ-ሐሳቦች ሰነድ እንዲሁም በማፑቶ ፕሮቶኮል ላይ እንደተመለከተው፤ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ማለት ማናቸውም አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ጉዳቶች ወይም ስቃይን የሚያስከትሉ ማናቸውም ፆታ ተኮር ድርጊቶች ሲሆኑ በአደባባይም ሆነ በግል ሕይወት የሚከሰቱ ድርጊቶችን የመፈጸም ዛቻ ማስገደድ ወይም ከሕግ ውጪ ነጻነትን የማሳጣት ሁኔታን የሚያጠቃልል ተግባር መሆኑን ያስቀምጣሉ::[48] ሀገራትም በፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ እንዲወስዱ ይደነግጋል::[49] ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነትን እና የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ፈራሚ ሀገራት በሴት ሕፃናት ላይ የሚደርሱ ወሲባዊ ብዝበዛዎች እና ጥቃቶችን ለመከላከል እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባቸው ይደነግጋሉ::[50]

147. የቤጂንግ መግለጫና የድርጊት መርሐ-ግብር ፆታዊ ጥቃት በጦርነት ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን፣ ማለትም ታቅደው የሚፈጸሙ የአስገድዶ መድፈር ተግባራትን፣ የወሲብ ባርነትንና የግዳጅ እርግዝናን፣ አስገድዶ መሃን ማድረግ፣ አስገድዶ ጽንስ ማቋረጥን እና አስገድዶ የወሊድ መከላከያ እንዲወስዱ ማድረግን የሚያካትት መሆኑን ይገልፃል::

148. በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ፆታዊ ጥቃቶች፣ አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ናቸው:: አስገድዶ መደፈር ሴትን በማስገደድ ወይም ያለ ፈቃዷ በማናቸውም መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ማለት ሲሆን በአጠቃላይ ፆታዊ ጥቃት ማሰቃየትን፣ የጭካኔ፣ ኢሰብአዊ ወይም አዋራጅ አያያዝ ክልከላዎችን የሚያስቀምጠውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግ ይጥሳል[51]:: በተጨማሪም ፆታዊ ጥቃት አካላዊ እና አዕምሯዊ ጤና የማግኘት መብትን ጨምሮ ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል::

[47] የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ፣አንቀፅ 9(4)፣አዋጅ ቁጥር 1/1987 ነጋሪት ጋዜጣ አንደኛ ዓመት ቁጥር 1 አዲስ አበባ ነሀሴ 15፣1987
[48] የአፍሪካ የሰብአዊና የህዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል /ማፑቶ ፕሮቶኮል/፣አንቀፅ 1(9)
[49] CEDAW Committee: General Recommendation No. 19 on Violence Against Women and General, Recommendation No. 35 on gender-based violence against women, updating general recommendation No. 19
[50] ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነትን አንቀጽ 34 እና የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀፅ 16
[51] ICCPR, Article 7 cum CAT Committee General Comment No. 2.

149. አስገድዶ መድፈር፣ ፆታዊ ባርነት፣ የግዳጅ ወሲብ አዳሪነት፣ የግዳጅ እርግዝና፣ የግዳጅ ማምከን እና ሌሎች ተመሳሳይ ወሲባዊ ጥቃቶች የጦር ወንጀሎች [52]ሲሆኑ በሰላማዊ ሰዎች ላይ በስፋት ወይም ስልታዊ በሆነ መልኩ ከተፈጸመ ደግሞ በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል ይሆናል::[53]

**የምርመራው ግኝቶች**

150. ኮሚሽኑ በአፋርና አማራ ክልሎች ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው አካባቢዎች የደረሱትን ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች አይነት፣ በማን እንደተፈጸሙ እና ፆታዊ ጥቃቱ በተጎጂዎች ላይ ያስከተለውን ጉዳት የተመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቧል:: ኮሚሽኑ ካነጋገራቸው ተጎጂዎች ውስጥ በርካቶቹ የተናጠል እና የቡድን አስገድዶ መድፈር ጥቃት የደረሰባቸው ናቸው::

151. ተጎጂዎች የደረሰባቸው ወሲባዊ ጥቃት በማህበረሰቡ ከታወቀ ሊደርስባቸው የሚችለውን መድሎ እና መገለል በመፍራት ብዙውን ጊዜ ጉዳታቸውን ለመናገር የማይፈልጉ በመሆኑ ይህን አይነቱን ምርመራ በተለየ ሁኔታ አስቸጋሪ ያደርገዋል:: በዚህም ምክንያት ጦርነቱ በተካሔደባቸው ስፍራዎች በተለይ የአስገድዶ መድፈር ድርጊት የተፈጸመባቸው በርካታ ተጎጂዎችን ለማነጋገር ባለመቻሉ የጥቃቱ ስፋት በዚህ ሪፖርት ከተመለከተው በእጅጉ ከፍ ያለ እንደሚሆን ኮሚሽኑ ያምናል::

**አስገድዶ መድፈር**

152. ኮሚሽኑ በዚህ ምርመራ ካነጋገራቸው ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴቶች ውስጥ አብዛኞቹ የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈጸመባቸው ናቸው:: ኢሰመኮ ምርመራ ባደረገባቸው በሁለቱ ክልሎች የሚገኙ አካባቢዎች በዋናነት ወሲባዊ ጥቃቱን የፈጸሙት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ሲሆኑ በአማራ ክልል በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎችም በሴቶች ላይ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ፈጽመዋል::

153. የትግራይ ኃይሎች በሁለቱም ክልሎች ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ስፍራዎች የቤት ለቤት ብርበራ ሲፈጽሙ እንደነበር እና ሴቶችን የመከላከያ ሠራዊት፣ የአማራ ልዩ ሀይል እና የፋኖ ሚስት ናችሁ በማለት የማንገላታት፣ ምግብ እንዲያበስሉ የማስገደድ እንዲሁም የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ይፈጽሙባቸው ነበር::

154. በአማራ ክልል ወልዲያ እና ሀይቅ ከተሞች የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በሴቶች ላይ ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች ሲፈጽሙ በነበረበት ጊዜ፤ የአካባቢው ማህበረሰብ ጥቃቱ በተፈጸመበት አካባቢ ለሚገኙ የትግራይ ኃይሎች አመራሮችና ኃላፊዎች በተጎጂዎች ላይ ስለደረሱ ጥቃቶች ቢገልፁም

52 Rome Statute, Article 8(2)(e)(vi).

53 Rome Statute, Article 7 (1) (g)

ኃላፊዎቹ ምንም አይነት እርምጃ እንዳልወሰዱ ከተጎጂዎች እና ከምስክሮች የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ።

155. በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን ያሎ ወረዳ ነዋሪ የሆነች ተጎጂ አንድ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂ ቤቷ መጥቶ የባሏን መሳሪያ እንድትሰጠው ሲጠይቃት ባለቤቷ ምንም አይነት መሳሪያ እንደሌለው በመግለጿ ካራ አውጥቶ ሊወጋት ሲል ይተወኛል በሚል ብር እንደሰጠችው እና ብሩን ከወሰደ በኋላ ግን በልጆቿ ፊት አስገድዶ እንደደፈራት ተናግራለች።

156. በአማራ ክልል በላስታ ወረዳ በላሊበላ ከተማ አንዲት የ23 ዓመት ሴት ከአንድ ዓመት ከሰባት ወር ሕጻን ልጇ ጋር እንዳለች የትግራይ ኃይሎች ታጣቂ ከነመሳሪያው ወደ ግቢዋ በመግባት የተለያዩ ጥያቄዎችን ሲጠይቃት ቆይቶ ሕፃን ልጇ ላይ መሳሪያ በመደቀንና በማስፈራራት የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ከፈጸመባት በኃላ ግንባሯን በሰደፍ በመምታት “ማታ ተመልሼ እመጣለሁ በርሽ ዝግ ሆኖ ባገኘው በሕይወትሽ ፍረጂ” እንዳላት ለኮሚሽኑ አስረድታለች።

157. በደቡብ ጎንደር ዞን ጋይንት ወረዳ ንፋስ መውጫ ከተማ የትግራይ ኃይሎች በርካታ ሴቶች ላይ ፆታዊ ጥቃት ፈጽመዋል። በከተማው ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባት ሴት ለኮሚሽኑ እንደገለፀችው የትግራይ ኃይሎች በነሐሴ ወር 2013 ዓ.ም. የንፋስ መውጫ ከተማን ከተቆጣጠሩ በኋላ ሁለት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አስገድደው ደፍረዋት ብዙ ደም እንደፈሰሳት እና በጓደኛዋ ቤት ስታገግም ቆይታ ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ አክስቷ ቤት ስትሄድ በድጋሚ የደረሰባትን ስታስረዳ፡

*“ ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ሁለት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በመንገድ አስቁመው ወዴት እንደምሄድ ጠየቁኝ፤ አክስቴ ቤት ብዬ መለስኩ። ከዛም እየጎተቱ መንገድ ዳር ከነበረ ባዶ ቤት ከአስገቡኝ በኋላ አንደኛው ሊደፍረኝ ሱሪዬን ሲያወልቅ ደም ሲመለከት አስጠላሁት እና ተፋብኝ፤ ሰደበኝ እኔም ተስፋ ቆርጬ ራሴን ላጠፋ እያሰብኩ ስለነበር አልፈራሁትም፤ መልሼ ስሠድበው ተናዶ የጠመንጃውን አፈ ሙዝ በማህፀኔ ውስጥ ከተተው። እኔ ህመሙ ከአቅም በላይ ስለነበር ራሴን ሳትኩ። አሁን ለፊስቱላ በሽታ ሕክምና እየተከታተልኩ ነው።” ብላለች።*

158. በመንዝ ቀያ ገብርኤል ዘመሮ አካባቢ የአስገድዶ መድፈር የደረሰባት ሴት ድርጊቱን ለኮሚሽኑ ስታስረዳ የትግራይ ኃይሎች ወደ ጓሳ አካባቢ መጡ ሲባል ልጆቿን ይዛ ሽሽታ እንደነበርና ልጆቿን ሌላ አካባቢ ትታ ቤቷን ለማየት ስትመለስ በርካታ የትግራይ ኃይሎች ቤቷ ውስጥና መኖሪያ አካባቢ ላይ ሰፍረው በማየቷ ወደ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሄዳ ለማደር ብትሞክርም የቤተክርስቲያኑ ጥበቃ ለትግራይ ኃይሎች አሳልፎ እንደሰጣት እና አንድ ታጣቂ መንገድ ላይ አስገድዶ ከደፈራት በኋላ በጥፊ እንደመታት፤ በጥፊውም ምክንያት በፊት ትንሽ ያማት የነበረው የግራ አይኗ አሁን ሙሉ በሙሉ ማየት እንዳቆመ ገልፃለች። በተመሳሳይ በመዘዞ ከተማ የትግራይ ኃይሎች ጥቃት ካደረሱባቸው ሴቶች መካከል አንድ የ22 ዓመት የ12ኛ ክፍል ተማሪ ስለሁኔታው የሚከተለውን አስረድታለች፡

*"በጦርነቱ ምክንያት ሸሽቼ ወደ ቤተሰቦቼ ገጠር ሄጄ ዋሻ ውስጥ ከሌሎች ጋር ተደበቅኩ፤ ከሶስት ቀን በኋላ ኅዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ምግብ ለማዘጋጀት ከዋሻ ወጥቼ ወደ ወላጆቼ ቤት ስሄድ አንድ መሳሪያ የያዘ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂ ያዘኝና የሚሊሺያ ቤት ጠቋሚኝ ብሎ ሦስት ጊዜ በጥፊ ከመታኝ በኋላ ወደ ቤት ይዞኝ ገባ። ልብሰሽን አውልቂ ሲለኝ እምቢ በማለቴ ደግሞ መታኝና አልጋው ላይ ወርውሮኝ አስገድዶ ደፈረኝ፤ ደም ይፈሰኝ ስለነበረ ሳለቅስ ጥሎኝ ሄደ።"*

159. የትግራይ ኃይሎች በአንዳንድ አካባቢዎች ሴቶችን በማስገደድ ምግብ እንዲሰሩላቸው ካደረጉ እና ከተመገቡ በኋላ ወሲባዊ ጥቃት ፈፅመውባቸዋል። ለአብነት በደባርቅ ወረዳ፣ ቦዛ ቀጠና፣ አዲ ጋግራ፣ አብርሃም እና አዳጋት ቀበሌዎችን ጥቃቱ ከተፈጸመባቸው ሴቶች ውስጥ አንዷ ለኮሚሽኑ ስትገልጽ፦

*"ወደ ቤቴ መጡና የሚበላ ስጭን አሉኝ። የለኝም ምግቤ ተበልቶብኛል ስል አንዱ ምግብሽን የበላብሽ የእናንተ ፋኖ ነው አለኝ። ፋኖ ይሁን የእናንተ ይሁን ምግቤ ተበልቶብኛል የለኝም አልኩት። የያዝኩትን ሕፃን አስቀምጪ አለኝ። ዝም ስለው ከመሞት እና ከመሰንበት ምረጪ አለኝ። እኔም መሰንበት አልኩት። ቀጥሎም ሲይዘኝ ዝም አልኩኝ። ከዛም ደፍሮኝ ሄደ። ጥቃቱ ከተፈጸመብኝ ጊዜ ጀምሮ በማህበረሰቡ "የጁንታ ባለቤት" እየተባልኩ መጠቋቆሚያ ሆንኩኝ እየተሰደብኩም ነው።" ብላለች።*

160. በዚሁ በደባርቅ ወረዳ ድብባህር አንዲት ሴት ከነሐሴ 14 ቀን እስከ ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በተከታታይ ለ15 ቀናት በተለያዩ 15 የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች መደፈሯን ለኮሚሽኑ እንደሚከተለው አስረድታለች፦

*"እኔ ቤቴ እያለሁ ነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. 2 ታጣቂዎች መጥተው አንዱ ደፈረኝ። እስከ ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በየተራ እየመጡ ይደፍሩኝ ነበር። ሲደፍሩኝ፣ የእናንተ ሰዎች የእኛ ሴቶች ለ10 ሆነው ነበር የሚደፍሩት ይሉኝ ነበር። እኛ እነሱን ለመበቀል ነው የመጣነው እንጂ በአክሲል ነበር የምንዳረው፣ ይላሉ። እየተመላለሱ 15 ታጣቂዎች ደፍረውኛል።"*

161. በደቡብ ወሎ ዞን ተሁለዴሬ ወረዳ ቀበሌ 017 ነዋሪ የሆነች ሴት መስከረም 24 ቀን 2014 ዓ.ም በመከላከያ ሠራዊት አባል የአስገድዶ መደፈር ጥቃት የተፈጸመባት ሴት ሀይቅ ከተማ በሚገኝ ሆስፒታል በመታከም ላይ እንደምትገኝ ምስክሮች፣ ከቀበሌው አስተዳዳር እና ከአካባቢው ነዋሪዎች ለኮሚሽኑ የገለጹ ቢሆንም፤ ጥቃት የደረሰባት ተጎጂ የደህንነት ስጋት አለብኝ በማለቷ ኮሚሽኑ ሊያነጋግራት ሳይችል ቀርቷል።

162. በሸዋ ሮቢት ከተማ በትግራይ ኃይሎች የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ከደረሰባቸው ተጎጂዎች መካከል የ34 ዓመት ሴት አጥቂዋ አብሯት አድሮ ከሔደ በኋላ ጠዋት ላይ በገመድ ታንቃ ሞታ ተገኝታለች፡፡ ስለ ሁኔታው አፈጻጸም የሚች የ14 ዓመት ልጅ ለኮሚሽኑ እንደሚከተለው አስረድቷል፦

*“ዕለቱ ሰኞ ቀን ነበር፣ ምሽት 12፡00 ሠዓት አካባቢ አንድ መሳሪያ የያዘ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂ መጥቶ እዚህ ቤት የገባ ሰው አለ ብሎ የኛን እና የጎረቤታችንን ቤት ፈትሾ እናቴን መረጃ ትሰጣለች በሚል እኔና ጎረቤታችንን ከኛ ቤት እንዳትንቀሳቀሱ ብሎ እናቴን ጎረቤት ቤት ወስዶ ደፈራት፡፡ መደፈሯን ያወቅሁት መጥታ ለጎረቤታችን ስትናገር ነው፡፡ ይህንን ካደረገ በኋላ እራት ስጡኝ ብሎ መጀመሪያ እኛን አስቀምሶን እራቱን በላ፡፡ እኔን ጎረቤት ቤት ወስዶ አስገብቶ በውጭ በኩል ዘጋብኝ፡፡ ከዚህ በኋላ የሆነውን አላውቅም፡፡ በዚሁ ቀን ታጣቂው አብሯት እንዳደረ ጎረቤታችን ነግራኛለች፡፡ እናቴ ጠዋት ከቤት ውስጥ ታንቃ ሙታ ተገኘች፡፡”*

163. የኮምቦልቻ ከተማን የትግራይ ኃይሎች ከጥቅምት 21 እስከ ኅዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም. ይዘው በቆዩበት ወቅት የአስገድዶ መድፈር ጥቃቶችን መፈጸማቸውን ከተጎጂዎች፣ ከተጎጂ ቤተሰቦችና ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ ከኮምቦልቻ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት፣ ከኮምቦልቻ ሴቶችና ሕፃናት ቢሮ፣ ከፌዴራል ዓቃብያነ ሕግ፣ ኮሚሽኑ ያገኛቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በከተማዋ በትግራይ ኃይሎች ቢያንስ 14 የአስገድዶ መደፈር ጥቃቶች ተፈጽመዋል፡፡ ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አስገድዶ መድፈር የተፈጸመባቸው የ16 ዓመት እና የ20 ዓመት ሴቶች ለኮሚሽኑ እንዳስረዱት በሚሰሩበት ግሮሰሪ ውስጥ ሲጠጡ ያመሹት ታጣቂዎች ከእኩለ ሌሊት በኋላ ተመልሰው በመምጣት የግሮሰሪውን ባለቤት ሴቶች ስጪን ብለው ሲጠይቁ እምቢ በማለቷ ተኩስ ከፍተው የግሮሰሪውን ባለቤት እና የ12 ዓመት ልጇ ላይ ጉዳት በመድረሱ የአካባቢው ሰዎች ተጎጂዎችን ወደ ሕክምና ይዘው ሲሔዱ አምስት ታጣቂዎች የግሮሰሪው ሰራተኞች ወደሚያድሩበት ክፍል በመሄድ በአራት ሴቶች ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል መፈጸማቸውን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

164. በደሴ ከተማ አይጠየፍ ቀበሌ ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. በ22 ዓመት ወጣት እና በ13 ዓመት ታዳጊ ላይ በሁለት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ወሲባዊ ጥቃት ተፈፅሟል፡፡ ሁለቱ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በአንድ ግቢ ውስጥ የሚኖሩ ጎረቤታሞች ሲሆኑ የትግራይ ኃይሎች ቤታችሁን ልንፈትሽ ነው በማለት ወደ ግቢ በመግባት የሁለቱንም ተጎጂዎች ቤቶች ፈትሸው ሲጨርሱ ተጎጂዎችን በየተራ በማስገባት የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የፈጸሙባቸው ሲሆን አንዱ ታጣቂ ጥቃቱን ፈጽሞ እስከሚወጣ ሌላኛው የተጎጂን አባት እና የአካባቢው ሰዎች ወደቤት እንዳይገቡ በመሳሪያ አስፈራርቶ በር ላይ እንዲቀመጡ በማድረግ በየተራ ጥቃት እንደፈጸሙባቸው ተጎጂዎች እና የዓይን እማኞች ገልጸዋል፡፡

### በቡድን አስገድዶ መድፈር

165. በአማራ ክልል ሀይቅ ከተማ ነዋሪ የሆነች ተጎጂ አራት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች የአስገድዶ መድፈር ድርጊት እንደፈጸሙባት ለኮሚሽኑ ገልፃለች። ተጎጂዋ በዕለቱ የነበረውን ሁኔታ ስታስረዳ ጥቅምት 25 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 7:00 ሰአት አካባቢ አራት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች መሳሪያ ደግነው ወደ መኖሪያዋ በመምጣት በር እንድትከፍት ካደረጓት በኋላ "መሳሪያ ደብቀሻል፣ የብልፅግና ደጋፊ ነሽ፣ የአብይ ቲሸርት ቤትሽ አለ እንፈትሻለን" በማለት ወደቤቷ ውስጥ ከገቡ በኋላ አንዱ ታጣቂ በር ላይ ሆኖ ሲጠብቅ፣ የተቀሩት ሁለቱ ድርጊቱን ቆመው ሲመለከቱ አንዱ የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ፈጽሞባታል። በዚህ አይነት መንገድ አራቱም ታጣቂዎች እየተፈራረቁ ጥቃቱን ፈጽመውባት እንደሄዱ ለኮሚሽኑ አስረድታለች። መንግሥት ቦታውን ከተቆጣጠረም በኋላ ሕክምና ስታደርግ በሄፐታይተስ ቢ ኢንፌክሽን መያዟ የተነገራት መሆኑን ገልጻለች።

**166.** ኮሚሽኑ ምርመራ ባካሄደባቸው የአፋር እና የአማራ ክልሎች በቡድን አስገድዶ መድፈር ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን ኮሚሽኑ ያገኛቸው መረጃዎች ያሳያሉ። በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን ጎቢዶራ ከተማ መስጊድ ቀበሌ በቡድን የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈጸመባት ሴት ለኮሚሽኑ እንደገለፀችው ከቤቷ በምዕራብ አቅጣጫ ወደ አባሂዶ ተራራ ሸሽታ ከሄደች ከአራት ቀናት በኋላ ምግብ እና ልብስ ለመውሰድ የጁማአ (አርብ) ማታ 3:00 ሰዓት ወደ ቤቷ ስትመጣ አራት የትግራይ ታጣቂዎችን ቤቷ ውስጥ እንዳገኘቻቸው እና ለምን መጣሽ ሲሏት ቤቴ ስለሆነ ምግብና ልብስ ልወስድ ነው ብትላቸውም *"የእኔ ቤት ነው የእኔ አገር ነው ማለት ድሮ ቀረ"* በማለት ከነሱ መሀከል አንደኛው ታጣቂ ግደሏት ወይ ድፈሯት በማለት ወደ ቤት እንድትገባ ሲያደርጋት ሌሎቹ ገፍትረው በጀርባዋ ጥለው አንደኛው እግሯን ሌላኛው እጇን በመያዝ ሁለቱ እየተፈረራቁ ከደፈሯት እና ከገረፏት በኋላ የተቀደደውን ልብሷን እንኳን ሳትቀይር ከቤቷ እንዳስወጧት ገልፃለች።

167. በሌላ በኩል በአማራ ክልል በጅሮሰን ቀበሌ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባት ሴት ለኮሚሽኑ እንደገለፀችው የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አካባቢውን በተቆጣጠሩበት ጊዜ ቤተሰቦቿ ሸሽተው ወደ ጫካ ሲሄዱ እሷ ልጆቿን ይዛ ጎረቤት ተደብቃ እንደነበር፤ ነገር ግን በቀጣዩ ቀን ቤቷን ለማየት ስትመለስ ቤቷ ውስጥ የነበሩ 5 የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በቡድን አስገድደው እንደደፈሯት እና ጥቃቱ በደረሰባት ወቅት የ3 ወር ነፍሰጡር እንደነበረች ገልፃለች።

168. በደሴ ከተማ ቧንቧ ውሃ በሚባል አካባቢ እድሜቸው ከ 13 እስከ 21 ዓመት የሆኑ 10 ሴቶች በትግራይ ኃይሎች ተደፍረዋል። ከተጎጂዎች መከላከል አንዷ በተከታታይ ለ20 ቀናት በሶስት የታጣቂዎች በቡድን የአስገድዶ መድፈር ጥቃት እንደደረሰባት ለኮሚሽኑ ገልጻለች።

169. በተመሳሳይ በመርሳ ከተማ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴቶች መካከል የአንድ ተጎጂ እናት ስለ ሁኔታው ሲያስረዱ መስከረም 14 ቀን 2013 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 10:00 ሰዓት አካባቢ በ02

ቀበሌ የትግራይ ኃይሎች ልጃቸውን በቡድን የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ሲፈፅሙባት የድረሱልኝ ጩኸት ቢያሰሙም ማንም ሊደርስላቸው እንዳልቻለ ገልጸዋል፡፡

170. በተመሳሳይ በመሀል ሜዳ መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ቀበሌ 03 የቡድን አስገድዶ መድፈር ጥቃት የደረሰባት የ20 ዓመት ተጎጂ እንደገለጸችው ቀኑን በማታስታውሰው ዕለት ሻይ ቡና ንግድ በምትሰራበትና በምትኖርበት የኮንቴይነር ቤት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በመምጣት አብረዋት የነበሩትን የ80 ዓመት አባቷን አውጥተው ውጪ ግንድ ላይ አስረው የ2 ዓመት ልጇ ባለበት ለ3 እንደደፈሯት አስረድታለች፡፡

171. በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ከሚሴ ከተማ የኦነግ ሸኔ ኃይሎችታጣቂዎች በሴቶች ላይ በቡድን አስገድዶ መድፈር ጥቃቶችን ፈጽመዋል፡፡ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች አካባቢውን ከተቆጣጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ጥቃቶችን ሲፈፅሙ እንደነበር ኮሚሽኑ ያነገራቸው ተጎጂዎች፣ የከተማ አስተዳደር እና የአካባቢው ፖሊስ ገልጸዋል፡፡ በከተማው ኬላ በሚባል እና በብዛት የአማራ ብሄር ተወላጆች ይኖሩበታል ተብሎ የሚታወቅ ሰፈር ኅዳር 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ ሁለት የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች ወደ መኖሪያ ቤቷ ለመሳሪያ ፍተሻ ብለው እንደገቡ እና ከገቡ በኋላ ብሔሯን ጠይቀው አማራ መሆኗን ሲያውቁ እየሰደቧት እና እያንገላቷት ከቆዩ በኋላ ጥይት መተኮሳቸውን እና ሊደፍሯት ሲሉ ልጄ ፊት አትፈፅሙብኝ ብላ በመለመኗ ወደ ጓሮ ይዘዋት በመሄድ በቡድን እንደደፈሯት ከዛም ወደ ቤቷ መልሰው ከሻንጣዋ ውስጥ ብር እንደወሰዱባት ገልፃለች፡፡ በተመሳሳይ ሌላዋ ተጎጂ ኅዳር 12 ቀን 2014 ዓ.ም. ሰባት የኦነግ ሸኔ አባላት ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ላይ በምትሰራበት ቦታ አግኝተዋት ወደሌላ ቦታ በመውሰድ ለሁለት ተከታታይ ሰዓታት ያህል የአስገድዶ መድፈር ጥቃት እንደፈጸሙባት ለኮሚሽኑ ገልፃለች፡፡

**የአስገድዶ መድፈር ሙከራ**

172. የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች የአስገድዶ መድፈር ሙከራ ወንጀል መፈጸማቸውንና፤ ተጎጂዎችና ሌሎች ሰዎች ያደረጉትን የመከላከል ጥረት የሚመለከት መረጃዎችም ለኮሚሽኑ ደርሷል፡፡ ለምሳሌ በመንዝ ጌራ ምድር የአስገድዶ መድፈር ሙከራ የተፈጸመባት የ28 ዓመት ተጎጂ ለኮሚሽኑ እንደሚከተለው አስረድታለች፡-

*“ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም. ባለቤቴ ወደቤቱ ለመምጣት ስለቆየብኝ ፍለጋ ወጣሁ፡፡ መንገድ ላይ 2 የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አገኙኝ፡፡ ወደ ካምፕ ወስደን እንደፍርሻለን ብለው ሊወስዱኝ ሲሉ በአቅራቢያችን የባለቤቴ እህት ቤት እንዳለ ነግሬ እዛ ወሰድኳቸው፡፡ ቤት ውስጥ ከገባን በኋላ በቤቱ የነበሩትን የባለቤቴን እህት፣ ባሏን፣ የአከራያቸውን ሴት ልጅ ጨምሮ ወደሳሎን ወሰዱን፡፡ እኛ ሴቶቹ ምግብ እንድናዘጋጅላቸው አዘውን የባለቤቴ እህት ባልን ደግሞ አንበረከኩት፡፡ ከበሉ በኋላ ባለቤቴ እኔን ፍለጋ መጣ፡፡ እሱን ኮቱን አስወልቀው አንበረከኩት መታወቂያ*

*እንዲያሳያቸው ጠይቀውም የብልፅግና ፓርቲ አባል ነህ ብለው አንደኛው ታጣቂ መታው። የባለቤቴን እህት በጥፊ መቶ ፍራሽ እንድታወርድ አስገደዳት። እኔንም ባሏ እያየ እንድፈራት ብለው ከአከራያቸው ልጅ ጋር ልብሳችንን እንድናወልቅ አደረጉን። መሳሪያ የያዘው ከአጠገቤ እንደተቀመጠ ባለቤቴ ከተንበረከከበት ተነስቶ ያዘው። መሳሪያውን ቀምተን ሁለቱንም ተረባርበን አንደኛውን በመሳሪያው አንደኛውን አጠገባችን ባገኘነው ቢላዋና ጠርሙስ ገደልናቸው።"*

173. በሰሜን ጎንደር ዞን አዲ አርቃይ ወረዳ ዛሪማ ንዑስ ወረዳ ነዋሪ የሆነች ሴት የትግራይ ኃይሎች መኖሪያ ቤቷ መጥተው ወንድሞችሽ የፋኖ አባላት ናቸው፤ የኛን ሰዎች መነኩሴ ሳይቀር ደፍረዋል በማለት በኤሌክትሪክ ገመድ አስረው ወደ ተራራ እንደወሰዷት ከዚያም ሶስት ቀን በጠፍር እየደበደቡ እንዳቆይዋት እና የአስገድዶ መድፈር ጥቃት ሊፈፅሙባት ሲሉ የHIV መድኃኒት እንደምትወስድ ስትነግራቸው እንደለቀቋት አስረድታለች።

**በሴቶች ላይ የደረሱ አካላዊ ጥቃቶች**

174. ኮሚሽኑ ምርመራ ካደረገባቸው ከሁለቱ ክልሎች ፆታን መሰረት ያደረጉ ኢ-ሰብአዊ አያያዞች እና አካላዊ ጥቃቶች የተፈጸሙባቸው ሴቶችን አስመልክቶ መረጃዎች ለማግኘት ችሏል። ፆታዊ ጥቃት የደረሰባት የአፋር ክልል ጉሊና ወረዳ ጋሊኮማ ቀበሌ ነዋሪ የሆነች የ30 ዓመት ሴት ስለሁኔታው ስትገልፅ ልጆቿን ይዛ ፉኪሳ ወደሚባል ገጠር ቦታ ከሸሸች ከቀናት በኋላ ምግብ ለማምጣት ወደመኖሪያ ቤቷ ሔዳ እቃዎች በአህያ ጭና ስትመለስ የትግራይ ኃይሎች አግኝተው ከፈተሿት በኋላ አሳድረው በጠዋት እንደሚለቋት በመንገር ወደ ተራራ ከወሰዷት በኋላ በነጋታው በደረቅ እንጨት ደጋግመው ዱላው እስኪሰበር እንደደበደቧት እና ወደ ከለዋን ከተማ ወስደው ለ5 ቀናት ቆርቆሮ ቤት ውስጥ አስረው እንዳቆዩዋት ገልጻለች። ኮሚሽኑም በተጎጂዋ ትከሻ ላይ ጠባሳዎችን ለመመልከት ችሏል።

***ፆታዊ ጥቃት በደረሰባቸው ሴቶች ላይ የደረሱ መገለሎች እና ለዳግም ሰለባነት መጋለጥ***

175. ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው በርካታ ሴቶች በአካባቢው ማህበረሰብ የሚደርስባቸውን መገለል በመፍራት እና ከደህንነት ስጋት አኳያ የደረሰባቸውን ጥቃት አስመልክቶ ለኮሚሽኑ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ስለደረሰባቸው ጥቃት መናገር የቤተሰብ ክብርን ማዋረድ ነው የሚል እሳቤ መኖሩንም ለመረዳት ተችሏል። በአንዳንድ አካባቢዎች ወሲባዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው የታወቀ ሴቶች በማህበረሰቡ *"የጁንታ ሚስት"* የሚል ስም እየተሰጣቸው እንደሚገለሉ እና እንደሚሰደቡ ተናግረዋል። በመሆኑም በእነዚህ ምክንያቶች ምርመራ በተደረገባቸው አካባቢዎች ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ቁጥር በዚህ ምርመራ ከተገለጸው በእጅጉ ሊበልጥ እንደሚችል ኮሚሽኑ ተገንዝቧል።

**የጥሰቱ ተፅዕኖ**

176. ወሲባዊ እና ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ከፍተኛ እና ውስብስብ ለሆነ የጤና፣ አካላዊ ፣ ሥነልቦናዊ ፣ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች ተዳርገዋል። ቢያንስ አንድ የጥቃቱ ሰለባ የሆነች ሴት ጥቃቱ በተፈጸመባት ማግስት የእራሷን ሕይወት አጥፍታ ተገኝታለች፤ ይህም የሥነልቦና ጉዳቱን የተፅዕኖ መጠን አስከፊነት የሚያሳይ ነው። እንዲሁም የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች ለተለያዩ አባላዘር በሽታዎችላልተፈለገ እርግዝና፣ ለፌስቱላ ጉዳት እና ለአዕምሮ መረበሽ ተጋልጠዋል። ተጎጂዎቹ ያሉበት ሥነልቦናዊ ሁኔታ በጦርነት ዐውድ ውስጥ ከመኖር ጋር ተደርቦ ያሉበትን ችግር በይበልጥ ያከብደዋል።

177. በግጭቱ ምክንያት በአብዛኛው በአቅራቢያቸው የሚገኙት የሕክምና ተቋማት አገልግሎት ባለመስጠታቸው ጥቃቱ እንደደረሰባቸው አፋጣኝ የጤና እና የሥነልቦና አገልግሎት አላገኙም፤ በተጨማሪም ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ኢኮኖሚያዊ ሕይወታቸው ላይ የመሳተፍ አቅማቸው እንዲቀንስ ያደርጋቸዋል። ከማህበረሰቡ የሚደርስባቸውን ችግሮች በመፍራት ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች እንደቀድሞው ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሕይወታቸው ላይ ለመሳተፍ እና ከማኅበረሰቡ ጋር የመቀላቀል አቅማቸው ውስን እንዲሆን እና ምርታማነታቸው እንዲቀንስ ስለሚያደርግ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ያጋጥማቸዋል።

178. ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በተለይም የአስገድዶ መድፈር በማኅበረሰቡ "የጁንታ ሚስት" በመባል ስድብ እና ማንቋሸሽ እንዲሁም በማኅበረሰቡ መገለላቸው የሚፈጥርባቸው አእምሮአዊ እና ስነልቦናዊ ችግር ከፍተኛ ነው። በሌላ በኩል ኮሚሽኑ የደረሱት ተደጋጋሚ ጥቆማዎች እንደሚያሳዩት ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ነገር ግን ከማኅበረሰቡ የሚደርስባቸውን መገለል እና ማንቋሸሽ በመፍራትና በመስጋት እንዲሁም የቤተሰብ ክብርን ማዋረድ ነው በሚል እሳቤ የደረሰባቸውን ጥቃት አውጥተው ያልተናገሩ ሴቶች ከሚድርስባቸው የሥነልቦና ጭንቀት በተጨማሪ በወቅቱ ሕክምና የማያገኙ በመሆኑ ለሌላ ከፍተኛ የአጭር እና የረጅም ጊዜ የጤና መታወክ እና ማኅበራዊ ጉዳት ያስከትልባቸዋል።ቤተሰባዊ ግንኙነታቸውም ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ይሆናል።

179. መንግሥትየትግራይ ኃይሎች አካባቢውን ለቀው ከወጡ በኋላ የአማራ ክልል መንግሥት እና በጎ ፈቃደኞች በአንዳንድ አካባቢዎች የዓባላዘር በሽታ ምርመራ፣ ሕክምና፣ የንጽህና መጠበቂያ እንዲሁም የስነ-ልቦና እና የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የተሞከረ ቢሆንም ጥቃቱ ከሚያስከትለው ውስብስብ ችግርና ውጤት፣ እንዲሁም ጥቃቱ የተፈጸመበት ስፋት እና ብዛት አንፃር ሲገመገም አነስተኛ በመሆኑ ዘርፈ ብዙ እና መጠነ ሰፊ ምላሽ ይሻል።

180. የተወሰኑ የጥቃቱ ሰለባዎች በኮሚሽኑ ምርመራ ወቅት የደረሰባቸውን ጥቃት ለኮሚሽኑ ለማሳወቅ በመቻላቸው ለደረሰባቸው ሥነልቦናዊ ጉዳት መጠነኛ መጽናናት እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል።

***መደምደሚያ***

181. የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች እና የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች በአፋርና አማራ ክልሎች በሴቶች ላይ (ሕፃናት ሴቶችን ጨምሮ) የፆታና ወሲባዊ ጥቃቶችን ስለመፈጸማቸው ምክንያታዊ አሳማኝ ሁኔታዎችና ማስረጃዎች አሉ። በተጨማሪም በተለይ በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በአፋርና አማራ ክልሎች ተስፋፍተው የተፈጸሙ ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃቶች የተጎጂዎችን እና የጥቃቱ ዒላማ የተደረጉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ሰብአዊ ክብር ለመጉዳት እና ለማዋረድ፣ በአብዛኛው በሴቶች ላይ በሙሉ ያለልዩነት፣ አልፎ አልፎም አጥቂዎቹ ሆነ ብለው ለጥቃቱ ዒላማነት በመረጧቸው ሴቶች ላይ ሆነ ተብሎ ታቅዶ በግፍና በጭካኔ፣ በግልጽ የበቀል ስሜት፣ በቡድን አስገድዶ በመድፈር፣ ድርጊቱን ሆነ ተብሎ በቤተሰብ ፊት በመፈጸምና፣ ባዕድ ነገር (የጠብ መንጃ አፈ ሙዝ) በመሀፀን በመክተት ጭምር፣በታጣቂዎቹ ኃላፊዎች ይሁንታ እና ዝምታ የተፈጸመ በመሆኑ፤የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በሴቶች ላይ የፈጸሙት ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃትን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለጦርነት አላማ እንዳዋሉት የሚያስረዳ ነው። እነዚህ የመብት ጥሰቶችም በጦርነት ዐውድ ውስጥ የተፈጸሙ በመሆናቸው፤ የጦር ወንጀልም ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው።

182. የጥቃቱ ሰለባ በሆኑ ሴቶችና ቤተሰቦቻቸው ላይ የደረሱባቸው ጉዳቶች የረጅምና የአጭር ጊዜ የጤና፣ የሥነልቦና፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶችን አስከትለውባቸዋል። ለደረሱባቸው ጉዳቶች በቂ የሆኑ አስፈላጊው ድጋፎች እያገኙ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል።

183. ይህን አይነት በተለይ በግጭት ዐውድ ውስጥ በሴቶች ላይ ያነጣጠረ ግፍና ጭካኔ የተሞላው ጥቃት ተደጋግሞ የመከሰት ባህሪይ እና አዝማሚያ ስላሳየ፤ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት በማረጋገጥ፣ የተጎዱ ሴቶችና ቤተሰቦቻቸውን በሁሉን አቀፍ ድጋፍና እርዳታ በመጠገን እንዲሁም ወደፊት ተመሳሳይ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ ረገድ አፋጣኝ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው።

## 6. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች

***መግቢያ***

184. በትግራይ ክልል የነበረው ጦርነት ወደ አጎራባች ክልሎች መስፋፋቱን ተከትሎ በተለይም የትግራይ ኃይሎች ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በአማራ እና በአፋር ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ወራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች ከቤታቸውና መኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለዋል። ኮሚሽኑ ምርመራውን በሚያከናውንበት ወቅት ወደ ቀያቸው የተመለሱ የተወሰኑ ተፋናቃዮች ቢኖሩም ሌሎች ተፈናቃዮች ወደ መኖሪያቸው ለመመለስ የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ በጊዜያዊ መጠለያዎች ውስጥ ይገኙ ነበር። በዚህ ሪፖርት ላይ ንብረት ላይ የተፈጸመ

ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ማበላሸት/ማውደም የሚዳስሰው ክፍል ከተፈናቃዮችና ተመላሽ ተፈናቃዮች የኑሮ ሁኔታ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ ሁለቱ የሪፖርቱ ክፍሎች አብረው የሚታዩ ናቸው::

185. ኮሚሽኑ በአፋር ክልል በሑደሌ ዳባ፣ ማዳዴራሎ እና ወረዳ ኢባይ ወይድል(ሀምሳ) ካምፖች እንዲሁም በኪልበቲ ረሱ ዞን፣ በርሃሌ ወረዳ የሚገኙ ጊዜያዊ መጠለያዎችን፤ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ደባርቅ ከተማ፣ በደሴ እና ኮምቦልቻ የትምህርት ቤት ጊዜያዊ መጠለያዎች በመገኘትና ተፈናቃዮችን በማነጋገር መረጃ አሰባሰቧል::

**የሕግ ማዕቀፍ**

186. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በጦርነት ወይም በትጥቅ ግጭት፣ በመጠነ ሰፊ ብጥብጦች፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ወይም ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ወይም በሚያስከትሏቸው ውጤቶች የተነሳ ከሚኖሩባቸው ቤቶች ወይም መደበኛ የመኖሪያ ቦታዎች እንዲሸሹ ወይም ለቀው እንዲወጡ የተገደዱ ነገር ግን የዓለም አቀፍ አውቅና ያለው የሀገር ድንበር ተሻግረው ያልተሰደዱ ሰዎች ወይም ቡድኖች ማለት ነው::[54]

187. በትጥቅ ግጭት ዐውድ በሚከሰት መፈናቀል ወቅት የግጭቱ ተሳታፊ ኃይሎች ለተፈናቃዮች ደህንነት፣ መጠለያ፣ ምግብ፣ ውሃ፣ ልብስ፣ የሕክምና እና የንፅህና አገልግሎቶችን ያካተተ በቂ የሰብአዊ ድጋፍ እንዲቀርብ የማድረግ ግዴታ አለባቸው:: [55] የእነዚህ አስፈላጊ አገልግሎቶች አቅርቦትም በተለይ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞችን ልዩ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል:: በተጨማሪም ተዋጊ ወገኖች ይህንን አገልግሎቶች ለማቅረብ በማይችሉበት ወቅት ሁሉ ሌሎች የሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያቀርቡ መፍቀድ እና ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል ::[56]

188. ተፈናቃዮች ለመፈናቀላቸው ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎች ሲወገዱ በፈቃደኝነት፣ ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ መኖሪያ ቤታቸው ወይም መደበኛ የመኖሪያ ስፍራቸው የመመለስ ወይም በፈቃደኝነት በሀገር ውስጥ በሚገኝ ሌላ ቦታ የመስፈር መብት አላቸው::[57] ተፈናቃዮች መኖሪያ ስፍራቸውን ለቀው በሄዱበት ወቅት ጥለዋቸው የሄዷቸው ንብረቶች ከውድመት፣ ከዘፈቀደ እና ሕጋዊ ካልሆነ መያዝ፣ ቁጥጥር ወይም ግልጋሎት ሊጠበቁ ይገባል::[58]

---

[54] Article I (K) of the African Union Convention for The Protection And Assistance Of Internally Displaced Persons In Africa (Kampala Convention) and proclamation No 1187/2020 to ratify the African union convention for the protection and assistance of internally displaced persons in africa (kampala convention). Ethiopia has specifically declared it accepts the definition as provided under Kampalla Convention.

[55] Article 17 (1) Additional protocol II to the Geneva conventions.

[56] ICRC, Customary IHL Database, Rule 55.

[57] Principle 6 (3) UN Guiding Principles on Internal Displacement; Rule 132 ICRC Study on Customary InternationalHumanitarian Law.

[58] Principle 21 (3) UN Guiding Principles on Internal Displacement.

**የምርመራው ግኝቶች**

189. በትግራይ ክልል የነበረው ጦርነት ወደ አማራ እና አፋር ክልል አካባቢዎች መስፋፋቱን ተከትሎ ከተለያዩ የክልሎቹ አካባቢዎች የበርካታ ነዋሪዎችን መፈናቀል አስከትሏል፡፡ በሁለቱም ክልሎች የግጭቱ ወደ ቀዬአቸው መቃረብ በፈጠረባቸው ስጋት፣ በሚኖሩበት አካባቢ በነበረ ውጊያ የከባድ መሳሪያ በመተኮሱ ምክንያት በተፈጠረ ስጋት ወይም የትግራይ ኃይሎች ተፈናቃዮቹ ይኖሩበት የነበረውን አካባቢ በተቆጣጠሩበት ወቅት ሲፈጸሙ በነበሩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሁኔታዎች መነሻነት መፈናቀላቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

190. በአፋር ክልል ከተለያዩ መንደሮች የተፈናቀሉ ሰዎች የጦርነቱን መስፋፋት ተከትሎ ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ መፈናቀላቸውን ለኮሚሽኑ ገልጸዋል፡፡ በደባርቅ ከተማ ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ተጠልለው ከነበሩ ተፈናቃዮች በተሰበሰበ መረጃ መሰረት የመፈናቀላቸው መንስኤ ቀያቸውን የትግራይ ኃይሎች መቆጣጠሩን ተከትሎ በከባድ መሳሪያ ጭምር ሰዎች ሲገድሉ፣ ሲዘርፉ፣ ወጣቶችን በኃይል እያፈኑ ሲወስዱ በመመልከታቸውና፣ ሴቶች በመደፈራቸው ነው በማለት አስረድተዋል፡፡ ተፈናቃዮች በመፈናቀል ሂደት በርካታ ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር መነጣጠላቸውን እና ይህ ምርመራ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ከቤተሰቦቻቸው ያልተገናኙ ሰዎች መኖራቸውን ይገልጻሉ፡፡

191. ከፌዴራል የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በተገኘ መረጃ መሰረት በአፋር ክልል 694,000፣ በአማራ ክልል 1.4 ሚሊዮን ሰዎች በጦርነቱ ምክንያት በመፈናቀላቸው፤ ነባር ተፈናቃዮችንና ሌሎች እርዳታ ፈላጊዎችን ጨምሮ በሁለቱ ክልሎች ብቻ የምግብ ክፍተት ያለባቸው ሰዎች ቁጥርን ከ10 ሚሊዮን በላይ አድርሶታል፡፡[59] በሁለቱም ክልሎች የተፈናቀሉ ሰዎች በመጠለያ ካምፖች፣ በትምህርት ቤቶች፣ ከማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀላቅለው እና በሌሎች ስፍራዎችም ተጠልለው የሚገኙ ሕፃናት፣ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን ጭምር ይገኙበታል፡፡

192. በአፋር ክልል በጭፍራ ወረዳ ኮሚሽኑ ታኅሣሥ ወር 2014 ዓ.ም. ባደረገው ክትትል እና ባገኘው መረጃ ኢባይ ወይደል (ሀምሳ) መጠለያ ካምፕ 8705 አባወራዎች፣ በአደአር ወረዳ ኡዳሌደባ እና ማዴራሎ ካምፖች በድምሩ 4423 አባወራዎች፣ እንዲሁም በበርሀሌ ወረዳ በት/ቤት፣ በሜዳ ላይ፣ በመንግሥት ቢሮዎች ውስጥ ተጠልለው የሚኖሩ እና የግለሰብ ቤቶች ተከራይተው ወይም ቤተሰብ ጋር በማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀላቅልው የሚኖሩ 2590 አባወራዎች (15,540 ሰዎች የሚገኙበት)፤ ከአብዓላ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች የተፈናቀሉ እና ጊዜአዊ መጠለያ ጣቢያ ባለመኖሩ በየተራራው ስር ተጠልለው የሚገኙ 1051 አባወራዎች፣ ቡሪቡሊ ወረዳ ሻሂጉቢ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠልለው የሚገኙ 1400 አባወራዎች እንደነበሩ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ይህ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅትም የጦርነቱ ሁኔታ በአፋር ክልል ቀጥሎ የነበረ በመሆኑ የተፈናቃዮች ቁጥር በፌዴራል የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ከተጠቀሰውም በላይ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

[59] ከፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በየካቲት 16 ቀን 2014 ዓ.ም. የተጻፈ ደብዳቤ፡፡ (አባሪ ቁጥር 12)

193. ከፌዴራል የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን እንዲሁም ከክልሎች በተገኘው መረጃ መሰረት የመንግሥት፣ የሰብአዊ ድርጅቶችንና በጎ ፈቃደኛ ሰዎችን ድጋፍ በማስተባበር ለተፈናቃዮች እርዳታ ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም፤ ከተፈናቃዮች ብዛት እና ልዩ ድጋፍ ከሚያስፈልጋቸው ነፍሰጡር ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ሕፃናት እና አረጋውያን ተፈናቃዮች አንጻር ሰብአዊ እርዳታው የተሟላ እንዳልሆነ ኮሚሽኑ ተመልክቷል።

194. ለአብነትም ከአፋር ክልል አብዓላ ወረዳ ተፈናቅለው በየተራራው ስር ተጠልለው የነበሩ ተፈናቃዮች ኮሚሽኑ ይህን የምርመራ ስራ ሲያካሂድ በነበረበት ጊዜ ድረስ በክልሉ መንግሥትም ሆነ በለጋሽ ድርጅቶች የተደረገላቸው ምንም አይነት ድጋፍ አልነበረም። ቡሪቡሊ ወረዳ ሻሂጉቢ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃዮች በቂ እና ቀጣይነት ያለው የምግብ አቅርቦት እና ምግብ ነክ ያልሆኑ እንደ የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች እና የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ የመሳሰሉ ግብአቶች አቅርቦት ካለመኖሩም ባሻገር በመጠለያው የንጹህ ውሃ አቅርቦት ባለመኖሩ ተፈናቃዮቹ በደርሶ መልስ የ3 ሰዓት የእግር መንገድ እየተጓዙ የወንዝ ውሃ እንደሚቀዱ ለመረዳት ተችሏል። እንዲሁም በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የሕክምና አገልግሎት አልነበረም።

195. በተመሳሳይም በአማራ ክልል በሚገኙ መጠለያዎች ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ አይነቶች ከክልሉ የአደጋ ስጋት ቢሮ፣ከሰብአዊ ድርጅቶችና በጎ ፈቃደኞች በማስተባበር ጥረት እየተደረገ ቢሆንም፤ የተሟላ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ለአብነትም በደሴ እና በኮምቦልቻ ከተሞች በሚገኙ የተፈናቃዮች ማቆያዎች የሰብአዊ እርዳታን በሚመለከት የምግብ፣ የአልባሳት፣ የመኝታ፣ የጤና አገልግሎቶች እንደሚሰጡ ነገር ግን የምግብ አቅርቦቱ ወቅቱን ጠብቆ እና ሙሉ ሆኖ እንደማይቀርብ ለማወቅ ተችሏል። ከፌዴራል የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በተገኘው መረጃ መሰረት፤ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ በአፋርና አማራ ክልሎች የተደረገውን የእርዳታ አቅርቦት ስርጭት ዝርዝር መረጃ የዚህ ሪፖርት አባሪ ሆኖ ተያይዟል።[60]

196. በተወሰኑ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሴቶች እና ወንዶችን ቦታ ለመለየት የሚደረግ ጥረት መኖሩን ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው ማቆያዎች ተመልክቷል። ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ የተለየ ድጋፍን በሚመለከት፤ ለሴቶች እና ለሕፃናት ቅድሚያ ተሰጥቶ እርዳታዎች እንደሚከፋፈል እንዲሁም በአንዳንድ ማቆያዎች ለሕፃናት እና ለነፍሰጡር እናቶች የተለየ የምግብ ድጋፍ የሚደረግ ቢሆንም በቂ እና ለሁሉም ተደራሽ አልነበረም። ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ሕፃናት እና ለአረጋውያን የተሟላ ተጨማሪ እርዳታ አለመቅረቡ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተፈናቃዮች ያለባቸውን ችግር አባብሶታል።

197. በትግራይ ኃይሎች ተይዘው የነበሩ ስፍራዎች ተመልሰው በፌደራል እና በክልል የፀጥታ ኃይሎች ቁጥጥር ስር መግባታቸውን ተከትሎ ተፈናቃዮች ወደ መኖሪያቸው መመለስ መጀመራቸውን ኮሚሽኑ ተመልክቷል። ኮሚሽኑ ምርመራ በሚያደርግበት ወቅት በአማራ ክልል በመሐል ሜዳ፣ መንዝ ጌራ

[60] ከፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በየካቲት 16 ቀን 2014 ዓ.ም. የተጻፈ ደብዳቤ፡፡ (አባሪ ቁጥር 12)

ምድር መዘዞ፣ ሸዋ ሮቢት፣ የለን፣ ሰንበቴ፣ አጣዬ፣ ከሚሴ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ሰዎች አብዛኞቹ ኮሚሽኑ ምርመራውን ባደረገበት ወቅት ወደ መኖሪያቸው መመለሳቸውን ለመረዳት ተችሏል። በተመሳሳይ በአፋር ክልልም ከፈንቲ ረሱ ዞን (ዞን 4) ከያሎ፣ አውራ፣ እዋ፣ ጉሊና፣ ቴሩ እና ጭፍራ ወረዳዎች የተፈናቀሉ 124,472 ነዋሪዎች በዲግዲጋ፣ ሂዳሉ፣ ጉራኢይ፣ ነፍቱ፣ መስኪድ፣ በእዋ እና ጭፍራ ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ተጠልለው ይገኙ የነበሩ ተፈናቃዮች ወደ ቀዬአቸው ተመልሰው ነበር። ሆኖም ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ይህ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅት በአፋር ክልል የጦርነቱ ሁኔታ የቀጠለ በመሆኑ የተፈናቃዮች ቁጥር በድጋሚ በከፍተኛ ሁኔታ ሊጨምር እንደሚችል ይገመታል።

198. ተፈናቃዮች ወደ መንደራቸው በሚመለሱበት ወቅት ድጋፍ ለማድረግ የተደረገ ጥረት ቢኖርም በቂ የሚባል አይደለም። የአፋር ክልል መንግሥት እና የሰመራ ዩኒቨርሲቲ 10,000 ለሚሆኑ ተመላሽ ተፈናቃዮች የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታ ያደረጉ ቢሆንም ድጋፉ በቂ አለመሆኑን የክልሉ አደጋ መከላከል እና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ባለሙያዎች አስረድተዋል። በአማራ ክልልም ተፈናቃዮች የተመለሱባቸው ዞኖች አስተዳደሮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታዎችን በተወሰነ መልኩ እንደሚያቀርቡ ለማወቅ ተችሏል።

**ተፅእኖ**

199. ከአፋር እና አማራ ክልሎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች ለከፍተኛ አካላዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሌሎች ጉዳቶች ተዳርገዋል። ከሁለቱም ክልሎች የተፈናቀሉ ሰዎች በመፈናቀሉ ሂደትና ተፈናቅለው በቆዩባቸው ስፍራዎች ላይ በገጠማቸው አስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታዎች ለከፋ ችግሮች ተዳርገው ነበር።

200. ተፈናቃዮች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከመለያየት በተጨማሪ፤ የምግብ፣ የአልባሳት፣ የመኝታ፣ የጤና አገልግሎቶች የመሳሰሉ የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት የተሟላላቸው ባለመሆኑ፣ በተለይም የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ፣ ለሕፃናት፣ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ እና የተሟላ አቅርቦት ባለመኖሩ ልዩ ድጋፍ የሚሹትን የሕብረተሰብ ክፍሎች ችግር ይበልጥ አባብሶታል።

201. ብዙ ተፈናቃዮቹ ወደመኖሪያ አካባቢያቸው በተመለሱበት ወቅትም፤ የመኖሪያ ቤቶቻቸው እና ልዩ ልዩ ንብረታቸው፣ የእርሻ ማሳዎች እንዲሁም የአካባቢያቸው መሰረታዊ አገልግሎት ተቋማት በመዘረፋቸው እና በመውደማቸው ምክንያት ተመላሽ ተፈናቃዮች የምግብ እጥረት፣ የሕክምና አገልግሎት ማጣትን ጨምሮ ለተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋልጠዋል።

**መደምደሚያ**

202. በትግራይ ክልል የነበረው ጦርነት ወደ አጎራባች ክልሎች መስፋፋቱን ተከትሎ በተለይም የትግራይ ኃይሎች በአማራ እና አፋር ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ወራት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች ከቤታቸው ተፈናቅለዋል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት በተፈጠረው የፀጥታ ስጋት እና በትግራይ ኃይሎች በተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እና የንብረት ዝርፊያዎች ነዋሪዎች ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል የፌደራል እና የክልል መንግሥት አካላት ነዋሪዎች ለመፈናቀል አደጋ እንዳይጋለጡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እና ጥበቃ አለማድረጋቸው፣ እንዲሁም ለተፈናቃዮች የተሟላ መጠለያ፣ ደህንነት፣ አስፈላጊ ምግብ፣ ውሃ፣ ልብስ፣ ሕክምና እና የንጽሕና አገልግሎት እንዳልነበረ ኮሚሽኑ በምርመራው ተመልክቷል፡፡

## 7. በንብረት ላይ የተፈጸመ ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ውድመት

**መግቢያ**

203. የኢሰመኮ የምርመራ ቡድን በጦርነቱ ወቅት በሁሉም ተሳታፊ ወገኖች በአፋርና አማራ ክልሎች የተፈጸሙ የንብረት ውድመት፣ ዘረፋ እና ገፈፋ (pillage) ክስተቶችን መርምሯል፡፡ በዚህ ክፍል ኢሰመኮ በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ ምርመራ ባደረገባቸው አካባቢዎች ዝርፊያ፣ ገፈፋ እና ውድመት የተፈጸመባቸው የመንግሥት፣ የንግድ፣ የግል እና ሌሎች ተቋማት ላይ የደረሰውን ጉዳት ይዳስሳል፡፡ ይህ ክፍል በዚህ ሪፖርት ውስጥ በጦርነቱ ሂደት በሲቪል ንብረቶች ላይ ከደረሱ ጉዳቶች እና ከኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና የባሕል መብቶች ጥሰቶች እና መፍትሔ ለመስጠት ከሚደረገው ጥረት ጋር አብሮ የሚታይ ነው፡፡

**የሕግ ማዕቀፍ**

204. የንብረት መብት በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እውቅና ያገኘና ጥበቃ የሚደረግለት መብት ነው፡፡[61] የግጭቱ ሁኔታ ይህን ማድረግ ግድ ካላለ በስተቀር በኃይል ወይም ስልታዊ በሆነ ሁኔታ የግል እና የሕዝብ ንብረቶችን መውሰድም ሆነ በሲቪል ንብረቶች ላይ የኃይል ተግባራት መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡[62] እንደዚህ አይነት የኃይል ተግባራት የጦር ወንጀልን ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

205. ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ለሲቪል ሰዎች ህልውና ጠቃሚ የሆኑ ምግብ፣ የእርሻ ቦታዎች፣ ሰብል ፣ እንስሳት፣ የውሃ መሠረተ-ልማት እና አቅርቦት፣ የሕክምና ቦታዎች እና መጓጓዣዎች፣ ለሰብአዊ እርዳታ ግልጋሎት የታለሙ ቁሳቁሶች፣ ባህላዊ እቃዎች እና ንብረቶች፣ የአምልኮ ቦታዎች፣

[61] Article 14, African Charter on Human and Peoples' Rights; Article 17, Universal Declaration of Human Rights; ICESCR and ICCPR do not expressly guarantee the right to property.
[62] ICRC, Customary IHL Database, Rule 50

አደገኛ ኃይል የያዙ ግድቦችን ወይንም የኒውክሌር ማብላያ ተቋማትን ጥበቃ ያደርጋል። በመሆኑም አንድ ወገን ያለ በቂ ወታደራዊ ምክንያት ይህን መሰል ንብረቶችን (ምግብ ፣ የእርሻ ቦታ፣ ሰብል ፣ እንስሳትን ጨምሮ) ያወደመ ፣ የወሰደ ፣ ያበላሸ፣ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገ እንደሆነ የዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ሕግ ጥሰት ፈጽሟል ማለት ነው።[63]

206. ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ዘረፋንም በግልጽ ይከለክላል። ዘረፋ ለግል ሆነ ለሕዝብ ጥቅም ለማዋል በማሰብ አንድን ንብረት ከባለቤቱ ላይ በኃይል መውሰድን/መውረስ ይመለከታል። የሚዘረፈው ንብረት የግልም የሕዝብም ሊሆን ይችላል። ተንቀሳቃሽ ወይን የማይንቀሳቀስ ንብረትም ሊሆን ይችላል። የዘረፋ ጽንሰ ሃሳብ ከዝርፊያ እና ንጥቂያ ጋር በተወራራሽነት ትርጉም ላይ ይውላል። ይሁን እንጂ ዘረፋ መጠነ-ሰፊ የሆነ ተግባርን የሚመለከት ሲሆን፤ በግል የሥነ-ምግባር ጉድለትም ሆነ በተደራጀ መልኩ የሚፈጸም ዘረፋ የተከለከለ ነው።[64] በውጊያ ኃይል ወይም በጦርነት በማሸነፍም ቢሆን የተያዘን ከተማ ወይንም አካባቢን መዝረፍ የተከለከለ እና የጦር ወንጀልን ሊያቋቁም የሚችል ነው። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ወንጀል ሕግም ይህንን ይከለክላል።[65]

**የምርመራው ግኝቶች**

207. ኢሰመኮ ባደረገው ምርመራ በተለያዩ ጊዜያት በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ እና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በተደራጀ መልኩ የትግራይ ኃይሎች በመንግሥት አስተዳደር ተቋማት፣ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (የጤና ተቋማት፣ የትምርህት ተቋማት ወዘተ) ፣ በግል ንብረቶች እና በንግድ ተቋማት ላይ ዘረፋ፣ ዝርፊያ እና የንብረት ውድመት ፈጽመዋል። በተጨማሪም  በአንዳንድ አካባቢዎች የሕግና ሥርአት መፍረሱን ተከትሎ የተወሰኑ የየአካባቢዎቹ ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎችም በዝርፊያው ተግባር ተሳትፈዋል።

208. በአብዛኛዎቹ ምርመራ በተደረገባቸው አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች ሆነ ተብሎ በታቀደ፣ በተጠና፣ በተደራጀ እና በባለሙያ ጭምር በተደገፈ ስልታዊ የዘረፋና ዝርፊያ ተግባር በተለይ የሕክምና መሳሪያ ቁሳቁስ፣ ማሽኖችን እና የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመዝረፍና በመዝረፍ፣ በመኪና በመጫን ወስደዋል። ምርመራው በተከናወነባቸው የአማራ እና የአፋር ክልሎች የሚገኙ ሆስፒታሎች፣ ቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ እንደዚህ አይነት ዝርፊያዎች ተፈጽሞባቸዋል።

209. የመርሳ፣ የኮምቦልቻ፣ እና የደሴ ሆስፒታሎችን ጨምሮ በተለይም ከሆስፒታሎች እና የሕክምና መስጫ ተቋማት መድኃኒቶችን፣ እንደ ኤክስ ሬይ፤ አልትራ ሳውንድ፤ የደም መመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ ማሽነሪዎች፣ አምቡላንሶች እና ሌሎችም የሕክምና መሳሪያዎች ተዘርፈው ተወስደዋል። በተለይ በሕክምና መሳሪያዎች እና ማሽኖች ላይ የተፈጸመው ዝርፊያ በባለሙያ እየታገዘና ማሽኖቹ በጥንቃቄ እየተፈቱና እየተነቀሉ መወሰዳቸውን ኮሚሽኑ ያገኘው መረጃ ያሳያል። ከፌዴራል ጤና

[63] Article 14, Additional Protocol II
[64] ICRC, Commentary on the Additional Protocols (Geneva, Martinus Nijhoff, 1997), p. 1376.
[65] Article 273, The criminal code of FDRE.

ሚኒስቴር በተሰበሰበ መረጃ መሰረት በአማራ ክልል 40 ሆስፒታሎች፣ 453 ጤና ጣቢያዎች፣ እና 1850 የጤና ኬላዎች (በአጠቃላይ 2343 የጤና ተቋማት)፤ እንዲሁም በአፋር ክልል 2 ሆስፒታሎች፣ 19 ጤና ጣቢያዎች እና 45 የጤና ኬላዎች (በአጠቃላይ 66 የጤና ተቋማት) ላይ ጥቃት፣ ጉዳትና ዝርፊያ በመድረሱ አገልግሎታቸው ተቋርጧል። ከዚህ በተጨማሪም በደሴ ከተማ ይገኝ የነበረ የመድኃኒት ማከማቻና ማሰራጫ እና የደም ባንክ ላይ ጉዳት መድረሱን ከጤና ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያሳያል። የጉዳቶቹ አይነት መጠነኛ ዝርዝር የዚህ ሪፖርት አባሪ የተደረገው የጤና ሚኒስቴር ማስረጃ ላይ ይገኛል።[66]

210. መጠኑ የተለያየ ቢሆንም ይህ ምርመራ በተካሄደባቸው በሁሉም አካባቢዎች ማሽኖች እና መሳሪያዎች በትግራይ ኃይሎች ተዘርፈው የተወሰዱ ሲሆን፣ በአብዛኛው አካባቢዎች በተለይም ዝርፊያ በተፈጸመባቸው ተቋማት የሚገኙ የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች፣ የፋብሪካ ልዩ ልዩ ኬሚካሎች፣ ጄኔሬተሮች፣ ኮምፑዩተሮች፣ የኃይል መቆጣጠሪያዎች፣ ትልልቅ የኤሌክትሪክ እቃዎች፣ የወርክ ሾፕ መሳሪያዎችና እና የቢሮ እቃዎችን ይጨምራሉ። በተወሰኑ ስፍራዎች የኮምፑዩተር ሀርድ ዲስኮች ተነቅለው ተወስደዋል። በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ለጠቅላላ የዩኒቨርስቲው ግቢ በሙሉ አገልግሎት የሚሰጥ ትልቅ ጄኔሬተር የተቀመጠበትን ቤት በማፍረስና ማሽኑን ፈትቶ በመንቀል በትግራይ ኃይሎች ተዘርፎ በመኪና ተጭኖ ተወስዷል። በኮምቦልቻ የሚገኘው የነዳጅ ዴፖ ውስጥ የነበረ 14 ሚሊዮን ሌተር ነዳጅ እና ጋሸና ከተማ ይገኝ የነበረ ለስምንት ወረዳ ሕዝብ ያገለግል የነበረ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ መሳሪያ (Electric Power sub-station) በባለሙያ እገዛ ተፈትቶና ተነቅሎ በተመሳሳይ መልኩ ተዘርፎ ተወስዷል።

211. በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የመንግሥት እና በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የግለሰብ ተሽከርካሪዎች ጭምር በትግራይ ኃይሎች በዝርፊያ ተወስደዋል። ከነዚህም ውስጥ በተለይ አምቡላንሶች እና የጭነት መኪናዎች ይገኙበታል። ከፌዴራል ጤና ሚኒስቴር በተገኘ መረጃ መሰረት በአማራ ክልል 131 አምቡላንሶች እና በአፋር ክልል 29 አምቡላንሶች ተዘርፈዋል ወይም ወድመዋል።[67] በመቄት ወረዳ ንብረትነቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን የሰሜን ወሎ ሀገረ-ስብከት ሊቀ-ጳጳስ የሆነ ቶዮታ ፕራዶ መኪና በትግራይ ኃይሎች የተወሰደ ሲሆን፣ በኮምቦልቻ ከተማ ከሚገኝ የግለሰብ ጋራዥ በጥገና ላይ የነበሩ 12 የመንግሥት እና 7 የግለሰብ መኪኖች መወሰዳቸው፤ ከኮምቦልቻ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሁለት የእሳት አደጋ፣ ሁለት አምቡላንስ እና 11 ፎርክሊፍት መኪናዎች መወሰዳቸው በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

212. የትግራይ ኃይሎች ከኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች ጋር በጋራ በተቆጣጠሯቸው ስፍራዎች በነበሩት የመንግሥት እና የግለሰብ ቤቶች ዝርፊያዎች ላይ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎችም ተሳትፈዋል። ከእነዚህም ውስጥ ቡርቃ ቀበሌ፣ ሰንበቴ ከተማ፣ አጣዬ ከተማዎች ውስጥ የመንግሥት ተቋማት፣ ንግድ ተቋማት እና የግለሰብ ንብረቶች ላይ በተፈጸሙት ዝርፊያዎች የኦነግ ሸኔ አባላትም ተሳትፈዋል፣ የዘረፉትን ንብረቶችም በመኪና ጭነው ወስደዋል።

[66] ከጤና ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እ. ኢ.ት. አ. በየካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. የተጻፈ ደብዳቤ፡፡ (አባሪ ቁጥር 9)
[67] ከጤና ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እ. ኢ.ት. አ. በየካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. የተጻፈ ደብዳቤ፡፡ (አባሪ ቁጥር 9)

213. በሌላ በኩል በተለያዩ ጊዜያት በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ እና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች በተለይም ትግራይ ኃይሎች ስፍራዎቹን በሚቆጣጠሩበት ወይም ለቀው በሚወጡበት ወቅት የሚከሰተውን የሕግና ሥርአት መፍረስ ተከትሎ በየአካባቢው የሚገኙ የተወሰኑ ሰዎች በመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የግለሰብና የንግድ ድርጅቶች ንብረቶች ላይ ስርቆት፣ ዝርፊያ እና ውድመት አድርሰዋል።

214. በአንዳንድ አካባቢዎች ዝርፊያዎቹ የተፈጸሙት ጦርነቱ በፈጠረው የሕግ ማስከበር ክፍተት ሲሆን፤ በአንጻሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ግን የትግራይ ኃይሎች የራሳቸውን ዝርፊያ ከፈጸሙ በኋላ ሌሎች ሰዎች ዝርፊያ እና ውድመት ሲፈጽሙ አካባቢውን ተቆጣጥረው የነበሩት የትግራይ ኃይሎች ሳይከላከሉ ቀርተዋል ወይም በዝምታ ሲመለከቱ ታይተዋል። ከእነዚህም ውስጥ በአማራ ክልል ዛሪማ ወረዳ፣ መዘዞ ንዑስ ወረዳ፣ መርሳ፣ ሀይቅ፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ አጣዬ፣ ሸዋ ሮቢት እና በአፋር ክልል ጭፍራ ከተማ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ሆስፒታሎች እና የግለሰቦችን ቤትና ንብረት ላይ የተፈጸሙ ዝርፊያዎች ይጠቀሳሉ። በዚህ ረገድ በመርሳ ከተማ የከተማውን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፤ሆስፒታሉን፤ ግብርና ኮሌጅን እና ሌሎች ተቋማት ላይ የተፈጸመው ዘረፋ እና በአፋር ክልል ጭፍራ ወረዳ በነዋሪዎች ንብረት እና በፋብሪካ ውስጥ በነበረ የስንዴ እህል ላይ የተፈጸሙት ዝርፊያዎች የሚጠቀሱ ናቸው።

215. በአንዳንድ ስፍራዎች ደግሞ በስፍራው የነበሩ የትግራይ ኃይሎች በተወሰኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ሲፈጸም የነበረውን ዝርፊያ እና ውድመት ሲያበረታቱ እና ሁኔታውን በቪዲዮ ሲቀርጹ ታይተዋል። ለምሳሌ በመርሳ ከተማ የትግራይ ኃይሎች የሚፈልጉትን ከወሰዱ በኋላ ሕብረተሰቡ በዘረፋ ድርጊቱ እንዲሳተፍ አበረታትተው አንዳንድ ነዋሪዎች በዘረፋው ሲሳተፉ ሁኔታውን በቪዲዮ ይቀርጹ ነበር። በተመሳሳይም ደሴ ንጉስ ሚካኤል ቤተመንግሥት (አይጠየፍ አዳራሽ) ለሕንጻው እድሳት ሊውል የነበረ ቀለም፣ ቆርቆሮ እና ሌሎች የቢሮ እቃዎች በትግራይ ኃይሎች ከተወሰደ በኋላ ቀሪውን በሌሎች ሰዎች እንዲዘረፍ አድርገዋል።

216. በዚህ ሁኔታ በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ በሁሉም አካባቢዎች የጉዳቱ መጠን ቢለያይም የማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ ከተፈጸመው ዘረፋ በተጨማሪ የተለያየ መጠንና ዓይነት ያላቸው የንብረት ውድመቶች ደርሰዋል። በተለይም ሆስፒታሎች፣ ጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች፣ የእንስሳት ሕክምና ክሊኒክ፣ የአርብቶ አደር ማሰልጠኛዎች ወንበሮች፣ መደርደሪያዎች፣ በሮች እና መስኮቶች ተሰባብረዋል፤ መድኃኒቶች ጥቅም እንዳይሰጡ ሆነው ተበታትነዋል፤ ልዩ ልዩ የሕክምና እና ሌሎች ቁሳቁሶች ሆነ ተብሎ ወድመዋል።

217. የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸው አንዳንድ አካባቢዎች የዘረፋ እና የንብረት ውድመት በፈጸሙባቸው የሕዝብ አስተዳደር ተቋማትና የግለሰብ ንብረቶች እንዲሁም ለወታደራዊ ካምፕ እና ሌሎች አገልግሎቶች የተጠቀሟቸው ትምህርት ቤቶች፣ ታሪካዊ ስፍራዎች እና ጤና ተቋማት ግድግዳዎች ላይ የስድብ መልዕክቶችን በመፃፍ እና በሕንጻዎች ወለል ላይ፣ ጠረጴዛና መሳቢያዎች እንዲሁም ወንበሮች ላይ በመፀዳዳት ጭምር አበላሽተዋል። በዚህ ረገድ ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል

የደሴ ንጉስ ሚካኤል ቤተመንግሥት (አይጠየፍ አዳራሽ) የንጉስ ኢያሱ እልፍኝ አዳራሽ በሚል በሚጠራው ቤት ላይ እና በአጣዬ ከተማ ጤና ጣቢያ ላይ የደረሱት ብልሽቶች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

218. በሌላ በኩል የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸው አንዳንድ አካባቢዎች በተለይ የመንግስት አስተዳደር ተቋማት ላይ ሆነ ተብሎ ትኩረት ያደረገ ዝርፊያ፣ ውድመት እና ጥቃት ፈጽመዋል፡፡ በተለይም የወረዳ አስተዳድር ቢሮዎች፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ ግብርና ቢሮዎች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ፍርድ ቤቶች ላይ ጥቃቶች ተፈጽመዋል፡፡ በዚህም የመንግሥት ተቋማት መዛግብት፣ ሰነዶች፣ ፋይሎችና ደረሰኞች ተቃጥለዋል፣ ተበታትነዋል ወይም ተወስደዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በአፋር ክልል ያሉ ወረዳ የፍርድ ቤትና የፖሊስ ጣቢያ መዝገቦችን ጨምሮ የተለያዩ መንግስታዊ ሰነዶች ተቃጥለዋል፣ ተቀዳደዋል፤ በፈንቲ ረሱ (ዞን 4) ማረሚያ ቤቶች መምሪያ የታራሚዎች ፋይሎች ተቃጥለዋል፡፡

219. ከጥቅምት 21 እስከ ኅዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም. ባሉ ቀናት በኮምቦልቻ ከተማ ብቻ በ68 የመንግስት እና በ32 የግል ተቋማት ላይ ከፊሉን ሙሉ በሙሉ በማቃጠል፣ ቀሪዎቹን በመሰባበር፣ በከፊል በማውደም እና በመዝረፍ መጠነ ሰፊ የንብረት ጉዳት መድረሱን ክስተቶቹን በቦታው ላይ እያጣሩ የሚገኙ ዓቃብያነ ሕግ እና የከተማው አመራሮች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል፡፡ በቃጠሎ ሙሉ በሙሉ እንዲወድሙ ከተደረጉት ተቋማት መካከል በቀበሌ 3 የሚገኘው ማረሚያ ቤት ይገኝበታል፡፡ በአማራ ክልል ኮምቦልቻ፣ ደሴ፣ ከሚሴ ከተሞች የዞን እና የከተማ የሕዝብ አስተዳደር ሰነዶች በተለይም የወሳኝ ኩነት እና የመሬት ልማት ማኔጅመንት መረጃዎች እንዲጠፉ መደረጉ፣ በሀሙሲት ከተማ የመንግሥት ተቋማት መዛግብት፣ ሰነዶች፣ ፋይሎችና ደረሰኞች መቃጠላቸው፤ በሀይቅ ከተማ የሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ጽ/ቤት፣ የአፈጉባኤ ዋና ጽ/ቤት፣ የቴክኒክና ሞያ ትምህርት ጽ/ቤት ሙሉ ለሙሉ በቃጠሎ መውደሙ፣ በመሀል ሜዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤትን ጨምሮ 6 የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት ከነሰነዳቸው እና ቁሳቁሶች ሙሉ በሙሉ መቃጠላቸው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

220. በአንዳንድ አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች የመንግሥት እና የፀጥታ አካላት አባላት የሆኑ ግለሰቦች ንብረቶች ላይ ሆነ ተብሎ ያነጣጠረ የተለየ ጥቃት ፈጽመዋል፡፡ በሀይቅ ከተማ የፖሊስ አመራር የሆኑ ግለሰብ የግል መኖሪያ ቤት ጥቅምት 13 ቀን 2014 ዓ.ም. በእሳት ተቃጥሎ ሙሉ ለሙሉ እንዲወድም ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በከተማው ቀበሌ 01 የሚኖር የፖሊስ አባል መኖሪያ ቤትም ጥቅምት 14 ቀን 2014 ዓ.ም. ሙሉ ለሙሉ በእሳት ተቃጥሎ እንዲወድም ተደርጓል፡፡

221. ይህ ምርመራ በተመለከታቸው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የበርካታ ሰዎች የንግድ መደብሮች እና የመኖሪያ ቤቶች የሚገኙ ከዕለት የምግብ ፍጆታና አልባሳት ጀምሮ እስከ ንግድ እቃዎች እና ሸቀጦች፤ አላቂ የምግብ ፍጆታዎች፣ እህሎች፣ አትክልቶች፣ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ እንስሳትና ሰብሎች እንዲሁም ገንዘብ በትግራይ ኃይሎች ተዘርፈው ተወስደዋል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ነዋሪዎች ከጦርነቱ ሲሸሹ ቆልፈዋቸው የሄዱትን መኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ተቋማት በጥይት ጭምር በሮቻቸውን በመስበር እየገቡ ተዘርፈዋል፡፡

222. በተለይም በገጠራማ አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች በአርሶ አደር ማሳ ላይ የሚገኙ ሰብሎችን በኃይል በመንጠቅ ተመግበዋል፣ በተመሳሳይ የቤት እንስሳት (በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ላም እና ዶሮ) በኃይል በመንጠቅ አርደው በልተዋል። ከእነዚህም ውስጥ በአማራ ክልል ዛሪማ ንዑስ ወረዳ ጠር አካባቢ በማሳ ላይ ያለ የበቆሎ ሰብል፣ በደባርቅ ወረዳ በቦዛ ቀጠና በአዲ ጋግራ፣ በአዳጋት እና በአብርሃም ቀበሌዎች በኃይል የወሰዱት የቤት እንስሳት (በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ላም እና ዶሮ) እንዲሁም በአፋር ክልል በአብዓላ ወረዳ ከአፋር አርብቶ አደሮች በኃይል የወሰዱት ፍየሎች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። በዳባት ወረዳ፣ በጭና እና በደባርቅ ወረዳ አካባቢዎች የነበሩ የትግራይ ኃይሎች ስፍራዎቹን ለቀው በሚወጡበት ወቅት የቤት እና የጋማ እንስሳትን በጥይት መትተው ገድለዋል።

223. የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በሚገኙ የባንክ ቅርንጫፎች፣ የሸማቾች የሕብረት ስራ ማኅበራት እና በአማራ ክልል የአማራ ብድር እና ቁጠባ ተቋም ላይ ዝርፊያ እና ውድመት ፈጽመዋል። በባንኮች ላይ የተፈጸመውን የዝርፊያ እና ጉዳቱን አይነት እና ዝርዝር የዚህ ሪፖርት አባሪ የተደረገው የኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ማስረጃ ላይ ይገኛል።[68]

224. በሌላ በኩል በተለይም በአማራ ክልል የትግራይ ኃይሎች ተቆጣጥረዋቸው ከነበሩ ስፍራዎች ከለቀቁ በኋላ በአንዳንድ አካባቢዎች ከትግራይ ኃይሎች ጋር ተባብረዋል የተባሉ ሰዎች እና ለደኅነታቸው በመስጋት ከተሞቹን ጥለው በሸሹ የትግራይ ተወላጆች ንብረቶች በልዩ ልዩ የመንግሥት ታጣቂዎችና በተወሰኑ የየአካባቢው ነዋሪ ሰዎች ተዘርፈዋል። በወቅቱ በስፍራው የነበሩ የፌደራል መንግሥት እና የአማራ ክልል የፀጥታ ኃይሎች በቂ ጥበቃና የመከላከል እርምጃ አልወሰዱም። ለምሳሌ በሸዋ ሮቢት ከተማ ውስጥ በግምት የ200 በላይ የትግራይ ተወላጆች መኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ድርጅቶች በተወሰኑ የአካባቢው ነዋሪ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ተዘርፈዋል። እንዲሁም በሰንበቴ ከተማ ጃራ ዋታ የገጠር ቀበሌ የፋኖ አባላት የሆኑ ሰዎች አንዳንድ መኖሪያ ቤቶችን እየሰበሩ መዝረፋቸውን፤ በአጣዬ ከተማም የግለሰቦች ቤቶች ተሰብረው ዘረፋ መፈጸሙን ነዋሪዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

**የጥሰቱ ተፅዕኖ**

225. በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ እና ኢሰመኮ ምርመራ ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በመንግስት፣ በንግድ፣ በግል እና ሌሎች ተቋማት ላይ በተፈጸሙት መጠነ ሰፊ የንብረት ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ውድመቶች፤ በሕዝብ ሀብት ላይ ከደረሰው ጉዳት በተጨማሪ በሲቪል ሰዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፣ የጤና እና የትምህርት መሰረተ ልማት ተጎድቷል፣ የጤና እና የትምህርት ስርአቱ በመስተጓጎል አገልግሎቱ ተቋርጧል።

226. ኮሚሽኑ ምርመራዎቹን ባከናወነበት ወቅት መንግሥት አብዛኛዎቹ የማኅበረሰብ አገልግሎቶች ተቋርጠዋል። በጤና ተቋማት ላይ በደረሰው ውድመትና ዝርፊያ ምክንያት ሰዎች መሰረታዊ የጤና

[68] ከኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ለኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በየካቲት 24 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ፡፡ (አባሪ ቁጥር ፲)

አገልግሎት ማግኘት አልቻሉም። በዚህ ምክንያት እናቶች ከወሊድ ጋር በተያያዘ ሕይወታቸው ማለፉን፣ በድንገተኛ ሕመምና ሕክምና በለመኖሩ ሰዎች መሞታቸውንና ተከታታይ ሕክምና ያላቸው ሰዎችም ሕክምናቸውን እንዳቋረጡ ነዋሪዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። ኢሰመኮ ይህን ምርመራ ባከናወነበት ወቅት የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት በደረሰባቸው ውድመትና ዘረፋ እንዲሁም ለተፈናቃዮችና ለመንግሥት ኃይሎች በካምፕነት እያገለገሉ ስለነበር ወደ መደበኛ ሥራቸው አልተመለሱም ነበር። በምርመራው በተሸፈኑ የከተማም ሆነ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችና ሕፃናት የትምህርት ዕድላቸውን ነፍጓቸዋል። የትግራይ ኃይሎች ተቆጣጥረዋቸው በነበሩ ከተሞች ውስጥ በተለይ እንደ ዞን፣ ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ተቋማት ላይ ከፍተኛ የንብረት እና የሰነዶች ውድመት አድርሰዋል። የወሳኝ ኩነት፣ የመሬት አስተዳደር፣ የፋይናንስ ወዘተ ሰነዶችን ከቀዳደዱና ከበታተኑ በኋላ የሕትመት ማሺን (ፕሪንተር ቶነር) ቀለም በላዩ ላይ በመነስነስ ሆነ ብለው አበላሽተዋል፣ አውድመዋል። በተጨማሪም ፖሊስ ጣቢያዎች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤቶች እና ማረሚያ ቤቶች ላይ ጉዳት በማድረስና በተቋማቱ ውስጥ በነበሩ መዝገቦችና ሰነዶች ላይም ተመሳሳይ ጉዳት በመድረሱ በአጠቃላይ በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን አድርሷል።

227. በሁሉም አካባቢዎች በግለሰብ ንብረቶች ላይ በደረሰው ዝርፊያ እና ውድመት ምክንያት ብዙዎች ንብረታቸውን አጥተዋል፤ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና እንዲሁም ለሥነልቦና ጉዳት ተዳርገዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች የምግብ ክምችቶች በመበላታቸው፣ በመዘረፋቸው እንዲሁም በርካታ ቋሚ እና አላቂ ንብረቶች፤ የቤት እንስሳት፣ የጋማ ከብቶች፣ ገንዘብ፣ እና ሌሎችም ንብረቶች ላይ የገፈፋ፣ የዘረፋ፣ የውድመት ጉዳት ስለደረሰባቸው በርካቶች ለረሃብ፣ ለድህነት፣ ለስደት ተዳርገዋል፣ እንዲሁም እራሳቸውን ለማስተዳደር ባለመቻላቸው እርዳታ ጠባቂ ሆነዋል።

***መደምደሚያ***

228. በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ እና ኢሰመኮ ምርመራ ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በመንግስት፣ በንግድድርጅቶች፣ በግለሰቦች እና ሌሎች ተቋማት ንብረቶች ላይ መጠነ ሰፊ የንብረት ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ውድመቶች ተፈጽመዋል።

229. ለእነዚህ ተግባራት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስዱት የትግራይ ኃይሎች መንግሥት ሲሆኑ በተወሰኑ ቦታዎች የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎችም ተመሳሳይ ዝርፊያ እና ውድመቶችን ፈጽመዋል። እነዚህ ተግባራት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃል-ኪዳኖች ውስጥ ጥበቃ የሚደረግለትን የንብረት መብትን የሚጥሱ ሲሆን፣ ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መብቶች ማለትም የመማር እና የጤና መብቶችን የሚጥሱ ድርጊቶች ናቸው። በተጨማሪም ድርጊቱ በተለይ ስልታዊ በሆነ መንገድ በመፈጸሙና በዓለም ዓቀፍ ሰብአዊነት ሕግ መሠረት የጦር ወንጀልን ሊያቋቁም የሚችል ነው።

## 8. የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ክልከላ

### መግቢያ

230. በትግራይ ክልል የተጀመረው ጦርነት ወደ አማራ እና አፋር ክልሎች መዛመቱን ተከትሎ ከፍተኛ ሰብአዊ ቀውስ አስከትሏል። በግጭቱ ሳቢያ አደጋ ውስጥ የወደቁ የሲቪል ሰዎች ቁጥር በእጅጉ የጨመረ ሲሆን የሰብአዊ እርዳታ ፍላጎት እና አስፈላጊነትም በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በጥር ወር 2014 ዓ.ም መጨረሻ ይፋ ባደረገው መረጃ በትግራይ፣ በአማራ እና አፋር ክልሎች ቢያንስ 9.4 ሚሊዮን ሰዎች አስቸኳይ ሰብአዊ እርዳታ ያስፈልጋቸው ነበር።[69] ኢሰመኮ ባደረጋቸው ምርመራዎች እና ክትትሎች በጦርነቱ ተሳታፊ በነበሩት አካላት የተለያዩ የሰብአዊ አቅርቦት ክልከላዎች መኖራቸውን ለይቷል።

### የሕግ ማዕቀፍ

231. ሰብአዊ እርዳታ ማለት ምግብ-ነክ እና ምግብ-ነክ ያልሆኑ መሰረታዊና (እንደ ምግብ፣ ውሀ፣ ሕክምና ቁሳቁሶች፣ መጠለያ፣ አልባሳት፣ የመኝታና የማብሰያ ቁሳቁሶች፣ ነዳጅ እና የመሳሰሉ) በሕይወት ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ ሰብአዊ ድጋፎችን ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የማቅረብ ሥራን ይጨምራል።[70] በዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት መንግሥታት አስፈላጊ የሆኑ የሰብአዊ እርዳታ ድጋፎችን ለችግር ለተዳረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። በተለይም በግጭት ምክንያት ሰብአዊ ቀውሱ በተባባሰ ጊዜ ሰብአዊ እርዳታዎችን ማሰባሰብ እና ማሳለጥ ይጠበቅባቸዋል።

232. በዚህ መልኩ የሚሰጥ እርዳታ ከአድልዎ የጸዳ፣ ያልአድልዎ የሚዳረስ እና ለሰብአዊ ዓላማ ብቻ ለሚውል መሆን አለበት። ይህን አይነት ሰብአዊ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ለማድረስ፤ የመንግሥትን ፈቃደኝነትና ትብብር እንደሚያስፈልግ የታወቀ ቢሆንም፤ የመንግሥት ፍቃድ ወይም የመተባበር ኃላፊነት በዘፈቀደ የሚከለከል መሆን የለበትም።[71] መንግሥታት በሰብአዊ እርዳታ አቅርቦቶች ላይ የማያስፈልጉ እና ምክንያታዊ ያልሆኑ ክልከላዎችን ከማድረግ መቆጠብ እንዳለባቸው ዓለም አቀፉ የኢኮኖሚያዊ፣ ማኀበራዊ እና የባሕል መብቶች ስምምነት ያስገድዳል። በጦርነት ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎችም በሚቆጣጠሯቸው አካባቢዎች ሰብአዊ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው በተለይ ሲቪል ሰዎች ከአድልዎ ነፃ የሆነ የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦትን መፍቀድ አለባቸው። ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ለሲቪል ሰዎች ህልውና ጠቃሚ የሆኑ ለሰብአዊ እርዳታ ግልጋሎት የታለሙ ቁሳቁሶች ከጥቃት መጠበቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል።

---

[69] UNOCHA- NORTHERN ETHIOPIA - HUMANITARIAN UPDATE Situation Report Last updated: 17 Feb 2022

[70] Article 18 (2) Protocol Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949, and Relating to the Protection of Victims of Non-International Armed Conflicts (Additional Protocol II); Rule 55 International Committee of the Red Cross, Customary International Humanitarian Law Volume I: Rules (ICRC Study on Customary International Humanitarian Law).

[71] ICRC, Customary IHL Database, Rule 55.

233. በማንኛውን አካል የሚፈጸም የሰብአዊ እርዳታ ክልከላ እና በተለይም ሲቪል ሰዎችን ማስራብን እንደ ጦርነት ዘዴ መጠቀም የጦር ወንጀል ሊሆን ሲችል፤ ሲቪል ሰዎችን በከፊል ወይም በሙሉ ለማጥፋት በማሰብ የሚደረግ ግልፅ የሰብአዊ እርዳታ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀልን ሊያቋቁም ይችላል::[72]የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግም በጦርነት ወቅት እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች አስፈላጊ አቅርቦቶችን መከልከልን በወንጀልነት ደንግጓል::[73]

**የምርመራ ግኝቶች**

234. ኢሰመኮ ባደረገው ምርመራ እና ክትትል በትግራይ ክልል እና በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ላይ የተለያዩ ክልከላዎች እንደነበሩ ተመልክቷል። በእርዳታ ሰጪ ተቋማት በኩል ለዚህ የሚሰጠው ዋነኛው ምክንያት በፀጥታ ችግር ምክንያት እርዳታ ለማቅረብ አለመቻሉን ሲሆን፣ በግጭቱ ተሳታፊ በሆኑ ኃይሎች የተደረጉ ክልከላዎችም ይጠቀሳሉ። የትግራይ ክልልን ጨምሮ ጦርነቱ በተስፋፋባቸው ሁሉም አካባቢዎች የስልክ እና ኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጥም ሰብአዊ እርዳታን ለማቅረብ ተጨማሪ እንቅፋት ፈጥሯል።

235. የፌደራል መንግሥት የትግራይ ክልልን አብዛኛው አካባቢዎች ከለቀቀበት ከሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በየብስ ወደ ክልሉ መግቢያ እና መውጫ መንገዶች ተዘግተው ቆይተው የነበረ ሲሆን፤ በአየር የነበረው የሰብአዊ እርዳታም ተቋርጦ ቆይቷል። የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት አየር በረራው ከኅዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ተመልሶ የተጀመረ ሲሆን፣ ከ ኅዳር 14 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በአፋር ክልል ሰመራ ከተማ በኩል የነበረው የየብስ መንገድ ተከፍቶ የነበረ ቢሆንም፤ በድጋሚ በተቀሰቀሰው ጦርነት ምክንያት ከታኅሣሥ 6 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ተቋርጧል።

236. በተባበሩት መንግሥታት መረጃ መሰረት ከሰኔ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በየብስ ወደ ትግራይ መግባት ከነበረበት የሰብአዊ እርዳታ መጠን ማድረስ የተቻለው 9 በመቶ የሚሆነውን ብቻ ነው።[74] በየብስ የነበረው እርዳታ አቅርቦት በአፋር ክልል ውስጥ በነበሩ ኬላዎች እና ክልከላዎች ምክንያትም ተጨማሪ ተግዳሮቶች ገጥመውታል። ወደትግራይ ክልል መድረስ የቻለውን እርዳታም ወደተለያዩ ስፍራዎች ለማሰራጨት ወደ ትግራይ ክልል ለመውሰድ ተፈቅዶ የነበረው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን እና ነዳጅ ወደ ክልሉ ማጓጓዝ ላይ ባለው ክልከላ ምክንያት ከፍተኛ ተግዳሮቶች እንደገጠማቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች ይገልፃሉ። በአንጻሩ የፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በሰጠው መረጃ እስከ ጥር 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ የመንግሥትና የአጋር ድርጅቶችን የእርዳታ ስራ በማስተባበር ከ 8 ሚሊዮን በላይ ለሆኑ በጦርነቱ ምክንያት እርዳታ ላስፈለጋቸው ሰዎች የምግብና ሌሎች አይነት አስፈላጊ እርዳታዎች መቅረቡን፣ በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግሥት እርዳታ እንዳይደርስ የተደረገ ክልከላ አለመኖሩንና ሆኖም በጸጥታ መደፍረስና በጦርነቱ ምክንያት የእርዳታ አቅርቦት መስተጓጎል እንደሚያጋጥም ገልጿል።

[72] Ibid, Rule 156.

[73] Criminal code of the FDRE, Article 270 (K)

[74] UNOCHA- NORTHERN ETHIOPIA - HUMANITARIAN UPDATE Situation Report Last updated: 17 Feb 2022

በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎች ስለተደረገው የእርዳታ ስርጭትና ተያያዥ ጉዳዮች መጠነኛ ዝርዝር የዚህ ሪፖርት አባሪ የተደረገው የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ማብራሪያ ላይ ይገኛል።[75]

237. የአፋርና አማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩበት ወቅት ወደ ስፍራዎቹ መድረስ አስቸጋሪ የነበረ እና በተወሰነ መጠን ሲደርስ የነበረው ሰብአዊ እርዳታ በጣም ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን፤ ለዚህም ዋነኛው ምክንያቶች የጦርነት ሁኔታው፣ የግጭቱ ተሳታፊ ኃይሎች ያስቀመጧቸው ኬላዎች እና በእርዳታ አቅርቦቱ እና ሰራተኞች ደኅንነት ላይ የነበረው ስጋት መሆኑ ይገለጻል። የአፋርና አማራ ክልል አብዛኛዎቹ ስፍራዎች በፌደራል እና በክልሎቹ መንግሥታት ቁጥጥር ስር ከገቡ በኋላ የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት የተሻሻለ ቢሆንም ካለው ፍላጎት አንፃር በቂ እንዳልሆነ ኮሚሽኑ ተገንዝቧል።

**የጥሰቱ ተፅዕኖ**

238. የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ላይ በነበሩ ክልከላዎች ምክንያት ሕይወት አድን እርዳታ ያስፈልጋቸው የነበሩና በግጭቱ በተጎዱ ሁሉም አካባቢዎች የነበሩ ሲቪል ሰዎች ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠዋል። በተለይ በትግራይ ክልል ኮሚሽኑ ባደረገው ክትትል፣ ከልዩ ልዩ ምንጮች በሰበሰበውና በአጣራው መረጃ መሰረት፤ ከፍተኛ የምግብ እጥረት መግጠሙን፣ የልብ፣ የካንሰር፣ የኩላሊት እጥበት፣ የስኳር፣ የደም ግፊት እና የኤች ኣይ ቪ መድኃኒቶችን ጨምሮ በክልሉ በክምችት ደረጃ መኖር ከነበረበት ሕይወት አድን መድኃኒቶች መጠን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱን፤ እንዲሁም በተለይ የኩላሊት እጥበት እና ለካንሰር ሕመምተኞች ይሰጡ የነበሩ አገልግሎቶች መቋረጣቸው ታውቋል። የዓለም ጤና ድርጅት በየካቲት ወር 2014 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ለትግራይ ክልል መድኃኒቶችን ማጓጓዝ የጀመረ ቢሆንም በክልሉ ካለው ከፍተኛ የመድኃኒት እጥረት አንጻር በቂ አለመሆኑን እና በነዳጅ እጥረት ምክንያት ወደ ሁሉም አካባቢዎች ለማሰራጨት መቸገሩን ይገልፃል።[76]

***መደምደሚያ***

239. በትግራይ፣ በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ በጦርነቱ ምክንያት ከፍተኛ ሰብአዊ ቀውስ የተከሰተ ሲሆን፣ የሰብአዊ እርዳታ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በተለይ በአፋር ክልል ጦርነቱ አሁንም በመቀጠሉ ምክንያት በአፋር እና ትግራይ ክልሎች ሰብአዊ እርዳታን ለማድረስ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል። የጦርነቱ እና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታ ለሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት የፈጠረው እንቅፋት የሚታወቅ ቢሆንም፤ በተለይ ወደ ትግራይ ክልል የሚደርሰው ሰብአዊ እርዳታ ላይ በፌደራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት የሚደረጉ አስተዳደራዊና ቢሮክራሲያዊ መስፈርቶችና የስራ ሂደቶች አስፈላጊው እርዳታ በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት እንዳይደርስ እንቅፋት መሆኑም ሊካድ አይችልም።

---

[75] ከፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በየካቲት 16 ቀን 2014 ዓ.ም. የተጻፈ ደብዳቤ። (አባሪ ቁጥር 12)

[76] https://www.who.int/news/item/14-02-2022-lack-of-fuel-prevents-distribution-of-critically-needed-medical-supplies-in-tigray-region

## 9. ኢኮኖሚያዊ፡ ማኅበራዊና የባሕል መብቶች

### መግቢያ

240. ጦርነቱ ከፍተኛ ሰብአዊ ቀውስ ከማስከተሉም በላይ የሰዎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ተጥሰዋል፡፡ በአፋር እና አማራ ክልሎች የሚገኙ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ለምግብ፣ ለውሃ እና ለመጠለያ ችግር የተጋለጡ ከመሆኑም በላይ የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶች ጨምሮ ሌሎች ማኅበራዊ አግልገሎቶችም ተቋርጠዋል፡፡ ይህ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች የሚመለከተው የሪፖርቱ ክፍል፤ በሲቪል ሰዎች እና ንብረት ላይ የደረሱ ጉዳቶች፣ በንብረት ላይ የተፈጸመ ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ውድመት፣ የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ክልከላ እና ሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ከሚመለከቱት የሪፖርቱ ክፍሎች ጋር በጋራ የሚታይ ነው፡፡

### የሕግ ማዕቀፍ

241. ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊና የባሕል መብቶች ስምምነት ፈርማ ያፀደቀች ሀገር ስትሆን፣ በስምምነቱ የተካተቱትን መብቶች ለማክበርና ለማሟላት፤ መንግሥት ያለው ሀብት በሚፈቅደው መጠን በመጠቀም ደረጃ በደረጃ እውን የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ እነዚህ መብቶች የመስራት መብት፤ የማኅበራዊ ደህንነት፤ በቂ የኑሮ ደረጃ (በቂ ምግብ፤ ልብስ፤ መኖሪያ)፣ ሊደረስበት የሚችል ከፍተኛው አካላዊ እና አዕምሮአዊ ጤና እና ትምህርትን የማግኘት መብቶችን ያካትታሉ፡፡

242. ሀገራት የማኅበራዊ፤ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መብቶችን ወደኋላ የሚመልሱ እርምጃዎችን ከመውሰድ መቆጠብ እንዳለባቸውም በስምምነቱ ተደንግጓል፡፡ይህ ክልከላ በጦርነትም ሆነ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅትም ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን መንግሥታት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መብቶቹን ከመጣስ መቆጠብ እና በሌላ ሶስተኛ ወገን (የታጠቁ ቡድኖችን ጨምሮ) እንዳይጣሱ መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ [77] የትጥቅ ግጭት በማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መብቶች ላይ ከፍ ያለ ተግዳሮት የሚፈጥር ቢሆንም ሃገራት ለመብቶቹ መከበር ቅድሚያ በመስጠት ቢያንስ ዋነኞቹ መብቶች እንዲከበሩና የሰብአዊ እርዳታና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲዳረሱ የሚቻላቸውን ሁሉ የማድረግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

243. በተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግጋት የተካተቱ ድንጋጌዎች የሲቪል ቁሶችና መሰረተ ልማትን ከጥቃት መጠበቅ፤ ሲቪሎችን ማስራብን እንደ ጦር ዘዴ የመጠቀም ክልከላ እና ለሲቪሎች አስፈላጊ የሆኑ እንደ ምግብ፤ ሰብሎችና የሲቪል መሰረተ ልማትን የማጥቃት ክልከላዎችን የያዙ ሲሆኑ፤ እነዚህም የትምህርት፤ የጤና፤ የምግብ፤ የመኖሪያ ቤት እና ውሃ የማግኘት መብቶችን መጠበቅ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በትጥቅ ግጭት ውስጥ የሚሳተፉ የታጠቁ ቡድኖች

[77] Report of the United Nations High Commissioner for Human Rights, E/2015/59, para 23-26.

ላይ ጭምር ሃላፊነት የሚጥሉ ናቸው::[78] በመሆኑም ታጣቂ ኃይሎች የተጠቀሱትን መብቶች የማክበርና ሲቪል ሰዎችን የመጠበቅ ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል::

## የምርመራው ግኝቶች

### የምግብ መብት

244. ኢሰመኮ ባደረገው ምርመራ በተለያዩ ጊዜያት በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ እና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ የአማራ እና አፋር ክልል አካባቢዎች አላቂ የምግብ ፍጆታዎች፣ እህሎች፣ የቤት ውስጥ እንስሳትና ሰብሎች እንዲሁም ገንዘብ በመዝረፋቸው፣ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች የአርሶ አደር ማሳዎች ጭምር በጦርነቱ ምክንያት በመውደማቸው ምክንያት ሰዎች ለምግብ እጥረት ተጋልጠዋል::

245. የተባበሩት መንግሥታት የአለም ምግብ ድርጅት በጥር ወር 2014 ዓ.ም ባወጣው መረጃ መሰረት በትግራይ ክልል ብቻ 40 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ለከፍተኛ የምግብ እጥረት ተጋልጧል:: በአማራ ክልል የምግብ እጥረት በ5 ወራት ብቻ አምስት እጥፍ ሲያድግ 14 በመቶ የሚሆኑ የክልሉ ሕፃናት ለምግብ እጥረት ተጋልጠዋል:: በአፋር ከአምስት ዓመት በታች በሆኑ ሕፃናት ላይ የታየው የምግብ እጥረት ሁኔታ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ መሆኑን አመላክቷል::[79]

246. በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች የባንክ እና የገበያ አገልግሎቶች በመቋረጣቸው ምክንያት፤ ሰዎች በገንዘባቸውም ምግብ ከገበያ መግዛት አልቻሉም:: ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው በየመጠለያው ውስጥ ያሉ ተፈናቃዮችም ከመንግሥት እና ከተለያዩ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የሚቀርብላቸው የምግብ አቅርቦት በቂ ባለመሆኑ ለምግብ እጥረት ተጋልጠዋል::

### የጤና መብት

247. በዚህ ሪፖርት በዝርዝር እንደተመለከተው፤ በአማራ እና በአፋር ክልሎች በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ አካባቢዎች የሚገኙ የጤና ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል:: ጤና ጣቢያዎች እና ሆስፒታሎች በትግራይ ኃይሎች ተዘርፈዋል፣ ወድመዋል እንዲሁም የሕክምና ቁሳቁሶች እና መድኃኒቶች ተዘርፈው ተወስደዋል:: በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ የጤና ተቋማት አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ደረጃ የወደሙ ሲሆን በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙት ተቋማት በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት አስፈላጊ የሆነ የጤና አገልግሎት ለማቋረጥ ተገድደዋል::[80]

[78] ICRC, Customary IHL Database, Rule 55.

[79] https://www.wfp.org/news/severe-hunger-tightens-grip-northern-ethiopia

[80] የጤና ሚኒስቴር በጦርነቱ የወደሙ የጤና ተቋማትን አስመልክቶ ለኮሚሽኑ በሰጠው መረጃ “በአማራ ክልል 1850 የጤና ኬላዎች፣ 453 የጤና ጣቢያዎች እና 40 ሆስፒታሎች እንዲሁም በአፋር ክልል 45 የጤና ኬላዎች፣ 19 የጤና ጣቢያዎች እና 2 ሆስፒታሎች ላይ በደረሰ ጉዳት አገልግሎት ማቋረጣቸውን ገልጿል።

### የትምህርት መብት

248. በጦርነቱ በተጎዱ የአማራ፣ የአፋር እና የትግራይ ክልሎች አካባቢዎች የትምህርት አገልግሎት በከፍተኛ ሁኔታ ተስተጓጉሏል። ኮሚሽኑ በዚህ ምርመራው በሸፈናቸው የአማራ እና አፋር ክልል አካባቢዎች በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። ከትምህርት ሚኒስቴር በተገኘ መረጃ መሰረት በአማራ ክልል 1,896,819 እና በአፋር ክልል 49,697 ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጭ ሲሆኑ 116,939 መምህራን በአማራ እና 4,376 በአፋር ተፈናቅለዋል። በአጠቃላይ 1,946,516 ተማሪዎች እና 121,315 መምህራን ተፈናቅለዋል። በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ወልድያ፤ ወሎ እና መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲዎች) በአጠቃላይ 46,792 ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጭ ሲሆኑ፤ 3,682 መምህራን እና 3,193 የአስተዳደር ሰራተኞች ተፈናቅለዋል። በተለይም በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች ትምህርት ቤቶችን እንደ ካምፕ በመጠቀማቸው ምክንያት የትምህርት መሰረተ ልማቶች ወድመዋል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች፣ የቴሌቪዥን ፕላዝማ ስክሪኖች እና ሌሎች ንብረቶች በትግራይ ኃይሎች ተዘርፈው የተወሰዱ ሲሆን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች አገልግሎት በማይሰጡበት ደረጃ ሆነ ተብሎ ተሰባብረዋል፣ ወድመዋል፣ ተቃጥለዋል።

### መሰረታዊ አገልግሎቶች መቋረጥ

249. ጦርነቱ በተስፋፋባቸው የአማራ እና አፋር ክልል አካባቢዎች መብራት፣ ኢንተርኔት፣ የስልክ፣ የባንክ እና የትራንስፖርት አገልግሎቶች ተቋርጠው መቆየታቸው ከላይ በተጠቀሱት የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ላይ የነበረውን ጥሰት አባብሶታል። እነዚህ አገልግሎቶች በትግራይ ክልል አሁንም ድረስ እንደተቋረጡ ናቸው። በአማራ እና አፋር ክልሎች በትግራይ ኃይሎች ተይዘው የነበሩት አካባቢዎች በፌደራል እና በክልሎቹ ቁጥጥር ስር ከተመለሱ በኋላ አገልግሎቶቹን ለመመለስ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎች በመሰረተ ልማቶቹ ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት አገልግሎቶቹን ለመመለስ ተግዳሮቶች ተፈጥረዋል።

250. በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማን ጨምሮ በአንዳንድ የክልሉ ቦታዎች የተወሰነ የኤሌትሪክ ኃይል አገልግሎት የተመለሰ ቢሆንም በክልሉ ከፍተኛ የምግብና የገንዘብ እጥረት መከሰቱን፣ የምግብና ሌሎች መሰረታዊ አቅርቦቶች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩን፣ እንዲሁም የነዳጅ አቅርቦትና የትራንስፖርት አገልግሎት ውስን ስለሆነ ሰዎች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ መቸገራቸውን ለማወቅ ተችሏል።

---

በተጨማሪም ጉዳት በደረሰባቸው ጤና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሕክምና መሳሪያዎች፣ መድኃኒት፣ የቢሮ እቃዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳትና ስርቆት እንደደረሰ በመስክ ምልከታ እና ከተለያዩ የዳሰሳ ጥናቶች መረዳቱን አሳውቋል። በተጨማሪም የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን አስመልክቶ ጉዳት የደረሰባቸውን ተቋማት ከሌሎች በሥራ ላይ ከሚገኙ የፌዴራል እና ክልል ተቋማት ጋር በማስተሳሰር እና ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በቅንጅት በመስራት 36 ሆስፒታሎችን፣ 290 የጤና ጣቢያዎችን እና 890 በላይ የጤና ኬላዎችን መሰረታዊ የሆኑ የሕክምና አገልግሎት ማስጀመር መቻሉን ገልጿል። ከጤና ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በየካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. የተጻፈ ደብዳቤ፡፡ (አባሪ ቁጥር 9)

**የጥሰቱ ተፅዕኖ**

251. የትግራይ ኃይሎች ከሐምሌ 2013 ጀምሮ የአማራ እና አፋር ክልሎችን የተለያዩ አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ጊዜያት በመንግሥት ተቋማት እና በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። ። በነዋሪዎች የመኖርያ ቤቶች፤ እርሻዎች እና የቤት እንስሳት ላይ ቡድኑ ባደረሰው ዝርፊያና ውድመት ነዋሪዎቹን ለመጠለያና ለምግብ ችግር አጋልጧቸዋል። በተለይም በጤና እና ትምህርት ተቋማት ላይ በደረሰው ዝርፊያ፤ ውድመት እና ቃጠሎ፤ ሰዎች የጤና እና ትምህርት አገልግሎት ማግኘት እንዳይችሉ ያደረገ ሲሆን በርካታ ነፍሰጡር እናቶች በሕክምና እጦት ሕይወታቸው አልፏል። ለአብነትም በአማራ ክልል መቄት ወረዳ ሸሆድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በወረዳው የሚገኝ ብቸኛ ሆስፒታል ሲሆን በደረሰበት ሰፊ ዘረፋ እና ውድመት ምክንያት አገልግሎት መስጠት በማቆሙ በወረዳው 8 ነፍሰጡር እናቶች ሕይወታቸው አልፏል።

252. ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል ባደረገው ክትትል በሰበሰው መረጃ መሰረትም በክልሉ የሚገኙ በተለይ ሕፃናት እና አጥቢ እናቶች ለከፍተኛ የምግብ እጥረት እና እጦት ተጋልጠዋል፣በምግብ እጥረት የሰዎች ሕይወት አደጋ ላይ መውደቁ ተነግሯል፣ የልብ፣ የካንሰር፣ የኩላሊት እጥበት፣ የስኳር፣ የደም ግፊት እና የኤች ኣይ ቪ መድኃኒቶችን ጨምሮ በክልሉ በክምችት ደረጃ መኖር ከነበረበት የሕይወት አድን መድኃኒት መጠን እጅግ በጣም መቀነሱ እና የኩላሊት እጥበትና ለካንሰር ሕመምተኞች ይሰጡ የነበሩ አገልግሎቶች ሙሉ ለሙሉ መቋረጡ ታውቋል።

**መደምደሚያ**

253. በትግራይ፣ በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ በጦርነቱ ምክንያት በሰዎች የጤና መብት፣ የትምህርት መብት እና መሰረታዊ አግልግሎቶች የማግኘት መብት ላይ ጥሰቶች ተፈጽመዋል። የትግራይ ኃይሎች ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በአማራ እና አፋር ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎችን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ወራት በመንግሥት ተቋማት፣ በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና በግለሰቦች ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። በዚህም ምክንያት የሰዎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ተጥሰዋል። በእነዚህ ክልሎች የሚገኙ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ለምግብ፣ ለውሃ እና ለመጠለያ ችግር የተጋለጡ ከመሆኑም በላይ የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶች ጨምሮ ማኅበራዊ አገልገሎቶች ተቋርጠዋል። በጦርነቱ ወቅት በሁሉም አካባቢዎች የነበረው የመብራት፣ የስልክ እና የባንክ አገልግሎቶች መቋረጥ በሰዎች መብቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳደረ ሲሆን ሰዎች ራሳቸውን ለማስተዳደር በሚያስችሉ የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ ባለመቻላቸው ለከፍተኛ ጉዳት ተዳርገዋል።ይህም በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃል-ኪዳኖች ውስጥ ጥበቃ የሚደረግላቸውን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶችን የሚጥስ ድርጊት ነው።

## 10.በሕፃናት ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶች

### መግቢያ

254. ሕፃናት በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች ለሞት፣ ለአካል እና ለሥነ ልቦና ጉዳት ተጋልጠዋል፣ የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች በመውደማቸው የጤና፣ የትምህርት እና በቂ የኑሮ ሁኔታ የማግኘት መብቶቻቸው ተጥሰዋል። ወላጆቻቸው እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት ላይ የተፈጸሙ ግድያዎች፣ ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃቶች፣ የአካል ጉዳቶች፣ እንዲሁም በርካታ ሲቪል ሰዎች በጦርነቱን ምክንያት የተፈናቀሉ በመሆኑ ካስከተለው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነልቦና ጉዳት በተጨማሪ፤ ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸው ሊያገኙት ይገባ የነበረውን ጥበቃ እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል።

255. በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተፈጸሙ ሲቪል ሰዎችን ያልለዩ እና ጥንቃቄ ያልተደረገባቸው የከባድ መሳሪያ ጥቃቶች፣ ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎች፣ የጭካኔ እና የማሰቃየት ድርጊቶች፣ የፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች፣ ከሕግ አግባብ ውጪ እስራቶች እንዲሁም መፈናቀልን የመሳሰሉ ከባድ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ሁሉ ሕፃናትንም ተጠቂ ያደረጉ ነበሩ።

### የሕግ ማዕቀፍ

256. ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነትን እና የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተርን በማፅደቅ የሀገሪቱ የሕግ አካል ያደረገች ሲሆን ሁለቱም ስምምነቶች ለሕፃናት በሕይወት የመኖር፣ የጤና፣ የትምህርት፣ በቂ የኑሮ ደረጃ እና የማደግ መብቶቻቸውን ጨምሮ የተለያዩ የሕፃናትን መብቶችን ያረጋገጡ ናቸው። የሕፃናት መብቶች ስምምነት እንዲሁም የአፍሪካ ሕፃናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር አራት መሠረታዊ መርሆዎች ያላቸው ሲሆኑ እነዚህም ከአድሎ የመጠበቅ መብት፣ ለሕፃናት ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፣ በሕይወት የመኖርና የእድገት መብት ፣ ሐሳብን የመግለጽ እና የተሳትፎ መብቶች ናቸው። መርሆዎቹ የስምምነቶቹን ተግባራዊነት እና ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ይረዳሉ።

257. የዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነት በግጭት ወቅት መንግሥታት ለተጎዱ ሕፃናት ጥበቃ እና እንክብካቤን ለማድረግ የሚያስችል አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይደነግጋል። [81] ኢትዮጵያም ከዓለም አቀፉ የሕፃናት መብቶች ስምምነት በተጓዳኝ የሕፃናትን ተሳትፎ በሚመለከት የተዘጋጀው የአማራጭ ፕሮቶኮል አባል እንደመሆኗ መጠን ከ18 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት በጦርነት ውስጥ ተሳታፊ እንዳይሆኑና ለጦርነት እንዳይመለመሉ ሁሉንም አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት አለባት። [82]

[81] CRC, Article 38(4)
[82] OP-CRC-AC, Articles 1 ,4(1) and (2)

258. የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ኮሚቴ በግጭት የተጎዱ ሕፃናትን ጥበቃ እና እንክብካቤን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን መለኪያዎች ያስቀመጠ ሲሆን አስፈላጊ እንክብካቤ እና የእርዳታ አቅርቦትን ማረጋገጥ፣ ከማሰቃየት፣ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኛ አያያዝ መጠበቅ፣ የሕፃናትን ባህላዊ ሕይወት መጠበቅ እንዲሁም በግጭት ውስጥ ላሉ ሕፃናት የሰብአዊ እርዳታ ተደራሽነትን ማረጋገጥ ከመለኪያዎቹ መካከል ይጠቀሳሉ::[83] በተጨማሪም በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መሰረት ሁሉም ዓለም አቀፍ ያልሆኑ ግጭቶች ውስጥ ያሉ ወገኖች ሕፃናት የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና እርዳታ የመስጠት ግዴታ አለባቸው:: [84]

**የምርመራው ግኝቶች**

259. ጦርነቱ በተካሄደባቸው እና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው የትግራይ፣ አማራ እና አፋር ክልል አካባቢዎች ሕፃናት ሰፊ የሆነ የመብት ጥሰት ደርሶባቸዋል:: ሕጻናት ተገድለዋል፤ ፆታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች ተፈጽመውባቸዋል፤ ያለ ተገቢ ጥንቃቄ በተዋጊ ኃይሎች በተተኮሱ ከባድ መሳሪያዎች፣ የአየር እና የድሮን ድብደባዎች ሕይወታቸውን እና አካላቸውን አጥተዋል ወይም የቅርብ ቤተሰቦቻቸው የነዚህ ድርጊቶች ሰለባ ሲሆኑ በቅርብ በመመልከታቸው ለከፍተኛ የሥነልቦና ጉዳት ተዳርገዋል::

260. በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን በያሎ ወረዳ ዋና ከተማ በሆነችው ጎቢዶራ ሐምሌ 9 ቀን 2013 ዓ.ም. በትግራይ ኃይሎች ወደ ከተማዋ በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ በመኖሪያ ቤታቸው የነበሩ 3 ሰዎች (አንድ የ85 ዓመት አዛውንት እና አንድ አራስ እናት ከነልጇ) መገደላቸውን የተጎጂ ቤተሰቦች እና ሌሎች ምስክሮች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል:: በተመሳሳይ በጋሊኮማ ቀበሌ የትግራይ ኃይሎች ሲቪል ሰዎችን ባልለየ መንገድ በፈጸሙት ጥቃት ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ዲግዲጋ ጤና ጣቢያ ለሕክምና ከሄዱ ሰዎች ውስጥ 68 የሞቱ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 27 ዕድሜያቸው ከ2-15 ዓመት የሆኑ ሕፃናት መሆናቸውን እንዲሁም በዚሁ ጥቃት ምክንያት ለሕክምና እርዳታ ወደ ዱብቲ አጠቃላይ ሆስፒታል ሐምሌ 29 እና 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ከሄዱ ሰዎች መካከል 8 ሰዎች ሲሞቱ ከሟቾች ውስጥ አንድ የዘጠኝ ዓመት ሕፃን እንደሚገኝበት የሕክምና ባለሙያዎች ገልጸዋል:: በአጠቃላይ በጋሊኮማ ቀበሌ በደረሰ ጥቃት ከሞቱት 107 ሰዎች ውስጥ 34ቱ ሕፃናት ናቸው::

261. የትግራይ ኃይሎች በቁጥጥራቸው ስር በነበሩ አካባቢዎች ሕፃናትን ተኩሰው መግደላቸውን የምርመራው ግኝቶች አሳይተዋል:: ለምሳሌ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት አካባበቢ በአፋር ክልል ካሳጊታ ከተማ አትኮማ አካባቢ አንድ የዘጠኝ ዓመት ሕፃን እና የ18 ዓመት ልጅ ውሃ ለመቅዳት ወደ አስኤላ ወንዝ በሄዱበት በትግራይ ኃይሎች ተገድለዋል:: ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የዓይን እማኝ እንደገለጹት ልጆቹ ውሃ እየቀዱ እያሉ ሶስት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች አንደኛዋን ሕፃን አንገቷ ላይ ሁለተኛዋን ደግሞ በግንባሯ ላይ በጥይት በመምታት ገድለዋቸዋል::

[83] UN Committee on the Right of the Child, Report of the second session, UN Doc. CRC/C/10, 19 October 1992, § 73.
[84] Additional Protocol II, Article 4(3).

262. በአማራ ክልል በዳባት ወረዳ፣ ጭና ቀበሌ በሕፃናት ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶችን የሚያሳዩ መረጃዎችን ኮሚሽኑ ለማግኘት ችሏል፡፡ በግጭቱ ቤተሰቦቿን ያጣች ሴት ለኮሚሽኑ ስትገልፅ የአዕምሮ ጭንቀትና የጤና ችግር ያለባት ልጇ ሕፃን ልጅ እንደያዘች በጦርነቱ ተረብሻ ከቤት እንደወጣችና ከያዘችው የ11 ወር ሕፃን ጋር በጥይት ተገድላ በሜዳ ወድቃ እንደተገኘች ተናግራለች፡፡

263. የተጎጂ ቤተሰብ እና የዓይን እማኝ የሆኑ የጭና ቀበሌ ነዋሪ ለኮሚሽኑ እንዳስረዱት ባለቤታቸውን ቤታቸው በር ላይ በጥይት መተው ከገደሉ በኋላ አስከሬኑ ለሦስት ቀናት አቆይተው በመጨረሻም የ7 ዓመት ሕፃን ወንድ ልጃቸውን "ይህ አድጎ ነው የሚወጋን" በማለት ሕፃኑን ገድለውት የሄዱ መሆኑን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

264. በጦርነቱ ተሳታፊ የነበሩ ሌሎች ተዋጊ ኃይሎችም በተለያዩ ምክንያቶች በሲቪል ሰዎች ላይ በወሰዷቸው የኃይል እርጃዎች ሕፃናት ላይ ሞት እና የአካል ጉዳትን አስከትለዋል፡፡ ለአብነት ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡00 ሰዓት አካባቢ የትግራይ ኃይሎች የዳቦ ከተማን ለቀው መውጣታቸውን ተከትሎ የአማራ ልዩ ኃይል አባላት በከተማዋ ዙሪያ የነበሩ ቤቶችን በመዞር ሲፈትሹ፤ ቤቷን ዘግታ እና ሕፃን ልጅ ይዛ የተቀመጠች እንዲት እናት ላይ "ታጣቂዎችን ቀልባችኋል" በሚል ቤቷ ላይ በመተኮሳቸው፤ እናትየውን ግራ እግር ላይ እንዲሁም ህጻኗን የግራ እጅ በመምታት ያቆሰላቸው ሲሆን ሕፃኗ በሕክምና ማጣት ደም ፈሷት ሕይወቷ አልፏል፡፡

265. ጦርነቱ በበርካታ አካባቢዎች በከተሞች እና በመኖሪያ አካባቢ በመካሔዱ ሕፃናት በተዋጊ ኃይሎች ተዋጊዎችን እና ሲቪል ሰዎችን ባልለየ መንገድ በተፈጸሙ የከባድ መሳሪያ ጥቃቶችም ሰለባ ሆነዋል፡፡ በአማራ ክልል አርቢት ከተማ 017 ቀበሌ ጥቅምት 3 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት በሲቪል ሰዎች መኖሪያ ቤት አቅራቢያ ተቆፍረው የነበሩ የትግራይ ኃይሎች ምሽጎችን ለመምታት መንግሥት በመከላከያ ሠራዊት ከገረገራ አቅጣጫ የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ እድሜያቸው ከ2 እስከ 4 ዓመት የሚሆናቸው 3 ሕፃናትን ጨምሮ በቤቱ ውስጥ የነበሩ ሰባት ሰዎች ሞተዋል፡፡ በተመሳሳይ በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ሐሙሲት ከተማ ኅዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ገደማ መንግሥት በመከላከያ ሠራዊት የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ የ2 ዓመት ሕፃን እና አባት ሲገደሉ ሌሎች ሁለት የቤተሰቡ አባላት ደግሞ ቆስለዋል፡፡ በዚሁ ከተማ ኅዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም. ቀትር አካባቢ በመኖሪያ ቤት ላይ ያረፈ ከባድ መሳሪያ የ5 ዓመት እና የ16 ዓመት እህትማማቾች ሕፃናትን ገድሏል፡፡ በአፋር ክልል ጭፍራ ወረዳ አስኮማ ቀበሌ ቡልቡላ ጃራ ( አንዳ ጃራ) መንደር ላይ ጥቅምት 6 ቀን 2014 ዓ.ም. ጠዋት 4፡00 ሰዓት አካባቢ የትግራይ ኃይሎች በተኮሱት ከባድ መሳሪያ የ10 ዓመት ሕፃን በከባድ መሳሪያው ፍንጣሪ ሰውነቷ ተቆራርጦ ሞታለች፤ እንዲሁም አንዲት ሌላ ሴት እግሯ በፍንጣሪው ተመትቶ የግራ እግሯ አጥንት ደቅቆ ማየቱን ኮሚሽኑ ያነጋገረው ነዋሪ ገልጿል፡፡ ምስክሩ ከባድ መሳሪያው በስፍራው ከመውደቁ በፊት መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት ከጭፍራ ከተማ አፈግፍጎ በግምት በ8 ኪ.ሜ. እርቀት ላይ ይገኝ እንደነበር አስረድቷል፡፡

266. በጦርነቱ ምክንያት ሕፃናት ኢሰብአዊ የሆነ አያያዝ እና የወሲባዊ ጥቃቶች ሰለባ ሆነዋል፣ ወይም ወላጆቻቸው እና የቅርብ ቤተሰቦቻቸው ሕፃናቱ ፊት አስገድዶ መድፈር ድርጊት ሲፈጸምባቸው በመመልከታቸው ለከፍተኛ የሥነ ልቦና ጉዳት ተዳርገዋል። ኮሚሽኑ ምርመራ ባካሄደባቸው አካባቢዎች በሕፃናት ላይ ወሲባዊ ጥቃትን የፈጸሙት በዋናነት የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ናቸው። በወልዲያ ከተማ ኮሚሽኑ ያነጋገራት አንዲት ነዋሪ እንደገለጸችው በነሐሴ 7 ቀን 2013 ዓ.ም. ከሌሊቱ 6፡00 ሰዓት ሲሆን በርካታ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ወደ መኖሪያ ግቢዋ ከገቡ በኃላ ከርሷ ጋር ተኝታ የነበረችን እድሜዋ በግምት 14-16 የሚሆናትን የጎረቤቷን እህት በማስነሳት በግቢ ውስጥ የነበረ ሌላ ቤት በመውሰድ አስገድደው እንደደፈሯት ገልጻለች። ቀጥሎ የተከሰተውን ስታስረዳ፦

*“አንዱ ታጣቂ ከእኔ ቤት በመቅረት ቤቱን ዘጋብኝ ምን ልታደርግ ነው? ስለው አንቺ የወታደር ሚስት ነሽ ስለዚህ የምፈልገውን ነገር ካላደረግሽ እገልሻለሁ ሲለኝ እኔና የሶስት ዓመቱ ወንድ ልጄ ጮህን። ልጄም እናቴን አትግደልብኝ እያለ ያለቅስ ነበር ነገር ግን ታጣቂው ደበደበኝ፤ ጉሮሮየን አንቆ መሬት ላይ ጣለኝ መሳርያውን በማቀባበል አንቺንም ልጅሽንም ከዚህ ነው ለቃቅሚያችሁ ነው የምሔደው አለኝ። እባክህን ጥቁር ልብሴን እንኳ አላወለቅኩም እናት የለህም? እህት የለህም? ብየ ብለምነውም እምቢ ስላለኝ ልጄም እዚያው እያየ ስለነበረ ልጄን ይገድልብኛል ብዬ እሱን ለማትረፍ ስል ተሸነፍኩ። አስገድዶ ከደፈረኝ በኋላ ወጥቶ ሲሄድ ከውጭ ሌሎች ብዙ ታጣቂዎች ጋር ያወራ ስለነበር በተጨማሪ ሌሎች መጥተው ተጨማሪ ጥቃት ያደርሱብኛል ብየ ልጄን አንጠልጥዬ ወጥቼ ጊዬርጊስ አካባቢ በሚገኝ ጫካ ውስጥ አደርኩ።” ብላለች።*

267. በአማራ ክልል በዳባት ወረዳ ጭና ቀበሌ የ6ኛ ክፍል ተማሪ የሆነች የ15 ዓመት ታዳጊ ላይ በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች የአስገድዶ መድፈር ጥቃት እንደተፈጸመባት ኮሚሽኑ ከተጎጂዋ ሕፃን ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ እና የሕክምና ማስረጃ ለማወቅ ችሏል። በድብ ባህር ንዑስ ወረዳ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባት የ14 ዓመት ታዳጊ ጥቃቱ የተፈጸመባትን ቀን እንደማታስታውሰው ነገር ግን እንጨት ለመልቀም በሄደችበት ወቅት ሁለት ነጭ በአረንጓዴ የወታደር ደንብ ልብስ የለበሱ፣ የታጠቁና በትግርኛ ቋንቋ የሚያወሩ ሰዎች ወደ እሷ መጥተው አንደኛው የአስገድዶ መድፈር ጥቃት እንደፈጸመባት እና ጥቃቱን ሲፈፅም በጥፊ መቷት *“የእናንተ ወታደሮች የእኛን እናቶችና እህቶች ደፍረዋል፤ ስለዚህ እናንተም መደፈር አለባችሁ”* እንዳላት ለኮሚሽኑ ገልፃለች። ጥቃቱ ከተፈጸመባት በኃላ ለረጅም ሰዓት መነሳት አቅቷት ጫካ ውስጥ ቆይታ እንደነበር እና ጥቃቱ ከተፈጸመባት በኃላ ለከፍተኛ ሕመም እና የስነ ልቦና ጭንቀት መዳረጓን ለኮሚሽኑ ገልፃለች።

268. ጦርነት በተካሄደባቸው አካባቢዎች በትምህርት እና ጤና ተቋማት ላይ በተለይ በትግራይ ኃይሎች አማካኝነት በደረሰው ከፍተኛ ዘረፋ እና ውድመት ሳቢያ የመማር እና የጤና አገልግሎቶች በመቋረጣቸውም በሕጻናት መብቶች ላይ ጉዳት ደርሷል። ሕፃናት በጦርነቱምክንያት ለመፈናቀል ተገድደዋል። ተፈናቅለው በቆዩባቸው ስፍራዎች በመንግሥትም ሆነ በሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች

ይቀርብ የነበረው እርዳታ የሕጻናትን ልዩ ፍላጎቶች ስለማያሟላ አጥጋቢ ያልነበረ መሆኑን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል።

**የጥሰቱ ተፅዕኖ**

269. በጦርነቱ ውስጥ የተፈጸሙ በርካታ ጥሰቶች በሕፃናት ላይ ከፍተኛ እና ዘርፈ-ብዙ ጉዳትን አስከትሏል። እነዚህም ሞት፣ የአካልና የሥነልቦና ጉዳት፣ ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃት፣ ከመኖሪያ አካባቢ መፈናቀል፣ከቤተሰብ ወይም አሳዳጊ መነጠል፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ማጣት፣ የምግብ እጥረትና እጦት፣ የሰብአዊ እርዳታ አለመሟላት፣ እና የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን ይጨምራል።

***መደምደሚያ***

270. ጦርነቱ እና በጦርነቱ ውስጥ የተፈጸሙ ጥሰቶች በሕፃናት መሰረታዊ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት፣ የመማር እና የጤና እንዲሁም ከቤተሰቦቻቸው እንክብካቤን የማግኘት መብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳትን አድርሷል። በጦርነቱ ተሳታፊ አካላት በተወሰዱ የኃይል እርምጃዎች በርካታ ሕፃናት ተገድለዋል፤ ለአካል እና የሥነልቦና ጉዳትም ተዳርገዋል፤ እንዲሁም የወሲባዊ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል። በአቅራቢያቸው ያሉ ሕክምና ተቋማት በመውደማቸው እና በመዘረፋቸው በቂ ሕክምና ለማግኘት ሳይችሉ ሕይወታቸው ያለፈ ሕፃናትም ነበሩ። ስለሆነም በጦርነቱ ተሳታፊ ኃይሎች በተወሰዱ እርምጃዎች በሕፃናት መብቶች ላይ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ስለመፈጸማቸው የሚያሳዩ ሲሆን፤ በምርመራው ግኝቶች የተመለከቱት በሕፃናት ላይ ሆን ተብለው የተፈጸሙ ግድያዎች እና ወሲባዊ ጥቃቶች በትግራይ ኃይሎች የተፈጸሙ ጥሰቶች ስለመሆናቸው ምክንያታዊ አሳማኝ ሁኔታዎችና ማስረጃዎች አሉ። የተወሰኑት የመብት ጥሰቶችም በጦርነት ዐውድ ውስጥ የተፈጸሙ በመሆናቸው፤ የጦር ወንጀል ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው።

## 11.አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን

***መግቢያ***

**271.** በጦርነቱ ምክንያት በአረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ስለመፈጸማቸው ኢሰመኮ መረጃዎች ደርሰውታል። ኮሚሽኑ በምርመራው በአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች (በተለይም የአዕምሮ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች) ላይ ከፍ ያለ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች መፈጸማቸውን ከተጎጂዎች፣ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከምስክሮች፣ ከመንግሥት አካላትና ሌሎችም ተዓማኒ ምንጮች በሰበሰባቸውና በአጣራቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች እንዲሁም በአካል ባደረጋቸው ምልከታዎች ተገንዝቧል።

**የሕግ ማዕቀፍ**

272. የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች ቻርተር የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል "አረጋውያን" ዕድሜያቸው 60 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያሉ ሰዎች እንደሆኑ ይደነግጋል። መንግሥታት ከአረጋውያን መብቶች አንጻር ራሳቸውን እንዲችሉ ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር፣ ሰብአዊ ክብራቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ የማድረግ፤ የተሳትፎ እንዲሁም ተገቢውን እንክብካቤ በማኅበረሰብ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲያገኙ፣ በትምህርት፣ በስራ እድሎች እንዲሁም በባሕል እና በመዝናኛ ራሳቸውን የሚያጎለብቱበት እድል እንዲኖር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። በጦርነት ሁኔታዎች ውስጥ ሌሎች መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው አረጋውያን ሰዎችን ከአደጋ የማዳን፣ የማስፈር እና የመልሶ ማስፈር ተግባራት ላይ ቅድሚያ የማግኘት መብቶችም አሏቸው።

273. ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ፈራሚ አገር ናት። ስምምነቱ ከአዕምሮ ህመም ጋር የተያያዙ እክሎችን በአካል ጉዳተኞች ትርጓሜው ላይ ያካተተ ሲሆን፤ አገራት ሁሉም አካል ጉዳተኞች ሰብአዊ ክብራቸው፣ ግለሰባዊ ነጻነታቸው፣ ከመድሎ የመጠበቅ እና በማኅበረሰብ ውስጥ እኩል እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ የማድረግ መብቶቻቸውን የማክበር እና የማስከበር እንዲሁም አገልግሎቶች እና መሰረተ ልማቶች ተደራሽ እንዲሆኑላቸው የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይኸው ስምምነት በአንቀጽ 11 ላይ አገራት በተለይም የሰብአዊነት ሕግጋትን እና የሰብአዊ መብቶችን ጨምሮ ከዓለም አቀፍ ሕግ የሚመነጩ ግዴታዎቻቸው በሚጠይቁት መሠረት በታጣቂዎች የሚካሄዱ ግጭቶችን፣ ሰብአዊነትን የሚነኩ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎችንና የተፈጥሮ አደጋ ክስተቶችን ጨምሮ በስጋት ሁኔታዎች ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጥበቃና ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል።

274. የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት በአንቀጽ 41 (5) ስር መንግሥት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን እና ያለ ወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ እንደሚያደርግ ይደነግጋል። በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግም አረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች ሌሎች ሰዎች ካሏቸው መብቶች በተጨማሪ ልዩ የሆኑ የክብር እና ጥበቃ መብቶች እንዳሏቸው ይደነግጋል። ይህ ልዩ የክብር እና የጥበቃ መብት እንደየአግባቡ በቂ የሕክምና እንክብካቤ ማግኘትን እና በአደጋ ጊዜ ተግባራዊ በሚደረጉ ሰዎችን ከአደጋ የማዳን ስራዎች ቅድሚያ ማግኘትን ያካትታል። አረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች በእድሜያቸው እና በጉዳቶቻቸው ምክንያት ተጋላጭነታቸው የሚጨምር በመሆኑ፣ ከመደበኛው የሕብረተሰብ ክፍል ከፍ ያለ የመብት ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ግዴታዎች በጦርነት ጊዜ በመንግሥትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ታጣቂ ኃይሎች ላይ እኩል ተፈጻሚነት አላቸው።

**የምርመራ ግኝቶች**

275. አረጋውያን በጦርነቱ ተፋላሚ ኃይሎች በተወሰዱ እርምጃዎች መሞታቸውን የኮሚሽኑ ምርመራ ያሳያል። በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን ያሎ ወረዳ ጎቢዶራ ከተማ በሕብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት የነበራቸው የ80 ዓመት የሃይማኖት አባት አዱላይ መስጊድ ውስጥ በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች መገደላቸውን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የሟች ቤተሰቦች እና ምስክሮች አስረድተዋል። በነሐሴ 26 ቀን 2013 ዓ.ም. በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቡ ወረዳ ቀበሌ 018 በነበረ ከባድ ውጊያ ወቅት የ75 ዓመት እናት በቤታቸው እንዳሉ በትግራይ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት ተመተው ሕይወታቸው እንዳለፈ እና አስክሬናቸውን በወቅቱ ማንሳት ባለመቻሉ ለመለየት እስኪያስቸግር ድረስ በጅብ ተበልቶ መገኘቱን የሟች ቤተሰብ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

276. በአማራ ክልል ሸዋ ሮቢት ከተማ ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ምስክሮች ኅዳር 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ጠዋት 3:00 ሰዓት አካባቢ አንድ የ70 ዓመት አረጋዊ ቀበሌ 05 ከሚገኘው ሱቃቸው በተቀመጡበት የትግራይ ታጣቂዎች ሲጋራ እንዲሰጧቸው ሲጠይቋቸው "ደሀ ዘርፈህ ብላ የሚል መንግሥት የለም" ብለው በመመለሳቸው ብቻ በሱቃቸው ውስጥ እንዳሉ በጥይት ደረታቸውን መትተው የገደሏቸው መሆኑን አስረድተዋል። በአማራ ክልል መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ 5 ቀበሌ የትግራይ ኃይሎች በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም ከቀኑ በ9:00 ሰዓት አካባቢ አንዲት የ65 ዓመት አረጋዊ በመኖሪያ ቤታቸው እያሉ የትግራይ ኃይሎች አካባቢውን በሚቆጣጠሩበት ወቅት በራቸው ላይ በመገኘታቸው በጥይት ተኩሰው በመምታት የአካል ጉዳት አድርሰውባቸዋል።

**277.** ጥቅምት 21 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 5:00 ሰዓት አካባቢ በኮምቦልቻ ቀበሌ 09 በሚገኘው ልዩ ስሙ ሎጎ ጊዮርጊስ በሚባል ስፍራ የቆሰሉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት ደብቃችኋል በሚል እድሜዋ 35 ዓመት የሆነች እና የ70 ዓመት ሴት አረጋዊ አብረው በቤት ውስጥ እንዳሉ መገደላቸውን፤ እንዲሁም የ27 ዓመት ወንድ ወጣት በጥይት ተመቶ መቁሰሉን ምስክሮች አስረድተዋል።

278. የትግራይ ኃይሎች በአፋር ክልል ካሳጊታ ከተማን በተቆጣጠሩ በሳምንቱ እንዲት የካሳጊታ ከተማ ነዋሪ የሆኑ የ65 ዓመት ሴት አዛውንት ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ.ም. ሰኞ ዕለት መኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ቁጭ ባሉበት መንግሥት በመከላከያ ሠራዊት የተተኮሰ ከባድ መስሪያ ፍንጣሪ በጀርባቸው ላይ ከባድ ጉዳት እንዳደረሰባቸውና ወደ ባቲ ሆስፒታል የተወሰዱ ቢሆንም፤ ሆስፒታል እንደደረሱ ሕይወታቸው እንዳለፈ ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የሟች ቤተሰቦች እና ምስክሮች ገልጸዋል።

279. በአፋር ክልል በካሳጊታ ከተማ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. መንግሥት በመከላከያ ሠራዊት የተፈጸመ የከባድ መሳሪያ ጥቃት አንድ የ80 ዓመት አዛውንት ቤት ላይ በመውደቁ ሕይወታቸው አልፏል። ታኅሣሥ 2 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 10:00 ሰዓት በአማራ ክልል ጋሸና ጥመጥማት በሚባል አካባቢ በመከላከያ ሠራዊት በተፈጸመ የድሮን ጥቃት አንድ የ65 ዓመት አዛውንት እና ባለቤታቸው ተገድለዋል። በዕለቱ ውጊያ ሲካሔድ ውሎ የትግራይ ኃይሎች ከተማውን ከተቆጣጠሩ

በኋላ ታጣቂዎች ወደ ሚቾች ቤት በመሔድ ውሃ ሲጠይቁ አረጋዊው ሚች ቁስ በመሆናቸው ታጣቂዎችን መስቀል ሲያሳልሙና ባለቤታቸው ደግሞ ውሃ በሚያቀርቡበት ቅጽበት በተፈጸመው የድሮን ጥቃት አረጋውያን ባልና ሚስቱ በስፍራው ከነበሩ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ጭምር የተገደሉ ሲሆን አንድ በቅርብ የነበረ ሲቪል ሰው የመቁሰል አደጋ ሲደርስበት ሁለት ቤቶች በቃጠሎ ወድመዋል፡፡

280. ጦርነቱ በተካሔደባቸውና በተለይም በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በቆዩ አካባቢዎች አስገድዶ መድፈር የተፈጸመባቸው ሴት አረጋውያን መኖራቸውን ኮሚሽኑ በምርመራው አረጋግጧል፡፡ የወልዲያ ከተማ ቀበሌ 04 ነዋሪና የሆኑ የ60 ዓመት አረጋዊ ነሐሴ 5 ቀን 2013 ዓ.ም. በአንድ የትግራይ ታጣቂ የአስገድዶ መድፈር ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ተጎጂዋ የነበረውን ሁኔታ እና የተፈጸመባቸውን ጥቃት ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ፦

*"ከምሽቱ በግምት 3:00 ሰዓት ሲሆን አንድ የትግራይ ታጣቂ የቤቴን በራፍ ቆረቆረ፡፡ አልከፍትም ስለው ክፈቺ አለዚያ ልተኩስ ነው አለኝ እኔም ለሕይወቴ ስለፈራሁ እሽ ቆይ ልክፈትህ በማለት በውስጥ ልብስ ብቻ እንዳለሁ ሰውነቴ እየተንቀጠቀጠ በሩን ከፈትኩለት፡፡.......ነይና ከአልጋው ላይ ተኚ አለኝ፡፡ አንተየ እናትህ አይደለሁ እንዴት ብየ ካንተ ጋር እተኛለሁ ስለው እናቴንማ መቀሌ ትቻት መጥቻለሁ አለኝ፡፡ ሲናገር አፉ ጋን ጋን ይሸታል አልጋ ላይ አልወጣም ስለው ይዞ በጥፊ ድርግም አደረገኝ አሁንም አልወጣም ስል ያንን ዝናር ካራ ምዝዝ ሲያደርገውና አርጀሽ ነው የምሄድ ሲለኝ ሊያርደኝ ነው ብየ መቼስ ነብስያ አይደለሁ እሽ እተኛለሁ አልኩኝና ወጥቼ ከአልጋው ላይ ተኛሁ፡፡ ....ከዚያ መቼም ምን ይደረጋል ተኛሁ አስገድዶም ደፈረኝ ከዚያ በኋላ ወጥቶ ሄደ በማግስቱ ደግሞ መጥቶ ተጨማሪ ጥቃት ያደርስብኛል ብየ ቤቴን ቆልፌ ሸሸሁ፡፡" በማለት አስረድተዋል፡፡*

281. የአዕምሮ ሕሙማን በተለይ በትግራይ ኃይሎች ከሌሎች ሲቪል ሰዎች በበለጠ የጥቃት ዒላማ ተደርገዋል፡፡ ሕሙማኑ የትግራይ ኃይሎች ወደ ተቆጣጠሯቸው ከተሞች ሲገቡ በመንገድ ላይ በመገኘታቸው፣ ወይም መንቀሳቀስ በተከለከለባቸው ሰዓታት ሲንቀሳቀሱ በመገኘታቸው፣ ወይም የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ባለመቻላቸው፣ ወይም ለሚጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ባለመቻላቸው፣ ወይም የመንግሥት ሰላዮች ናቸው በሚል ጥርጣሬ መገደላቸውን ኮሚሽኑ ያሰባሰባቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በርካታዎቹ የአዕምሮ ሕሙማን ለመገደላቸው ዋነኛው ምክንያት ለመንግሥት ኃይሎች መረጃ የሚያቀብሉ ሰዎች እንደ አዕምሮ ሕሙማን መስለው በትግራይ ቁጥጥር ስር በሚገኙ ቦታዎች ውስጥ ይሰልላሉ የሚል ጥርጣሬ ነው፡፡

282. ነሐሴ 19 ቀን 2013 ዓ.ም. የትግራይ ኃይሎች ከድብኮ ከተማ መግባት፣ መውጣት እና መንቀሳቀስ በከለከሉበት ወቅት ከድብኮ ወደ ዳቦ ከተማ በመሄድ ላይ የነበረ አንድ የአዕምሮ ሕመምተኛን፤ ዳቦ ከተማ መግቢያ ድልድዩ ላይ የነበረው ኬላ ላይ አስቁመው ገድለውታል፡፡ ቀኑ በትክክል ባልታወቀ

በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም. ቅዳሜ ዕለት ከምሽቱ በ12፡30 ሰዓት ሲሆን አንድ የ34 ዓመት የአዕምሮ ሕመምተኛ ወደ መስጊድ እየሄደ በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች ጀርባውን በጥይት ተመትቶ ተገድሏል፡፡ በተመሳሳይ በአፋር ክልል ጭፍራ ከተማ ጥቅምት 7 ቀን 2014 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት አካባቢ አንድ የአዕምሮ ሕመምተኛ ከአስፋልቱ አቅራቢያ የትግራይ ታጣቂዎች እያሯሯጡ የተኮሱበት መሆኑን እና ተመትቶ ሲወድቅም በወደቀበት ጆሮው ጋር ጥይት ተኩሰው እንደገደሉት ምስክሮች ያስረዳሉ፡፡ ኮሚሽኑ ያነጋገራት አንድ ምስክር በአፋር ክልል አውራ ወረዳ ፈርፈርሲ የተባለ ቦታ ዕድሜው 40 ዓመት የሆነው የአእምሮ ሕመምተኛ የነበረ የእህቷ ልጅ በትግራይ ኃይሎች ተገድሏል ስትባል እየሸሸች ካለችበት በመመለስ የሚችን አስከሬን ልጇ እንዳገኘችው እና እንደቀበረችው ለኮሚሽኑ አስረድታለች፡፡

283. ታኅሣሥ 8 ቀን 2014 ዓ.ም. በአማራ ክልል ውጫሌ አቅራቢያ ደንካ ከተባለው አካባቢ አንዲት የ30 ዓመት የአዕምሮ ሕመምተኛ ሴት ደንካ ከተባለው ሰፈር በ3 ጥይት ጭቅላቷን ተመታና አንገቷ ላይ በስለት ተቆርጦ ተገኝታለች፡፡ ሟች በዕለቱ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት አካባቢ ከቤት ወጥታ ሳትመለስ የቀረች መሆኑንና በማግስቱ ከቀኑ 12፡00 ሰዓት አካበቢ ከብት ጠባቂዎች ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ሜዳ ላይ ወድቃ አግኝተዋት መልዕክት ለወላጆቿ መድረሱን ተከትሎ አስከሬኗ መነሳቱን የሟች ቤተሰቦች አስረድተዋል፡፡ ሟችን ማን እንደገደላት ማረጋገጥ ባይቻልም የሟች አስክሬን የተገኘችበትን አካባቢ የትግራይ ኃይሎች እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ ተቆጣጥረው መንግሥት ከመከላከያ ጋር ሲዋጉ የዋሉበት ሲሆን ከቀኑ 10፡00 በኋላ ግን አካባቢው መንግሥት በመከላከያ ሠራዊት እጅ የገባ መሆኑን የአካባቢው ነዋሪዎች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

284. የአዕምሮ ሕሙማንን በሰላይነት የመጠርጠር አመለካከት በመንግሥት ኃይሎች ዘንድም እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሰንበቴ ከተማ ይኖር የነበረ አንድ የአዕምሮ ሕመምተኛን መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት አባላት "የትግራይ ኃይሎች ተላላኪ ነው" በማለት ሁለት ጊዜ ወስደውት የአካባቢው ሰው ሕመምተኛ መሆኑን አስረድቶ ያስጣሉት ቢሆንም በመጨረሻ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት ምሽግ ሰርቶ የነበረበት ቦታ ተገሎ እንደተገኘና ይህ የተፈጸመው የትግራይ ኃይሎች ወደአካባቢው ከመግባታቸው አስቀድሞ መሆኑን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ነዋሪዎች ገልጸዋል፡፡ ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም የትግራይ ኃይሎች ከዳቦ ከተማ በሚያፈገፍጉበት ወቅት የአማራ ልዩ ኃይል ከከተማው አቅራቢያ በሚገኝ ጫካ ከእናቱ ጋር ከዳቦ ከተማ ሸሽቶ የተደበቀን አንድ የአዕምሮ ታማሚ አግኝተው "ጁንታ ነህ?" ብለው ሲጠይቁት "አዎ ጁንታ ነኝ" ብሎ በመመለሱ ወዲያውኑ በጥይት መትተው ገድለውታል፡፡

285. አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት መልኩ ከደረሱባቸው የመብት ጥሰቶች በተጨማሪ፤ በአቅራቢያቸው ይገለገሉባቸው የነበሩ የጤና ተቋማት እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች በመውደማቸው እና በመዘረፋቸው በሕክምና እጦት ለተጨማሪ ጉዳት ተዳርገዋል፡፡ ጦርነቱን ለመሸሽ አቅማቸው እና የጤና ሁኔታቸው ፈቅዶ የሸሹትም በቂ ሰብአዊ እርዳታ በማይቀርብበት ሁኔታ ውስጥ ተፈናቅለው ለጤና፣ ለምግብ እና መጠለያ እጦት ተዳርገዋል፡፡

**የጥሰቱ ተፅዕኖ**

286. የኮሚሽኑ የምርመራ ግኝቶች እንደሚያሳዩት በጦርነቱ ተፋላሚ ኃይሎች በተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ምክንያት በርካታ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ተገድለዋል፤ የአካል እና የሥነልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ሴት አረጋዊያን ወሲባዊ ጥቃቶች ተፈጽሞባቸዋል፤ በተጨማሪም የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ቤት ንብረታቸው ወድሟል፣ በሚጦሯቸው፣ በሚንከባከቧቸው እና በሚደግፏቸው ቤተሰቦቻቸው ላይ በተፈጸሙ ግድያዎች፣ የአካል ጉዳቶች እና የንብረት ዘረፋ እና ውድመቶች ምክንያትም ያለጧሪ እና ደጋፊ ቀርተዋል፤ ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነልቦናዊ ቀውስ ተዳርገዋል። ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ የሚገባቸው የአዕምሮ ሕመምተኞች በጥርጣሬ ብቻ በሕመማቸው ምክንያት በግፍ በመገደላቸው የቤተሰቦቻቸውን ሀዘን መሪር አድርጎታል።

**መደምደሚያ**

287. በጦርነት ተሳታፊ በሆኑ ኃይሎች አረጋዊያን እና አካል ጉዳቶኞች (በተለይም የአዕምሮ ጉዳት ያለባቸው) ላይ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች መፈጸማቸውን የሚያሳዩ ምክንያታዊ አሳማኝ ሁኔታዎችና ማስረጃዎች የተገኙ ሲሆን፤ በምርመራው ግኝቶች የተመለከቱት በሴት አረጋዊያን ላይ የተፈጸመ ወሲባዊ ጥቃት በትግራይ ኃይሎች ታጣቂ የተፈጸመ ጥሰት መሆኑ ምክንያታዊ አሳማኝ ማስረጃ አለ። የተወሰኑት የመብት ጥሰቶችም በጦርነት ዐውድ ውስጥ የተፈጸሙ በመሆናቸው፤ የጦር ወንጀል ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው።

**የምርመራው አጠቃላይ ግኝቶች**

288. ኢሰመኮ ባደረገው ምርመራ፣ በሰበሰበው መረጃና ማስረጃ መሰረት የምክንያታዊ አሳማኝነት መስፈርትን (reasonable grounds to believe) በሚያሟላ መልኩ በጦርነቱ ተሳታፊ በሆኑ አካላት የተስፋፋ እና ስልታዊ የሆነ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች መፈጸማቸውን ለይቷል። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት አጠቃላይ ግኝቶች ተጠቃሽ ናቸው፦

289. በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች በተለይም የመከላከያ ሠራዊት እና የትግራይ ኃይሎች ከመለየት፣ ከጥንቃቄ እና ከተመጣጣኝነት መርህ ውጪ የጦር መሳሪያዎችን (ከባድ መሳሪያዎችን፣ የአየርና ድሮን መሳሪያዎችን ጨምሮ) በመጠቀም፤ እንዲሁም የትግራይ ኃይሎች ሲቪል ሰዎችን እንደ ከለላ በመጠቀም በሲቪል ሰዎች፣ በሲቪል ተቋማት እና ሌሎች ጥበቃ በሚደረግላቸው ሰዎችና ቁሶች ላይ የጦር ወንጀልን ሊያቋቁም (መስፈርቶችን ሊያሟላ) በሚችል ሁኔታ ጉዳት አድርሰዋል።

290. በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ኃይሎች ከሕግ አግባብ እና የዳኝነት ሥርዓት ውጪ በሲቪል ሰዎች ላይ የጦር ወንጀል እና በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ሊያቋቁም በሚችል መልኩ ግድያዎች እና የአካል ጉዳቶችን አድርሰዋል። በዋነኝነት የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸው አብዛኞቹ የአፋር እና አማራ አካባቢዎች በጦርነት ውስጥ ተሳትፎ ያልነበራቸው በርካታ ሲቪል ሰዎች ላይ ሕገወጥ

እና ከዳኝነት ሥርዓት ውጪ የሆነ የግፍ ግድያ ፈጽመዋል፤ የአካል እና የሥነልቦና ጉዳት አድርሰዋል። የኦነግ ሸኔ ኃይሎችም በተመሳሳይ መልኩ በነበሩባቸው አካባቢዎች ሕገወጥ እና ከዳኝነት ሥርዓት ውጪ የሆነ በሲቪል ሰዎች ላይ የግፍ ግድያዎች እና የአካል ጉዳቶችን ፈጽመዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች የመከላከያ ሠራዊት፣ የአማራ ልዩ ኃይል እና የፋኖ ታጣቂዎችም ከትግራይ ኃይሎች ወይም ከኦነግ ሸኔ ጋር ተባብረዋል ወይም ደጋፊ ናቸው ያሏቸው ሰዎች ላይ ሕገወጥ እና ከዳኝነት ሥርዓት ውጪ የሆነ የግፍ ግድያ እና ጥቃት አድርሰዋል።

291. የትግራይ ኃይሎች ጦርነቱ በተካሄደባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች ነዋሪ በሆኑ ሲቪል ሰዎች በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ሊያቋቁም በሚችል መልኩ የጭካኔ እና የማሰቃየት ተግባር ፈጽመዋል።

292. ጦርነቱ በተካሄደባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች ዓለም አቀፍ የጦር ወንጀልን እና በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ሊያቋቁም በሚችል መልኩ የእገታ እና አስገድዶ መሰወር ተግባራትን ፈጽመዋል። በሌላ በኩል የፌዴራል፣ የአማራ እና የአፋር ክልል የፀጥታ ኃይሎች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ዐውድ ውስጥም ቢሆን፤ ሊገደቡ የማይችሉ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎችና መርሆችን የጣሰ መጠነ ሰፊ የዘፈቀደ እስር ፈጽመዋል።

293. የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸውና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች ተጎጂዎችን በመደብደብና በማስፈራራት፣ በተናጠል እና በቡድን ሴቶችን አስገድዶ በመድፈር፣ እንዲሁም ቢያንስ በአንድ ተጎጂ ላይ ባዕድ ነገር (የጠብመንጃ አፈ ሙዝ) በማኅፀን ውስጥ በመክተት ጭምር የጦር ወንጀልን እና በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ሊያቋቁም በሚችል መልኩ የተስፋፋ ፆታዊ ጥቃት ፈፅመዋል። በትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በአፋርና አማራ ክልሎች ተስፋፍተው የተፈጸሙ ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃቶች የተጎጂዎችን እና የጥቃቱ ዒላማ የተደረጉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ሰብአዊ ክብር ለመጉዳት እና ለማዋረድ፣ በአብዛኛው በሴቶች ላይ በሙሉ ያለልዩነት፣ አልፎ አልፎም አጥቂዎቹ ሆነ ብለው ለጥቃቱ ዒላማነት በመረጧቸው ሴቶች ላይ ሆነ ተብሎ ታቅዶ በግፍና በጭካኔ፣ በግልጽ የበቀል ስሜት፣ በቡድን አስገድዶ በመድፈር፣ ድርጊቱን ሆነ ተብሎ በቤተሰብ ፊት በመፈጸምና፣ በታጣቂዎቹ ኃላፊዎች ይሁንታ እና ዝምታ የተፈጸመ በመሆኑ፤ የትግራይ ኃይሎች ታጣቂዎች በሴቶች ላይ የፈጸሙት ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃትን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለጦርነት አላማ እንዳዋሉትም የሚያስረዳ ነው።

294. ጦርነቱ በተስፋፋባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች በጦርነቱ ምክንያት በተፈጠረው የፀጥታ ስጋት እና በትግራይ ኃይሎች በተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው፤ ያለበቂ ሰብአዊ እርዳታ፣ በቂ ባልሆነ ጥበቃ፣ በመጠለያ እጥረት፣ ባልተሟላ የጤና አገልግሎት፣ ምግብ፣ ውሃ እና ሌሎች አቅርቦቶች በጊዜያዊ መጠለያዎች ለመቆየት በመዳረጋቸው ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠዋል።

295. የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸው የአፋር እና የአማራ ክልል አካባቢዎች የግል ንብረቶች እና የመንግሥት ተቋማት ንብረቶች ላይ መጠነ ሰፊ ገፈፋ፣ ዘረፋ እና ውድመት ፈጽመዋል፤ በተለይም የጦር ወንጀልን እና በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ሊያቋቁም በሚችል መልኩ ለሲቪል ሰዎች ሕልውና አስፈላጊ የሆኑ የማሳ ሰብሎችን፣ የምግብ እህሎች፣ የቤት እንስሳትን አውድመዋል፣ ዘርፈው ወስደዋል። በተለይ በርካታ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት እና የመንግሥት ድርጅቶች ላይ ዒላማ ያደረገ፣ ሆን ተብሎና ስልታዊ በሆነ መንገድ የተፈጸመ የዘረፋ፣ የገፈፋ እና የማውደም ተግባር ፈጽመዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች በጦርነቱ የተነሳ የሕግና ሥርዓት መፍረሱን ተከትሎ የየአካባቢው ነዋሪ የሆኑ የተወሰኑ ሰዎች በንብረት ዝርፊያ እና ውድመት ተግባር የተሳተፉ ሲሆን፤ በስፍራዎቹ የነበሩት የትግራይ ኃይሎች የመከላከል እርምጃ ካለመውሰዳቸውም በላይ፤ ይልቁንም የንብረት ዝርፊያና ውድመት ሲያበረታቱ ነበር። የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች በነበሩባቸው አካባቢዎችም ተመሳሳይ ዝርፊያ እና ውድመቶችን ፈጽመዋል። በሌላ በኩል ከትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ተለቅቀው በፌዴራል እና በክልል የፀጥታ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በገቡ አካባቢዎች፤ ከትግራይ ኃይሎች ጋር ተባብራችኋል በሚል በተጠረጠሩ ሰዎች እና በትግራይ ተወላጆች ላይ በፋኖ ታጣቂዎች እና በተወሰኑ የአካባቢው ነዋሪ ሰዎች ዝርፊያዎች ተፈጽመዋል።

296. በፌደራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት በሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ላይ የተደረጉ አስተዳደራዊ እና ሌሎች ክልከላዎች/ገደቦች አስፈላጊው ሰብአዊ እርዳታ በሚፈለገው መጠን እና ፍጥነት ወደ ትግራይ ክልል እንዳይደርስ ምክንያት ሆኗል። በአማራ እና በአፋር ክልል የሚገኙ አካባቢዎች በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩበት ወቅት ወደ ስፍራዎቹ ሲደርስ የነበረው ሰብአዊ እርዳታ በጣም ዝቅተኛ የነበረና በእነዚህ ጊዜያት የስልክ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የባንክ፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶች ተቋርጠው የነበረ መሆኑ ሰብአዊ ሁኔታውን አባብሶት ቆይቷል። እንዲሁም ይህ ሪፖርት ይፋ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ፤ ወደ ትግራይ ክልል በአየር በረራ የሚደርሰው ሰብአዊ እርዳታ በተወሰነ መጠን እየተሻሻለ መምጣቱ ቢታወቀም፤ አቅርቦቱ ከፍላጎት ጋር ባለመመጣጠኑ እና የስልክ፣ የተሟላ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ባንክ፣ እና ትራንስፖርት የመሰሉ መሰረታዊ አገልግሎቶች በትግራይ ክልል እንደተቋረጡ መሆናቸው በክልሉ ያለውን ሰብአዊ ቀውስ አባብሶታል።

297. በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸውና ለጥሰት ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑ ሲቪል ሰዎች (በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች እና በአረጋዊያን) ላይ መጠነ ሰፊ የመብት ጥሰት አድርሰዋል።

298. በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች በፈጸሟቸው ጥቃቶች፣ ዝርፊያዎችና ውድመቶች፣ እንዲሁም ሰብአዊ አቅርቦት እና መሰረታዊ አገልግሎቶች ክልከላዎች ምክንያት፤ በተለይ የጤና፣ የትምህርት፣ የምግብ እና መጠለያ መብቶችን ጨምሮ መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚያዊ እና የማኅበራዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል።

299. የምርመራው አጠቃላይ ግኝቶች እንደሚያመላክቱት በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ዓለም አቀፍ ወንጀሎችን ማለትም የጦር ወንጀልን እና በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚያቋቁም መልኩ ጥሰቶችን መፈጸማቸውን የሚጠቁሙ ምክንያታዊ አሳማኝ ማስረጃዎች በመገኘታቸው አጥፊዎችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ የወንጀል ምርመራ እና የክስ ሂደት በአፋጣኝ መጀመር እንዳለበት ኢሰመኮ ያሳስባል።

# ተጠያቂነት

### መግቢያ

300. ይህ ምርመራ የተከናወነው በአፋር እና በአማራ ክልሎች በተካሄደው ጦርነት በተፋላሚ ኃይሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን ከእነዖታዊ እንድምታቸው በመለየት እውነቱን ለማሳወቅ፣ የመብት ጥሰቶችን የፈጸሙ ሰዎችና ቡድኖች ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶችን ለማገዝ፣ ለተጎጂዎች ፍትሕ እና ተገቢውን የካሳ እንዲሁም የመልሶ መቋቋም ድጋፍ እንዲያገኙ ለማስቻል እና ወደፊት ተመሳሳይ ጥሰቶች ዳግም እንዳይፈጸሙ ለማስቻል ነው።

301. በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ የትግራይ ኃይሎች፣ የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ወይም ኦነግ ሸኔ፣ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት፣ የአማራ ልዩ ኃይሎች፣ የፋኖ እና ሚሊሺያ አባሎች፤ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን ለመፈፀማቸው ምክንያታዊ አሳማኝ ሁኔታዎችና ማስረጃዎች ስለመኖራቸው ኢሰመኮ በምርመራው አረጋግጧል። ኮሚሽኑ በምርመራው የለያቸው በርካታዎቹ ጥሰቶች በሰብአዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ወይም የጦር ወንጀሎች ሊሆኑ የሚችሉ በመሆናቸው፤ የተሟላ የወንጀል ምርመራ በማድረግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ ነው።

### የሕግ ማዕቀፍ

302. የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብትና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን አስመልክቶ ተጠያቂነትን የማስፈን ኃላፊነት በቀዳሚነት የመንግሥት በመሆኑ፤ ተፈጸሙ የተባሉ የመብት ጥሰቶችን መመርመር፤ አጥፊዎችን ተጠያቂ ማድረግ እና ለተጎጂዎች ፍትሕን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። ከዚህ አንፃር የሚከናወኑ ምርመራዎች በፍጥነት፣ በገለልተኝነት፣ በግልጽነት እና በውጤታማነት ሊከናወኑ ይገባል።[85] ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ሥራን በሰፊው በመረዳት ከፍ ያሉ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰት የፈጸሙ ግለሰቦች እና ቡድኖች ላይ የወጀል ምርመራዎችን ማካሄድን፣ እንደ አስፈላጊነቱ አጣሪ ኮሚሽኖችን ማቋቋምን እንዲሁም ከአሠራር የሚመነጩ ጥሰቶችን ለመለየት የአሠራር ሥርዓቶችን እና ሕጎችን መፈተሽ እና ማስተካከልን ባካተተ መልኩ ማከናወን ያስፈልጋል። እነዚህን ተግባራት በተሟላ መልኩ በመፈጸም የአጥፊዎችን ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ ወደፊትም ተመሳሳይ ጥፋቶች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል እና ለተጎጂዎች ፍትሕ፣ ካሳ እና መልሶ ማቋቋምን ለማረጋገጥ ከመደበኛ የፍትሕ ስርዓቱ ጋር ተመጋጋቢ የሆኑ ሌሎች ተቋማትን እና ስልቶችን ጥቅም ላይ ማዋልን ይጠይቃል።

303. በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች መሰረት መንግሥታት ከፍ ያሉ ወይም ከባድ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች የተፈጸሙበት ማንኛውም ሰው ካሳ ማግኘትን

[85] Basic Principles and Guidelines on the Right to a Remedy and Reparation for Victims of Gross Violations of International Human Rights Law and Serious Violations of International Humanitarian Law

ጨምሮ ተደራሽ እና ውጤታማ የሆነ ፍትሕ እንዲያገኝ የማስቻል ግዴታ አለባቸው::[86] ለተጎጂዎች ተደራሽ መሆን ያለባቸው ፍትሕ የማግኘት አማራጮች ከጥሰቱ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስን፣ ካሳ፣ የተሃድሶ አገልግሎቶችን፣ ጥሰቶች በድጋሚ እንደማይፈጸሙ የሚያረጋገጥ ዋስትና ማግኘትን፣ ጥሰቶችን አስመልክቶ እውነቱን የማወቅን እና በይፋ መገለጽን፣ ይፋዊ ይቅርታ መጠየቅን እና ለጥሰት መንስዔ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎች ላይ ማሻሻያ ማድረግን ያካትታሉ::[87] የተጎጂዎች ውጤታማ መፍትሔ እና ፍትሕ የማግኘት መብቶች በየትኛውም ሁኔታ ሊቀሩ የማይችሉና በግጭት ወይም በጦርነት ወቅትም ቢሆን ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው::[88]

304. በተመሳሳይ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የትጥቅ ግጭት ሕግጋትን የጣሰ ሀገር ላደረሰው ጥፋት ወይም ጉዳት ሙሉ ማካካሻ የመስጠት ግዴታ የተጣለበት ሲሆን ይህ ግዴታ መንግስታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች ላይም ተፈፃሚነት ሊኖረው ይችላል::[89] ውጤታማ መፍትሔ የመስጠት ግዴታ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከመብት ጥሰቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በሌላቸው ሶስተኛ ሀገራት ላይ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ ማሰቃየት፤ ሌሎች የጭካኔ፤ ኢሰብአዊና አዋራጅ አያያዝ ወይም ቅጣትን ለመከልከል የወጣው ስምምነት በሦስተኛ ሀገራት ላይ ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ ሳይገድባቸው በግዛታቸው ውስጥ የሚገኙ ወንጀለኞች ላይ ክስ የመመስረት ወይም አሳልፎ የመስጠት ግዴታን ይጥላል::[90] በዓለም ዓቀፍ የሰብአዊነት ሕግ፤ሀገራት በግዛታቸው ውስጥ የተፈጸሙ የጦር ወንጀሎችን የመመርመር እና ተገቢ ሆኖ ሲገኝ በአጥፊዎች ዜግነት ሳይገደቡ መክሰስ ይኖርባቸዋል::[91] በሌሎች ሁኔታዎች፤ አንዳንድ ጥሰቶች መላውን ዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰቡን የሚመለከቱ ወንጀሎች ተደርገው ስለሚወሰዱ ማንኛውም ሀገር ጥፋተኞች ላይ ክስ መመስረት ይችላል::[92]

305. ፍትሕ የማግኘት መብት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት የተረጋገጠ ሲሆን በሕገ-መንግስቱ እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው በሕግ የሚወሰንን ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ወይም ፍርድ የመስጠት ስልጣን ወዳለው አካል በማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው::[93] ሁሉም የፌዴራልና የክልል ተቋማት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት ውስጥ የተካተቱትን መሰረታዊ መብቶች የማክበርና የመተግበር ግዴታ የተጣለባቸው እንደመሆኑ፤ እነዚህ ተቋማት ፍትሕ የማግኘት መብትን የማክበር፤ የመጠበቅና የማመቻቸት ኃላፊነት አለባቸው:: በተጨማሪም የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን እና የጦር ወንጀሎችን በወንጀልነት የደነገገ ሲሆን የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥትም እነዚህ ወንጀሎች በተመለከተ በገደብ፤ ምህረት እና ይቅርታ ቀሪ እንደማይሆኑ ያመለክታል::[94]

---

[86] ICCPR, Article 2(3) (a), (b), (c); Article 7(1), (a); Human Rights Committee General Comment No. 31; Supra note 70.

[87] Supra note 70, Principles 19-23

[88] Human Rights Committee General Comment Number 29, States of Emergency, paragraph 14

[89] ICRC, Customary IHL Database, Rule 150; supra note 70

[90] CAT, Article 5

[91] ICRC, Customary IHL Database, Rule 158. 8

[92] *Ibid*, Rule 157

[93] የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37 (1)

[94] የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀፅ 138፣ የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 28 (1)

### ሀገራዊ የተጠያቂነት ሥርዓቶች

### የሲቪል ፍትሕ ሥርዓት

306. የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት የፍርድ ሥልጣንን ለፌዴራልና ለክልሎች የሰጠ ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ ለየብቻ እንዲሁም በጋራ የተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው። በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የዚህ ምርመራ ትኩረት የሆነውን "በዓለም ዓቀፍ ሕግ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን" ጨምሮ ሀገሪቷ ያጸደቀቻቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን መሰረት ያደረጉ የወንጀል ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን ለፌደራል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል። በተጨማሪም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች "በሀገር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን"፤ "በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ጎሣዎች፣ በሃይማኖት ተከታዮች ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ከተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን"፣ እና "የፌዴራል መንግስቱ ባለስልጣኖች በማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች እና የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች በሥራቸው ወይም በኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ የሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮችን" የመመልከት ሥልጣን አላቸው።[95] የፍትሕ ሚኒስቴርና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በፌዴራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን የመመርመር ኃላፊነት አለባቸው።

### የወታደራዊ ፍትሕ ሥርዓት

307. ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ እና የይግባኝ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶችን (ፍ/ቤት) የሚያካትት ሲሆን፤ ወታደራዊ ፖሊስ፤ ወታደራዊ ዐቃቤ ሕግና ወታደራዊ የተከላካይ ጠበቃን ጨምሮ የወታደራዊ ፍትሕ አካላት ናቸው።[96] በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ[97] በግልጽ ከተዘረዘሩት ጉዳዮች በተጨማሪ፤ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በሲቪሎች፤ በመደበኛ ፖሊሶች ወይም መንግሥት ከመከላከያ ሠራዊት ጋር በጋራ የተሰማሩ ሚሊሺያዎች እና በትጥቅ ግጭት ወቅት በተያዙ ሰዎች ላይ (በጦር እስረኝነት የሚወሰዱ ሆኑም አልሆኑም) የዳኝነት ሥልጣን አላቸው።[98] ማንኛውም ተከሳሽ የተከሰሰበት ወንጀል በወታደራዊ ፍ/ቤት እና በመደበኛ ፍ/ቤት ሥልጣን ስር የሚወድቅ ከሆነ፤ ሁሉም ክሶች ተጠቃለው የሚቀርቡት ከፍተኛውን ቅጣት የሚያስከትለው ወንጀል ላይ ፍርድ የመስጠት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ነው።[99] ወታደራዊ ፍ/ቤቶች የሚዳኙት በኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ውስጥ በሚገኙ ሥነ-ሥርዓቶች እና ሕጎች መሰረት ነው።[100]

308. ሁሉም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት ወታደራዊ ጥፋት መፈጸሙን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ የተጣለባቸው ሲሆን፤ ማንኛውም የወንጀል ሪፖርት የደረሰው ኮማንደር፤ መርማሪ ወይም

[95] የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁ. 1234/2014 አንቀፅ 1, 3, 9, 14
[96] በመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀፅ 40 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወታደራዊ ይግባኝ ፍ/ቤት ውሳኔዎችን መሰረታዊ የህግ ስህተት ከተሰራ በሰበር የማየት ስልጣን አለው።
[97] የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀፅ 284-322
[98] የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ አንቀፅ 38 (1) (ሸ)፣ (ቀ)
[99] የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀፅ 38 (2)
[100] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 43 (1)

ዐቃቤ ሕግ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ተገቢ እርምጃ መውሰድ አለበት::[101] በወንጀሉ ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ ለወታደራዊ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል::[102] ምርመራን የማቋረጥ ውሳኔ ሕገወጥ ሆኖ ሲገኝ ውሳኔውን የሰጠው አካል ወይም ግለሰብ ተጠያቂ ይሆናል::[103]

309. ማንኛውም የመካላከያ ሠራዊት አባል ከሁለት ዓመት የሚበልጥ እስራት የተፈረደበት እንደሆነ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሚሰናበት ሲሆን፣ ቅጣቱን ከፈጸመ በኋላም ወደሠራዊቱ እንዲመለስ አይፈቀድለትም::[104] ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታወስ የሚገባው፤ በዚህ የምርመራ ሪፖርት ውስጥ በኢትዮጵያ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት እንደተፈጸሙ በምክንያታዊነት የታመኑት አብዛኞቹ ጥሰቶች ከሁለት ዓመት የሚበልጥ ቅጣት የሚያስቀጡ ናቸው::

### የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

310. ከመደበኛው የሲቪል እና ወታደራዊ የፍትሕ ሥርዓት በተጨማሪ የተጠያቂነት ሂደትን ለማመቻቸት ከሚያግዙ ስልቶች አንዱ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ነው:: የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ም/ቤት) ታኅሣሥ 20 ቀን 2014 ዓ.ም. የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን ለማቋቋም አዋጅ ቁጥር 1265/2014 አጽድቋል:: የኮሚሽኑ አጠቃላይ ዓላማዎች ውስጥ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለውን ልዩነት የስር መንስኤዎችን መለየትና፣ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል በአንኳርና ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ምክክሮችን ማመቻቸት ነው:: እንዲሁም በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል እንዲሁም በህብረተሰቡና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት ማሻሻልና ለተለዩት አሳሳቢ ጉዳዮች ዘላቂ መፍትሄ ማግኘት ነው:: ስለዚህም ኮሚሽኑ በዚህ ሪፖርት በተሸፈኑት የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ምክክር የሚያደርግና የመፍትሄ ሐሳቦችንም የሚያቀርብ ቢሆን፤ ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ረገድ አጋዥ ስልቶች አንዱ ሊሆን ይችላል::

311. የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ አደረጃጀት፤ ዋና እና ምክትል ኮሚሽነርን ጨምሮ 11 አባላት ያሉትን የኮሚሽነሮች ምክር ቤት፣ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት፣ እንደአስፈላጊነቱ ኮሚቴዎችና አስፈላጊ ሰራተኞችን ያካተተ ነው:: የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የካቲት 14 ቀን 2014 ዓ.ም. የ 11 ኮሚሽነሮችን ሹመት አጽድቋል:: የኮሚሽኑ የሥልጣን ዘመን ለሦስት ዓመት ሲሆን፤ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል::

### ዓለም ዓቀፍ ዘዴዎች

312. ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍ/ቤት በዘር ማጥፋት ወንጀል፤ በሰብአዊነት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች እና በጦር ወንጀሎች ላይ የዳኝነት ሥልጣን አለው:: ይህ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን የሚኖረው ወንጀሉ የሮም ስምምነትን ባጸደቀ ሀገር ግዛት ክልል ውስጥ የተፈጸመ ከሆነ ወይም የሮም ስምምነትን

[101] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 30 (3)
[102] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 30 (2)
[103] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 32 (3)
[104] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 13 (1) (በ)

በፈረመ ሀገር ዜጋ ከሆነ፤ የሮም ስምምነትን ያልፈረመ ሀገር የፍ/ቤቱን የዳኝነት ሥልጣን ከተቀበለ ወይም ወንጀሉ በዚህ ፍ/ቤት እንዲታይ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ከተመራ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሮም ስምምነትን ያልፈረመች ሀገር በመሆኗ ዓለም ዓቀፉ የወንጀል ፍ/ቤት በዚህ ምርመራ በተለዩት የጦር ወንጀሎች ላይ የዳኝነት ሥልጣን የሚኖረው ጉዳዩ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ለፍ/ቤቱ ከተመራ ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት የፍ/ቤቱን የዳኝነት ሥልጣን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነ ነው፡፡

313. በግጭቱ ሂደት የተፈጸሙ ከባድ ጥሰቶች ላይ ማስረጃዎችን የሚሰበስብ እና በብሔራዊ ወይም በዓለም ዓቀፍ ችሎት ለሚቀርብ የወንጀል ክስ ሰነዶችን የሚያዘጋጅ ዓለም ዓቀፍ እና ነፃ የምርመራ አካል ሊቋቋም ይችላል፡፡ ይህን የመሰሉ እርምጃዎች በሶሪያና ሚያንማር ተተግብረዋል፡፡[105] የፍርድ ሂደቱን ለማስኬድ ሀገራዊና ዓለም ዓቀፍ አካላትን ያካተቱ ልዩና ድብልቅ (hybrid) ፍ/ቤቶች ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው የሴራሊዮን ልዩ ፍ/ቤት በሴራሊዮን መንግሥት እና በተባበሩት መንግሥታት ስምምነት የተቋቋመ ሲሆን ልዩ የአፍሪካ ችሎት ደግሞ በአፍሪካ ሕብረትና በሴኔጋል ስምምነት በቻድ ውስጥ ከ1975 እስከ 1983 በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎችን ለመዳኘት የተቋቋመ ነው፡፡[106]

314. ከላይ የተጠቀሱት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አማራጮች ሲሆኑ ዓለም ዓቀፍ መንገዶችን ለመውሰድ ከተወሰነ፤ የትኛው አማራጭ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንደሚኖረው የሚመለከታቸው የሀገር ውስጥ እና የዓለም ዓቀፍ አካላት የሚወስኑት ይሆናል፡፡ ሆኖም ፤ ሀገራዊ የተጠያቂነት ዘዴዎች ወይም ተቋሞች ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ ካልቻሉ በስተቀር ዓለም ዓቀፍ ዘዴዎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው አይሆኑም፡፡

**መደምደሚያ**

315. የተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት የማክበር፤ የመጠበቅ እና የማመቻቸት ኃላፊነት በቀዳሚነት የሀገራት ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ኅዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም. "በሰሜን ኢትዮጵያ ከተከሰተው ግጭት ጋር በተያያዘ ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተሰጡ ምክረ-ሐሳቦችን የሚያስፈጽምና የመፍትሄና የተጠያቂነት እርምጃዎችን የሚከታተል" የሚኒስትሮች ግብረ ኃይል ማቋቋሙን አስታውቋል፡፡ መንግሥትየሚኒስትሮች ግብረ ኃይሉ ተግባርና ኃላፊነት ወሰን በተለይ በሦስት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እና የወንጀል ምርመራ ሪፖርቶች የተለዩ ጥሰቶችን እንደሚያጠቃልል የሚጠበቅ ሲሆን፣ እነርሱም፤ "የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንና የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ጽ/ቤት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በትግራይ ክልል ግጭት በሁሉም ተሳታፊዎች ተፈጽመዋል በተባሉ ዓለም ዓቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሕግ ጥሰቶች፤ የሰብአዊነት ሕግና የስደተኞች ሕግ ጥሰቶችን በተመለከተ የተካሄደ የጋራ

[105] The International, Impartial and Independent Mechanism, General Assembly resolution 71/248, A/RES/71/248 (adopted 21 December 2016); Independent Investigative Mechanism for Myanmar, Human Rights Council resolution 39/2, A/HRC/39/2 (adopted 27 September 2018).
[106] UNGA Res. 1315(2000)

ምርመራ[107]፣" "በፌዴራልና በክልል መንግሥታት የተከናወነና በአማራና አፋር ክልሎች በሲቪሎች ላይ የተፈጸሙ ከባድ ወንጀሎችን የተመለከተ የወንጀል ምርመራ"፣ (የምርመራው ቅድመ ግኝት በጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. የወጣ) እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን "በጦርነት የተጎዱ የአማራ ክልል አካባቢዎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶችና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ምርመራ ሪፖርት" በሚል ርዕስ በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም. የወጣ ሪፖርት ናቸው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪም ይህ ሪፖርት የዚሁ ግብረ-ኃይል ተግባርና ኃላፊነት ተጨማሪ ግብዓት እንደሚሆን ይታመናል፡፡

316. የሚኒስትሮች ግብረ ኃይሉ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የሰላም ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ የፋይናንስ ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የፍትሕ ሚኒስቴር ከፍተኛ ኃላፊ ተወካዮችን ያካተተ ሲሆን፣ የፍትሕ ሚኒስቴር የግብረ ኃይሉን አጠቃላይ ስራ የሚያስተባብር እና በተቋማት መካከል የሚኖርን ትብብር የሚያመቻች ይሆናል፡፡ የሚኒስትሮች ግብረ ኃይሉ ስራውን የሚያከናውነው ለዚሁ ጉዳይ በተቋቋመው ልዩ ጽ/ቤት እና በአራት የውስጥ ኮሚቴዎቹ በኩል ነው፡፡ እነዚህም፣ የምርመራና ክስ ኮሚቴ፣ የስደተኞች እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ኮሚቴ፣ የፆታዊ ጥሰቶች ኮሚቴ እና የሃብት ማሰባሰብ ኮሚቴ ናቸው፡፡ የሚኒስትሮች ግብረ ኃይሉ የተጠያቂነት እና የመፍትሔ ሂደቱን ለማከናወን የሚያስችል ዕቅድና የትግበራ መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ስራውን መጀመሩን አስታውቋል፡፡

317. የሚኒስትሮች ግብረ ኃይሉ ስራውን በጀመረ ጊዜ ይህ ሪፖርት ገና በመዘጋጀት ላይ የነበረ ቢሆንም፣ ግብረ ኃይሉ የሚሸፍናቸውን ጉዳዮችና ጥሰቶች የሚመለከት በመሆኑ፣ ከዚህ በላየ እንደተገለጸው የሚኒስትሮች ግብረ ኃይሉ በዚህ ምርመራ የተካተቱ ምክረ ሃሳቦችን በስራው ውስጥ እንደሚያካትታቸው ይታመናል፡፡ መከራል፡፡

[107] https://ehrc.org/download/ehrc-ohchr-joint-investigation-report-on-tigray-conflict/

# ምክረ ሃሳብ

318. ኢሰመኮ ባደረገው ምርመራ በጦርነቱ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ዓለም አቀፍ ወንጀሎችን ማለትም የጦር ወንጀልን እና በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚያቋቁም መልኩ መጠነ ሰፊ ጥሰቶችን መፈጸማቸውን በመለየቱ የሚከተሉትን ምክረ ሃሳቦች ያቀርባል፦

319. **በጦርነቱ ተሳታፊ ለሆኑ ሁሉም ወገኖች፦**

1. ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተኩስ አቁም በማድረግ ለጦርነቱ ሰላማዊ መፍትሔ ለማፈላለግ በቁርጠኝነት እንዲሰሩ፣
2. በማናቸውም የጦርነት ወይም የትጥቅ ግጭት ሂደት የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን ከመፈጸም እንዲቆጠቡ፣ በጦርነት ወይም በግጭቱ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን በይፋ እንዲያወግዙ እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ እርምጃዎችን እንዲወስዱ፣
3. አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ ፆታዊ ጥቃትን በአፋጣኝ እንዲያስቆሙ እና ለአባላቶቻቸው ግልጽ እና የማያሻሙ መመሪያዎች እንዲሰጡ፣
4. በሚቆጣጠሯቸው አካባቢዎች ሰብአዊ መብቶችን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ፣ በነዋሪዎች፣ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና መሰረተ ልማቶች ላይ ጥቃት ከማድረስ እንዲቆጠቡ ከጉዳት እና ከዘረፋ እንዲጠብቁ፤ በሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት ላይ የተቀመጡ ማንኛቸውንም ክልከላዎችን ያለ ቅድመ ሁኔታ በማንሳት ተደራሽነትን እንዲያረጋግጡ፣ መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዲያስጀምሩ፣
5. ኢሰመኮ የሚያከናውናቸውን የሰብአዊ መብቶች ክትትሎች እና ምርመራዎች እንዲደግፉ፣ እንቅፋት ከመሆን እንዲቆጠቡ እና አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉ፣

320. **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግሥት፦**

1. ፆታዊ ጥቃት የፈጸሙትን ጨምሮ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕጎች ጥሰት የፈጸሙ እና ያስፈጸሙ ኃላፊዎችን እና አባላትን ተጠያቂ ለማድረግ ነፃ፣ ግልጽ እና የሰብአዊ መብቶች ደረጃውን የሚያሟላ የወንጀል ምርመራ እና የክስ ሂደቶች እንዲያስጀምሩ፣

321. **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግሥት፣ ለአፋርና አማራ የክልል መስተዳድር እንዲሁም ለትግራይ ክልል ባለስልጣኖች፦**

1. በክልሎቹ የሚኖሩ ነዋሪዎችን ደኅንነት ያለ ምንም አይነት መድልዎ እና ልዩነት እንዲጠብቁ እና እንዲያስጠብቁ፤

2. በጦርነቱ በሰው ሕይወት፣ በአካል፣ በስነልቦና እና በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት በማጣራት ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ስራ እንዲያከናውኑ፤
3. በጦርነቱ ውድመት የደረሰባቸው የጤና፣ ትምህርት እና ሌሎች አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች እና የሕዝብ አገልግሎቶች መልሶ ለመገንባት ተገቢው ትኩረት እንዲሰጡ እና በአፋጣኝ ወደ መደበኛ ሥራቸው እንዲመለሱ እንዲያደርጉ፤
4. ምግብ ነክ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ሰብአዊ ድጋፎች ለተፈናቃዮች እና እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ የማቅረብ ስራ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የሰብአዊ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር በመቀናጀት እና በመተባበር በአፋጣኝ እንዲከናወን፣ እንዲሁም ተፈናቃዮችን በዘላቂነት መመለስ ወይም ማቋቋም እስከሚቻል ድረስ የተፈናቃይ ማቆያ ስፍራዎች ደኅንነታቸውና ንጽሕናቸውን እንዲጠበቅ፣ መሰረታዊ የጤና፣ ትምህርት እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች እንዲሟሉ እንዲያደርጉ፤

**322. ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለአፋር ክልል እና ለአማራ ክልል ምክር ቤቶች እንዲሁም ለትግራይ ክልል ባለስልጣኖች፦**

1. በዚህ ምርመራ እና ከተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር በጋራ በተደረገው ምርመራ የተለዩትን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምርመራዎች ላይ የተሰጡት ምክረ ሃሳቦች መፈጸማቸውን እንዲከታተሉ፣ ጥሰቶቹን ለማስቆም አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ፣ ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣

**323. ለሀገራዊ፣ አሁጉራዊና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ፦**

1. ለጦርነቱ ሰላማዊ መፍትሔ እንዲገኝ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ፣
2. በጦርነቱ የደረሰውን መጠነ ሰፊ ሰብአዊ ጉዳት በመገንዘብ ለመልሶ መቋቋም፣ ለሰብአዊ እርዳታ እና መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር አስፈላጊ ድጋፍ እና እገዛ እንዲያደርጉ፣
3. ተጠያቂነትን ለማስፈን ለሚደረጉ ሀገራዊ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ድጋፍ እና እገዛ እንዲያደርጉ፣

**324. ከላይ ለተዘረዘሩት ሁሉም አካላት፦**

1. ኢሰመኮ ከተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ባካሄዱት ጣምራ ምርመራ እንዲሁም ኮሚሽኑ የሰሜን ኢትዮጵያን ግጭት አስመልክቶ ከዚህ ቀደም ባወጣቸው የምርመራ ሪፖርቶችና መግለጫዎች የሰጣቸውን ምክረ ሃሳቦች በሚመለከታቸው አግባብ እንዲፈጽሙ፣ እንዲሁም ለተፈጻሚነታቸው ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ኮሚሽኑ ጥሪውን ያቀርባል።